# ኦሪት ዘልደት ።

ምዕራፍ ፩ ።

፩ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ።

፪ ወምድርሰ ሀለወት እምትክት ዕራቃ ወኢታስተርኢ ወኢክኑት ድሉተ ወጽልመት መልዕልተ ቀላይ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጹልል መልዕልተ ማይ ።

፫ ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ፡ ወኮነ ብርሃን ።

፬ ወርእዮ እግዚአብሔር ለብርሃን ከመ ሠናይ ውእቱ ፡ ወፈለጠ እግዚአብሔር ማእከለ ብርሃን ወማእከለ ጽልመት ፡

፭ ወሰመዮ እግዚአብሔር ለብርሃን ዕለተ ወለጽልመት ፡ ሌሊተ ፡ ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ወኮነ አሐደ ዕለተ ።

፮ ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ጠፈር ማእከለ ማይ ከመ ይፍልጥ ማእከለ ማይ ወማይ ፡ ወኮነ ከማሁ ።

፯ ወገብረ እግዚአብሔር ጠፈረ ፡ ወፈለጠ እግዚአብሔር ማእከለ ማይ ዘመልዕልተ ጠፈር ፡ ወማእከለ ማይ ዘመትሕተ ጠፈር ።

፰ ወሰመዮ እግዚአብሔር ለውእቱ ጠፈር ሰማየ ፡ ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ፡ ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ፡ ወኮነ ክልኤተ ዕለተ ።

፱ ወይቤ እግዚአብሔር ለይትጋባእ ማይ ዘመትሕተ ሰማይ ውስተ አሐዱ መካን ፡ ወያስተርኢ የብስ ፡ ወኮነ ከማሁ ፡ ወተጋብአ ማይ ውስተ ምእላዲሁ ወአስተርአየ የብስ ።

፲ ወሰመዮ እግዚአብሔር ለየብስ ምድረ ፡ ወለምእላዲሁ ለማይ ሰመዮ ባሕረ ፡ ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ።

፲፩ ወይቤ እግዚአብሔር ለታብቍል ምድር ሐመልማለ ሣዕር ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ ፡ ወበበአርአያሁ ፡ ወዕፀ ዘይፈሪ ወይገብር ፍሬሁ ዘእምውስቴቱ ዘርኡ ዘይወፅእ ወዘይከውን በበዘመዱ ዲበ ምድር ፡ ወኮነ ከማሁ ።

፲፪ ወአውጽአት ምድር ሐመልማለ ሣዕር ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ ወበበአርአያሁ ፡ ወዕፀ ዘይፈሪ ወዘይገብር ፍሬሁ ዘእምውስቴቱ ዘርኡ ዘይወፅእ በበዘመዱ መልዕልተ ምድር ፡ ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ።

፲፫ ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ፡ ወኮነ ሠለስተ ዕለተ ።

፲፬ ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩኑ ብርሃናት ውስተ ጠፈረ ሰማይ ከመ ያብርሁ ዲበ ምድር ፡ ወይፍልጡ ማእከለ ዕለት ወማእከለ ሌሊት ፡ ወይኩኑ ለትእምርታት ፡ ወለአዝማናት ፡ ወለመዋዕላት ፡ ወለዓመታት ።

ምዕራፍ ፩ ።

በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ። መዝ ፴፫ ፡ ፮ ። ፻፴፮ ፡ ፭ ። ዮሐ. ፩ ፡ ፩ - ፲፫ ።

ምድር ግን ባዶዋን ነበረች ፡ አትታይም ነበር ፡ አልተዘጋጀችም ነበር ፡ ጨለማውም በቀላይ ላይ ነበር ፡ እግዚአብሔር የፈጠረውም ነፋስ በውኃው ላይ ይሰፍ ነበር ።

እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ ፡ ብርሃንም ሆነ ።

እግዚአብሔርም ብርሃንን መልካም እንደሆነ አየ ፡ እግዚአብሔርም ብርሃንና ጨለማን ለየ ። ቆ. ፲፫ ።

እግዚአብሔር ብርሃኑን ቀን ፡ ጨለማውን ሌሊት አለው ፡ መሸም ነጋም ፡ አንድ ቀን ሆነ ።

እግዚአብሔርም በውኃ መካከል ጠፈር ይሁን አለ ፡ በውኃና በውኃ መካከል እንዲለይ ፡ እንዳለውም ሆነ ። ኢዮ. ፴፯ ፡ ፲፰ ። ኤር ፲ ፡ ፲፪ ።

እግዚአብሔርም ጠፈርን ፈጠረ ፡ ከጠፈር በታች ባለው ውኃና ከጠፈር በላይ ባለው ውኃ መካከል ድንበር ለየ ። መዝ. ፻፵፰ ፡ ፬ ።

እግዚአብሔር ይህን ጠፈር ሰማይ አለው ፡ እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ አየ ፡ መሸም ነጋም ሁለት ቀን ሆነ።

እግዚአብሔር ከሰማይ በታች ያለ ውኃ በአንድ በታ ላይ ይወሰን ፡ ደረቁም ይገለጥ አለ ፡ እንዳለውም ሆነ ፡ ውኃውም በመጠራቀሚያው ተወሰነ ፡ ደረቁም ተገለጠ ። መዝ. ፴፫ ፡ ፯ ።

እግዚአብሔር ደረቁን ምድር አለው ፡ የውኃውንም መጠራቀሚያ ባሕር አለው ፡ እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ አየ ።

እግዚአብሔርም ምድር በየዘሩ በየወገኑ በየመልኩ የሚዘራውን የሣር ቡቃያ የሚያፈራውን ፍሬ የሚሰጠውን ዘሩ ከውስጡ የሚገኘውን ፡ በምድር ላይ በየወገኑ የሚተከለውን የሚበቅለውን ተክል ታውጣ አለ ፡ እንዳለውም ሆነ ።

ምድርም በየዘሩ ፡ በየወገኑ ፡ በየመልኩ የሚዘራውን የሣር ቡቃያ አወጣች ፡ የሚያፈራውን ፍሬ የሚሰጠውን ዘሩ ከውስጡ የሚገኘውን ፡ በምድር ላይ በየወገኑ የሚበቅለውን ተክል አስገኘች ፡ እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ ።

መሸ ጠባ ፡ ሦስት ቀንም ሆነ ።

እግዚአብሔርም አለ በሰማይ ጠፈር ውስጥ ብርሃናት ይሁኑ ፡ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ ፡ ቀኑንና ሌሊቱን ይለዩ ዘንድ ፡ ለዘመን ፡ ለቀናት ፡ ለዓመታት ምልክት ይሆኑ ዘንድ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይኩኑ ለአብርሆ በጠፈረ ሰማይ ከመ ያብርሁ ዲበ ምድር፤ ወኮነ ከማሁ ። | ፲፭ | ለማብራት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፤ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ፤ እንዳለውም ሆነ ። |
| ወገብረ እግዚአብሔር ክልኤተ ብርሃናተ ዐበይተ፤ ዘየዐቢ ብርሃን ከመ ይምልክ መዓልተ፤ ወዘይንእስ ብርሃን ከመ ይምልክ ሌሊተ ምስለ ከዋክብት ። | ፲፮ | እግዚአብሔር ሁለቱን ታላላቅ ብርሃናት ፈጠረ ከፍተኛው ብርሃን ቀኑን እንዲያበራ፤ ታናሹ ብርሃንም ከከዋክብት ጋር ሌሊቱን እንዲያበራ አደረገ። መዝ. ፻፴፭፥፯-፲ ። |
| ወሤሞሙ እግዚአብሔር በጠፈረ ሰማይ ከመ ያብርሁ ዲበ ምድር ። | ፲፯ | እግዚአብሔር በሰማይ ጠፈር አኖራቸው፤ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ ። |
| ወይኰንንዎሙ ለዕለት ወለሌሊት ወይፍልጡ ማእከለ ዕለት ወማእከለ ሌሊት፤ ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ። | ፲፰ | መዓልትንና ሌሊትን ያበሩ ዘንድ፤ መዓልቱንና ሌሊቱንም ይለዩ ዘንድ፤ እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ አየ ። |
| ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ፤ ወኮነ አርብዕተ ዕለተ ። | ፲፱ | መሸም ጠባም አራት ቀን ሆነ ። |
| ወይቤ እግዚአብሔር ለታውጽእ ማይ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ወአዕዋፈ ዘይሠርሩ መልዕልተ ምድር ወመትሕተ ሰማይ፤ ወኮነ ከማሁ ። | ፳ | እግዚአብሔርም ውኃዎቹ የሚንቀሳቀሱትን፤ የሕይወት እስትንፋስ ያለውን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የሚበርሩ ወፎችን ታውጣ አለ፤ እንዳለውም ሆነ ። |
| ወገብረ እግዚአብሔር አናብርተ ዐበይተ ወኵሎ ነፍሰ ሕይወት ዘይትሐወስ ዘአውጽአ ማይ በበዘመዱ ወኵሎ አዕዋፈ ዘይሠርሩ በበዘመዶሙ፤ ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ። | ፳፩ | እግዚአብሔር ታላላቅ አንበሪዎችን ውኃ ያወጣውን ተንቀሳቃሽ ሕያው ፍጥረት ሁሉ በየወገኑ፤ የሚበርሩ አዕዋፍን ሁሉ በየወገናቸው ፈጠረ፤ እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ ። |
| ወባረኮሙ እግዚአብሔር ወይቤ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልኡ ለቀላይ፤ ወአዕዋፍኒ ይብዝኁ ውስተ ምድር ። | ፳፪ | እግዚአብሔርም ብዙ ተባዙ፤ ባሕርንም ሙሉት አለ፤ አዕዋፍም በምድር ይበዙ ዘንድ ባረካቸው ። |
| ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ፤ ወኮነ ኃምስተ ዕለተ ። | ፳፫ | መሸ፤ ጠባ አምስት ቀንም ሆነ ። |
| ወይቤ እግዚአብሔር ለታውጽእ ምድር ዘመደ እንስሳ ወዘይትሐወስ ወአራዊተ ምድር በበዘመዶሙ፤ ወኮነ ከማሁ ። | ፳፬ | እግዚአብሔር ምድር የእንስሶችን ወገን የሚንቀሳቀሰውንም የምድር አራዊትንም በየወገናቸው ታውጣ አለ፤ እንዳለውም ሆነ ። |
| ወገብረ እግዚአብሔር እንስሳ በበዘመዱ ወኵሎ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር በበዘመዱ፤ ወአራዊተ ምድር በበዘመዶሙ፤ ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ። | ፳፭ | እግዚአብሔር እንስሳውን በየወገኑ፤ በምድር የሚንቀሳቀሰውንም ሁሉ በየወገኑ፤ የምድር አራዊትንም በየወገናቸው ፈጠረ፤ እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ ። |
| ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፤ ከመ ይኰንን ዓሣተ ባሕር ወአራዊተ ምድር ወአዕዋፈ ሰማይ ወእንስሳሂ ወኵሎ ምድረ ወኵሎ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ። | ፳፮ | እግዚአብሔርም አለ፤ በመልካችን በምሳሌያችን ሰውን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሣዎችን፤ የምድር አውሬዎችን፤ የሰማይ ወፎችን፤ እንስሳንም፤ ምድሩንም ሁሉ፤ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውን ሁሉ ይገዛ ዘንድ ። |
| ወገብሮ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው በአምሳለ እግዚአብሔር፤ ተባዕተ ወአንስተ ገብሮሙ ። | ፳፯ | እግዚአብሔርም ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል ፈጠረው፤ ወንድና ሴትም አደረጋቸው ። |
| ወባረኮሙ እግዚአብሔር ወይቤሎሙ፤ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር ወቅንይዋ፤ ወኰንንዎሙ ለዓሣተ ባሕር ወለአራዊተ ምድር ወለአዕዋፈ ሰማይ፤ ወለኵሉ እንስሳ ወለኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ። | ፳፰ | እግዚአብሔርም ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፤ ግዟት፤ የባሕር ዓሣዎችንም የምድር አውሬዎችንም፤ የሰማይ ወፎችንም፤ እንስሳንም ሁሉ፤ በምድር ላይ የሚኖረውንም ሁሉ ግዟቸው ። |
| ወይቤ እግዚአብሔር ናሁ ወሀብኩክሙ ኵሎ ሐመልማለ ሣዕር ዘይዘርእ ወይበቊል በበዘርኡ ወትዘርእ ዲበ ኵሉ ምድር፤ ወኵሉ ዕፀ ዘቦ ውስቴቱ ዘርአ ዘይዘርእ በበፍሬሁ ለክሙ ይኩንክሙ መብልዐ ። | ፳፱ | እግዚአብሔርም አለ፤ የሚዘራውን በየዘሩ የሚበቅለውን፤ በምድር ሁሉ ላይ የምትዘሩትን የእኽል ፍሬ፤ ዘሩ በውስጡ የሚገኘውን፤ በየፍሬው የሚዘራውን ተክልም እነሆ ሰጠኋችሁ፤ ለእናንተ ምግብ ይሁናችሁ ። |
| ወለኵሉ አራዊተ ምድር፤ ወለኵሉ አዕዋፈ ሰማይ ወለኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ዘቦ መንፈሰ ሕይወት፤ ወኵሉ ሐመልማለ ሣዕር ይኩንክሙ መብልዐ፤ ወኮነ ከማሁ ። | ፴ | የምድር አውሬዎችም ሁሉ፤ የሰማይ ወፎችም ሁሉ፤ በምድር ላይ የሚኖረውም ሁሉ፤ ደመ ነፍስ ያለውም ሁሉ፤ የእኽል ቡቃያ ሁሉ ምግብ ይሁናቸው፤ እንዳለውም ሆነ ። |
| ወርእየ እግዚአብሔር ኵሎ ዘገብረ ከመ ጥቀ ሠናይ፤ ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ፤ ወኮነ ሳድስተ ዕለተ ። | ፴፩ | እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ እጅግ መልካም እንደሆነ አየ፤ መሸ ጠባ፤ ስድስት ቀንም ሆነ ። መክ. ፯፥ ፳፱ ። |

| ምዕራፍ ፪። | | ምዕራፍ ፪። |
|---|---|---|
| ወተፈጸመ ሰማይ ወምድር ወኵሉ ዘውስቴቶሙ። | ፩ | ሰማይና ምድር ተከናወኑ፤ በውስጣቸው ያለውም ሁሉ፤ ዘዳ. ፬፡ ፲፱። መዝ. ፴፫፡ ፯። |
| ወፈጸመ እግዚአብሔር ገቢረ ግብር በስሱ ዕለት፤ ወአዕረፈ እግዚአብሔር በሳብዕት ዕለት እምኵሉ ግብሩ። | ፪ | እግዚአብሔርም በ፯ ቀን ሥራውን ሠርቶ ጨረሰ፤ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ፤ ዕብ. ፬፡ ፬። |
| ወባረካ እግዚአብሔር ለዕለት ሳብዕት ወቀደሳ እስመ ባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ ዘአኀዘ ይግበር። | ፫ | እግዚአብሔር ሰባተኛይቱን ቀን ባረካት፤ ቀደሳት፤ ሊሠራው ከጀመረው ሥራ ሁሉ ዐርፎባታልና። |
| ዝንቱ ጽሕፈተ ሰማይ ወምድር ዘእምአመ ኮነ ዕለት እንተ ባቲ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ። | ፬ | እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን መፍጠር ከጀመረበት ቀን ጀምሮ የሆነው የሰማይና የምድር አፈጣጠር ይህ ነው፤ ዘፍ. ፩፡ ፩። |
| ወኵሉ ሐመልማለ ሐቅል እምቅድመ ይኩን በምድር፤ ወኵሉ ሐመልማለ ምድር እምቅድመ ይብቊል፤ ወእምቅድመ ይትፈጠር አዳም ኢያዝነመ እግዚአብሔር ዲበ ምድር። | ፭ | የምድረ በዳ አዝርእት አትክልት ሁሉ በምድር ሳይፈጠር፤ የምድር አዝርእት አትክልትም ሁሉ ሳይበቅል አዳምም ሳይፈጠር እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ዝናም አላዘነመም ነበር። |
| ወአልቦ ሰብእ ዘይትገበራ ለምድር አላ ነቅዕ ማይ የዐርግ በሕቲቱ እምድር ወይሰቅያ ለየብስ። | ፮ | ምድርንም የሚያርሳት የሚቈፍራት አልነበረም፤ የውኃ ምንጭ ብቻ ከምድር ወጥቶ ደረቁን ያጠጣ ነበር እንጂ። |
| ወገብሮ እግዚአብሔር ለሰብእ እመሬተ ምድር ወነፍሐ በገጹ መንፈሰ ሕይወት ወኮነ እጓለ እመሕያው በመንፈሰ ሕይወት። | ፯ | እግዚአብሔርም ሰውን ከምድር አፈር ፈጠረው፤ በፊቱም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም በሕይወት እስትንፋስ ከበረ። መዝ. ፻፫፡ ፲፱። መክ. ፲፪፡ ፯። |
| ወተከለ እግዚአብሔር አምላክ ውስተ ኤዶም ገነተ መንገለ ጽባሕ፤ ወሤሞ ህየ ለእጓለ እመሕያው ዘገብሮ። | ፰ | እግዚአብሔር አምላክ በምሥራቅ በኩል በኤዶም ገነትን አዘጋጀ፤ የፈጠረው ሰውንም በገነት አኖረው። |
| ወአብቈለ ዓዲ እግዚአብሔር እምድር ኵሉ ዕፀወ ዘሠናይ ለበሊዕ፤ ወሠናይ ለርእይ፤ ወዕፀ ሕይወትኒ ተከለ ማእከለ ገነት፤ ወዕፀኒ ዘያርኢ ወያሌቡ ሠናየ ወእኩየ። | ፱ | ዳግመኛም እግዚአብሔር ሊበሉት ሊያዩት ያማረ የተወደደ አትክልትን ሁሉ ከምድር አበቀለ፤ ዕፀ ሕይወትንም በገነት መካከል ተከለ፤ ክፉውን በጎውን የሚያስታውቀውን ዕፅንም። ራእ. ፪፡ ፯። ፳፪፡ ፪-፬። |
| ወፈለግ ይወፅእ እምቅድሜሁ ከመ ይሥቅያ ለገነት፤ ወእምህየ ይትፈለጥ ለአርባዕቱ መዓዝነ ዓለም። | ፲ | ገነትንም ያጠጣ ዘንድ ከፈለገ ለፈቱ ፈለገ ይወጣ ነበር፤ ከዚያም ወደ አራቱ መዓዝነ ዓለም ይከፈላል። |
| ስሙ ለአሐዱ ፈለግ ኤፌሶን፤ ውእቱ ዘየዐውድ ውስተ ኵሉ ምድረ ኤውላጦን፤ ወህየ ሀሎ ወርቅ። | ፲፩ | የአንዱ ወንዝ ስሙ ኤፌሶን ነው፤ እርሱ የኤውላጦንን ምድር ሁሉ የሚያጠጣ ነው፤ በዚያም ወርቅ አለ። ዘኍ. ፲፩፡ ፯። ፳፭፡ ፲፰። |
| ወወርቃ ለይእቲ ምድር ሠናይ፤ ወህየ ሀሎ ዕንቍ ዘየኀቱ ወዕንቍ ሐመልሚል። | ፲፪ | የዚያችም ምድር ወርቅ ጥሩ ነው፤ ከዚያ የሚያበራ ዕንቍ (ሉል) ዝንጕርጕር ዕንቍም ነበር። ዘፀ. ፳፭፡ ፯። ፴፱፡ ፯-፲፫። ፩ ዜና መዋ. ፳፱፡ ፰። |
| ወስሙ ለካልእ ፈለግ ግዮን፤ ወውእቱ ዘየዐውድ ኵሉ ምድረ ኢትዮጵያ። | ፲፫ | የሁለተኛውም ወንዝ ስሙ ግዮን ነው፤ እሱም የኢትዮጵያን ምድር ዙሮ የሚያጠጣ ነው። |
| ወፈለግ ሣልስ ጤግሮስ፤ ውእቱ ዘየሐውር ላዕለ ፋርስ፤ ወፈለግ ራብዕ ውእቱ ኤፍራጥስ። | ፲፬ | የሦስተኛውም ወንዝ ጤግሮስ ነው፤ ይህም ፋርስን ዙሮ የሚያጠጣ ነው፤ አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው። |
| ወነሥኦ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው ዘገብረ፤ ወሤሞ ውስተ ገነት ከመ ይትገበራ ወይዕቀባ። | ፲፭ | እግዚአብሔርም የፈጠረውን ሰው ወስዶ በገነት አኖረው፤ ያርሳት ይቈፍራት ይጠብቃት ዘንድ። |
| ወአዘዞ እግዚአብሔር ለአዳም ወይቤሎ እምኵሉ ዕፅ ዘሀሎ ውስተ ገነት ብላዕ። | ፲፮ | እግዚአብሔርም አዳምን እንዲህ ብሎ አዘዘው፤ በገነት ካለው ተክል ሁሉ ብላ። |
| ወእምዕፀሰ ዘያርኢ ወያሌቡ ሠናየ ወእኩየ ኢትብላዕ እምኔሁ፤ እስመ በዕለተ ትበልዕ እምኔሁ ሞተ ትመውት። | ፲፯ | ክፉውንና መልካሙን ከሚያስታውቀውን ዕፅ ግን አትብላ፤ ከእሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና። |
| ወይቤ እግዚአብሔር ኢኮነ ሠናየ ለእጓለ እመሕያው ይንበር በሕቲቱ፤ አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘይረድኦ። | ፲፰ | እግዚአብሔርም ለሰው ብቻውን መኖር መልካም አይደለም፤ የሚረዳው ጓደኛ እንፍጠርለት እንጂ አለ። |
| ወገብረ እግዚአብሔር ዓዲ አራዊተ ገዳም እምድር ወኵሎ አዕዋፈ ሰማይ ወአምጽኦሙ ኀበ አዳም ከመ ይር | ፲፱ | ዳግመኛም እግዚአብሔር በምድረ በዳ አውሬዎችን ከምድር አስገኘ የሰማይ ወፎችንም ሁሉ አይቶ በማን |

አይ ወምንተ ይሰምዮሙ ወኵሉ ዘሰመዮሙ አዳም ለለነ ፍስተ ሕይወት ውእቱ ይኩን ስሞሙ።

ኛውም ስም ይጠራቸው ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው፤ ሲየተንቀሳቃሹ አዳም ያወጣላቸው ስም ሁሉ መጠሪያ እንዲሆናቸው ነው። ዘፍ. ፩፣ ፳፬።

፳ ወሰመየ አዳም ኵሎ አስማቲሆሙ ለእንስሳ ወለኵሉ አዕዋፈ ሰማይ ወለኵሉ አራዊተ ገዳም፤ ወለአዳምሰ ኢተረክበ ሎቱ ረድኤቱ ዘከማሁ።

አዳምም ለእንስሳ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ ለምድረ በዳ አውሬዎችም ሁሉ ስማቸውን ሁሉ አወጣላቸው፤ ለአዳም ግን እንደሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም።

፳፩ ወአምጽአ እግዚአብሔር ድቃሰ ላዕለ አዳም ወኖመ፤ ወነሥአ እግዚአብሔር አሐደ እምዐፅመ ገቦሁ ወመልአ ሥጋ መከና።

እግዚአብሔርም በአዳም እንቅልፍን አመጣበት ተኛ፤ እግዚአብሔርም ከጐኑ ዐጥንት አንድ ዐጥንትን ነሣ፤ በታዋንም ሥጋ መላ።

፳፪ ወነደቃ እግዚአብሔር ለይእቲ ዐፅመ ገቦ እንተ ነሥአ እምአዳም ወረሰያ ብእሲተ ወአምጽአ ኀበ አዳም።

እግዚአብሔርም ይህችን ከአዳም ጐን የነሣትን ዐጥንት ቀረፀላት፤ ሴት አደረጋት፤ ወደ አዳምም አመጣት።

፳፫ ወይቤ አዳም ዕቤሃ፤ ዛቲ ዐፅም እምዐፅምየ ወሥጋ እምሥጋየ ለትኩነኒ ብእሲትየ እስመ እምታ ወጽአት ይእቲ።

ያን ጊዜም አዳም ይህቺ ከዐጥንቴ ዐጥንት፤ ከሥጋዬ ሥጋ ናት፤ ሚስቴ ትሁነኝ አለ፤ አርዷ ከባሏ ተገኝታለችና። ዘፍ. ፳፱፣ ፲፬። መሳ. ፱፣ ፪። ፩ ቆሮ. ፲፩፣ ፰።

፳፬ ወበእንተ ዝንቱ የኀድግ ብእሲ አቡሁ ወእሞ ወይተለዋ ለብእሲቱ ወይከውኑ ክልኤሆሙ አሐደ ሥጋ።

ስለዚህም ነገር ሰው እናቱን አባቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል፤ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ። መዝ. ፵፭፣ ፲።

፳፭ ወሀለዉ አዳም ወብእሲቱ ዕራቃኒሆሙ ወኢይትኃፈሩ።

አዳምና ሔዋንም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤ አይተፋፈሩም ነበር።

## ምዕራፍ ፫።

፩ ወአርዌ ምድርሰ ይጠበብ እምኵሉ አራዊተ ምድር ዘገብረ እግዚአብሔር፤ ወይቤላ አርዌ ምድር ለብእሲት ምንትኑ ውእቱ ዘይቤለክሙ እግዚአብሔር ኢትብልዑ እምኵሉ ዕፀ ዘውስተ ገነት።

የምድር እባብ ግን እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ከምድረ በዳ አውሬዎች ሁሉ ይልቅ ይተነኰል ነበር፤ የምድር እባብም ሔዋንን እግዚአብሔር በገነት ካሉ ዕንጨት ሁሉ አትብሉ ያላችሁ ለምንድር ነው አላት። ማቴ. ፲፣ ፲፮። ፪ ቆሮ. ፲፩፣ ፫። ራእ. ፲፪፣ ፱። ፳፪፣ ፪።

፪ ወትቤሎ ብእሲት ለአርዌ ምድር እምዕፀ ዘይፈሪ ዘሀሎ ማእከለ ገነት ንበልዕ።

ሔዋንም የምድር እባብን በገነት ውስጥ ከሚያፈራው ዕንጨት እንበላለን አለቻት።

፫ ወእምዕፀሰ ብሑቱ ዘሀሎ ማእከለ ገነት ይቤለነ እግዚአብሔር ከመ ኢንብላዕ እምኔሁ ወከመ ኢንግሥሦ ከመ ኢንሙት ይቤ።

በገነት መካከል ካለው ዛፍ ግን ከእሱ እንዳንበላ እንዳንነካውም እግዚአብሔር አዝዞናል፤ እንዳንሞት ይሆን አለ። ዘፍ. ፪፣ ፲፯።

፬ ወይቤላ አርዌ ምድር ለብእሲት፡ አኮ ሞተ ዘትመውቱ።

የምድር እባብም ሔዋንን እንዲህ አለቻት፤ የምትሞቱስ አይደለም።

፭ አላ እስመ የአምር እግዚአብሔር ከመ አመ ዕለተ ትበልዑ እምኔሁ ይትፈተሕ አዕይንቲክሙ፤ ወትከውኑ ከመ እግዚአብሔር ወተአምሩ ሠናየ ወእኩየ።

ከሱ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንደሚከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም እንደምትሆኑ፤ መልካሙንና ክፉውን እንደምታውቁ እግዚአብሔር ያውቃልና ነው እንጂ።

፮ ወሶበ ርእየት ብእሲት ከመ ሠናይ ዕፁ ለበሊዕ ወሠናይ ውእቱ ለርእይ ወሠናየ ያጤይቅ፤ ነሥአት እምፍሬሁ ወበልዐት፤ ወወሀበቶ ለብእሲሃ ምስሌሃ ወበልዐ።

ሴቲቱም ዕንጨቱ ለመብላት የሚያስጎመጅ ሊያዩትም የሚያስደስት፤ ዕውቀትን የሚገልጽ እንደሆነ በየች ጊዜ ከፍሬው ቈረጠችና በላች፤ ለባሏም እንደአርዷ ሰጠችው በሉም። ፩ ጢሞ. ፪፣ ፲፬።

፯ ወተፈትሐ አዕይንቲሆሙ ወአእመሩ ከመ ዕራቃኒሆሙ እሙንቱ ወኀፈሩ ወሰፈዩ ቈጽለ በለስ ወገብሩ ሎሙ መዋርዕተ።

የሁለቱም ዓይናቸው ተከፈተ፤ እነሱ ዕራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁና አፈሩ፤ የበለስን ቅጠል ሰፍተው ለዕርቃናቸው መሸፈኛ አደረጉ።

፰ ወሰምዑ ቃለ እግዚአብሔር እንዘ ያንሶሱ ውስተ ገነት ፍና ሠርክ፤ ወተኀብኡ አዳም ወብእሲቱ እምቅድመ እግዚአብሔር ማእከለ ዕፀዊሃ ለገነት።

ማታ ጊዜም በገነት ውስጥ ሲመላለስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።

፱ ወጸውዖ እግዚአብሔር ለአዳም ወይቤሎ አይቴ ሀሎከ አዳም።

እግዚአብሔርም አዳምን ጠርቶ አዳም ወዴት አለህ፤ አለው።

፲ ወይቤ አዳም ሰማዕኩ ቃለከ እንዘ ታንሶሱ ውስተ ገነት ወፈራህኩ እስመ ዕራቅየ አነ ወተኀባእኩ።

አዳምም በገነት ውስጥ ስትመላለስ ቃልህን ሰምቼ ፈራሁ ዕራቁቴን ነኝና ተሸሸግሁ አለ።

፲፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር መኑ አይድዐከ ከመ ዕራቅከ አንተ እምዕፀ ዘአዘዝኩከ ከመ ኢትብላዕ እምኔሁ በላዕከ።

እግዚአብሔርም ዕራቁትህን እንደሆንክ ማን ነገረህ ፡ ከሱ እንዳትበላ ከዘዝኩህ ዕንጨት በላህን ፡ አለው ።

፲፪ ወይቤ አዳም ብእሲት እንተ ወሀብከኒ ምስሌየ ትንበር ይእቲ ወሀበተኒ ወበላዕኩ ።

አዳምም ከኔ ጋር ትኖር ዘንድ የሰጠኸኝ ሴት ሰጠችኝና በላሁ አለ ። ዘፍ. ፪ ፡ ፲፰ ። ኢዮብ ፴፩ ፡ ፴፫ ።

፲፫ ወይቤላ እግዚአብሔር ለብእሲት ለምንት ገበርኪ ዘን ተ ፡ ወትቤ ብእሲት አርዌ ምድር አስፈጠተኒ ወበላዕኩ ።

እግዚአብሔርም ሴቲቱን ይህን ለምን አደረግሽ ፡ አላት ፡ ሴቲቱም የምድር እባብ አሳተችኝና በላሁ አለች ። ዘፍ. ፫ ፡ ፬ ። ፪ ቆሮ. ፲፩ ፡ ፫ ። ፩ ጢሞ. ፪ ፡ ፲፬ ።

፲፬ ወይቤላ እግዚአብሔር ለአርዌ ምድር እስመ ገበር ኪዮ ለዝንቱ ግብር ርግምተ ኩኒ እምኵሉ እንስሳ ወእ ምኵሉ አራዊተ ምድር ፡ ወበእንግድዓኪ ሑሪ ወመሬተ ብልዒ ኵሉ መዋዕለ ሕይወትኪ ።

እግዚአብሔርም የምድር እባብን እንዲህ አላት ፡ ይህን ሥራ ሠርተሽዋልና ከምድር አውሬዎችና ከእንስሳት ሁሉ ተለይተሽ የተረገምሽ ሁኚ ፡ በደረትሽ ሂጂ ፡ በለሽበት ዘ መን ሁሉ አፈርን ብዪ ።

፲፭ እስተፃርር ማእከሌኪ ወማእከለ ብእሲት ፡ ማእከለ ዘር እኪ ወማእከለ ዘርአ ፡ ውእቱ ለይዕቀብ ርእሰኪ ፡ ወአን ቲኒ ዕቀቢ ሰኰናሁ ።

በአንቺና በሴቲቱ መካከል ጥልን እፀናለሁ ፡ በዘርሽና በዘሩ መካከልም እርሱ ራስሽን ይጠብቅ ፡ አንቺም ሰኰና ውን ጠብቂ ።

፲፮ ወለብእሲትኒ ይቤላ እግዚአብሔር አብዝኆ አበዝኆ ለኀዘንኪ ወለሥቃይኪ ፡ ወበፃዕር ለዲ ወወሊደኪ ኀበ ምትኪ ይኩን ምግባእኪ ፡ ወውእቱ ይቀንይኪ ።

እግዚአብሔርም ሴቲቱን ኀዘንሽን ሥቃይሽን የብዙ ብዙ አደርገዋለሁ ፡ በምጥ ውለጂ ፡ ወልደሽም መመለሻሽ ወደ ባልሽ ይሁን ፡ እርሱ ይግዛሽ አላት ።

፲፯ ወለአዳምኒ ይቤሎ እግዚአብሔር እስመ ሰማዕከ ቃለ ብእሲትከ ወበላዕከ እምውእቱ ዕፅ ዘአዘዝኩከ ከመ ኢት ብላዕ እምኔሁ ፡ ርግምተ ትኩን ምድር በተግባርከ ፡ ወበፃ ዕር ብላዕ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትከ ።

አዳምንም እግዚአብሔር እንዲህ አለው ፡ የሚስትህን ቃል ሰምተህ ከእሱ እንዳትበላ ከዘዝኩህ ዕፅ በልተሃልና ምድር በሥራህ የተረገመች ትሁን ፡ በሕስህበት ዘመን ሁ ሉም በፃር ብላ ።

፲፰ አሥዋከ ወአሜከላ ይብቍልከ ፡ ወብላዕ ሣዕረ ገዳም ።

እሾኽ አሜከላ ይብቀልብህ ፡ በምድረ በዳ ያለ እኽል ንም ብላ ።

፲፱ ወበሐፈ ገጽከ ብላዕ ኅብስተከ እስከ ትገብእ ውስተ መ ሬት እንተ እምኔሃ ወፃእከ ፡ እስመ መሬት አንተ ወውስተ መሬት ትገብእ ።

አንተ መሬት ነህና ወደ መሬትም ትመለሳለህና ፡ ከቢ ወደ ተገኘህበት ወደ መሬት እስክትመለስ ድረስ እንጀራ ህን ጥረህ ግረህ ብላ አለው ። ዘፍ. ፪ ፡ ፯ ። ኢዮ. ፴፬ ፡ ፲፭ ። መዝ. ፺፱ ፡ ፳፱ ። መክ. ፺፫ ፡ ፳ ።

፳ ወሰመየ አዳም ስማ ለብእሲቱ ሔዋን ፡ እስመ ይእቲ እሞሙ ለሕያዋን ።

አዳምም የሚስቱን ስም ሔዋን አለው ፡ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና ።

፳፩ ወገብረ እግዚአብሔር ለአዳም ወለብእሲቱ አልባሰ ዘማ እስ ወአልበሶሙ ።

እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የቍርበትን ልብስ አዘጋጅቶ አለበሳቸው ።

፳፪ ወይቤ እግዚአብሔር ናሁ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እም ኔነ ያእምር ሠናየ ወእኩየ ፡ ወይእዜኒ ዮጊ ያሌዕል እዴሁ ወይነሥእ እምዕፀ ሕይወት ወይበልዕ ወየሐዩ ለዓለም ።

እግዚአብሔርም እንዲህ አለ ፡ ክፉና በጎን ያውቅ ዘንድ እነሆ አዳም ከኛ እንደ አንዱ ሆነ ፡ አሁንም ወይም እኮ እጁን ከፍ ከፍ አድርጎ ከዕፀ ሕይወት ቈርጦ በልቶ ዘለዓ ለም ይኖር ይሆናል ። ዘፍ ፫ ፡ ፰ ። ፪ ፡ ፱ ።

፳፫ ወአውፅአ እግዚእ እግዚአብሔር ለአዳም እምገነተ ት ድላ ከመ ይትገበራ ለምድር እንተ እምኔሃ ወፅአ ወአኅ ደሮ ቅድመ ገነተ ትፍሥሕት ።

ጌታ እግዚአብሔርም ከእሷ የተገኘባትን ምድርን ያርስ ይቈፍር ዘንድ አዳምን ከተድላ ገነት አወጣው ፡ በተድላ ገነት ፊት ለፊትም አኖረው ።

፳፬ ወአዘዞሙ ለኪሩቤል ወለሱራፌል ዘውስተ እደዊሆሙ ሰይፈ እሳት እንተ ትትመየየጥ ከመ ይዕቀቡ ፍኖተ ዕፀ ሕይወት ።

የምታብለጨልጭ የእሳት ሰይፍ በእጃቸው ያለች ኪሩ ቤልና ሱራፌልንም የዕፀ ሕይወት መንገድን ይጠብቁ ዘንድ አዘዛቸው ። ዘፍ. ፪ ፡ ፰ ።

## ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወአእመራ አዳም ለሔዋን ብእሲቱ ወፀንሰት ወወለደቶ ለቃየል ፡ ወትቤ አጥረይኩ ብእሴ ዘእግዚአብሔር ።

አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቃት ፡ ፀንሳ ቃየልንም ወለደችው ፡ "እግዚአብሔር የሰጠንን ልጅ ገንዘብ አደ ረግን" አለች ።

፪ ወደገመት ወወለደቶ ለአቤል እኁሁ ፡ ወኮነ አቤል ኖላዌ አባግዕ ፡ ወቃየልሰ ኮነ መስተገብረ ምድር ።

ዳግመኛም ወንድሙ አቤልን ወለደችው ፡ አቤልም በጎ ችን የሚጠብቅ ሆነ ፡ ቃየል ግን ምድርን የሚያርስ የሚ ቈፍር ሆነ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወከነ እምድኅረ ብዙኅ መዋዕል አምጽአ ቃየል እምነ ፍሬ ምድር መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ። | ፫ | ከብዙ ዘመን በኋላ እንዲህ ሆነ ቃየል ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ ። |
| ወአቤልሂ አምጽአ መሥዋዕተ እምበኵረ አባግዒሁ ወእምስቡሓኒሆሙ ፡ ወነጸረ እግዚአብሔር ላዕለ አቤል ወላዕለ መሥዋዕቱ ። | ፬ | አቤልም ከበጎቹ መጀመሪያ የተወለደውን ከሰቡትም መሥዋዕት አቀረበ ፡ እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ አየ ። ዘኍ. ፲፰ ፡ ፲፯ ። ዕብ. ፲፩ ፡ ፬ ። |
| ላዕለ ቃየልሰ ወላዕለ መሥዋዕቱ ኢነጸረ ፡ ወአኅዘኖ ለቃየል ጥቀ ወወድቀ ገጹ ። | ፭ | ወደ ቃየልና ወደ መሥዋዕቱ ግን አላየም ፡ ቃየልንም እጅግ አሳዘነው ፊቱም ጠቈረ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለቃየል ለምንት ተኀዝን ወለምንት ወድቀ ገጽከ ። | ፮ | እግዚአብሔርም ቃየልን ለምን ታዝናለህ ፡ ፊትህስ ለምን ጠቈረ ፡ አለው ። |
| አኮ በጽድቅ ዘአምጻእከ ሊተ ፡ ወርቱዕሰ በጽድቅ ታምጽእ ሊተ ፡ አበስከ አንከ አርምም ወኀቤከ ምግባኢሁ ለእኁከ ወአንተ ትኬንኖ ። | ፯ | ያቀረብክልኝ በእውነት አይደለም ነገር ግን በእውነት ታቀርብልኝ ዘንድ ይገባህ ነበር ፡ በደልህ እንግዲህስ ዝም በል ፡ ይ ወንድምህም መመለሻው ወደ አንተ ነው ፡ አንተ ትገድለዋለህ ። |
| ወይቤሎ ቃየል ለአቤል እኁሁ ነዓ ንሑር ሐቅለ ፡ ወከነ እንዘ ሀለዉ ገዳመ ተንሥአ ቃየል ላዕለ አቤል እኁሁ ወቀተሎ ። | ፰ | ቃየልም ወንድሙን አቤልን ና ወደ ምድረ በዳ እንሂድ አለው ፡ በምድረ በዳም ሳሉ እንዲህ ኾነ ፡ ቃየል በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሥቶ ገደለው ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለቃየል አይቴ ውእቱ አቤል እኁከ ፡ ወይቤሎ ቃየል ኢየአምር በኑ አነ ዐቃቢሁ ለአቤል እኁየ ። | ፱ | እግዚአብሔርም ቃየልን አቤል ወንድምህ ወዴት ነው ፡ አለው ፡ ቃየልም አላውቅም ፡ በውኑ እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝ ! አለው ። ዮሐ. ፰ ፡ ፴፬ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ምንተ ገበርከ ቃየል ፡ ቃለ ደሙ ለአቤል እኁከ በጽሐ ኀቤየ እምድር ። | ፲ | እግዚአብሔርም እንዲህ አለው ፡ ቃኤል ምን አድርገ ኻል ፡ የወንድምህ የአቤል ደም ጩኸት ከምድር ወደኔ ደርሷል ። |
| ወይእዜኒ ርግምተ ትኩን ምድር አንተ አብቀወት አፉሃ ከመ ትስተይ ደሞ ለእኁከ እምእዴከ ። | ፲፩ | አሁንም በእጅህ የፈሰሰውን የወንድምህን ደም ትጠጣ ዘንድ አፏዋን የከፈተች ምድር የተረገመች ትሁን ። |
| እስመ ትትጌበራ አንተ ወኢትዌስከ ከመ ተሀብከ ኀይለ ፡ ርዑደ ወድንጉፀ ኩን ላዕለ ምድር ። | ፲፪ | አንተ ታርሳታለህና ጉልበትን ትሰጥህ ዘንድ አትጨምርም ፡ በምድር ላይ ፈሪ ቀበዝባዥ ሁን ። |
| ወይቤሎ ቃየል ለእግዚአብሔር ተዐቢኑ ኃጢአትየ ዘእምትትኀደግ ሊተ ። | ፲፫ | ቃየልም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፡ ኃጢአቴ ቻላ ቅ ናትን ፡ ልትሠረይልኝ ሲገባት ። |
| ወናሁ ታወፅአኒ እምድር ወእምቅድመ ገጽከ እትኀባእ ወእከውን ርዑደ ወድንጉፀ በዲበ ምድር ወኵሉ ዘረከበኒ ይቀትለኒ ። | ፲፬ | እነሆ ከምድር ታሳድደኛለህ ፡ ከፊትህስ እሠወራለሁን ፡ በምድር ላይ ድንጉፅ ቀበዝባዥ እሆናለሁ ፡ ያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል ። ዘፍ. ፱ ፡ ፮ ። ፪ ነገ. ፲፫ ፡ ፳፫ ። ነገ. ፳፬ ፡ ፳ ። መዝ. ፶፩ ፡ ፲፬ ። ኤር. ፶፪ ፡ ፫ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር አኮ ከማሁ ፡ ኵሉ ዘቀተሎ ለቃየል ሰብዓተ በቀለ ያቀውም ፡ ወገብረ እግዚአብሔር ተአምረ ለቃየል ከመ ኢይቅትሎ ኵሉ ዘረከቦ ። | ፲፭ | እግዚአብሔርም እንዲህ አይደለም ፡ ቃየልን የገደለው ሰው ሁሉ ሰባት ዕፅፍ ፍዳ ይቀበላል አለው ፡ እግዚአብሔርም ቃየልን ያየው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገለት ። |
| ወወፅአ ቃየል እምቅድመ ገጸ እግዚአብሔር ወኀደረ ውስተ ምድረ ፋይድ ዘአንጻረ ኤዶም ። | ፲፮ | ቃየልም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ ፡ በኤዶም አንጻር ባለችው በምድረ ፋይድ ኖረ ። |
| ወአእመራ ቃየል ለብእሲቱ ወፀንሰት ወወለደቶ ለሄኖኅ ፡ ወሐነፀ ሀገረ ወሰመያ ለይእቲ ሀገር በስመ ወልዱ ሄኖኅ ። | ፲፯ | ቃየልም ሚስቱን አወቃት ፀነሰች ሄኖኅንም ወለደች ፡ አገር ቈረቈረ ያችንም አገር በልጁ ስም ሄኖኅ ብሎ ጠራት ። |
| ወሄኖኅ ወለዶ ለጋይዳድ ፡ ወጋይዳድ ወለዶ ለሜኤል ፡ ወሜኤል ወለዶ ለማቱሳላ ፡ ወማቱሳላ ወለዶ ለላሜህ ። | ፲፰ | ሄኖኅም ጋይዳድን ወለደው ፡ ጋይዳድም ሜኤልን ወለደው ፡ ሜኤልም ማቱሳላን ወለደው ፡ ማቱሳላም ላሜህን ወለደው ። |
| ወነሥአ ላሜህ ለርእሱ ክልኤ አንስትያ ስማ ለአሐቲ ሐዳ ፡ ወስማ ለካልእታ ሲላ ። | ፲፱ | ላሜህም ለራሱ ሁለት ሚስቶችን አገባ ፡ የአንዲቱ ስሟ ሐዳ ይባላል ፡ የሁለተኛዪቱ ስሟ ሲላ ይባላል ። |
| ወወለደቶ ሐዳ ለዮሴድ ፡ ወውእቱ ከነ አቡሆሙ ለእለ የኀድሩ ውስተ አዕጻዳተ ኖሎተ እንስሳ ። | ፳ | ሐዳም ዮሴድን ወለደችው ፡ እሱም የከብት እረኞች በሚኖሩበት ለሚኖሩት ዘላኖች አባት ሆነ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወስመ እኁሁ ኢዮቤል ፡ ወውእቱ አርአየ ማኅሌተ ወመሰንቆ ። | ፳፩ | የወንድሙም ስም ኢዮቤል ይባላል ፡ እሱም ዘፈንና መሰንቆ መምታትን አስተማረ ። |
| ወሲላኒ ወለደቶ ለቶቤል ወውእቱ ኮነ ነሀቤ ብርት ወኃፂን ፡ ወእኅቱ ለቶቤል ኖሂም ስማ ። | ፳፪ | ሲላም ቶቤልን ወለደችው ፡ እሱም ብረትና ናስን የሚሠራ ሆነ ፡ የእኅቱም ስሟ ኖሂም ይባላል ። |
| ወይቤሎን ላሜህ ለአንስቲሁ ሐዳ ወሲላ ስምዓኒ ቃልየ አንስትያየ ወአፅምዓኒ ነገርየ ፡ እስመ ብእሴ ቀተልኩ በቍስልየ ወወሬዛ በጸልእየ ። | ፳፫ | ላሜህም ሚስቶቹን ሐዳንና ሲላን እንዲህ አላቸው ፡ ሚስቶቼ ፤ ቃሌን ስሙኝ ነገሬንም አዳምጡኝ ፡ በቍስሉ ሰውን ፡ በስብራቱ ጐልማሳውን ገድያለሁና ። ዘፀ. ፳፩ ፡ ፳፭ ። |
| እስመ ስብዓ ይትቤቀሉ በቃየል ፡ ወበላሜህሰ ስብዐ ስለ ስብዕ ። | ፳፬ | በቃየል ሰባት ዕዕፍ ይበቀላሉና ፡ በላሜህ ግን ሰባት ጊዜ ሰባት ይሆናል ። ዘፍ. ፬ ፡ ፲፭ ። |
| ወአእመራ አዳም ካዕበ ለብእሲቱ ወፀንሰት ወወለደት ሎቱ ወልደ ወሰመዮ ስሞ ሴት ፡ እንዘ ትብል አንሥአ ሊተ እግዚአብሔር እግዚእየ ዘርአ ካልአ ህየንተ አቤል ዘቀተሎ ቃየል ። | ፳፭ | አዳምም ዳግመኛ ሚስቱን አወቃት ፀነሰች ፡ ወንድ ልጅም ወለደች ፡ ስሙንም ሴት አለችው ፡ ቃየል ስለ ገደለው ስለ አቤል ፈንታ ጌታዬ እግዚአብሔር ሌላ ልጅ ተካልኝ ስትል ። ዘፀ. ፲፰ ፡ ፬ ። |
| ወሴትሂ ወለደ ወልደ ወሰመየ ስሞ ሄኖስ ፡ ወውእቱ ዘአኀዘ ከመ ይጸውዕ ስመ እግዚአብሔር ። | ፳፮ | ሴትም ወንድ ልጅ ወለደ ስሙንም ሄኖስ አለው ፡ እሱም የእግዚአብሔርን ስም ሊጠራ የጀመረ ነው ። |

ምዕራፍ ፭ ።

ምዕራፍ ፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዝ መጽሐፈ ፍጥረተ እጓለ እመሕያው ፡ ወበዕለተ አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም በአምሳለ እግዚአብሔር ገብሮሙ ተባዕተ ወአንስተ ወባረኮሙ ። | ፩ | ይህ የሰው የመፈጠሩ መጽሐፍ ነው ፡ እግዚአብሔር አዳምን በእግዚአብሔር አምሳል በፈጠረው ቀን ወንድና ሴት አደረጋቸው ፡ ባረካቸውም ። |
| ወሰመየ ስሞ አዳም በዕለት እንተ ባቲ ፈጠሮሙ ። | ፪ | በፈጠራቸው ቀን አዳም ብሎ ጠራው ። |
| ወሐይወ አዳም ፪፻ወ፴ ዓመተ ወወለደ ዘከመ ራእዩ ወዘከመ አምሳሊሁ ወሰመየ ስሞ ሴት ። | ፫ | አዳምም ፪፻፴ ዓመት ኖረ ፡ በመልክ የሚመስለውን ልጅ ወለደ ፡ ስሙንም ሴት አለው ። ዘፍ. ፬ ፡ ፳፭ ። |
| ወኮነ መዋዕሊሁ ለአዳም ዘሐይወ እምድኅረ ወለዶ ለሴት ፯፻ ክረምተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ። | ፬ | ሴትንም ከወለደው በኋላ አዳም የኖረው ዘመን ፯፻ ዓመት ሆነ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችን ወለደ ። ዘፍ. ፭ ፡ ፴፪ ። ፩ ዜና. ፩ ፡ ፬ ። |
| ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለአዳም ፱፻ወ፴ ዓመተ ፡ ወሞተ ። | ፭ | የአዳም ዘመኑ ሁሉ ፱፻፴ ዓመት ሆነ ፡ ሞተም ። ዘፍ. ፫ ፡ ፲፱ ። |
| ወሐይወ ሴት ፪፻ወ፭ ዓመተ ወወለዶ ለሄኖስ ። | ፮ | ሴትም ፪፻፭ ዓመት ኖረ ፡ ሄኖስንም ወለደው ። ዘፍ. ፬ ፡ ፳፮ ፡ |
| ወሐይወ ሴት እምድኅረ ወለዶ ለሄኖስ ፯፻ወ፯ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ። | ፯ | ሄኖስንም ከወለደ በኋላ ሴት ፯፻፯ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ። |
| ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለሴት ፱፻፲ወ፪ ዓመተ ፡ ወሞተ ። | ፰ | የሴትም መላ ዘመኑ ፱፻፲፪ ዓመት ሆነ ፡ ሞተ ። |
| ወሐይወ ሄኖስ ፻ወ፺ ዓመተ ወወለዶ ለቃይናን ። | ፱ | ሄኖስም ፻፺ ዓመት ኖረ ፡ ቃይናንንም ወለደው ። |
| ወሐይወ ሄኖስ እምድኅረ ወለዶ ለቃይናን ፯፻፲ወ፭ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ። | ፲ | ቃይናንንም ከወለደ በኋላ ፡ ሄኖስ ፯፻፲፭ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ። |
| ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለሄኖስ ዘሐይወ ፱፻ወ፭ ዓመተ ፡ ወሞተ ። | ፲፩ | ሄኖስ የኖረው መላ ዘመኑ ሁሉ ፱፻፭ ዓመት ሆነ ፡ ሞተ ። |
| ወሐይወ ቃይናን ፻ወ፸ ዓመተ ወወለዶ ለመላልኤል ። | ፲፪ | ቃይናንም ፻፸ ዓመት ኖረ ፡ መላልኤልንም ወለደው ። |
| ወሐይወ ቃይናን እምድኅረ ወለዶ ለመላልኤል ፯፻ወ፵ ዓመተ ፡ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ። | ፲፫ | መላልኤልንም ከወለደው በኋላ ቃይናን ፯፻፵ ዓመትን ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ። |
| ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለቃይናን ፱፻ወ፲ ዓመተ ፡ ወሞተ ። | ፲፬ | የቃይናንም መላ ዘመኑ ሁሉ ፱፻፲ ዓመት ሆነ ፡ ሞተ ። |
| ወሐይወ መላልኤል ፻፷ወ፭ ዓመተ ወወለዶ ለያሬድ ። | ፲፭ | መላልኤልም ፻፷፭ ዓመት ኖረ ፡ ያሬድንም ወለደው ። |
| ወሐይወ መላልኤል እምድኅረ ወለዶ ለያሬድ ፯፻ወ፴ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ። | ፲፮ | መላልኤልም ያሬድን ከወለደው በኋላ ፯፻፴ ዓመት ኖረ ፡ ወንዶች ልጆችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ ። |
| ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለመላልኤል ፰፻፺ወ፭ ዓመተ ፡ ወሞተ ። | ፲፯ | የመላልኤልም መላ ዘመኑ ሁሉ ፰፻፺፭ ዓመት ሆነ ፡ ሞተ ። |
| ወሐይወ ያሬድ ፻፷ወ፪ ዓመተ ፡ ወወለዶ ለሄኖክ ። | ፲፰ | ያሬድም ፻፷፪ ዓመት ኖረ ፡ ሄኖክንም ወለደው ። ይሁ. ፩ ፡ ፲፬ ። |

፲፱ ወሐይወ ያሬድ እምድኅረ ወለዶ ለሄኖክ ፰፻ ዓመተ፤ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ።
ያሬድም ሄኖክን ከወለደ በኋላ፤ ፰፻ ዓመት ኖረ፤ ወንዶች ልጆችንና ሴቶች ልጆችንም ወለደ።

፳ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለያሬድ ፱፻፷ወ፪ ዓመተ፤ ወሞተ።
ያሬድም መላ ዘመኑ ሁሉ ፱፻፷፪ ዓመት ሆነ፤ ሞተ።

፳፩ ወሐይወ ሄኖክ ፻፷ወ፭ ዓመተ፤ ወወለዶ ለማቱሳላ።
ሄኖክም ፻፷፭ ዓመት ኖረ፤ ማቱሳላንም ወለደው።

፳፪ ወአሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሔር፤ ወሐይወ ሄኖክ እምድኅረ ወለዶ ለማቱሳላ ፪፻ ዓመተ፤ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ።
ሄኖክም እግዚአብሔርን አገለገለው፤ ማቱሳላንም ከወለደው በኋላ ሄኖክ ፪፻ ዓመት ኖረ፤ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ። ዘፍ. ፭፥ ፳፬። ፮፥፱።

፳፫ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለሄኖክ ፫፻፷ወ፭ ዓመተ።
የሄኖክ መላ ዘመኑ ሁሉ ፫፻፷፭ ዓመት ሆነ።

፳፬ ወአሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሔር ወኢተረክበ፤ እስመ እግዚአብሔር ነሥኦ።
ሄኖክም እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው፤ እግዚአብሔር ወሰደታልና አልተገኘም። ፪ ነገ ፪፥ ፲፩። ዕብ. ፲፩፥ ፭።

፳፭ ወሐይወ ማቱሳላ ፻፹ወ፯ ዓመተ፤ ወወለዶ ለላሜሕ።
ማቱሳላም ፻፹፯ ዓመት ኖረ፤ ላሜሕንም ወለደው።

፳፮ ወሐይወ ማቱሳላ እምድኅረ ወለዶ ለላሜሕ ፯፻፹ወ፪ ዓመተ፤ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ።
ላሜሕንም ከወለደው በኋላ ማቱሳላ ፯፻፹፪ ዓመት ኖረ፤ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ።

፳፯ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለማቱሳላ ፱፻፷ወ፱ ዓመተ፤ ወሞተ።
የማቱሳላንም መላ ዘመኑ ሁሉ ፱፻፷፱ ዓመት ሆነ፤ ሞተ።

፳፰ ወሐይወ ላሜሕ ፻፹ወ፰ ዓመተ ወወለደ ወልደ።
ላሜሕም ፻፹፰ ዓመት ኖረ፤ ወንድ ልጅም ወለደ።

፳፱ ወሰመዮ ስሞ ኖኅ፤ ወይቤ ዝንቱ ሀለዎ ያዕርፈኒ እምቅኔየ ወእምኀዘንየ ዘእምንዳቤየ ወእምድር እንተ ረገማ እግዚአብሔር።
ስሙንም ኖኅ አለው፤ ከድካሜ በእጄ ከመጣሁት ኀዘን እግዚአብሔር ከረገማት ምድርም ያሳርፈኛል ብሎ። ዘፍ. ፫፥ ፲፯ - ፲፱።

፴ ወሐይወ ላሜሕ እምድኅረ ወለዶ ለኖኅ ፭፻፷ወ፭ ዓመተ፤ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ።
ኖኅንም ከወለደው በኋላ ላሜሕ ፭፻፷፭ ዓመት ኖረ፤ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ።

፴፩ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለላሜሕ ፯፻፶ወ፫ ዓመተ፤ ወሞተ።
የላሜሕ መላ ዘመኑ ሁሉ ፯፻፶፫ ዓመት ሆነ፤ ሞተ።

፴፪ ወኮነ ለኖኅ ፭፻ ዓመተ፤ ወወለደ ኖኅ ፫ ደቂቀ፤ ዘውእቶሙ ሴም፤ ወካም፤ ወያፌት።
ለኖኅም ፭፻ ዓመት ሆነው፤ ኖኅም ፫ ልጆችን ወለደ፤ እነርሱም ሴም፤ ካም፤ ያፌት፤ ናቸው። ዘፍ. ፲፥ ፩።

## ምዕራፍ ፮።

፩ ወኮነ ሶበ አኀዙ ይብዝኁ ደቂቀ ሰብእ በዲበ ምድር ተወልዳ ሎሙ አዋልድ ላህያት።
የሰው ልጆች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤ መልከ መልካም ቈንጆች ተወለዱላቸው።

፪ ወሶበ ርእዩ ደቂቀ እግዚአብሔር ከመ ሠናያት እማንቱ አዋልደ ሰብእ፤ ነሥኡ ሎሙ አንስትየ እምእለ ኀረዩ።
የእግዚአብሔር ልጆችም የሰው ሴቶች ልጆች መልከ መልካሞች እንደሆኑ በዩ ጊዜ ከመረጧቸው ለያንዳንዳቸው ሴቶችን ወሰዱ። ዘዳ. ፯፥፫-፬። ኢያ. ፩፥ ፯። ፪፥፩።

፫ ወይቤ እግዚአብሔር ኢይነብር መንፈስየ ላዕለ እጓለ እመሕያው ለዓለም እስመ ዘሥጋ እሙንቱ፤ ወይኩን መዋዕሊሆሙ ፻ወ፳ ዓመተ።
እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም ሥጋውያን ናቸውና፤ ዘመናቸውም ፻፳ ዓመት ይሁን። መዝ. ፸፯፥ ፴፱። ገላ. ፭፥ ፲፯።

፬ ወሀለዉ እለ ያርብሕ በእማንቱ መዋዕል ውስተ ምድር፤ ወእምድኅሬሁኒ ሶበ ቦኡ ደቂቀ እግዚአብሔር ኀበ አዋልደ ሰብእ ወለዳ ሎሙ፤ ወእሙንቱኒ ኮኑ እለ ያርብሕ እለ እምፍጥረተ ዓለም እደው እለ አስመዩ ስመ።
በዚያ ወራት በምድር ላይ አርበኞች ነበሩ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሰው ልጆች በገቡ ጊዜ ወለዱላቸው፤ እነርሱም አርበኞች ከቀድሞ ጀምሮ ስማቸውን ያስጠሩ ጀግኖች ሆኑ።

፭ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ በዝኀ እከዮሙ ለእጓለ እመሕያው ላዕለ ምድር ወበኵሉ ጊዜ ውስተ እኪት ወኵሉ ሕሊናሆሙ ውስተ እከይ እምንእሶሙ በኵሉ መዋዕሊሆሙ።
እግዚአብሔርም የሰው ልጆች ኃጢአት በምድር ላይ እንደበዛ በየጊዜውም ወደ ክፋት እንደሚሄዱ ከሕፃንነታቸውም ጀምሮ ባለ በዘመናቸው ሁሉ ሐሳባቸው ወደ ክፋት እንደሚያዘነብል በየ ጊዜ።

፮ ወነስሐ እግዚአብሔር እስመ ገብሮ ለእጓለ እመሕያው ላዕለ ምድር።
ሰውን በምድር ላይ ስለ ፈጠረው እግዚአብሔር ተፀፀተ።

፯ ወሐለየ ወይቤ እግዚአብሔር እደመስሶ ለእጓለ እመሕያው ዘገበርክዎ እምገጸ ምድር እምሰብእ እስከ እንስሳ ወአራዊት ወአዕዋፈ ሰማይ ወዘይትሐወስ፤ እስመ ነሳሕኩ ዘገበርክዎ።
እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ አሰበ የፈጠርኩትን ሰው ከምድር ገጽ እደመስሰዋለሁ፤ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ አራዊትን ወፎችን የሚንቀሳቀሰው ሳይቀር ስለ ፈጠርኩት ተፀፅቻለሁና።

| | | |
|---|---|---|
| ወኖኅሰ ረከበ ሞገሰ በቅድመ እግዚአብሔር ። | ፰ | ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት በለሟልነትን አገኘ ። ዘፍ. ፲፱ ፡ ፲፱ ። ዘፀ ፴፫ ፡ ፲፪ ። ሉቃ. ፩ ፡ ፴ ። ዮሐ. ፮ ፡ ፵፯ ። |
| ወከመዝ ውእቱ ፍጥረቱ ለኖኅ ወብእሲ ጻድቅ ውእቱ ወፍጹም ፡ ወእምልደቱ አሥመሮ ለእግዚአብሔር ። | ፱ | የኖኅም ፍጥረቱ እንዲህ ነው ፡ ጻድቅ ሰው ፍጹም ነበር ከመወለዱ ጀምሮ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው ። ዘፍ. ፭ ፡ ፳፪ - ፳፬ ። ሕዝ ፲፬ ፡ ፲፬ - ፳ ። ፪ ጴጥ. ፪ ፡ ፭ ። |
| ወወለደ ኖኅ ፫ ደቂቀ ሴም ፡ ወካም ፡ ወያፌት ። | ፲ | ኖኅም ፫ ልጆችን ወለደ ሴም ፡ ካም ፡ ያፌት ። |
| ወማሰነት ምድር በቅድመ እግዚአብሔር ወመልአት ዐመፃ ። | ፲፩ | ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች ፡ ኃጢአትንም ተመላች ። ዘፍ. ፲፰ ፡ ፳፩ ። መዝ. ፲፬ ፡ ፪ ። ፶፫ ፡ ፪ - ፫ ። |
| ወርእየ እግዚአብሔር ለምድር ከመ ማሰነት ወከመ አማሰኑ ፍኖቶሙ በዲበ ምድር ኵሉ ዘሥጋ ። | ፲፪ | እግዚአብሔርም ምድርን እንደተበላሸች አየት ፡ ሥጋ የለበሱ ሁሉ ሥራቸውን በምድር ላይ እንዳበላሹ አየ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር አምላኩ ለኖኅ ጊዜሁ ለእጓለ እመሕያው በጽሐ ቅድሜየ እስመ መልአ ዐመፃ ዲበ ምድር እምኔሆሙ ፡ ወናሁ አነ አደመስሶሙ እምድር ። | ፲፫ | እግዚአብሔር አምላኩ ኖኅን እንዲህ አለው ፡ የሰው ጊዜው በፊቴ ደረሰ ፡ ከእነሱ የተነሣ በምድር ላይ ኃጢአት በዝቶአልና እነሆ እኔም ከምድር አጠፋቸዋለሁ ። ሕዝ. ፯ ፡ ፪ ። ፫ ፡ ፮ ። |
| ወግበር ለከ ታቦተ እንተ ዕፀ ርብዕተ ወትቀብኦ እንተ ውስጣ ወእንተ አፍአሃኒ በፒሳ ። | ፲፬ | አራት መዓዝን አድርገህ ላንተ የዕንጨት መርከብን ሥራ ፡ አዳሪዋንና ውስጧንም የዶሮ ማር ሙጫ ቅባት አለው ። |
| ወከመዝ ትገብራ ፫፻ተ በእመት ኑኃ ፡ ወ፶ በእመት ርኅባ ፡ ወ፴ በእመት ቆማ ። | ፲፭ | አቈልቋይዋን ፫፻ ፡ ወርድዋንም ፶ ፡ ቁመትዋን ፴ ክንድ አድርገህ ሥራት አለው ። |
| ወመስኮተ ግበር ለይእቲ ታቦት ፡ ወሰበ በጽሐት ለተፈጽሞ አሐቲ እመት እንዘ ትተርፍ ግበር ሀየ ኖኅተ ውስተ ገቦሃ ወግበር ላቲ መዓርጋተ ተጽራሐ ወተሥላሰ ግበር ። | ፲፮ | ለዚያችም መርከብ መስኮት አውጣላት ፡ አንዲት ክንድ ስትቀር ለመጨረስም በደረሰች ጊዜ በዚያ የጐድን ደጃፍ አውጣላት ፡ የአዳራሽነትዋ እርከንን ሥራላት ሦስት ክፍል አድርገህ ሥራት ። |
| ወናሁ አነ አመጽእ ማየ አይኅ በዲበ ምድር ወእደመስስ ኵሎ ዘሥጋ ዘበ መንፈሰ ሕይወት ዘሀሎ ላዕለ ምድር ፡ ወዘሀሎ መትሕተ ሰማይ ወይመውት ኵሉ ዘሥጋ ። | ፲፯ | እነሆ እኔ የጥፋት ውኃን በምድር ላይ አመጣለሁ ፡ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ የሚኖረውን የሕይወት እስትንፋስ ያለውን ሥጋ የለበሰውን ሁሉ አጠፋለሁ ፡ ሥጋ የለበሰውም ሁሉ ይሞታል ። |
| ወአቀውም ኪዳንየ ምስሌከ ወትበውእ አንተ ውስተ ታቦት ወብእሲትከ ወደቂቅከ ወአንስትያ ደቂቅከ ምስሌከ። | ፲፰ | ከአንተ ጋራም ኪዳኔን አፀናለሁ ፡ አንተ ወደ መርከብ ትገባለህ ፡ ሚስትህ ፡ ልጆችህ ፡ የልጆችህም ሚስቶች ካንተ ጋራ ። |
| ወእምኵሉ እንስሳ ወአዕዋፍ ወዘይትሐወስ ፡ ወእምኵሉ አራዊት ወእምኵሉ ዘሥጋ ታበውእ ምስሌከ ውስተ ታቦት ተባዕተ ወአንስተ ። | ፲፱ | ከእንስሳ ከወፎች ከሚንቀሳቀሰው ሁሉ ፡ ሥጋ ከለበሰው ሁሉ ወንድና ሴትን ይዘህ ትገባለህ ። |
| እምኵሉ አዕዋፍ ዘይትሐወስ በበዘመዱ ፡ ወእምኵሉ እንስሳ በበዘመዱ ፡ ወእምኵሉ አራዊተ ምድር በበዘመዱ ፡ ይበውኡ ኀቤከ በበክልኤቱ ከመ ይሴሰዩ ምስሌከ ተባዕተ ወአንስተ ። | ፳ | ከወፍ እንደ ወገኑ ፡ ከእንስሳም እንደወገኑ ፡ ከምድር ተንቀሳቃሽም ሁሉ እንደወገኑ ፡ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወንድና ሴት ካንተ ጋር ይመገቡ ዘንድ ወደ አንተ ይግቡ ። |
| ወንሣእ ለከ እምነ ኵሉ መባልዕት ዘይሴሰዩ ፡ ወአስተጋብእ ኀቤከ ወይኩንከ መብልዐ ለከ ወለኵሎሙ አራዊት ወእንስሳ ። | ፳፩ | ከሚመገቧቸው መብሎች ሁሉ አግባ ፡ በንተ ዘንድ አኑር ፡ ላንተ ምግብ ይሆንልሃል ለአውሬዎችም ለከብቶችም ሁሉ ። |
| ወገብረ ኖኅ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር አምላኩ ። | ፳፪ | ኖኅም ፈጣሪው እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ። ዘፀ. ፵ ፡ ፫ - ፮ ። ዕብ. ፲፩ ፡ ፯ ። |

ምዕራፍ ፯ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ባእ አንተ ወኵሉ ቤትከ ውስተ ታቦት ፡ እስመ ኪያከ ረከብኩ ጻድቀ በቅድሜየ በዛቲ ትውልድ ። | ፩ | እግዚአብሔርም ኖኅን በዚች ትውልድ በፊቴ አንተን ደግ ሰው አግኝቻለሁና አንተ ከወገኖችህ ሁሉ ጋራ ወደ መርከብ ግባ አለው ። ማቴ. ፳፬ ፡ ፴፰ - ፴፱ ። ሉቃ. ፲፯ ፡ ፳፮ - ፳፯ ። |
| ወእምእንስሳ ዘንጹሕ አብእ ምስሌከ ሰብዓተ ሰብዓተ | ፪ | ከንጹሐን እንስሳት ሰባት ሰባት ተባትና እንስት አድርግ |

ተባዕተ ወአንስተ ፡ ወእምእንስሳ ዘኢኮነ ንጹሐ ክልኤተ ክልኤተ ተባዕተ ወአንስተ ።
ንህ ከአንተ ጋር አግባ ፡ ንጹሐን ካልሆኑ እንስሳት ደግሞ ሁለት ሁለት ተባትና እንስት ። ዘፍ. ፰ ፡ ፩ ። ዘሌ. ፲፩ ፡ ፩ ።

፫ ወእምነ አዕዋፈ ሰማይ ዘንጹሕ ሰብዐተ ሰብዐተ ተባዕተ ወአንስተ ፡ ወእምነ አዕዋፈ ሰማይ ዘኢኮነ ንጹሐ ክልኤተ ክልኤተ ተባዕተ ወአንስተ ፡ ዘትሴሲይ ወበይከውን ዘርእ በዲበ ምድር ።
ከንጹሐን የሰማይ ወፎች ሰባት ሰባት ተባትና እንስት ፡ ንጹሐን ካልሆኑ የሰማይ ወፎችም ሁለት ሁለት ተባትና እንስት የምትመገበው በምድር ላይ ዘር የሚሆን ።

፬ እስመ እስከ ሰቡዕ መዋዕል አመጽእ ዝናመ ዲበ ምድር ፵ ዕለተ ወ፵ ሌሊተ ወእደመስስ ኵሎ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ።
እስከ ሰባት ቀን ድረስ በምድር ላይ ዝናምን አመጣለሁ ፡ ፵ ቀን ፵ ሌሊት ይዘንማል ፡ በምድር ላይ የሚኖረውንም ሁሉ አጠፋለሁ ።

፭ ወገብረ ኖኅ ኵሎ ዘአዘዞ እግዚአብሔር አምላክ ።
ኖኅም እግዚአብሔር አምላክ ያዘዘውን ሁሉ አደረገ ። ዘፍ. ፮ ፡ ፳፪ ።

፮ ወእሚሁ ኮኖ ለኖኅ ፮፻ ዓመተ ፡ ወመጽአ ማየ አይኅ ላዕለ ኵሉ ምድር ።
የዚያን ጊዜ ለኖህ ፮፻ ዓመት ሁኖት ነበር ፡ የጥፋት ውኃም በምድር ላይ ሁሉ መጣ ።

፯ ወቦአ ኖኅ ወብእሲቱ ወደቂቁ ወአንስትያ ደቂቁ ምስሌሁ ውስተ ታቦት በእንተ ማየ አይኅ ።
ኖኅም ወደ መርከብ ገባ ሚስቱ ልጆቹና የልጆቹ ሚስቶችም ከእርሱ ጋር ገቡ ፡ ከጥፋት ውኃ ለመዳን ።

፰ ወእምአዕዋፍ ዘንጹሕ ወዘኢኮነ ንጹሐ ፡ ወእምእንስሳ ዘንጹሕ ወዘኢኮነ ንጹሐ ፡ ወእምኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ።
ከንጹሐን አዕዋፍና ንጹሐን ካልሆኑትም ከንጹሐን እንስሳና ንጹሐን ካልሆኑትም በምድር ላይ ከሚኖረው ሁሉ ።

፱ ቦኡ ኀበ ኖኅ ውስተ ታቦት ተባዕት ወአንስት በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለኖኅ ።
እግዚአብሔር ኖኅን እንዳዘዘው ወንድና ሴት እየሆኑ ወደ ኖኅ ወደ መርከብ ውስጥ ገቡ ።

፲ ወኮነ እምድኅረ ሰቡዕ መዋዕል መጽአ ማየ አይኅ ላዕለ ኵሉ ምድር ።
ከሰባት ቀንም በኋላ እንዲህ ሆነ ፡ በምድር ላይ ሁሉ የጥፋት ውኃ መጣ ።

፲፩ አመ ኮነ ፮፻ ዓመተ ሕይወቱ ለኖኅ በካልእ ወርኅ አመ ፲ወ፯ ፡ አመ ፲ወ፯ ለጽልመት ፡ ወበይእቲ ዕለት ተሠጥቁ ኵሉ ቀላያት ወተርኅወ አስራበ ሰማይ ።
የኖኅ ዕድሜ ፮፻ ዓመት በሆነ ጊዜ በሁለተኛው ወር ጨረቃ፤ ሠርቅ በደረገች በ፲፯ኛው ወይም በ፲፯ኛው ቀን በምድር ላይ የጥፋት ውኃ ሆነ ፡ በዚያች ቀን ምንጮች ሁሉ ተነደሉ ፡ የሰማይ መሸረብ ተከፈተ ። ዘፍ. ፰ ፡ ፪ ። ፪ ነገ. ፯ ፡ ፲፱ ። ምሳ ፰ ፡ ፳፰ ። ኢሳ. ፲፬ ፡ ፲፰ ።

፲፪ ወኮነ ዝናም ላዕለ ምድር ፵ ዕለተ ወ፵ ሌሊተ ።
በምድር ላይ ፵ ቀን ፵ ሌሊት ዝናም ሆነ ።

፲፫ ወበይእቲ ዕለት ቦአ ኖኅ ወሴም ወካም ወያፌት ደቂቁ ወብእሲቱ ወአንስትያ ደቂቁ ውስተ ታቦት ።
በዚያች ቀን ኖኅ ልጆቹ ሴም ካም ያፌትም ሚስቱም የልጆቹ ሚስቶችም ወደ መርከብ ገቡ ።

፲፬ ወአራዊትኒ በበዘመዱ ፡ ወኵሉ እንስሳ በበዘመዱ ፡ ወዘይትሐወስ ወአዕዋፍ በበዘመዱ ።
አውሬዎችም በየወገናቸው ፡ እንስሳትም ሁሉ በየወገናቸው ፡ የሚንቀሳቀሱም ወፎችም በየወገናቸው ።

፲፭ ቦኡ ውስተ ታቦት ኀበ ኖኅ እምነ ኵሉ ዘሥጋ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ።
ሥጋ ከለበሰው ሁሉ የሕይወት እስትንፋስ ያላቸው ወደ ኖኅ ወደ መርከብ ውስጥ ገቡ ። ዘፍ. ፮ ፡ ፳ ።

፲፮ ቦኡ ተባዕት ወአንስት እምነ ኵሉ ዘሥጋ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለኖኅ ፡ ወዐጸዋ እግዚአብሔር ለታቦት እምአፍአሃ ።
እግዚአብሔር ኖኅን እንዳዘዘው ሥጋ ከለበሰው ሁሉ ተባትና እንስት እየሆኑ ገቡ ፡ እግዚአብሔርም መርከቢን በውጭ በኩል ዘጋት ። መሰ. ፱ ፡ ፶፩ ።

፲፯ ወኮነ አይኅ ላዕለ ምድር ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ ፡ ወመልአ ማይ ወአልዐላ ለታቦት ወተለዐለት እምድር ።
በምድር ላይ ፵ ቀን ፵ ሌሊት የጥፋት ውኃ ዘነመ ፡ ውኃውም መልቶ መርከቢቱን አንሳፈፋት ፡ ምድርንም ለቀቀች ።

፲፰ ወፀንዐ ማይ ጥቀ ላዕለ ምድር ወበዝኀ ፡ ወጸለለት ይእቲ ታቦት ላዕለ ማይ ።
ውኃውም በምድር ላይ እጅግ በረታ በዛ ፡ መርከቢቱም በውኃው ላይ ተንሳፈፈች ።

፲፱ ወፈድፈደ በዝኀ ጥቀ ማይ ዲበ ምድር ፡ ወከደነ ኵሎ አድባረ ነዋኃተ ዘመትሕተ ሰማይ ።
ውኃውም በምድር ላይ እጅግ በዛ ፡ ከሰማይ በታች ያሉትን ረጃጅም ተራራዎችን ሁሉ ሸፈነ ።

፳ ፲ወ፭ እመተ ተለዐለ መልዕልቶሙ ማይ ።
ውኃውም በላያቸው ፲፭ ክንድ ያህል ከፍ ከፍ አለ ።

፳፩ ወሞተ ኵሉ ዘሥጋ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር እምነ አዕዋፍ ወእምነ እንስሳ ወእምነ ኵሉ አራዊተ ምድር ወኵሉ እጓለ እመሕያው ።
ሥጋ የለበሰ ሁሉ ከአዕዋፍ ከእንስሳት ከምድር አራዊት ሁሉ በምድር የሚኖረውና ሰውም ሁሉ ሞተ ።

፳፪ ወኵሉ ዘመንፈስ ወኵሉ ዘሀሎ ላዕለ የብስ ሞተ ።
በሕይወት የነበረ በየብስ ያለ ሁሉ ሞተ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወተደምሰሰ ኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ገጸ ምድር እምእጓለ እመሕያው እስከ እንስሳ ወአዕዋፈ ሰማይ ፡ ወተርፈ ኖኅ ባሕቲቱ ወእለ ገብኡ ምስሌሁ ውስተ ታቦት ። | ፳፫ | ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳና እስከ ሰማይ ወፎችም ድረስ በምድር ላይ የሚኖረው ሁሉ ጠፋ ፡ ኖኅ ብቻውን ቀረ ፡ ወደ መርከብ ከእርሱ ጋራ የገቡትም ብቻ ። |
| ወተለዐለ ማይ መልዕልተ ምድር ፻ወ፶ ዕለተ ። | ፳፬ | ውኃውም ፻፶ ቀን በምድር ላይ ተንሰፈፈ ። |
| ምዕራፍ ፰ ። | | ምዕራፍ ፰ ። |
| ወተዘከሮ እግዚአብሔር ለኖኅ ወለኵሉ አራዊት ወለ ኵሉ እንስሳ ወለኵሉ ዘሀሎ ምስሌሁ ውስተ ታቦት ፡ ወአ ምጽአ እግዚአብሔር ነፋሰ ላዕለ ምድር ወነትገ ማይ ። | ፩ | እግዚአብሔርም ኖኅን አሰበው ፡ አውሬዎችንም ሁሉ ከብቶችንም ሁሉ ከሱ ጋራ በመርከብ ያለውንም ሁሉ ፡ እግዚአብሔርም ነፋስን በምድር ላይ አመጣ ውኃውም ጐደለ ። ዘፍ. ፲፱ ፡ ፲፱ ። ዘፀ. ፪ ፡ ፳፬ ። ፩ ሳሙ. ፩ ፡ ፲፱ ። |
| ወተበዕወ አንቅዕተ ቀላይ ወአስራበ ሰማይኒ ተእኅዘ ፡ ወቆመ ዝናም እምሰማይ ። | ፪ | የቀላይ ምንጮች ተደፈኑ ፡ የሰማይም መስኮት ተገታ ፡ ከሰማይ የሚወርደውም ዝናም ቆመ ። |
| ወአኅዘ ይኅልቅ ማይ ወይሐውር እምነ ምድር ፡ ወእም ድኅረ ፻ወ፶ ዕለት ሐፀ ማይ ። | ፫ | ውኃውም እያለቀ ከምድር ይሸሽ ጀመር ፡ ከ፻፶ ቀን በኋላ ውኃው ጐደለ ። ዘፍ. ፯ ፡ ፳፬ ። ሕዝ. ፳ ፡ ፳፫ - ፴፩ ። ፪ ቆሮ. ፪ ፡ ፲፫ ። ኤፌ. ፭ ፡ ፪ ። |
| ወነበረት ይእቲ ታቦት በሳብዕ ወርኅ አመ ፳ወ፪ ፡ አመ ፲ወ፯ ለጽልመት ላዕለ ደብረ አራራት ። | ፬ | መርከቢቱም በሰባተኛው ወር በ፲፪ኛው ቀን በ፲፯ኛው ሠርቀ ሌሊት በአራራት ተራራ ላይ ዓረፈች ። |
| ወማይሰ የሐፅፅ ወይነትግ እስከ ፲ቱ ወርኅ ፡ ወአመ ኮነ ፲ወ፩ አውራኅ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ አስተርአዩ አርእስቲሆሙ ለአድባር ። | ፭ | ውኃው ግን እስከ ፲ኛው ወር ድረስ እየጐደለ ይሄድ ነበር ፡ ፲፩ ወር በሆነ ጊዜ ከወሩ በመጀመሪያው ቀን የተራራዎች ራሶቻቸው ታዩ ። |
| ወኮነ እምድኅረ ፵ ዕለት አርኀወ ኖኅ መስኮተ ለታቦት እንተ ገብረ ወፈነዎ ለቋዕ ከመ ይርአይ እመ ነትገ ማይ እምገጸ ምድር ። | ፮ | ከ፵ ቀን በኋላ እንዲህ ሆነ ፡ ኖኅ የሠራውን የመርከቢን መስኮት ከፈተ ፡ ውኃውም ከምድር ላይ ጐድሎ እንደሆነ ያይ ዘንድ ቍራን ላከው ። |
| ወሖረ ወኢገብአ እስከ አመ ኀልቀ ማይ እምነ ምድር ። | ፯ | ሄደ ግን ውኃው ከምድር እስከ አለቀ ድረስ አልተመለሰም ። |
| ወፈነዎ ለርግብ እምድኅሬሁ ከመ ትርአይ እመ ነትገ ማይ እምገጸ ምድር ። | ፰ | ከእሱ ቀጥሎም ርግብን ላከች ውኃው ከምድር ላይ ጐድሎ እንደሆነ ታይ ዘንድ ። |
| ወኢረከበት ኀበ ታዐርፍ እገሪሃ ወገብአት ኀቤሁ ው ስቴ ታቦት እስመ ማይ ሀሎ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር ፡ ወሰ ፍሐ እዴሁ ወነሥኣ ውስተ ታቦት ኀቤሁ ። | ፱ | እግሯንም የምታሳርፍበት ቦታ አላገኘችም ወደ እርሱ ወደ መርከብም ተመለሰች ፡ ውኃው በምድር ሁሉ ላይ ነበርና እጁን ዘርግቶ ወደ እርሱ ወደ መርከብ አገባት ። |
| ወተዐገሠ ሰቡዓ መዋዕለ ካዕበ ፈነዋ ለርግብ ውስተ ምድር ከመ ትርአይ ። | ፲ | ሰባት ቀንም ቈይቶ ምድርን ታይ ዘንድ ዳግመኛ ርግ ብን ላከች ። |
| ወገብአት ኀቤሁ ርግብ ፍና ሠርክ ወባቲ ውስተ አፉሃ ቈጽለ ዘይት ፡ ወአእመረ ኖኅ ከመ ነትገ ማይ እምነ ምድር ። | ፲፩ | ርግብም በማታ ጊዜ ወደሱ ተመለሰች በአፏም የዘ ይት ቅጠል ይዛ ነበር ፡ ኖኅም ውኃው ከምድር ላይ እንደ ጐደለ ዓወቀ ። |
| ወተዐገሠ ካዕበ ሰቡዐ መዋዕለ ፈነዋ ለርግብ ወኢደገ መት ገቢአ ኀቤሁ ። | ፲፪ | ሰባት ቀን ቈይቶ ዳግመኛም ርግብን ላከት ፡ እንደገና ወደ እሱ አልተመለሰችም ። |
| ወአመ ኮነ ፮፻ወ፩ ዓመተ ሕይወቱ ለኖኅ አመ ርእሰ ሠ ርቀ ወርኅ ቀዳማይ ኀልቀ ማይ እምድር ፡ ወከሠተ ኖኅ ጠፈራ ለታቦት እንተ ገብረ ወርእየ ከመ ኀልቀ ማይ እም ገጸ ምድር ። | ፲፫ | የኖኅም ዕድሜ ፮፻፩ ዓመት በሆነ ጊዜ በመጀመርያው ወደ መበቻ ውኃው ከምድር ተቋረጠ ፡ ኖኅም የሠራውን የመርከብ ድፍንት (ጣራ) ገለጠ ፡ ውኃውም ከምድር ላይ እንደ ደረቀ አየ ። |
| ወበካልእ ወርኅ አመ ፳፪ ለጽልመት የብሰት ምድር ። | ፲፬ | ጨረቃ ሠርቅ በደረገች በ፲፪ኛው ቀን በሁለተኛው ወር ምድር ደረቀች ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ፃእ እምነ ታቦት ። | ፲፭ | እግዚአብሔርም ኖኅን እንዲህ አለው ከመርከብ ውጣ ። |
| አንተ ወብእሲትከ ወደቂቅከ ወአንስትያ ደቂቅከ ወኵ ሉ ዘሀሎ ምስሌከ ። | ፲፮ | አንተ ሚስትህም ፡ ልጆችህም ፡ የልጆችህ ሚስቶችም ካንተ ጋራም ያለው ሁሉ ። |
| ወኵሉ ዘሥጋ እምአዕዋፍ እስከ እንስሳ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር አውፅእ ምስሌከ ፡ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምል እዋ ለምድር ። | ፲፯ | ከወፍ እስከ እንስሳ ድረስ ሥጋ የለበሰውን በምድር የሚኖረውንም ሁሉ ካንተ ጋር አውጣ ፡ ብዙ ተባዙ ምድ ርንም ምሏት ። ዘፀ. ፩ ፡ ፳፪ - ፳፰ ። |

፲፰ ወወፅአ ኖኅ ወብእሲቱ ወደቂቁ ወአንስትያ ደቂቁ ምስሌሁ ።
ኖኅም ወጣ ፡ ሚስቱ ልጆቹም ፡ የልጆቹ ሚስቶችም ከርሱ ጋራ ።

፲፱ ወኵሉ አራዊት ወእንስሳ ወአዕዋፍ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር በበዘመዱሙ ወፅኡ እምነ ታቦት ።
አውሬዎችም ሁሉ እንስሳትም ወፎችም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውም ሁሉ በየወገናቸው ከመርከብ ወጡ ።

፳ ወነደቀ ኖኅ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ፡ ወነሥአ እምእንስሳ ወእምነ አዕዋፍ ወእምኵሉ ዘንጹሕ ወአዕረገ ቍርባነ ዲበ ምሥዋዑ ።
ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ ፡ ከእንስሳት ፡ ከአዕዋፍ ንጹሕ ከሆነው ሁሉ መርጦ በመሠዊያው ላይ መሥዋዕትን አቀረበ ።

፳፩ ወአጼነወ እግዚአብሔር መዓዛ ሠናየ ፡ ወይቤ እግዚአብሔር ሐለይኩ ከመ ኢይድግም ረጊሞታ ለምድር በእንተ ምግባሩ ለእጓለ እመሕያው ፡ እስመ ሥዩም ውስተ ልቦሙ ለእጓለ እመሕያው እከይ በኵሉ ጊዜ እምንእሰሙ ፡ ወኢይደግም እንከ አማስኖቶ ለኵሉ ዘሥጋ ዘሕያው በከመ ገበርኩ ።
እግዚአብሔርም መልካም መዓዛን አሸተተ ፡ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ ስለ ሰው ክፋት ምድርን ሁለተኛ እንዳላጠፋ ተናገርኩ ። በሰዎች ልቡና ክፋት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ሁልጊዜ ፀንቶ ኑሯልና ከዚህ በፊት እንዳደረግሁት ሥጋ የለበሰውን በሕይወት ያለውን ሁሉ ዳግመኛ አላጠፋም ። ዘፀ. ፳፱ ፡ ፲፰ ። ፳፭ ፡ ፵፩ ። ዘሌ. ፩ ፡ ፱ ። ፲፫ ፡ ፲፯ ።

፳፪ ኵሉ መዋዕሊሃ ለምድር ዘርእ ወማእረር ፡ ቍር ወሐፍ ፡ ወሐጋይ ወክረምት ፡ መዓልት ወሌሊት ኢይትኃደግ ።
ምድር ፀንታ በምትኖርበት ዘመን ሁሉ ዘር መከር ፡ ቅዝቃዜና ሙቀት ፡ በጋና ክረምት ፡ መዓልትና ሌሊት አይቋረጥም ። ኢሳ. ፶፬ ፡ ፱ ። ኤር. ፴፫ ፡ ፳ ። ፳ ፡ ፳፭ ።

## ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወባረኮሙ እግዚአብሔር ለኖኅ ወለደቂቁ ፡ ወይቤሎሙ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር ወኰንንዋ ።
እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው እንዲህም አላቸው ፡ ብዙ ተባዙ ምድርን ምሏት ፡ ግዟት ። ዘፍ. ፩ ፡ ፳፪ - ፳፰ ።

፪ ወይፍርሁክሙ ወይርዓዱ እምኔክሙ ኵሉ አራዊተ ገዳም ወአዕዋፈ ሰማይ ወእንስሳ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር ወዓሣተ ባሕር ።
በምድረ በዳ የሚኖሩ አውሬዎች የሰማይ ወፎች እንስሳት ፡ በምድር ላይ የሚኖረውም ሁሉ ፡ የባሕር ዓሣም ይፍሩዋችሁ ፡ ከእናንተም የተነሣ ይራዱ ።

፫ ወሀብኩክሙ ውስተ እዴክሙ ፡ ወይኩንክሙ ለክሙ ኵሉ ዘይትሐወስ ዘሕያው ለክሙ ይኩንክሙ መብልዐ ከመ ሐመልማለ ማዕር ወሀብኩክሙ ኵሉ ።
በሕይወት ያለውን የሚንቀሳቀሰውን ሁሉ ለእናንተ ሀብት ይሆናችሁ ዘንድ በእጃችሁ ሰጥቻችኋለሁ ፡ እንደ እኽል ምግብ ይሁናችሁ ፡ ሁሉንም ሰጥቻችኋለሁ ። ዘዳ. ፲፪ ፡ ፲፭ ። ግብ. ሐዋ. ፲ ፡ ፲፪ - ፲፭ ። ሮሜ ፲፬ ፡ ፲፬ ።

፬ ወበሕቱ ኵሉ ሥጋ ዘበ ደም ኢትብልዑ ፡ እስመ ደም ነፍስክሙ ውእቱ ።
ነገር ግን ደም ያለበት ሥጋ ሁሉ አትብሉ ፡ ደም ሕይወታችሁ ነውና ።

፭ ወእትኃሠሥ እምእደ ኵሉ አራዊት ወእምኵሉ እደ ሰብእ ወእምእደ ብእሲ ዘእኍሁ እትኃሠሥ ነፍሰ ኵሉ እጓለ እመሕያው ።
የሰውን ሁሉ ነፍስ ፡ ከአራዊት ሁሉ ፡ ከሰውም ሁሉ ፡ ወንድሙንም ከወንድሙ እሻለሁ ። ዘፍ ፬ ፡ ፲ - ፲፩ ። ዘፀ. ፳፩ ፡ ፳፰ ።

፮ ዘከዐወ ደመ ሰብእ ህየንተ ደመ ዝክቱ ይትከዐው ደሙ ፡ እስመ በአምሳለ እግዚአብሔር ገበርክዎ ለሰብእ ።
የሰውን ደም ያፈሰሰ ስለ አፈሰሰው ስለዚያ ደም ፈንታ ደሙ ይፈሰል ፡ ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል ፈጥሬዋለሁና ። ዘፀ. ፳፩ ፡ ፲፪-፲፬ ። ዘሌ. ፳፬ ፡ ፲፯ ። ማቴ. ፳፯ ፡ ፲፪ ።

፯ ወአንትሙሰ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር ።
እናንተ ግን ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሏት ።

፰ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ወለደቂቁ ምስሌሁ እንዘ ይብል ።
እግዚአብሔርም ኖኅን ተናገረው ፡ ልጆቹንም ከእርሱ ጋር እንዲህ ብሎ ።

፱ ናሁ አነ አቀውም ኪዳንየ ምስሌክሙ ወምስለ ዘርእክሙ እምድኅሬክሙ ።
እኔ ከእናንተ ጋር ኪዳኔን አፀናለሁ ፡ በኋላም ከዘራችሁ ጋር ።

፲ ወምስለ ኵሉ ነፍሰ ሕያው እንተ ምስሌክሙ እምነ አዕዋፍ ወእንስሳ ወአራዊተ ምድር ዘወፅኡ ምስሌክሙ እምውስተ ታቦት አቀውም ኪዳንየ ምስሌክሙ ።
ከመርከብ ከወጡት ከአራዊት ፡ ከእንስሳት ፡ ከአዕዋፍ ወገን ከእናንተ ጋር ካለው የሕይወት እስትንፋስ ካለው ሁሉ ጋር ።

፲፩ ወኢይመውት እንከ ኵሉ ዘሥጋ በማየ አይኅ ፡ ወኢያመጽእ እንከ ማየ አይኅ ለአማስኖ ኵሉ ምድር ።
ከናንተ ጋራ ኪዳኔን አፀናለሁ ፡ እንግዲህ ወዲህ ሥጋ የለበሰ ሁሉ በጥፋት አይሞትም ፡ ምድርም ሁሉ ለማጥፋት እንግዲህ ወዲህ የጥፋት ውኃን አላመጣም ። ኢሳ. ፬ ፡ ፱ ።

፲፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ
እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው ፡ በናንተና በኔ መካ

| | | |
|---|---|---|
| ኪዳንየ ዘእሁበክሙ አነ ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ወማእከለ ኵሉ ነፍሰ ሕይወት እንተ ሀለወት ምስሌክሙ ለትውልድ ዘለዓለም ። | | ከል ከናንተ ጋራ ባለች ሕይወት ባለች ፍጥረት ሁሉ መከከል ለዘላለም ለትውልድ ፀንታ የምትኖር፡ እኔ የምሰጣችሁ የኪዳኔ ምልክት ይህ ነው ። |
| ቀስትየ እሠይም በደመና ወትከውን ተእምረ ለኪዳንየ ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ወማእከለ ምድር ። | ፲፫ | በናንተና በኔ መከከል በምድርም መከከል ለመሐላዬ ምልክት አድርጌ ቀስቴን በደመና አኖራለሁ ። |
| ወይከውን ሶበ አጼምን ደመና ላዕለ ምድር፡ ታስተርኢ ቀስትየ ላዕለ ደመና ። | ፲፬ | ደመናን በምድር በጋረድኩ ጊዜ እንዲህ ይሆናል፡ ቀስቴ በደመናው ላይ ትታያለች ። |
| ወእዜከር እንከ ኪዳንየ ዘሀሎ ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ወማእከለ ኵሉ ነፍሰ ሕይወት ወበኵሉ ዘሥጋ ኢያመጽእ እንከ ማየ አይኅ ከመ እደምስሶ ለኵሉ ዘሥጋ ። | ፲፭ | ከዚያ ወዲያ በናንተና በኔ መከከል ሕያው በሚሆን ሰውነት ሁሉ መከከል ያለ መሐላዬን አስቤ ሥጋዊ ፍጥረትን ሁሉ አጠፋው ዘንድ የጥፋት ውኃን በሥጋዊ ፍጥረት ሁሉ አላመጣም ። ዘሌዋ. ፳፯ ፡ ፴፪-፴፫ ። ሕዝ. ፲፬ ፡ ፳ ። |
| ወትወጽእ ቀስትየ ውስተ ደመና ወእሬእያ ከመ እዘከር ኪዳንየ ዘለዓለም በማእከሌየ ወማእከለ ኵሉ ዘሥጋ ዘበመንፈሰ ሕይወት ዘሀሎ መልዕልተ ምድር ። | ፲፮ | ቀስተ ኪዳኔ ከደመና ውስጥ ትወጣለች፡ በምድርም ላይ ባለ ሕይወት ባለው በሥጋዊ ፍጥረት ሁሉ መከከልና በኔ መከከል ያለ ለዘላለም ፀንቶ የሚኖር ኪዳኔንም አስብ ዘንድ እሷን እመለከታለሁ ። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፯ ። ፲፫ ፡ ፲፱ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ኪዳንየ ዘአቀውም ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ። | ፲፯ | እግዚአብሔር ኖኅን በናንተና በኔ መከከል የማፀናው የመሐላዬ ምልክት ይህ ነው አለው ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቁ ለኖኅ እለ ወፅኡ እምውስተ ታቦት፡ ሴም፡ ወካም፡ ወያፌት፡ ወካምሰ አቡሁ ውእቱ ለከነአን ። | ፲፰ | ከመርከብ የወጡ የኖኅ ልጆች እሊህ ናቸው፡ ሴም፡ ካም፡ ያፌት፡ ካም ግን የከነአን አባት ነው ። ዘፍ. ፲ ፡ ፯ ። |
| ወእሉ እሙንቱ ሠለስቱ ደቂቁ ለኖኅ እለ ተዘርዉ ውስተ ኵሉ ምድር ። | ፲፱ | በምድር ሁሉ ላይ የተበተኑ የኖኅ ልጆች እሊህ ናቸው ። |
| ወእምድኅረ አይኅ አኀዘ ኖኅ ይትገበራ ለምድር፡ ወተከለ ዐፀደ ወይን ። | ፳ | ከጥፋትም በኋላ ኖኅ ምድርን ይቈፍር ጀመረ፡ የወይን ተክልንም ተከለ ። |
| ወሰትየ እምኔሁ ወሰክረ ወተዐርቀ በውስተ ቤቱ ። | ፳፩ | ወይን ጠጥቶ ሰክሮ በድንኳኑ ውስጥ ተራቈተ ። |
| ወርእዮ ካም አቡሁ ለከነአን ዕርቃነ አቡሆሙ ሰሐቀ፡ ወወፂአ ወነገሮሙ ለክልኤሆሙ አኀዊሁ በአፍአ ። | ፳፪ | የከነአን አባት ካም የአባታቸውን ዕርቃን አይቶ ሳቀ፡ ወደ ውጭ ወጥቶም ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው ። |
| ወነሥኡ ሴም ወያፌት ልብሰ ወወደዩ ላዕለ ክልኤሆሙ ዲበ ዘባናቲሆሙ ወሖሩ ድኅሬተ ወከደኑ ዕርቃነ አቡሆሙ፡ ወገጾሙ ድኅሬሆሙ አግብኡ ወኢርእዩ ዕርቃነ አቡሆሙ ። | ፳፫ | ያፌትና ሴም ልብስ ወስደው ሁለቱም በትከሻቸው ላይ አደረጉ፡ የኋሊት ሄደው የአባታቸውን ዕርቃን ሸፈኑ፡ ፊታቸውን ወደ ኋላ አዞሩ (እንደገቡ ወጡ) የአባታቸውንም ዕርቃን አላዩም ። |
| ወሶበ ጽሕወ ኖኅ እምስካረ ወይኑ አእመረ ኵሎ ዘገብረ ሎቱ ወልዱ ዘይንእስ ። | ፳፬ | ኖኅም ከወይኑ ስካር በነቃ ጊዜ ታናሹ ልጁ ያደረገበትን ሁሉ ዐወቀ ። |
| ወይቤ ኖኅ ርጉመ ለይኩን ከነአን ወገብረ ወነባሬ ይኩን ለአኀዊሁ ። | ፳፭ | ኖኅም እንዲህ አለ ከነአን የተረገመ ይሁን ለወንድሞቹም ተገዥ አገልጋይ ይሁን ። |
| ወይቤ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ለሴም፡ ወይኩን ከነአን ገብሮ ። | ፳፮ | የሴም ፈጣሪ እግዚአብሔር ይመስገን፡ ከነአንም አገልጋዩ ይሁነው ። ዘፍ. ፱ ፡ ፳፯ ። ዕብ. ፲፩ ፡ ፲፯ ። |
| ወለያርኅብ እግዚአብሔር ብሔሮ ለያፌት፡ ወይኅድር ውስተ ቤቱ ለሴም፡ ወይኩን ከነአን ገብሮ ። | ፳፯ | እግዚአብሔር የያፌትን ሀገር ያስፋ፡ በሴም ቤትም ይደር፡ ከነአንም አገልጋዩ ይሁን ። ዘፍ. ፵፱ ፡ ፳ ። ፲፯ ፡ ፲፱ ። |
| ወሐይወ ኖኅ እምድኅረ አይኅ ፫፻ወ፶ ዓመተ ። | ፳፰ | ኖኅም ከጥፋት ውኃ በኋላ ፫፻፶ ዓመት ኖረ ። |
| ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለኖኅ ፱፻ወ፶ ዓመተ፡ ወሞተ ። | ፳፱ | የኖኅ ዘመን ሁሉ ፱፻፶ ዓመት ሆነ፡ ሞተ ። |
| **ምዕራፍ ፲ ።** | | **ምዕራፍ ፲ ።** |
| ወከመዝ ውእቱ ልደቶሙ ለደቂቀ ኖኅ ሴም፡ ወካም፡ ወያፌት፡ ወተወልዱ ሎሙ ደቂቅ እምድኅረ አይኅ ። | ፩ | የኖኅ ልጆች ትውልዳቸው እንዲህ ነው ሴም፡ ካም፡ ያፌት፡ ናቸው፡ ከጥፋት ውኃ በኋላም ልጆች ተወለዱላቸው ። |
| ወደቂቀ ያፌት፡ ጋሜር፡ ወያኅግ፡ ወማዴ፡ ወያህያን፡ ወቶቤል፡ ወሞሳሕ፡ ወቴርሳሕ ። | ፪ | የያፌት ልጆች ጋሜር፡ ያኅግ፡ ማዴ፡ ያህያን፡ ቶቤል፡ ሞሳሕ፡ ቴርሳሕ ናቸው ። ዘፍ. ፲፫ ፡ ፬-፭ ። ፩ ዜና. ፩ ፡ ፭-፯ ። ሕዝ. ፴፰ ፡ ፪-፫ ። ፴፱ ፡ ፩ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወደቂቀ ጋሜር ፡ አስከናዝ ፡ ወሪፋት ፡ ወቴርጋሞ ። | ፫ | የጋሜር ልጆች አስከናዝ ፡ ሪፋት ፡ ቴርጋሞ ናቸው ። ኤር. ፶፩ ፡ ፳፯ ። |
| ወደቂቀ ያውያን ኤሊሳዕ ፡ ወኤምትራሲስ ፡ ወቄጥኤ ፡ ወሮድኤ ። | ፬ | የያውያን ልጆች ኤሊሳዕ ፡ ኤምትራሲስ ፡ ቄጥኤ ፡ ሮድኤ ናቸው ። መዝ. ፸፩ ፡ ፲ ። ሕዝ. ፴፰ ፡ ፲፫ ። |
| ወእምኔ እሉ ተፈልጡ ደሰያቲሆሙ ለአሕዛብ በበምድሮሙ ለለአሐዱ አሐዱ በበነገሮሙ ፡ ወበበነገዶሙ ፡ ወበበ ሕዘቢሆሙ ። | ፭ | ከእነዚህም የአሕዛብ ጎሳዎች አንዱም አንዱ በየአገራቸው በየቋንቋቸው በየነገዳቸው በየወገናቸው ተለዩ ። |
| ወደቂቀ ካም ኩሳ ፡ ወምስጥራይም ፡ ወፉጥ ፡ ወከነአን ። | ፮ | የካም ልጆች ኩሳ ፡ ምስጥራይም ፡ ፉጥ ፡ ከነአን ናቸው ። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፲፰ ። ፩ ዜና ፩ ፡ ፰ ። ፱ ፡ ፲ ። ኤር. ፵፰ ፡ ፱ ። |
| ወደቂቀ ኩሳ ሰባ ፡ ወኤውላጥ ፡ ወሰቤቃ ፡ ወራጌም ፡ ወሰብቃታ ፡ ወደቂቀ ራጌም ሳባ ፡ ወዮዳድን ። | ፯ | የኩሳ ልጆች ሰባ ፡ ኤውላጥ ፡ ሳቤቃ ፡ ራጌም ፡ ሰብቃታ ፡ ናቸው ፡ የራጌም ልጆች ሰበና ዮዳድን ናቸው ። |
| ወኩሳ ወለዶ ለናምሩድ ፡ ወውእቱ ዘከነ ያርብሐዌ ነዓዌ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፰ | ኩሳ ናምሩድን ወለደው ፡ በእግዚአብሔር ፊት አርበኛ አዳኝ የሆነ እሱ ነው ። |
| ወበእንተ ዝንቱ ይቤሉ ከመ ናምሩድ ያርብሕ ከነ ነዓዌ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፱ | ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እንደ አርበኛው ናምሩድ አዳኝ የሆነ የለም አሉ ። |
| ወከነ ቅድመ ቀንቀ መንግሥቱ በባቢሎን ፡ ወኤሬክ ፡ ወአርከድ ፡ ወካሌድን በምድረ ሰናአር ። | ፲ | አስቀድሞ የመንግሥቱ መጀመርያ በባቢሎን በኤሬክ በአርከድና በካሌድን በሰናአር ምድርም ነበረ ። ዘፍ. ፲፩ ፡ ፱ ። ፳፯ ፡ ፳፱ ። ፴፯ ፡ ፴፯ ። ሚክ ፭ ፡ ፯ ። |
| ወእምይእቲ ምድር ወጽአ አሶር ወነደቃ ለነነዌ ወለሮቢቶ ሀገር ዓቢይ ወለካላክ ። | ፲፩ | አሶርም ከዚያች አገር ወጣ ፡ ነነዌን ታላቂቱን ሀገር ሮቢት ካላክንም ሠራ ። |
| ወዳሰ ዘሀሎ በማእከለ ነነዌ ወካላክ ዘሀገር ዓቢይ ። | ፲፪ | በነነዌና በካላክ መካከል ያለችውን ዳሰንም እሷ ታላቅ ሀገር ናት ። |
| ወምስጥራይም ወለዶሙ ለሉድኬም ፡ ወለሰሚዊኤም ፡ ወለፋቢኤል ወለንፍቢኤም ወለጲዮርስናኤም ወለክሰሮንኤም ። | ፲፫ | ምስጥራይምም ሉድልኪምን ፡ ሰሚዊኤምን ፡ ፋቢኤልን ፡ ንፍቢኤምን ፡ ጴዮርስናኤምን ፡ ክሰሮኖምኤን ወለደ ። |
| ወእምኔሁ ወፅኡ ፍልስጥኤም ፡ ወቆፍሮናኤም ። | ፲፬ | ቆፍሮናኤምና ፍልስጥኤምም ከሱ ተወለዱ ። |
| ወከነአን ወለዶ ለሲዶን በኵሩ ፡ ወለኬጤዎን ፡ ወለኢያቡሴዎን ፡ ወለአሞሬዎን ። | ፲፭ | ከነአንም የበኵር ልጁን ሲዶንን ፡ ኬጤዎንን ፡ ኢያቡሴዎንን ፡ አሞሬዎንን ወለደ ። |
| ወለጌርጌሴዎን ፡ ወለኤዌዎን ፡ ወለፊርኬዎን ፡ ወለሴዎን ። | ፲፮ | ጌርጌሴዎንን ፡ ኤዌዎንን ፡ ፊርኬዎንን ፡ ሴዎንን ። |
| ወለኤራዴዎን ፡ ወለሰማንኤር ፡ ወለአማቲ ። | ፲፯ | ኤራዴዎንን ፡ ሰማንኤርን ፡ አማቲን ወለደ ፡ (ሲሥራ አንድ ይሆናሉ) ። |
| ወእምድኅረ ዝንቱ ተዘርዉ ነገደ ከነአን ። | ፲፰ | ከዚህ በኋላ የከነአን ወገኖች ተበተኑ ። |
| ወኮነ ደወሎሙ ለከነአን እምነ ሲዶን እስከ ጌራራ ወጋዛ ወይበጽሕ እስከ ሰዶም ፡ ወገሞራ ፡ ወሲዳማ ፡ ወሴበዮ እስከ ሴላ ። | ፲፱ | የከነአን አገራቸው ከሲዶን ጀምሮ እስከ ጋዛና እስከ ጌራራ ድረስ ሆነ ፡ እስከ ገሞራና እስከ ሰዶም ፡ እስከ ሲበዮን እስከ ሲዳማ ፡ እስከ ሴላ ድረስ ይደርሳል ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ለካም በበነገዶሙ ፡ ወበበነገሮሙ ፡ ወበበብሔሮሙ ፡ ወበበሕዘቢሆሙ ። | ፳ | በየነገዳቸው ፡ በየቋንቋቸው ፡ በየአገራቸው ፡ በየወገናቸው የሚጠሩ የካም ልጆች እሊህ ናቸው ። |
| ወለሴምኒ ተወልዱ ሎቱ ደቂቅ ። | ፳፩ | ለሴም ልጆች ተወለዱለት ። |
| ወውእቱ አቡሆሙ ለኵሉ ደቂቀ ኤቦር እኁሁ ለያፌት ዘየዐቢ ፡ ወደቂቀ ሴም ፡ ኤላም ፡ ወአሶር ፡ ወአርፋክስድ ፡ ወሉድ ፡ ወአራም ። | ፳፪ | እሱም የኤቦር ልጆች ሁሉ አባት የያፌት ታላቅ ወንድም ነው ፡ የሴምም ልጆች ኤላም ፡ አሶር ፡ አርፋክስድ ፡ ሉድ ፡ አራም ፡ ናቸው ። ዘፍ. ፲ ፡ ፳፫ ። |
| ወደቂቀ አራም ኡሳሕ ወዮምኤል ፡ ወያቴር ፡ ወሞሳሕ ። | ፳፫ | የአራም ልጆች ዮምኤልና ኡሳሕ ፡ ሞሳሕና ያቴር ፡ ናቸው ። ዘፍ. ፲፩ ፡ ፲፪ ። ፩ ዜና. ፩ ፡ ፲፯ ። |
| ወአርፋክስድ ወለዶ ለቃይናም ፡ ወቃይናም ወለዶ ለሳላ ፡ ወሳላ ወለዶ ለኤቦር ። | ፳፬ | አርፋክስድም ቃይናምን ወለደው ፡ ቃይናምም ሳላን ወለደው ፡ ሳላም ኤቦርን ወለደው ። ዘፍ. ፲፩ ፡ ፲፪ ። |
| ወለኤቦር ተወልዱ ሎቱ ክልኤቱ ደቂቅ ፡ ስሙ ለአሐዱ ፋሌቅ ፡ እስመ በመዋዕሊሁ ተከፍለት ምድር ፡ ወስመ እኁሁ ዮቃጢን ። | ፳፭ | ለኤቦርም ሁለት ልጆች ተወለዱለት ፡ የአንደኛ ልጁ ስሙ ፋሌቅ ይባላል በዘመኑ ምድር ተከፍላለችና ፡ የወንድሙም ስም ዮቃጢን ይባላል ። |
| ወዮቃጢን ወለዶሙ ለኤልሞዳድ ፡ ወለሳሌፍ ፡ ወለሴራሴርሞት ፡ ወለሴራኅ ። | ፳፮ | ዮቃጢንም ኤልሞዳድን ፡ ሳሊፍን ፡ ሴራሴርሞትን ፡ ሴራኅን ወለደ ። |

፳፯ ወለሐዶራ ፡ ወለአዜላ ፡ ወለዴቄላ ።

ሐዶራን ፡ አዜላን ፡ ዴቄላን ።

፳፰ ወለኡባል ፡ ወለአቤሚሴክ ፡ ወለሴኔሆ ።

ኡባልን ፡ አቤሚሴክን ፡ ሴኔሆንን ።

፳፱ ወለሑፌር ፡ ወለኄዊ ፡ ወለኢዮባር ፡ ወእሉ ኵሎሙ ደቂቁ ለዮቃጤን ።

ሑፌርን ፡ ኄዊን ፡ ኢዮባርን እነዚህ ሁሉ የዮቃጤን ልጆች ናቸው ።

፴ ወኮነ ምንባራቲሆሙ እምነ ማሴ እስከ ሳፊራ ፡ ወይበጽሕ ደብረ ሠረቃዊ ።

ስፍራቸውም ከማሴ እንሥቶ ወደ ሳፊራ ሲል እስከ ምሥራቅ ተራራ ድረስ ነው ።

፴፩ እሉ እሙንቱ ደቂቁ ለሴም በበነገዶሙ ፡ ወበበነገሮሙ ፡ ወበበብሔሮሙ ፡ ወበበሕዘቢሆሙ ።

የሴም ልጆች በየነገዳቸውና ፡ በየቋንቋቸው ፡ በየምድራቸውና ፡ በየሕዝባቸው ፡ እነዚህ ናቸው ።

፴፪ ወእሉ ነገደ ደቂቁ ለኖኅ በበዘመዶሙ ፡ ወእምነ እሉ ትውልድ ተዘርዉ አሕዛብ ውስተ ገጸ ምድር እምድኅረ አይኅ ።

የኖኅ ልጆቹ ነገዶች እንደ ትውልዳቸው በየሕዝባቸው እነዚህ ናቸው ፡ ከእነዚህም ተወልደው አሕዛብ ከጥፋት በኋላ በምድር ላይ ተበተኑ ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወአሐዱ ነገሩ ለኵሉ ዓለም ፡ ወአሐዱ ቃሉ ።

የሰው ሁሉ ቋንቋው ፡ አነጋገሩም አንድ ነበር ።

፪ ወኮነ እምድኅረ ተንሥኡ እምጽባሕ ረከቡ ገዳመ በምድረ ሰናአር ፡ ወኀደሩ ህየ ።

ከምሥራቅም በተነሡ ጊዜ እንዲህ ኾነ ፡ በሰናአር ምድር ሰፊ ሜዳ አገኙ ፡ በዚያም ሰፈሩ ።

፫ ወተባሀሉ አሐዱ ምስለ ካልኡ ንዑ ንጥፋሕ ግንፋለ ወናብስሎ በእሳት ፡ ወኮኖሙ ግንፋሎሙ እብነ ፡ ወጊሶ ጽቡሮሙ ።

አንዱ ከንዱ ጋር ኑ ፡ ጡብ እንሥራ በእሳት ተኰስን እናብስለው ተባባሉ ፡ ጡባቸው ደንጊያ ሆነላቸው ፡ ጭቃቸውም ሙጫ ነበር ። ዘፍ. ፲፩ ፡ ፲ ። ዘፀ ፪ ፡ ፫ ።

፬ ወተባሀሉ በበይናቲሆሙ ንዑ ንንድቅ ሀገረ ወማኅፈደ ዘይበጽሕ ርእሱ እስከ ሰማይ፡ ወንግበር ለነ ስመ እንበለ ንዘረው ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር ።

እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ ፡ ኑ ፡ መንደር እንቈር ቍር ጫፉ እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብም እንሥራ ፡ በምድር ሁሉ ከመበተናችን በፊት ፡ ለእኛ የስማችን መጠሪያ እናድርግ ። ዘፀ ፩ ፡ ፳፫ ። ዘዳ. ፪ ፡ ፳፫ ።

፭ ወወረደ እግዚአብሔር ውስተ ሀገሮሙ ከመ ይርአይ ውእተ ማኅፈደ ዘነደቁ እጓለ እመሕያው ።

እግዚአብሔርም ሰዎች የሠሩትን ያንን ግንብ ያይ ዘንድ ወደ መንደራቸው ወረደ ።

፮ ወይቤ እግዚአብሔር ናሁ አሐዱ ዘመድ ውእቱ ኵሉ ፡ ወአሐዱ ነገሩ ፡ ወከመዝ አኀዙ ይግበሩ ወኢየኀድጉ ይእዜኒ ገቢረ ዘሐለዩ በልቦሙ ።

እግዚአብሔርም እንዲህ አለ ሁሉም አንድ ቤተ ሰብ፡ አንድ ቋንቋ ናቸው ፡ እንደዚህ ያለ ሥራም ሊሠሩ ጀመሩ፤ አሁንም በልባቸው ያሰቡትን መሥራታቸውን አይተዉም፤

፯ ንዑ ንረድ ወንዝርዎ ለነገሮሙ ከመ ኢይሰምዑ ነገሮሙ አሐዱ ምስለ ካልኡ ።

ኑ ፡ እንውረድ ቋንቋቸውን እንለያየው ፡ አንዱ ከንዱ ጋር የሚናገሩትን እንዳይሰማሙ ። ዘፍ. ፩ ፡ ፳፯ ።

፰ ወዘረወ እግዚአብሔር ነገሮሙ ወዘረዎሙ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር ፡ ወኀደጉ እንከ ነዲቆታ ለይእቲ ሀገር ወለውእቱ ማኅፈድ ።

እግዚአብሔርም ቋንቋቸውን ለያየ ፡ በምድርም ሁሉ በተናቸው ፡ ከዚህ በኋላ ያቺን መንደር መቈርቈር ፡ ያንንም ግንብ መሥራትን ተዉ ። ዘፍ. ፲ ፡ ፳፩ - ፴፪ ።

፱ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስማ ባቢሎን ፡ እስመ በህየ ዘረዎሙ እግዚአብሔር ለነገረ ኵሉ በሐውርት ፡ ወእምህየ ዘረዎሙ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር።

ስለዚህም ስሟ ባቢሎን ተባለ ፡ እግዚአብሔር በዚያ የሀገሩን ሁሉ ቋንቋ ለያይቷልና ፡ ከዚያም እግዚአብሔር ሰዎችን በምድር ሁሉ በትኗቸዋልና ።

፲ ወከመዝ ውእቱ ልደቱ ለሴም ፡ ፻ ዓመት ሎቱ እምአመ ተወልደ አመ ይወልዶ ለአርፋክስድ በካልእ ዓም እምድኅረ አይኅ ።

የሴምም ልደቱ እንዲህ ነው ከጥፋት በኋላ በሁለተኛው ዓመት አርፋክስድን ሲወልድ ለእርሱ ከተወለደ ፻ ዓመት ሁኖት ነበር ። ዘፍ. ፲ ፡ ፳፪ - ፳፭ ።

፲፩ ወሐይወ ሴም እምድኅረ ወለዶ ለአርፋክስድ ፭፻ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፡ ወሞተ ።

ሴምም አርፋክስድን ከወለደው በኋላ ፭፻ ዓመት ኖረ ፡ ወንዶችንና ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፡ ሞተ ።

፲፪ ወሐይወ አርፋክስድ ፻፴ወ፭ተ ዓመተ ወወለዶ ለቃይንም ።

አርፋክስድም ፻፴፭ ዓመት ኖረ ፡ ቃይንምን ወለደ ። ሉቃ. ፫ ፡ ፴፯ ።

፲፫ ወሐይወ አርፋክስድ እምድኅረ ወለዶ ለቃይንም ፬፻ወ፴ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፡ ወሐይወ ቃይንም ፻ወ፴ ዓመተ ወወለዶ ለሳላ ፡ ወሐይወ ቃይንም እምድኅረ ወለዶ ለሳላ ፬፻ወ፴ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ፡ ወሞተ ።

አርፋክስድ ቃይንምን ከወለደው በኋላ ፬፻፴ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ሞተ ፡ ቃይንምም ፻፴ ዓመት ኖረ ሳላንም ወለደ፡ ቃይንም ሳላን ከወደው በኋላ ፬፻፴ ዓመት ኖረ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ፡ ሞተ ።

፲፬ ወሐይወ ሳላ ፻ወ፴ ዓመተ ወወለዶ ለኤቦር ።

ሳላም ፻፴ ዓመት ኖረ ኤቦርንም ወለደ ።

፲፭ ወሐይወ ሳላ እምድኅረ ወለዶ ለኤቦር ፫፻ወ፴ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፡ ወሞተ ።
ሳላም ኤቦርን ከወለደው በኋላ ፫፻፴ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ፡ ሞተ ።

፲፮ ወሐይወ ኤቦር ፻፴ወ፬ ዓመተ ወወለዶ ለፋሌቅ ።
ኤቦርም ፻፴፬ ዓመት ኖረ ፋሌቅንም ወለደው ።

፲፯ ወሐይወ ኤቦር እምድኅረ ወለዶ ለፋሌቅ ፫፻ወ፴ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፡ ወሞተ ።
ኤቦርም ፋሌቅን ከወለደ በኋላ ፫፻፴ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ፡ ሞተ ።

፲፰ ወሐይወ ፋሌቅ ፻ወ፴ ዓመተ ወወለዶ ለራግው ።
ፋሌቅም ፻፴ ዓመት ኖረ ፡ ራግውንም ወለደ ።

፲፱ ወሐይወ ፋሌቅ እምድኅረ ወለዶ ለራግው ፪፻ወ፱ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፡ ወሞተ ።
ፋሌቅም ራግውን ከወለደው በኋላ ፪፻፱ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ፡ ሞተ ።

፳ ወሐይወ ራግው ፻፴ወ፪ ዓመተ ወወለዶ ለሴሩኅ ።
ራግውም ፻፴፪ ዓመት ኖረ ፡ ሴሮኅንም ወለደ ።

፳፩ ወሐይወ ራግው እምድኅረ ወለዶ ለሴሩኅ ፪፻ወ፯ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፡ ወሞተ ።
ራግውም ሴሮኅንም ከወለደ በኋላ ፪፻፯ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ፡ ሞተ ።

፳፪ ወሐይወ ሴሩኅ ፻ወ፴ ዓመተ ወወለዶ ለናኮር ።
ሴሮኅም ፻፴ ዓመት ኖረ ፡ ናኮርንም ወለደ ።

፳፫ ወሐይወ ሴሩኅ እምድኅረ ወለዶ ለናኮር ፪፻ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፡ ወሞተ ።
ሴሮኅም ናኮርን ከወለደው በኋላ ፪፻ ዘመን ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ፡ ሞተ ።

፳፬ ወሐይወ ናኮር ፸ወ፱ ዓመተ ወወለዶ ለታራ ።
ናኮርም ፸፱ ዓመት ኖረ ፡ ታራንም ወለደ ።

፳፭ ወሐይወ ናኮር እምድኅረ ወለዶ ለታራ ፻፳ወ፱ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፡ ወሞተ ።
ናኮርም ታራን ከወለደ በኋላ ፻፳፱ ዓመት ኖረ ፡ ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችንም ወለደ ፡ ሞተ ።

፳፮ ወሐይወ ታራ ፸ ዓመተ ወወለዶሙ ለአብራም ፡ ወለናኮር ፡ ወለአራን ።
ታራም ፸ ዓመት ኖረ ፡ አብራምን ፡ ናኮርን ፡ አራንንም ወለደ ።

፳፯ ወአራን ወለዶ ለሎጥ ።
አራንም ሎጥን ወለደ ።

፳፰ ወሞተ አራን በቅድመ ታራ አቡሁ በምድር እንተ በውስቴታ ተወልደ በምድረ ከላውዴዎን ።
አራንም ከአባቱ በፊት በተወለደበት አገር በከላውዴዎን ምድር ሞተ ።

፳፱ ወነሥኡ አብራም ወናኮር አንስትያ ሎሙ ፡ ወስማ ለብእሲተ አብራም ሶራ ፡ ወለብእሲተ ናኮር ሚልካ ፡ ወለተ አራን አቡሃ ለሚልካ ወአቡሃ ለዮስካ ።
ናኮርና አብራምም ሚስቶች አገቡ ፡ የአብራም ሚስት ሶራ ትባል ነበር ፡ የናኮር ሚስትም ሚልካ ትባል ነበር ፡ ሚልካም የሚልካና የዮስካ አባት የአራን ልጅ ናት ።

፴ ወሶራሰ መካን ይእቲ ወአልቦቲ ውሉድ ፡ ወነሥኦሙ ታራ ለአብራም ወልዱ ወለሎጥ ወልደ አራን እኁሁ ለአብራም ፡ ወለሶራ መርዓቱ ብእሲተ አብራም ወልዱ ።
ሶራ ግን መካን ነበረች ልጅም አልነበራትም ፡ ታራም ልጁን አብራምን የአብራምን የወንድም ልጅ ሎጥንም ፡ የልጁን የአብራምን ሚስት ምራቱ ሶራን ወሰዳቸው ።

፴፩ ወአውጽኦሙ እምነ ምድረ ከላውዴዎን ከመ ይሑሩ ምድረ ከነአን ፡ ወበጽሑ ካራን ኅደሩ ህየ ።
ወደ ከነአን ምድርም ይሄዱ ዘንድ ከከላውዴዎን አወጣቸው ፡ ወደ ካራንም በደረሱ ጊዜ በዚያ አደሩ ።

፴፪ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለታራ ፪፻ወ፭ ዓመተ ፡ ወሞተ ታራ በካራን ።
ታራም በሕይወት የኖረበት ዘመኑ ሁሉ ፪፻፭ ዓመት ሆነ ፡ ታራም በካራን ሞተ ።

## ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብራም ፃእ እምድርከ ወእምዘመድከ ወእምቤተ አቡከ ወሑር ውስተ ምድር እንተ አርእየከ አነ ።
እግዚአብሔርም አብራምን ከገርህ ወጥተህ ከዘመድህ ከባትህም ወገን ተለይተህ ፡ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ አለው ። ምዕ. ፲፰ ፡ ፯ ። ግብ. ሐዋ. ፯ ፡ ፫ ። ዕብ. ፲፩ ፡ ፰ ።

፪ ወእሬስየከ ሕዝበ ዓቢየ ፡ ወእባርከከ ፡ ወአዓቢ ስመከ ፡ ወትከውን ቡሩከ ።
ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ ፡ ስምህም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ ፡ የተባረክህም ትሆናለህ ።

፫ ወእባርኮሙ ለእለ ይባርኩከ ፡ ወእረግሞሙ ለእለ ይረግሙከ ፡ ወይትባረኩ ብከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ።
የሚያከብሩህንም አከብራቸዋለሁ ፡ የሚረግሙህንም እረግማቸዋለሁ ፡ የዚህ ዓለም አሕዛብም ሁሉ በንተ ይከብራሉ አለው ። ዘፍ. ፳፯ ፡ ፳፱ ። ፲፰ ፡ ፲፰ ። ዘኍ. ፳፬ ፡ ፱ ። ሉቃ. ፫ ፡ ፴፬ ።

፬ ወሖረ አብራም በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ወሖረ ሎጥሂ ምስሌሁ ፡ ወአመ ወፅአ አብራም እምካራን ፸ወ፭ቱ ክራማት ሎቱ ።
አብራምም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሄደ ፡ ሎጥም ከሱ ጋራ ሄደ ፡ አብራምም ከካራን በወጣ ጊዜ ዕድሜው ፸፭ ነበር ።

፭ ወነሥአ አብራም ለሶራ ብእሲቱ ወለሎጥሂ ወልደ እኁሁ ወኵሎ ንዋዮሙ ዘአጥረዩ በካራን ወወፅኡ ወሖሩ ወበጽሑ ምድረ ከነአን ።
አብራምም ሚስቱ ሶራን ወሰደ ፡ የወንድሙን ልጅ ሎጥንም በካራን ያጠራቀሙትን ገንዘባቸውንም ሁሉ ይዞ ወደ ከነአንም ምድር ደረሱ ። ዘፍ. ፲፩ ፡ ፴፩ ። ፲፭ ፡ ፲፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወሖዳ አብራም ለይእቲ ምድር እስከ ሴኬም ኀበ ዕፅ ነዋኅ ፡ ወሰብአ ከነአንሰ ሀለዉ ይእተ አሚረ ውስተ ይእቲ ምድር ። | ፮ | አብራምም ያችን ሀገር ረጅም ዕንጨት እስከ አለበት እስከ ሴኬም ድረስ ዞራት ፡ የከነአን ሰዎች ግን የዚያን ጊዜ በዚያች አገር ነበሩ ። ዕብ ፲፩ ፡ ፱ ። |
| ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለአብራም ወይቤሎ ለዘር እከ እሁብ ለዛቲ ምድር ፡ ወነደቀ አብራም በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ዘአስተርአዮ ። | ፯ | እግዚአብሔርም ለአብራም ታየው ፡ ይችንም አገር ለልጆችህ እሰጣታለሁ አለው ፡ አብራምም በዚያ ለተገለጠለት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አዘጋጀ ። ዘፍ ፲፫ ፡ ፲፭ ። |
| ወግዕዘ እምህየ መንገለ ሠርቅ ውስተ ምድረ ቤቴል ወተከለ ሐይመቶ ውስተ ቤቴል እንጻረ ባሕር ዘመንገለ ጋይ ወኃደረ ህየ፡ ወነደቀ ህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር፡ ወጸውዐ ስመ እግዚአብሔር ። | ፰ | ከዚያም ወደ ምሥራቅ ወደ ቤቴል ምድር ሄደ ፡ በቤቴልም በጋይ በኩል በስተምዕራብ ድንኳኑን ተከለ ፡ በዚያም ተቀመጠ ፡ በዚያም ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ ፡ የእግዚአብሔርንም ስም ጠራ ። ዘፍ ፲፫ ፡ ፬ ። |
| ወተንሥአ ወሖረ ወግዕዘ አብራም ውስተ አዜብ ከመ ይኅድር ህየ ። | ፱ | አብራምም ከዚያ ተነሥቶ ሄደ ፡ በዚያም ሊኖር ወደ አዜብ ተጓዘ ። |
| ወሰበ ጸንዐ ረኃብ ውስተ ብሔር ወረደ አብራም ውስተ ግብጽ ከመ ይኅድር ህየ፡ እስመ ጸንዐ ረኃብ ውስተ ብሔር ። | ፲ | በገርም ራብ በጸና ጊዜ አብራም በዚያ ሊኖር ወደ ግብጽ ወረደ ፡ በአገሩ ረኃብ ጸንቷልና ። ዘፍ ፳፮ ፡ ፩ ። ፵፫ ፡ ፩ ። |
| ወከነ ሰበ ቀርበ አብራም ከመ ይባእ ውስተ ግብጽ ይቤላ አብራም ለሰራ ብእሲቱ አአምር ከመ ብእሲት ላህይተ ገጽ አንቲ ። | ፲፩ | አብራም ወደ ግብጽ ይገባ ዘንድ በቀረበ ጊዜ እንዲህ ሆነ ፡ አብራም ሚስቱን ሶራን እንዲህ አላት ፡ አንቺ መልከ መልካም ሴት እንደሆንሽ አውቃለሁ ። |
| ወእምከመ ርእዩኪ ሰብአ ግብጽ ይብሉ ብእሲቱ ይእቲ ወይቀትሉኒ፡ ወኪያኪሰ ያሐይውኪ ። | ፲፪ | የግብጽም ሰዎች ካዩሽ ሚስቱ ናት ይሉና ይገድሉኛል ፡ አንችን ግን አይገድሉሽም ። ዘፍ ፳ ፡ ፲፩ ። |
| ወበሊዮሙ እንከ እኅቱ አነ ከመ ያሠንዩ ሊተ በእንቲአኪ ፡ ወትሕየው ነፍስየ በእንቲአኪ በዕብሬትኪ ። | ፲፫ | እንግዲህ እኔ እኅቱ ነኝ በዪያቸው ስለ አንቺ ይራሩልኝ ዘንድ ፡ በአንቺ ምክንያትም ሰውነቴ ትድን ዘንድ ። |
| ወከነ ሰበ በጽሐ አብራም ውስተ ግብጽ ርእይዋ ለብእሲቱ ሰብአ ግብጽ ከመ ሠናይት ጥቀ ። | ፲፬ | አብራምም ወደ ግብጽ በደረሰ ጊዜ እንዲህ ሆነ ፡ የግብጽም ሰዎች ሚስቱን እጅግ መልከ መልካም እንደሆነች አይዋት ። |
| ወርእይዋ መላእክተ ፈርዖን ወወሰድዋ ኀበ ፈርዖን ወአብእዋ ውስተ ቤቱ ። | ፲፭ | የፈርዖን ሹማምንቶችም አይተው ወደ ፈርዖን ወሰዷት ወደ ቤቱም አገቧት ። |
| ወአሠነዩ ለአብራም በእንቲአሃ ወአጥረየ አግብርተ ወአእማተ ወአባግዐ ወአልሕምተ ወአግማለ ወአብቅለ ወአእዱገ ። | ፲፮ | ስለሷም ለአብራም በጎ ነገር አደረጉለት ፡ ሴቶች አገልጋዮችና ወንዶች አገልጋዮችን ፡ ላሞችንና በጎችንም ፡ በቅሎዎችንና ፡ ግመሎችን ፡ አህዮችንም ፡ አገኘ ። |
| ወሳቀዮ እግዚአብሔር ለፈርዖን ዐቢየ ሥቃየ ወእኩየ ሎቱሂ ወለቤቱሂ በእንተ ሰራ ብእሲቱ ለአብራም ። | ፲፯ | እግዚአብሔርም በአብራም ሚስት በሶራ ምክንያት ፈርዖንን ጽኑ ሥቃይ አሠቃየው ፡ እርሱንም ቤተ ሰቡንም ። ዘፍ ፳ ፡ ፲፰ ። ፩ ዜና መዋ ፲፯ ፡ ፳፩ ። መዝ ፻፭ ፡ ፲፬ ። |
| ወጸውዖ ፈርዖን ለአብራም ወይቤሎ ምንትኑዝ ዘገበርከ ላዕሌየ ዘኢነገርከኒ ከመ ብእሲትከ ይእቲ ። | ፲፰ | ፈርዖንም አብራምን ጠርቶ እንዲህ አለው በእኔ ላይ ያደረግኸው ይህ ነገር ምንድነው ፤ ሚስትህ መሆኗን ያልነገርከኝ ። |
| ለምንት ትቤለኒ እኅትየ ይእቲ፡ ወነሣእክዋ ትኩነኒ ብእሲተ ፡ ወይእዜኒ ነያ ብእሲትከ ንሥአ ወሑር ። | ፲፱ | ለምን እኅቴ ናት አልከኝ፤ ሚስት ልትሆነኝ ወስጃት ነበር ፡ አሁንም ሚስትህ ያቻት ይዘሃት ሂድ ። |
| ወአዘዘ ፈርዖን ያስተፋንውዎ እደው ለአብራም ወለብእሲቱ ወለኵሉ ንዋዮሙ ። | ፳ | ፈርዖንም ብላቴኖች አብራምን እንዲሸኙት አዘዘ ሚስቱንም ገዛቸውንም ሁሉ ። |

ምዕራፍ ፲፫ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወዐርገ አብራም እምግብጽ ውእቱ፡ ወብእሲቱ ፡ ወኵሉ ንዋዩ ወሎጥሂ ምስሌሁ ውስተ አዜብ ። | ፩ | አብራም ከግብጽ ወጣ እሱም ፡ ሚስቱም ፡ ጓዙም ሁሉ ሎጥም ከሱ ጋራ ወደ አዜብ ወጣ ። |
| ወአብራምሰ ብዑለ ጥቀ በእንስሳ ወበወርቅ ወበብሩር ። | ፪ | አብራም ግን በከብት በወርቅም በብርም እጅግ ባለ ፀጋ ሆነ ። |
| ወገብአ እምኀበ መጽአ እምአዜብ ውስተ ቤቴል ውስተ መከን ኀበ ሀሎ ቀዲሙ በህየ ዐፀዱ በማእከለ ቤቴል ወበማእከለ ጋይ ። | ፫ | ወደ መጣበት ወደ አዜብ ከዚያውም ወደ ቤቴል ተመለሰ ፡ ቀድሞ ድንኳኑ ወደ ነበረበት በጋይና በቤቴል መካከል ወደ አለው ቦታ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ውስተ መከን ኀበ ገብረ ምሥዋዐ ህየ ቀዲሙ፡ ወጸውዐ አብራም ስመ እግዚአብሔር በህየ ። | ፬ | ቀድሞ መሠዊያው ሠርቶ የእግዚአብሔርን ስም ይጠራ ወደ ነበረበት ሥፍራ፡ አብራምም በዚያ የእግዚአብሔርን ስም ጠራ ። ዘፍ. ፲፪፡ ፯-፰ ። ፲፬፡ ፲፫ ። ዘዳ. ፲፭፡ ፴ ። |
| ወሎጥኒ ዘሖረ ምስሌሁ ለአብራም አጥረየ አባግዐ ወአልሕምተ ወአንስሳ ። | ፭ | ከአብራም ጋራ የሄደ ሎጥም ላሞችንና በጎችን ፈረስና በቅሎን አገኘ ። |
| ወኢአከሎሙ ምድር ከመ ይኅድሩ ኅቡረ እስመ ብዙኅ ንዋዮሙ ። | ፮ | አንድነትም ይኖሩ ዘንድ ቦታ አልበቃቸውም፡ ሃብታቸው ብዙ ነበርና ። |
| ወኮነ ጋእዝ ማእከለ ኖሎት ዘሎጥ ወዘአብራም፡ ወሀለዉ ይእተ አሚረ ሰብአ ከነአን ወፌርዜዎን ኅዱራን ውስተ ይእቲ ምድር ። | ፯ | በአብራም እረኞችና በሎጥ እረኞች መካከልም ፀብ ሆነ፡ የዚያን ጊዜ የፌርዜዎንና የከነአን ሰዎችም በዚያች አገር ይኖሩ ነበር ። |
| ወይቤሎ አብራም ለሎጥ ኢይኩን ጋእዝ ማእከሌየ ወማእከሌከ፡ ማእከለ ኖሎትየ ወማእከለ ኖሎትከ እስመ አኀው ንሕነ ። | ፰ | አብራምም ሎጥን እንዲህ አለው በንተና በኔ መካከል ፀብ አይኑር፡ በእረኞችህና በእረኞቼም መካከል፡ እኛ ወንድማማቾች ነንና ። ግብ. ሐዋ. ፯፡ ፳፮ ። |
| ወናሁ ኵላ ምድር ቅድሜከ ይእቲ ተሌለይ እምኔየ እመ የማነ አነ፡ ወአንተ ጸጋመ፡ ወእመ አኮ አንተ የማነ ወአነ ጸጋመ ። | ፱ | እነሆ ምድር ሁሉ በፊትህ ናት ከኔ ተለይ፡ እኔ በቀኝ ብሆን አንተ በግራ ትሆናለህ፡ ያለዚያም አንተ በቀኝ ብትሆን፡ እኔ በግራ እሆናለሁ ። ዘፍ. ፳፡ ፲፭ ። ፴፬፡ ፲ ። ፲፱፡ ፲፯ ። ዘዳ. ፴፬፡ ፫ ። ኢሳ. ፩፡ ፯ ። |
| ወአልዐለ ሎጥ አዕይንቲሁ ወርእየ ኵሎ አሕቃላቲሁ ለዮርዳኖስ ርዉይ ውእቱ ኵሉ ምድሩ ዘእንበለ ይገፍትዖን እግዚአብሔር ለሰዶም ወለገሞራ ከመ ገነተ እግዚአብሔር ውእቱ ወከመ ምድረ ግብጽ እስከ ሴጎር ። | ፲ | ሎጥም ዓይኖቹን አንሥቶ የዮርዳኖስን አውራጃ ሁሉ አየ፡ አውራጃው በሙሉ ለምለም ነበር፡ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ሳያጠፋቸው እስከ ሴጎር ድረስ ያለው አገር እንደ እግዚአብሔር ገነትና እንደ ምድረ ግብጽ ነበር ። ዘፍ. ፲፱፡ ፳፬-፳፭ ። ፪፡ ፰ ። ኢሳ. ፶፩፡ ፫ ። ኢዩ. ፪፡ ፫ ። |
| ወኀረየ ሎቱ ሎጥ ኵሎ አሕቃላተ ዮርዳኖስ ወግዕዘ ሎጥ እመንገለ ሠርቅ፡ ወተሌለዩ አሐዱ እምካልኡ ። | ፲፩ | ሎጥ ለራሱ የዮርዳኖስን አውራጃ መረጠ፡ ሎጥም ከምሥራቅ ተጓዘ፡ አንዱ ከንዱ (ወንድም ከወንድሙ) ተለየ ። |
| አብራም ኀደረ ምድረ ከነአን፡ ወሎጥሂ ኀደረ ውስተ አድያም ወግዕዘ ውስተ ሰዶም ። | ፲፪ | አብራም በምድረ ከነአን ኖረ፡ ሎጥም በዳርቻ ኖረ፡ ወደ ሰዶምም ተጓዘ ። |
| ወሰብአ ሰዶምሰ እኩያን ወኃጥአን ጥቀ በቅድመ እግዚአብሔር ። | ፲፫ | የሰዶም ሰዎች ግን በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ክፉዎች ኃጢአተኞችም ነበሩ ። ዘፍ. ፯፡ ፲፩ ። ፲፰፡ ፳ ። ሕዝ. ፲፯፡ ፵፱ ። ፪ ጴጥ. ፪፡ ፯-፰ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብራም እምድኅረ ተሌለየ እምኔሁ ሎጥ ነጽር በአዕይንቲከ ወርኢ እምዝንቱ መከን ኀበ ሀለውከ ለመንገለ መስዕ ወአዜብ ወሠርቅ ወባሕር ። | ፲፬ | ሎጥ ከሱ ከተለየ በኋላ እግዚአብሔር አብራምን እንዲህ አለው፡ ከዚህ ካለህበት ቦታ ጀምሮ ወደ ምዕራብና ወደ ምሥራቅ ወደ አዜብና ወደ መስዕ በዓይኖችህ እይ ተመልከት አለው ። ዘፍ. ፳፡ ፰-፲፬ ። |
| እስመ ኵለንታሃ ለዛቲ ምድር እንተ ትሬኢ ለከ እሁባ ወለዘርእከ እስከ ለዓለም ። | ፲፭ | ይህችን የምታያትን ምድር በሙሉዋ ላንተ እሰጣታለሁ፡ ለዘርህም እስከ ዓለም ፍጻሜ ። ፲፯፡ ፰ ። ፳፰፡ ፲፫ ። ዘዳግ. ፴፬፡ ፬ ። |
| ወእሬስዮ ለዘርእከ ከመ ኆፃ ባሕር፡ እመበ ዘይክል ኈልቆቶ ለኆፃ ባሕር ይኌልቆ ለዘርእከኒ ። | ፲፮ | ዘርህንም እንደ ባሕር አሸዋ አደርገዋለሁ፡ የባሕር አሸዋን መቍጠር የሚችል ሰው ካለ ዘርህንም ሊቈጥረው ይችላል ። ዘፍ. ፳፪፡ ፲፯ ። |
| ተንሥእ ወዑዳ ለምድር ውስተ ኑኃ ወራኅባ እስመ ለከ እሁባ ። | ፲፯ | ተነሥ ምድርንም ወርዷን ስፋቷን ቃኘት፡ ለአንተ እሰጣታለሁና ። |
| ወግዕዘ አብራም ኀበ ዕፅ እንተ ውስተ ኬብሮን ወነደቀ በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ። | ፲፰ | አብራምም በኬብሮን ወደ አለው ዛፍ ተጓዘ፡ በዚያም ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ ። ዘፍ. ፴፭፡ ፳፯ ። ፴፡ ፯-፲፬ ። |
| ምዕራፍ ፲፬ ። | | ምዕራፍ ፲፬ ። |
| ወኮነ በመዋዕለ አሚሬፌርን ንጉሠ ሰናአር፡ ወአርዮክ ንጉሠ ሴላስድ፡ ወኮሎዶጎሞር ንጉሠ ኤሎም፡ ወቲርጋ ንጉሠ አሕዛብ ። | ፩ | በሰናአር ንጉሥ በአሚሬፌርን፡ በሲላስድ ንጉሥ በአርዮክ፡ በኤሎም ንጉሥ በከሎዶጎሞርና፡ በአሕዛብ ንጉሥ በቲርጋ ዘመን እንዲህ ሆነ ። ዘፍ. ፲፩፡ ፪ ። ፲፡ ፳፪ ። ኢሳ. ፲፩፡ ፲፩ ። |

፪ ፀብእዎሙ ለበላቅ ንጉሠ ሰዶም ፡ ወለበርስ ንጉሠ ገሞራ ወለሰናአር ንጉሠ ሰዶም ፡ ወለሴሜድር ንጉሠ ሴበዮ ፡ ወንጉሠ በላ እንተ ይእቲ ሴጎር ።

የሰዶምን ንጉሥ በላቅን ፡ የገሞራን ንጉሥ ብርስን ፡ የአዳማን ንጉሥ ሰናአርን ፡ የሲባዮን ንጉሥ ሴሜድርን ፡ ሴጎር የምትባለውን የባላ ንጉሥን ወጉዋቸው ። ዘፍ. ፲፱ ፡ ፳፬ ። ዘዳግ. ፳፱ ፡ ፳፫ ።

፫ ወእሉ ኵሎሙ ተጋብኡ ለዐለ ቈላተ ኤሴቄን እንተ ይእቲ ባሕረ ኤሉን ።

እነዚህ ሁሉ በኤሴቄን ሸለቆ ተሰበሰቡ ፡ እርሱም የጨው ባሕር ናት ። ዘሌዋ. ፲፩ ፡ ፴፩ ። ዘኁ ፴፬ ፡ ፲፪ ። ዘዳግ. ፫ ፡ ፲፯ ። ኢያ. ፫ ፡ ፲፮ ።

፬ ወተቀንዩ ፲፪ተ ዓመተ ለኮሎዶጎሞር ወለነገሥት እለ ምስሌሁ ።

ከሱ ጋራ ላሉ ነገሥታትና ለኮሎዶጎሞርም ፲፪ ዓመት ተገዙ ።

፭ ወአመ ኮነ ፲፫ ዓመት አዕረሩ ፡ መጽአ ኮሎዶጎሞር ወነገሥት እለ ምስሌሁ ወቀተልዎሙ ለእለ ያርብሕኒ በአስጣሮስ ወለቀራንዮን ወሕዝብኒ ጽኑዓን ምስሌሆሙ ወለአሚዎስ ወለሀገረ ሴዊ ።

፲፫ ዓመት በሆነ ጊዜ ግን ግብር ከለከሉ ፡ ኮሎዶጎሞር መጣ ከሱ ጋራ ያሉ ነገሥታትም መጡ ፡ አርበኞችንም በአስጣሮስ ወጉአቸው ፡ ቀርናይንንም ኃያላኑን ሕዝብም ከእነርሱ ጋር ፡ አሚዎስንም የሴዊንም አገር ። ዘፍ. ፲፭ ፡ ፳ ። ዘዳ. ፪ ፡ ፳ ። ፫ ፡ ፲፩ ። ኢያ. ፲፪ ፡ ፬ ። ፪ ሳሙ. ፭ ፡ ፲፰ ።

፮ ወለኬሬዎስ እለ በአድባረ ሴይር እስከ አድባረ ወራሜስ ወፋራን እንተ ውስተ ሐቅል ።

በምድረ በዳ እስካለች ፋራንና እስከ ወራሜስ ተራሮች ድረስ በሴይር ተራራ ያሉ አርበኞችንም ሁሉ አጠፉ ። ዘፍ ፴፮ ፡ ፰ - ፲፱ ። ዘዳግ. ፪ ፡ ፲፪ ። ዘኁ. ፲፪ ፡ ፲፮ ።

፯ ወተጋቢአሙ መጽኡ እንተ ዐዘቅተ ተስናን እንተ ይእቲ ቃዴስ ወቀተልዎሙ ለመላእክተ ዐማሌቅ ኵሎሙ ወለአሞሮስ ወለእለ ይነብሩ ውስተ አስቃና ።

ተሰብስበውም ፀብ ወደሚደረግበት ጉድጓድ መጡ ፡ ይህችውም ቃዴስ ትባላለች ፡ ያማሌቅን አለቆች ሁሉ ወጉዋቸው ፡ አምሞስንና በአስቃና የሚኖሩ ሰዎችን ወጉ ። ፪ ዜና ፳ ፡ ፪ ።

፰ ወወጽኡ ንጉሠ ሰዶም ፡ ወንጉሠ ገሞራ ፡ ወንጉሠ አዳማ ፡ ወንጉሠ ሴበዮን ፡ ወንጉሠ ባላ እንተ ይእቲ ሴጎር ፡ ወተአኀዙ በቈላተ ኤሴቄን ምስለ ኮሎዶጎሞር ንጉሠ ኤሎም ።

የገሞራ ንጉሥና ፡ የሰዶም ንጉሥ ፡ የሲባዮን ንጉሥና ፡ የአዳማ ንጉሥ ፡ ሴጎር የምትባለው የባላን ንጉሥም ወጡ በኤሴቄም ሸለቆ ከኤሎም ንጉሥ ከኮሎዶጎሞር ጋር ተጋጠሙ ።

፱ ወቲርጋ ንጉሠ አሕዛብ ፡ ወአሜሬፎን ንጉሠ ሰናአር ፡ ወአርዮ ንጉሠ ሴላስድ እሉ አርባዕቱ ነገሥት ምስለ ኀሙስቱ ነገሥት ።

ከአሕዛብ ንጉሥ ከቲርጋ ፡ ከሰናአር ንጉሥ ከአሜሬፎን ፡ ከሴላስድ ንጉሥ ከአርዮን ጋር እነዚህ ፬ቱ ነገሥታት ከ፭ቱ ነገሥታት ጋር ተዋጉ ።

፲ ወውእቱሰ ቈላተ ኤሴት ምሉእ ዐዘቅተ ኰለንታሁ ፡ ወተሰብሩ ንጉሠ ሰዶም ወንጉሠ ገሞራ ወቀተልዎሙ በህየ ፡ ወእለሰ ተሰብሩ ጐዩ ውስተ አድባር ።

ይህ የኤሴቄን ሸለቆ ግን ሁለንተናው ረግረግ ነው ፡ የገሞራ ንጉሥና የሰዶም ንጉሥም ድል ተነሡ ፡ በዚያም ወጉዋቸው ድል የተነሡት ግን ወደ ተራራ ሸሹ ። ዘፍ. ፲፭ ፡ ፫ ። ፲፱ ፡ ፲፯ ።

፲፩ ወነሥኡ ኵሉ አፍራሰ ሰዶም ወገሞራ ወኵሉ ስንቆሙ ።

የገሞራንና የሰዶምን ፈረሶች ወሰዱ ስንቃቸውንም ሁሉ ። ዘፍ. ፲፬ ፡ ፲፯ - ፳፩ ።

፲፪ ወሖሩ ወነሥእዎ ለሎጥሂ ወልደ እኁሁ ለአብራም ወንዋያቲሁኒ እስተዉ ወውእቱ ይነብር በሰዶም ።

የአብራም የወንድሙን ልጅ ሎጥንም ይዘዉት ሄዱ ፡ ገንዘቡንም ዘረፉት እሱም በሰዶም ይኖር ነበር ። ዘፍ. ፲፪ ፡ ፭ ። ፲፫ ፡ ፲፪ ።

፲፫ ወበጽሐ አለ አምሠጡ ወዜነውዎ ለአብራም እንዘ ሀለዉ ኀበ ዕፀ ምስለ አምርስ እኁሁ ለኤስክል ፡ ወለአውናን እለ ቅሩባን እሙንቱ ለአብራም ።

ለአብራም አቅራቢያ ከሚሆኑ ከአውናንና ከኤስክል ወንድም ከአምርስ ጋራ በዛፍ ሥር አንድነት ሳለ ከሞት ያመለጡ ሰዎች ደርሰው ለአብራም ነገሩት ። ዘፍ. ፲፫ ፡ ፲፰ ። ፲ ፡ ፬ - ፳፬ ።

፲፬ ወሰበ ሰምዐ አብራም ከመ ተፄወወ ሎጥ ወልደ እኁሁ ኈለቆሙ ለአሊአሁ ወለኵሎሙ ሰብአ ቤቱ ወኮኑ ፫፻፲ወ፰ ወዴገኖሙ ወተለዎሙ እስከ ዳን ።

አብራምም የወንድሙ ልጅ ሎጥ እንደ ተማረከ በሰማ ጊዜ ፡ ወገኖቹን ቤተ ሰቦቹንም ሁሉ ቈጠራቸው ፫፻፲፰ ሆኑ ፡ እስከ ዳን ድረስ ተከተላቸው ። ዘፍ. ፲፫ ፡ ፰ ። ፲፪ ፡ ፭ ። ዘዳግ. ፴፬ ፡ ፩ ። መሳ. ፲፰ ፡ ፳፱ ። መክ. ፪ ፡ ፯ ።

፲፭ ወበጽሖሙ ሌሊተ ምስለ ደቂቁ ወቀተሎሙ ወዴገኖሙ እስከ ኮቤር እንተ ፀጋማ ለደማስቆ ።

ከአሽከሮቹ ጋራ ሌሊት ደረሰባቸው ወጋቸው ፡ በደማስቆ ግራ እስከ አለችው እስከ ኮቤር ድረስ ተከተላቸው ። ፩ ሳሙ. ፳፫ ፡ ፲ - ፳፱ ።

፲፮ ወነሥአሙ አብቅሊሆሙ ወነሥአ ለሎጥሂ ወልደ እኁ
ሁ ወንዋዮሙኒ ወአንስቲኒ ወሕዝበኒ አእተወ ።

በቅሎቻቸውንም ወሰደባቸው፡ የወንድሙን ልጅ ሎጥ
ንም አመጣው፡ ገንዘባቸውንም ሴቶችንም ወንዶችንም
መለሰ ።

፲፯ ወወጽአ ንጉሠ ሰዶም ወተቀበሎ እምድኅረ ገብአ እም
ኀበ ቀተሎ ለኮሎዶጎሞር ወለነገሥት እለ ምስሌሁ በቈ
ላተ ሴዊ ወውእቱ ገዳም ዘመንግሥቱ ውእቱ ።

ከሱ ጋራ ያሉ ነገሥታትና ኮሎዶጎሞርንም፡ በሴዊ ሸለቆ
ወግቶ ከተመለሰ በኋላ የሰዶም ንጉሥ ወጥቶ ተቀበለው፡
ይኸውም በግዛቱ ያለ ምድረ በዳ ነው ። ፪ ሳሙ. ፲፰፡ ፲፰።

፲፰ ወመልከ ጼዴቅ አምጽአ ኅብስተ ወወይነ፡ ወካህኑ ለእ
ግዚአብሔር ልዑል ውእቱ፡ ወንጉሠ ሳሌም ውእቱ ።

መልከ ጼዴቅም ኅብስተ አኰቴትን ጽዋዐ በረከትን
አመጣ፡ እሱም ገናና የሆነ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው፡
የሳሌም ንጉሥም ነው ። መዝ. ፻፲፡ ፬ ። ዕብ ሐዋ. ፲፯፡
፲፯ ። ዕብ. ፫፡ ፯ ። ፯፡ ፩ ።

፲፱ ወባረኮ ለአብራም ወይቤሎ ቡሩኩ አብራም ለእግዚአ
ብሔር ልዑል ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ ።

አብራምንም በረከውና እንዲህ አለው አንተ ሰማይንና
ምድርን ለፈጠረ ገናና ለሆነ እግዚአብሔር ደግ ፍጥረት
ነህ ። ሩት ፫፡ ፳ ። ፪ ሳሙ. ፰፡ ፭ ። ዘፍ. ፲፬፡ ፳፪ ።

፳ ወቡሩክ እግዚአብሔር ልዑል ዘአግብአሙ ለጸላእትከ
ውስተ እዴከ፡ ወወሀበ አብራም ዐሥራተ እድ እምዙሉ ።

ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ እግዚአብሔር የተመ
ሰገነ ነው፡ አብራምም ከገንዘቡ ሁሉ ዐሥራት ሰጠው ።
ዘፍ. ፳፩፡ ፳፯ ። ፳፰፡ ፳፪ ። ዕብ. ፯፡ ፬ ።

፳፩ ወይቤሎ ንጉሠ ሰዶም ለአብራም ሀበኒ ሰብአ፡ ወጥሪ
ተሰ ኅደጉ ለከ ።

የሰዶም ንጉሥም አብራምን ሰዎችን ስጠኝ፡ ገንዘቡን
ግን ትቸልሃለሁ አለው ።

፳፪ ወይቤሎ አብራም ለንጉሠ ሰዶም አሌዕል እዴየ ኀበ
እግዚአብሔር ልዑል ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ።

አብራምም የሰዶምን ንጉሥ እንዲህ አለው፡ ሰማይንና
ምድርን ወደ ፈጠረ ወደ እግዚአብሔር እጄን ዘርግቼ
እምላለሁ ። ዘኁ. ፲፩፡ ፴ ። ዘዳግ. ፴፪፡ ፵ ። ሕዝ. ፳፡ ፭ ።
ዘዳግ. ፲፪፡ ፯ ።

፳፫ ከመ ኢይነሥእ ኢ ፈትለ ወኢ ቶታነ አሣእን እምንዋ
ይከ ከመ ኢትበል አነ አብዐልክዎ ለአብራም እንበለ ዘበ
ልዑ ሰብእየ እክል ።

ፈትል የጫማ ማዘቢያ ጠፍርም ቢሆን ከገንዘብህ እንዳ
ልወስድ እኔ አብራምን አበለጸግሁት እንዳትል፡ ቤተ ሰቦ
ቹ ከበሉት እኽል በቀር ። አስቴ. ፱፡ ፲፭ ።

፳፬ ዳእሙ እደው እለ ሖሩ ምስሌየ ኤስኮል ወመምሬ እሙ
ንቱ ይንሥኡ ክፍሎሙ ።

ግን ከኔ ጋራ የሄዱት መምሬና ኤስኮል እነርሱ ፈንታ
ቸውን ይውሰዱ ።

## ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ
አብራም በራእይ ወይቤሎ ኢትፍራህ አብራም አነ አፀን
ዐከ ወአዐብየከ ወዐስብከኒ ብዙኅ ውእቱ ጥቀ በኀቤየ ።

ከዚህ ነገር በኋላ በራእይ የእግዚአብሔር ቃል ወደ
አብራም መጣ አብራም አትፍራ እኔ አበረታሃለሁ፡ ከፍ
ከፍ አደርግሃለሁ፡ ዋጋህም በኔ ዘንድ እጅግ ብዙ ነው፡
አለው ። ዘፍ. ፳፯፡ ፳፬ ። ፪ ሳሙ. ፳፪፡ ፫ ። መዝ. ፫፡ ፫ ።
ምሳ. ፲፩፡ ፲፰ ። ሉቃ. ፩፡ ፲፫ ።

፪ ወይቤሎ አብራም ምንት ውእቱ እግዚኦ ዘትሁበኒ ወና
ሁ እመውት እንዘ አልብየ ውሉድ፡ ወናሁ ወልደ ማሴቅ
ዘደማስቆ ዘይብልዎ ኢያውብር ዘእምነ ወልደ ዘመድየ
ውእቱ ይወርሰኒ ።

አብራምም አቤቱ! የምትሰጠኝ ምንድር ነው፡ እነሆ
ልጅ ሳልወልድ እሞታለሁ፡ ከዘመዴ ወገን የሚሆን ሰው
ን ኢያውብር የሚሉት የደማስቆ ሰው የማሴቅ ልጅ እሱ
ይወርሰኛል አለው ።

፫ ይቤ አብራም እስመ ሊተ ኢወሀብከኒ ዘርአ ወልደ
ዘመድየ ውእቱ ይወርሰኒ ።

አብራም ለኔ ልጅ አልሰጠኸኝምና የዘመዴ ልጅ ይወር
ሰኛል አለ ። ዘፍ. ፲፬፡ ፲፬ ።

፬ ወበጊዜሃ ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ አብራም ወይ
ቤሎ ውእቱሰ ኢይወርሰከ አላ ከልእ ዘይወጽእ እምሐ
ቋከ ውእቱ ይወርሰከ ።

በዚያችም ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ወደ አብራም
መጣ፡ ከአብራክህ የተወለደ ልጅ ይወርስሃል እንጂ እሱ
አይወርስህም ብሎ ነገረው ። ፪ ሳሙ. ፯፡ ፲፪ ። ፪ ዜና
መ. ፴፪፡ ፳፩ ።

፭ ወአውጽአ አፍኣ ወይቤሎ ነጽር ውስተ ሰማይ ኣዕለ
ወኈልቆሙ ለከዋክብት ለእመ ትክል ኈልቆቶሙ፡ ወይ
ቤሎ ከማሁ ውእቱ ዘርእከ ።

ወደ ውጭ አውጥቶ ወደ ሰማይ እይ መቍጠር ትችል
እንደሆነ ከከቦችን ቍጠራቸው፡ ልጆችህም እንደዚያ ይበ
ዛሉ አለው ። ዘፍ. ፲፫፡ ፯ ። መዝ. ፻፵፯፡ ፬ ። ዘዐ. ፴፪፡
፲፫ ። ዘዳግ. ፩፡ ፲ ። ፩ ዜና መ. ፳፯፡ ፳፫ ። ኤር. ፴፫፡ ፳፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወአምኖ አብራም ለእግዚአብሔር ወተኈለቆ ሎቱ ጽድቀ ። | ፮ | አብራምም እግዚአብሔርን አመነው ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ። መዝ ፻፮ ፡ ፴፩ ። ሮሜ ፬ ፡ ፱ ። ገላ. ፫ ፡ ፯ ። |
| ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአውጻእኩከ እምድረ ከላውዴዎን ከመ አሀብከሃ ለዛቲ ምድር ትትዋረሳ ። | ፯ | እግዚአብሔርም ልትወርሳት ይህችን አገር እሰጥህ ዘንድ ከከላውዴዎን ያወጣሁህ ፈጣሪህ እኔ ነኝ አለው ። ዘፍ. ፲፩ ፡ ፳፰ ። መዝ. ፻፭ ፡ ፵፪ ። ሮሜ ፬ ፡ ፲፫ ። |
| ወይቤሎ እግዚኦ በምንት አአምር ከመ እወርሳ ። | ፰ | አቤቱ ! እንድወርሳት በምን አውቃለሁ ! አለው ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፲፫ ። መሳ ፯ ፡ ፲፯ ። ፩ ሳሙ. ፲፬ ፡ ፱ ። ፪ ነገ. ፳ ፡ ፰ ። |
| ወይቤሎ ንሣእ ለከ ላሕመ ዘ፫ ዓመቱ ፡ ወጠሊ ዘ፫ ዓመቱ ፡ ወበግዐ ዘ፫ ዓመቱ ፡ ወማዕነቀ ወርግበ ፡ ወንሣእ ከማሁ ዘንተ ኵሎ ወምትሮሙ እማእከሎሙ ፡ ወለአዕዋፍሰ ኢትምትሮን ። | ፱ | ፫ ዓመት የሆነው ላም ፡ ፫ ዓመት የሆነው ፍየል ፡ ፫ ዓመት የሆነው በግ ፡ ዋኖስንም ርግብንም ፡ አምጣ ፡ ይህንም ሁሉ አምጥተህ ከሁለት ከሁለት ቊረጣቸው ፡ ወፎችን ግን አትቊረጣቸው ፡ አለው ። |
| ወነሥአ ሎቱ ከማሁ ዘንተ ኵሎ ወመተሮሙ እማእከሎሙ ወአንበረ ዘተመትረ አንፃረ ቢጹ ወለአዕዋፍሰ ኢመተሮን ። | ፲ | እንዳዘዘውም ይህን ሁሉ አምጥቶ ከሁለት ከሁለት ቈረጣቸው ፡ የተቈረጠውንም በአንፃር በአንፃር አስቀመጠው ፡ ወፎቹን ግን አልቈረጣቸውም ። ዘሌ. ፩ ፡ ፲፯ ። ኤር. ፴፬ ፡ ፲፰ ። |
| ወወረዱ አልክቱ አዕዋፍ ላዕለ አብድንት ዘተመትሩ ፡ ወነበረ አብራም ኀቤሆሙ ወሜጠሙ ። | ፲፩ | ወፎችም ወደ ታረዱት ላሞች ወረዱ ፡ አብራምም ከሥጋው አጠገብ ተቀምጦ ከለከላቸው ። |
| ወሶበ የዐርብ ፀሐይ ድንጋፄ መጽአ ለአብራም ወናሁ ግሩም ጽልመት ወዐቢይ መጽአ ላዕሌሁ ። | ፲፪ | ፀሐይም በገባች ጊዜ አብራምን ድንጋጤ መጣበት ፡ ያን ጊዜም የሚያስፈራ ፅኑዕ ጨለማ መጣበት ። ዘፍ. ፪ ፡ ፳፩ ። ኢዮብ ፬ ፡ ፲፫ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብራም አእምሮ አእምር ከመ ሀለዎሙ ለዘርእከ ይኩኑ ፈላስያነ ውስቴ ምድር እንተ ኢኮነት እንቲአሆሙ ወይቀንይዎሙ ወይሣቅይዎሙ ወያሤዕርዎሙ ፬፻ ዓመተ ። | ፲፫ | እግዚአብሔርም አብራምን እንዲህ አለው ፤ ልጆችህ የእነሱ በልሆነች አገር መጻተኞች እንዲሆኑ ዕወቅ ፡ ፬፻ ዓመት ይገዟቸዋል ፡ ያሠቃዩአቸዋል ፡ ያስጨንቋቸዋል ። ዘፀ. ፩ ፡ ፲፩ ። ፲፪ ፡ ፵ ። ግ፡ ሐዋ. ፯ ፡ ፮ - ፯ ። |
| ወክዕበ ለሕዝብ እለ ሣቀይዎሙ አነ እኴንኖሙ ፡ ወእምድኅረ ዝንቱ ይወጽኡ ዝየ ምስለ ብዙኅ ንዋይ ። | ፲፬ | እኔም መከራ ያፀኑባቸውን ወገኖች ዳግመኛ እፈርድባቸዋለሁ ፡ ከዚያም በኋላ ከብዙ ገንዘብ ጋራ ወደዚህ (ወደ ከነአን) ይወጣሉ ። ዘፀ. ፲፪ ፡ ፴፮ ። መዝ ፻፭ ፡ ፴፯ ። |
| ወአንተሰ ተሐውር ወትገብእ ኀበ አበዊከ በርስዐ ሠናይ ። | ፲፭ | አንተ ግን በበጎ እርጅና ወደ አባቶችህ ትሄዳለህ ትሞታለህ ። ዘፍ. ፳፭ ፡ ፰ ። ኢዮብ ፭ ፡ ፳፯ ። ግብ. ሐዋ. ፲፫ ፡ ፴፯ ። |
| ወበራብዕ ትውልድ ይገብኡ ዝየ እስመ እስከ ይእዜ ኢተፈጸመ ኀጣውኢሆሙ ለአሞሬዎን ። | ፲፮ | የአሞሬዎን ኃጢአት እስከ ዛሬ ድረስ አልተፈጸመምና በአራተኛው ትውልድ ወደ ከነአን ይመለሳሉ ። ዘፍ. ፲፰ ፡ ፳፩ ። ኢያ. ፭ ፡ ፩ ። ፩ ነገ. ፳፬ ፡ ፳፯ ። ዳን. ፰ ፡ ፳፫ ። |
| ወሶበ ከነ ጊዜ የዓርብ ፀሐይ መጽአ ነድ ወመጽአ እሳት ወመጽአ እቶን ዘይጠይስ ወኀለፈ እንተ ማእከሉ ለውእቱ ዘተመትረ ። | ፲፯ | ፀሐይም በገባች ጊዜ የሚነድ የሚቃጠል የሚጤስ እሳት መጣ ፡ በተከፈለው ሥጋ መካከልም አለፈ ። |
| ወበይእቲ ዕለት አቀመ እግዚአብሔር ለአብራም ኪዳነ ዘአሰፈዎ ወይቤሎ ለዘርእከ እሁብ ለዛቲ ምድር እምነ ፈለገ ግብጽ እስከ ፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ ። | ፲፰ | በዚያችም ዕለት እግዚአብሔር ለአብራም ቀድሞ የሰጠውን ኪዳን አፀና ፡ እንዲህም አለው ፤ ይህችን ምድር ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ ኤፍራጥስ ድረስ ለዘርህ እሰጣታለሁ ። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፰ ። ዘፀ ፳፫ ፡ ፴፩ ። |
| ዘቄኔዎስ ወዘቄኔዝዮስ ወዘቄኔሚሎስ ። | ፲፱ | የቄኔዎስን ፡ የቄኔዚዎስን ፡ የቄኔሚሎስን አገር ። |
| ወዘኬጤዎን ወዘፌርዜዎን ወዘፈራዮን ። | ፳ | የኬጤዎንን ፡ የፌርዜዎንን ፡ የፈራዮንን አገር ። |
| ወዘአሞሬዎን ወዘከናኔዎን ወዘጌርጌሴዎን ወዘኢያቡሴዎን ። | ፳፩ | የአሞሬዎንን የከናኔዎንን የጌርጌሴዎንን የኢያቡሴዎንን አገር ። |

| ምዕራፍ ፲፮ ። | | ምዕራፍ ፲፮ ። |
|---|---|---|
| ወሶራሰ ብእሲቱ ለአብራም ኢወለደት ሎቱ ወባቲ አመት ግብጻዊት እንተ ስማ አጋር ። | ፩ | የአብራም ሚስት ሶራ ግን ልጅ አልወለደችለትም ነበር ፡ ስሟን አጋር የሚሏት ግብፃዊት አገልጋይ ነበረቻት ። ዘፍ ፲፩ ፡ ፲፫ ። ፲፪ ፡ ፲፯ ። ገላ. ፬ ፡ ፳፬ ። |
| ወትቤሎ ሶራ ለአብራም ናሁ ዐፀወኒ እግዚአብሔር | ፪ | ሶራም እነሆ እግዚአብሔር እንዳልወልድ ከለከለኝ ፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ከመ ኢይወልድ ሐር ኀበ አመትየ ከመ ትለድ እም ኔሃ ፡ ወሰምዐ አብራም ቃላ ለሶራ ብእሲቱ ። | | ወደ አገልጋዬ ግባ ከእሷ እንድትወልድ አለችው ፡ አብራምም የሚስቱን የሶራን ቃል ሰማ። ዘፍ. ፴፫ ፡ ፱ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ። |
| ወነሥአታ ሶራ ለአጋር አመታ ግብፃዊት እምድኅረ ፲ ዓመት ዘነደረ አብራም ውስተ ምድረ ከነአን ወወሀበቶ ለአብራም ትኩኖ ብእሲተ ። | ፫ | አብራም በከነአን መኖር ከጀመረ ከ፲ ዓመት በኋላ ፡ ሶራ ግብፃዊት አገልጋይዋ አጋርን ወስዳ ሚስት ትሆነው ዘንድ ለአብራም ሰጠችው ። ዘፍ. ፲፪ ፡ ፭ ። |
| ወቦአ አብራም ኀበ አጋር ወፀንሰት ወሶበ ርእየት ከመ ፀንሰት ኀደገት አክብሮታ ለእግዝእታ ። | ፬ | አብራምም ወደ አጋር ገባ እሷም አረገዘች ፡ እንዳረገዘችም ባየች ጊዜ እመቤትዋን ማክበርን ተወች ። ምሳ. ፴ ፡ ፳፩ - ፳፫ ። |
| ወትቤሎ ሶራ ለአብራም እትገፋዕ አንሰ እምኔከ እስ ወሀብኩከ አመትየ ውስተ ኅፅንከ ወሶበ ርእየት ከመ ፀንሰት ኀደገት አክብሮትየ ፡ ለይፍታሕ እግዚአብሔር ማእከሌየ ወማእከሌከ ። | ፭ | ሶራም አብራምን እኔ ከንተ የተነሣ እገፋለሁ ፡ እኔም አገልጋዬን በብብትህ ልታቅፋት ሰጠሁህ ፡ እንደፀነሰችም ባየች ጊዜ እኔን ማክበርን ተወች ፡ እግዚአብሔር በንተና በኔ መካከል ይፍረድ አለችው ። ዘፍ. ፴፩ ፡ ፶፫ ። ፩ ሳሙ. ፳፬ ፡ ፲፪ ። |
| ወይቤላ አብራም ለሶራ ብእሲቱ ነያ አመትኪ ውስተ እዴኪ ግበርያ ዘከመ ይኤድመኪ ፡ ወሣቀየታ ሶራ ለአጋር ወተኀጥአት እምኔሃ ። | ፮ | አብራምም ሚስቱን ሶራን እነሆ አገልጋይሽ በጅሽ ናት ፡ እንደወደድሽ አድርጊያት አላት ፡ ሶራም አጋርን አሠቃየቻት እሷም ከእመቤቷ ኰበለለች ። |
| ወረከባ መልአከ እግዚአብሔር በኀበ ዐዘቅተ ማይ በገዳመ ሱር በፍኖት ። | ፯ | የእግዚአብሔር መልአክም በሱር ምድረ በዳ ባለ በወኃ ጉድጓድ አጠገብ በጐዳና አገኛት ። ዘፍ. ፳ ፡ ፩ ። ፳፭ ፡ ፲፰ ። ዘፀ. ፲፭ ፡ ፳፪ ። ፩ ሳሙ. ፲፭ ፡ ፯ ። |
| ወይቤላ መልአከ እግዚአብሔር አጋር አመተ ሶራ እም አይቴ መጻእኪ ወአይቴ ተሐውሪ ፡ ወትቤሎ እምነ ገጸ ሶራ እግዝእትየ እትኀጣእ አንሰ ። | ፰ | የእግዚአብሔር መልአክም የሶራ አገልጋይ አጋር ከየት መጣሽ ፡ ወዴትስ ትሄጃለሽ አላት ፡ ከእመቤቴ ከሶራ ፊት እኰበልላለሁ አለችው ። |
| ወይቤላ መልአከ እግዚአብሔር ግብኢ ኀበ እግዝእትኪ ወአትሕቲ ርእሰኪ ታሕተ እዴሃ ። | ፱ | የእግዚአብሔር መልአክም ወደ እመቤትሽ ተመለሽና ራስሽን ከሥልጣኗ በታች አድርጊ አላት ። |
| ወይቤላ እግዚአብሔር አብዝኆ አበዝኆ ለዘርእኪ እስከ ኢይትኌለቍ እምነ ብዝኁ ። | ፲ | እግዚአብሔርም ከብዛቱ የተነሣ የማይቈጠር እስኪሆን ድረስ ዘርሽን አበዛዋለሁ አላት ። ዘፍ ፲፯ ፡ ፳ ። ፳፩ ፡ ፲፰ ። |
| ወይቤላ መልአከ እግዚአብሔር ናሁ ፅንስት አንቲ ወት ወልዲ ወልደ ወትሰምዪዮ ስሞ ይስማኤል እስመ ሰምዐ እግዚአብሔር ሥቃየኪ ። | ፲፩ | የእግዚአብሔር መልአክም እነሆ አንቺ አርግዘሻል ፡ እግዚአብሔር መከራሽን ሰምቷልና ወንድ ልጅ ትወልጂያለሽ ፡ ስሙንም ይስማኤል ትዪዋለሽ አላት ። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፲፱ ። ማቴ ፩ ፡ ፳፩ ። ሉቃ. ፩ ፡ ፲፫ - ፴፩ ። |
| ወይከውን ብእሴ ሐቅል እደዊሁ ላዕለ ኵሉ ወእደወ ኵሉ ላዕሌሁ ፡ ወየኀድር ቅድመ አኀዊሁ ። | ፲፪ | የአደን ሰው ይሆናል ፡ እጆቹ በሁሉ ላይ ናቸው ፡ የሰውም ሁሉ እጅ በሱ ላይ ነው ፡ በወንድሞቹ ፊትም ይኖራል ። ዘፍ. ፳፩ ፡ ፳ ። ፳፭ ፡ ፲፰ ። |
| ወጸውዐት አጋር ስመ እግዚአብሔር ዘተናገራ ወትቤ አንተ እግዚአ ዘመሀከኒ ፡ እስመ ቅድሜየ ርኢክዎ ለዘአስተርአየኒ ። | ፲፫ | አጋርም የተናገራት የእግዚአብሔርን ስም ጠራች ፡ አቤቱ! የራራህልኝ አንተ ነህ ፡ የታየኝን በፊቴ አይቸዋለሁና አለች ። |
| ወበእንተ ዝንቱ ሰመየቶ ስሞ ለውእቱ ዐዘቅት ዘቅድሜየ አስተርአየኒ ማእከለ ቃዴስ ወማእከለ ጋሬድ ወገብአት አጋር ። | ፲፬ | ስለዚህም ነገር ያንን ጕድጓድ ስሙን በፊቴ እግዚአብሔርን የአየሁበት አለችው ፡ ይኸውም ጕድጓድ በቃዴስና በጋሬድ መካከል ነው ፡ አጋርም ተመለሰች ። ዘፍ ፲፬ ፡ ፯ ፡ ። ፳፬ ፡ ፷፪ ። ዘኍ. ፲፫ ፡ ፳፯ ። |
| ወእምድኅረ ዝንቱ ወለደት ሎቱ አጋር ለአብራም ወሰመዮ ስሞ አብራም ለውእቱ ሕፃን ዘወለደት ሎቱ አጋር ይስማኤል ። | ፲፭ | ከዚህም በኋላ አጋር ለአብራም ልጅ ወለደችለት ፡ አብራምም አጋር የወለደችለትን የዚያን ልጅ ስሙ ይስማኤል አለው ። |
| ወ፹ወ፮ ዓመቱ ለአብራም አመ ወለደት ሎቱ አጋር ይስማኤልሃ ። | ፲፮ | አጋር ይስማኤልን በወለደችለት ጊዜ ለአብራም ፹፮ ዓመቱ ነበር ። |
| ምዕራፍ ፲፯ ። | | ምዕራፍ ፲፯ ። |
| ወእምዝ አመ ኮነ ለአብራም ፺ወ፱ ዓመተ አስተርአዮ እግዚአብሔር ለአብራም ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብ | ፩ | ከዚህም በኋላ ለአብራም ፺፱ ዓመት በሆነው ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለት እንዲህም አለው ፡ በፊ |

| | | |
|---|---|---|
| ሔር ፈጣሪከ ዘሖርኩ ቅድሜከ ኦሥምር ቅድሜየ ወኩን ንጹሐ ። | | ትህ የሄድኩ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ፤ በፊቴ በጎ ነገር አድርግ ንጹሕ ሁን ። ዘፍ. ፯ ፥ ፱ ። ፳፰ ፥ ፫ ። ፴፭ ፥ ፲፩ ። ዘፀ. ፳፬ ፥ ፵ ። ፪ ነገ. ፳ ፥ ፫ ። ዘዳ. ፲፰ ፥ ፲፫ ። ኢዮ. ፩ ፥ ፩ ። |
| ወእሠይም ኪዳነ ማእከሌየ ወማእከሌከ ወአበዝኀከ ጥቀ ። | ፪ | ባንተና በኔም መካከል ኪዳኔን አፀናለሁ ፤ ፈጽሜም አበዛሃለሁ ። |
| ወወድቀ አብራም በገጹ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብራም ። | ፫ | አብራም በግምባሩ ወድቆ ሰገደ ፤ እግዚአብሔርም አብራምን እንዲህ አለው ። |
| ናሁ እሠይም ኪዳንየ ማእከሌየ ወማእከሌከ ወትከውን አበ ለብዙኃን አሕዛብ ። | ፬ | እነሆ በኔና ባንተ መካከል ኪዳኔን አፀናለሁ ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆናለህ ። ሮሜ. ፬ ፥ ፲፩ ። ገላ. ፫ ፥ ፳፱ ። |
| ወኢይሰመይ እንከ ስምከ አብራም አላ አብርሃም ይሰመይ ፤ እስመ አበ ብዙኃን አሕዛብ ረሰይኩከ ። | ፭ | እንግዲህ ስምህ አብራም አይባልም አብርሃም እንጂ ፤ ለብዙዎች አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና ። ፱ ፥ ፯ ። ሮሜ. ፬ ፥ ፲፯ ። |
| ወአስተባዝኀከ ጥቀ ፈድፋደ ወእሬስየከ ከመ ይፃኡ እምኔከ አሕዛብ ወነገሥት ። | ፮ | እጅግ አበዛሃለሁ አሕዛብ ነገሥታት ከአንተ እንዲወለዱ አደርጋለሁ ። ዘፍ. ፴፭ ፥ ፲፩ ። ፲፯ ፥ ፲፯ ። |
| ወእሠይም ኪዳንየ ማእከሌየ ወማእከሌከ ወማእከለ ዘርእከ እምድኅሬከ በትውልዶሙ ከመ ይኩንከ ሕገ ዘለዓለም ከመ እኩ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ወለዘርእከ እምድኅሬከ ። | ፯ | በኔና ባንተ መካከል ከንተም በኋላ መሐላዬን በዘርህ መካከል ኪዳኔን አፀናለሁ ፤ ላንተ ከንተም በኋላ ለዘርህ አምላክህ እንድሆን በልጅ ልጃቸው የዘላለም ሕግ ይሆን ዘንድ ። ዘፍ. ፳፯ ፥ ፳፱ ። ገላ. ፫ ፥ ፲፯ ። ዕብ. ፲ ፥ ፯ ። |
| ወእሁብ ለዘቲ ምድር እንተ ውስቴታ ትኀድር ለዘርእከ ወኵሎ ምድረ ከነአን ከመ ይኩንንዋ ለዓለም ፤ ወእከውኖሙ አምላኮሙ ። | ፰ | ይህቺን አንተ ያለህባትን ምድር ለዘርህ እሰጣታለሁ ፤ የከነአንንም ምድር ሁሉ ፤ ለዘላለም ይገዟት ዘንድ ፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ ። ዘፀ. ፯ ፥ ፯ ። ዘሌዋ. ፳፯ ፥ ፲፪ ። ዘዳ ፲፬ ፥ ፪ ። ፳፮ ፥ ፲፰ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም አንተ ዕቀብ ሕግየ ወዘርእከ እምድኅሬከ በትውልዶሙ ። | ፱ | እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤ አንተ ሕጌን ጠብቅ ፤ ከንተም በኋላ ዘርህ ለትውልዳቸው ። |
| ወዛቲ ይእቲ ሥርዓትየ እንተ ትትዐቀብ ማእከሌየ ወማእከሌከ ወማእከለ ዘርእከ እምድኅሬከ ከመ ትትገዘሩ ኵሉ ተባዕትክሙ ከተማ ነፍስትክሙ ። | ፲ | ባንተና በኔ መካከል ከንተም በኋላ በልጆችህ መካከል የምትጠበቅ ሥርዓቴ ይህች ናት ፤ ወንዶቻችሁ ሁሉ ትገዘሩ ዘንድ ። |
| ወይኩንክሙ ትእምርተ ለኪዳንየ ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ። | ፲፩ | የሰውነታችሁን ቍልፍ ትገዘራላችሁ ፤ ባንተና በኔ መካከልም ለኪዳኔ ምልክት ይሆናል ። ግብ ሐ. ፯ ፥ ፰ ። ሮሜ. ፬ ፥ ፲፩ ። |
| ወለሕፃን ትገዝርዎ በሳምንት ዕለት ወኵሎ ተባዕተክሙ በትውልድክሙ ወልደ ቤትክሙኒ ወኵሎ ዘተሣየጥክሙ በወርቅክሙ ። | ፲፪ | ሕፃኑንም በ፰ኛው ቀን ትገዝሩታላችሁ ፤ ወንዱንም ሁሉ በትውልዳችሁ ትገዝሩታላችሁ ፤ በቤታችሁ የተወለደውን በወርቅ የገዛችሁትንም ሁሉ ። ዘሌዋ. ፲፪ ፥ ፫ ። |
| ወትኩን ሥርዓትየ ውስተ ሥጋክሙ ለኪዳንየ ዘለዓለም ። | ፲፫ | ለዘለዓለም ኪዳኔ ሥርዓቴ በሥጋችሁ ላይ ትሁን ። |
| ወዘኢተገዝረ ከተማ ነፍስቱ በሳምንት ዕለት ለትደምሰስ ይእቲ ነፍስ እምነ ዘመዳ፡እስመ ኀደገት ሥርዓትየ ። | ፲፬ | በ፰ኛው ቀን የሥጋውን ቍልፈት ያልተገዘረ ያቺ ነፍስ ከወገኗ ተለይታ ትጥፋ ፤ ሕጌን አፍርሳለችና ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ሶራ ብእሲትከ ኢትሰመይ እንከ ሶራ አላ ይኩን ስማ ፤ ሳራ ። | ፲፭ | እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤ ሚስትህ ሶራ ከእንግዲህ ወዲህ ሶራ አትባል ፤ ስሟ ሳራ ይባል እንጂ ። |
| እስመ እባርካ ወእሁብ ውሉደ እምኔከ ፤ አሕዛብ ወነገሥት አሕዛብ ይወፅኡ እምኔሃ ። | ፲፮ | እባርካታለሁና ከንተም ልጅ እሰጣታለሁና. አሕዛብ የአሕዛብ ነገሥታትም ከሷ ይወጣሉና ። ዘፍ ፯ ፥ ፱ ። ፲ ፥ ፲፰ ። ፳፬ ፥ ፮ ። ገላ. ፬ ፥ ፴፩ ። ፩ ጴጥ. ፫ ፥ ፯ ። ዘዳ ፲፰ ፥ ፲፫ ። |
| ወወድቀ አብርሃም በገጹ ወሰሐቀ ወሐለየ በልቡ እንዘ ይብል እንዘ ፻ትኑ ዓመት ሊተ እወልድ አነ ወልደ ፤ ወሳራኒ እንተ ፺ ዓም ላቲ ትወልድ ። | ፲፯ | አብርሃምም በግንባሩ ወደቀ በልቡም እኔ ፻ ዓመት ሲሆነኝ ልጅ እወልዳለሁን ፤ ፺ ዓመት የሆናት ሳራስ ትወልዳለችን ብሎ አሰበና ሳቀ ። ዘፍ. ፳፩ ፥ ፯ ። ፲፰ ፥ ፲፪ ። ፲፫ ፥ ፲፬ - ፲፭ ። ዮሐ ፰ ፥ ፯ ። ሮሜ ፬ ፥ ፲፱ ። |
| ወይቤሎ አብርሃም ለእግዚአብሔር ዝንቱ ይስማኤል ውእቱ ዳእሙ ይሕየወኒ በቅድሜከ አስተበቍዓከ እግዚኦ ። | ፲፰ | አብርሃምም እግዚአብሔርን ይህ ይስማኤል ብቻ ይኑርልኝ ፤ አቤቱ! እለምንሃለሁ አለው ። ዘፍ. ፲፭ ፥ ፲፯ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም አሆ! ወናሁ ሳራኒ | ፲፱ | እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤ እሺ ሚስ |

ብእሲትከ ትወልድ ለከ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ ይስሐቅ፡
ወአቀውም ሥርዓትየ ኀቤሁ ለኪዳን ዘለዓለም ወለዘርኡ
እምድኅሬሁ ።
፳ ወበእንተ ይስማኤልኒ ናሁ ሰማዕኩከ አበርኮ ወአበዝኖ
ወአስተበዝኖ ጥቀ ወ፲ተ ወ፪ተ አሕዛበ ይወልድ ወእ
ገብሮ ሕዝበ ዐቢየ ።
፳፩ ወኪዳንየሰ አቀውም ምስለ ይስሐቅ ዘትወልድ ለከ
ሳራ፡ በዝንቱ ጊዜ በካልእት ዓመት ።
፳፪ ወሶበ ፈጸመ እግዚአብሔር ተናግሮቶ ዐርገ እምኀቤሁ
ለአብርሃም ።
፳፫ ወነሥአ አብርሃም ለይስማኤል ወልዱ ወለኵሉ ልደ
ቤቱ፡ ወለኵሉ ተሣዩት ዘተማየጠ በወርቁ ወለኵሉ ሰብአ
ቤቱ፡ ወገዘሮሙ ከተማ ነፍስቶሙ በከመ ይቤሎ እግዚ
አብሔር ።
፳፬ ወይእተ አሚረ ፺ወ፱ ዓመት ሎቱ ለአብርሃም አመ
ተገዝረ ከተማ ነፍስቱ ።
፳፭ ወለይስማኤልኒ ወልዱ ፲ወ፫ቱ ዓመቱ አመ ተገዝረ ።
፳፮ ወበጊዜሃ በይእቲ ዕለት ተገዝረ አብርሃም ።
፳፯ ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ተገዝሩ ።

## ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለአብርሃም በኀበ ዕፀ መም
ሬ እንዘ ይነብር ኀበ ኆኅተ ሐይመት ቀትረ ።
፪ ወሶበ አልዐለ አዕይንቲሁ ነጸረ ወናሁ ሠለስቱ እደው
ይቀውሙ መልዕልቴሁ ፡ ወርእየ ወሮጸ ለተቀብሎቶሙ
እምኆኅተ ሐይመት ወሰገደ ውስተ ምድር ።

፫ ወይቤሎ እግዚኦ እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድመ አዕይን
ቲከ ኢትኅልፍ እምገብርከ ።
፬ ናምጽእ ለክሙ ማየ ወንሕጽብ እገሪክሙ ወታጽልሉ
ታሕተ ዕፅ ።
፭ ወናምጽእ ኅብስተ ወትብልዑ ወእምዝ ትሐውሩ ኀበ
ሐለይክሙ እምከመ ገኅሥክሙ ኀበ ገብርክሙ ወይቤ
ልዎ ግበር ከማሁ በከመ ትቤ ።
፮ ወሮጸ አብርሃም ኀበ ሳራ ብእሲቱ ውስተ ሐይመታ
ወይቤላ አፍጥኒ ወአብስኢ ሠለስተ መስፈርተ ሥንዳሴ
ወግበሪ ዳፍንተ ።
፯ ወሮጸ አብርሃም ኀበ አልሕምት ወነሥአ እሐደ ላሕመ
ንኡሰ ወሠናየ ወወሀበ ለቍልዔሁ ወአፍጠነ ገቢሮቶ ።

፰ ወአምጽአ ዕቋነ ወመዓረ ወውእተ ላሕመ ዘገብረ ወአቅ
ረበ ሎሙ ወበልዑ ፡ ወውእቱሰ ይቀውም ኀበ ዕፅ ወይ
ሜጥዎሙ ።
፱ ወይቤሉ አይቴ ሳራ ብእሲትከ፡ ወይቤሎ ነያ ውስተ
ሐይመት ።
፲ ወይቤሎ ሰበ ገባእኩ እመጽእ ኀቤከ ዓመ ከመ ዮም
ወትረክብ ሳራ ወልደ፡ ወሰምዐት ሳራ እንዘ ትቀውም
ኀበ ኆኅት እንዘ ሀለወት ድኅሬሁ ።

ትህ ሳራም እነሆ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፡ ስሙንም
ይስሐቅ ትለዋለህ፡ ለዘለዓለም ኪዳኔም አፀናለቻለሁ፡
ከሱም በኋላ ለዘሩ ። ዘፍ. ፲ ፡ ፰ ። ፳፩ ፡ ፪ ። ገላ. ፬ ፡ ፳፫ ።
ስለ እስማኤልም እነሆ ሰማሁ አበርከዋለሁ፡ አበዛዋ
ለሁ፡ የብዙ ብዙ አደርገዋለሁ ፲፪ ነገድ ይወልዳል፡ ታላቅ
ሕዝብም አደርገዋለሁ፡ ዘፍ. ፲፯ ፡ ፲ ። ፲፩ ፡ ፲፯ ። ፳፩ ፡ ፲፰ ።
ቃል ኪዳኔን ግን በ፪ኛው ዓመት በዚህ ጊዜ ሳራ ከም
ትወልድልህ ከይስሐቅ ጋራ አፀናለሁ ።
እግዚአብሔርም ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ከአብርሃም
ዘንድ ወጣ ። ዘፍ. ፴፭ ፡ ፲፫ ።
አብርሃም ልጁን ይስማኤልን በቤቱም የተወለደውን
ሁሉ ፡ በወርቁ የገዛውን ወንድ ሁሉ ፡ ቤተ ሰቡንም ሁሉ፡
ወሰደ፡ በዚያችው ዕለት እግዚአብሔር እንዳለው የሰውነ
ታቸውን ቍልፈት ገዘራቸው ።
ያን ጊዜም የሰውነቱን ቍልፈት በተገዘረ ጊዜ ለአብር
ሃም ፺፱ ዓመት ሁኖት ነበር ።
ልጁ ይስማኤልም በተገዘረ ጊዜ ፲፫ ዓመት ሆኖት ነበር።
ያን ጊዜ አብርሃም በዚያች ቀን ተገዘረ ።
ቤተ ሰቦቹም ሁሉ ተገዘሩ ።

## ምዕራፍ ፲፰ ።

አብርሃም በቀትር ጊዜ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ፡
እግዚአብሔር በዛፍ አጠገብ ተገለጠለት ። ዘፍ. ፲፫ ፡ ፲፰ ።
ዐይኑንም አንሥቶ ተመለከተ እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ
ቁመው ነበር፡ አይቶም ከድንኳኑ በር ሊቀበላቸው ሮጠ
በምድር ላይም ሰገደ ። ዘፍ. ፲፰ ፡ ፳፪ ። ፲፱ ፡ ፩ ። ዕ፩ ፡
፲፩ - ፲፫ ። ፵፰ ፡ ፲፯ ። ዘፀ. ፮ ፡ ፫ ። ፲፫ ፡ ፳፩ ። ፳ ፡ ፩ ።
እንዲህም አለው ፡ አቤቱ ! በፊትህ ባለሟልነትን አግ
ኝቼ እንደሆነ አገልጋይህን አትለፈኝ ።
ውኃ አምጥተን እግራችሁን እንጠባችሁ፡ ከዋላው ዕረ
ፉ ። ዘፍ. ፲፱ ፡ ፪ ። ፳፬ ፡ ፴፪ ። ፵፫ ፡ ፳፩ ።
እንጀራ እናምጣላችሁና ብሉ ፡ ከአገልጋያችሁ ከረፉችሁ
ከዚህ በኋላ ወደ አሰባችሁት ትሄዳላችሁ፡ እንዳልክ እን
ዲሁ አድርግ አሉት ።
አብርሃምም ሩጦ ወደ ሳራ ሚስቱ ወደ ድንኳን፡ ቶሎ
በዪ ሦስቱን መስፈርያ ዱቄት አቡክተሽ አንድ ዳቦ ጋግሪ
አላት ።
አብርሃምም ላሞች ወደ አሉበት ሮጠ፡ አንድ የሰባ
ወይፈን ወስደና ለብላቴናው ሰጠው፡ ብላቴናውም ፈጥኖ
አዘጋጀው ።
ማርና እርጎን ያዘጋጀውንም ሥጋ አምጥቶ አቀረበላ
ቸው በሉ ! እሱ ግን ከዛፍ አጠገብ ቁሞ ያሰልፍላቸው
ነበር ።
እሱም ሚስትህ ሳራ ወዴት ናት ! አለው እነሆ በድን
ኳን ውስጥ አለች አለው ። ዘፍ. ፳፩ ፡ ፳፯ ።
በተመለስኩ ጊዜ የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ወደ አንተ
እመጣለሁ፡ ሳራም ወንድ ልጅ ታገኛለች፡ ሳራም በድን
ኳኑ ደጃፍ በስተኋላው ቁማ ሳለች ይህን ሰማች ። ፲፰ ፡
፲፬ ። ፲፯ ፡ ፲፬ - ፳፩ ።

፲፩ ወአብርሃምሰ ወሳራ ልህቁ ጥቀ ወኀለፈ መዋዕሊሆሙ ፤ ወኀደጋ ለሳራሂ ትክቶ አንስት ።

አብርሃምና ሳራ ግን ፈጽመው አርጅተው ነበር ፤ ዘመናቸውም አልፎ ነበር ፤ ሳራንም የሴቶች ልማድ ትቷት ነበር። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፲፯ ። ፴፩ ፡ ፴፭ ። ሮሜ ፬ ፡ ፲፱ ። ዕብ. ፲፩ ፡ ፲፩ ።

፲፪ ወሰሐቀት ሳራ በበሕቲታ እስመ ትቤ በልባ ዓዲየኑ እስከ ይእዜ ፤ ወእግዚእየኒ ልህቀ ።

ሳራም ለብቻዋ ሳቀች ፤ በልቧ እንዲህ ብላለችና እስከ ዛሬ ገና ነኝን ! ጌታዬም አርጅቷል ። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፲፯ ። ሉቃ. ፩ ፡ ፲፰ ። ፩ ጴጥ. ፫ ፡ ፮ ።

፲፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ምንት አስሐቃ ለሳራ በበሕቲታ እንዘ ትብል ዓዲየኑ እስከ ይእዜ ፤ ወአማንኑ እወልድ እግዚእየኒ ልህቀ ወናሁ ረሳእኩ አንሰ ።

እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤ ሳራን ለብቻዋ ምን አሳቃት ፤ እስከ ዛሬ ገና ነኝን! በውነትስ እወልዳለሁን! ጌታዬም አርጅቷል ፤ እኔም አሁን አርጅቻለሁ ብላ ።

፲፬ ቦኑ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር በዝንቱ ጊዜ ሰበ ገባእኩ ኀቤከ በሳብዕት ትረክብ ሳራ ወልደ ።

ነገር ግን በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን! በቀጠርኩህ ዓመት ወደ አንተ በተመለስኩ ጊዜ ሳራ በሰባተኛ ወርዋ ልጅን ታገኛለች ። ኤር. ፴፪ ፡ ፲፯ ። ዘካ. ፰ ፡ ፮ ። ማቴ. ፲፱ ፡ ፳፮ ። ሉቃ. ፩ ፡ ፴፯ ። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፳፩ ።

፲፭ ወክሕደት ሳራ እንዘ ትብል ኢሰሐቁ እስመ ፈርሀት ፤ ወይቤላ አላ ሰሐቂ ።

ሳራም ፈርታለችና አልሳቅሁም ብላ ካደች ፤ የለም ሰቀሻል እንጂ አላት ።

፲፮ ወተንሥኡ ክልኤቱ እደው እምህየ ወአንጸሩ ወሖሩ መንገለ ሰዶም ወገሞራ ወሖረ አብርሃም ምስሌሆሙ ያስተፋንዎሙ ፤ ወተመይጠ አብርሃም ወቆመ ቅድመ እግዚአብሔር ።

ሁለቱ ሰዎች ከዚያ ተነሥተው ወደ ሰዶምና ወደ ገሞራ ጕዞአቸውን አቀኑ ፤ አብርሃምም ሊሸኛቸው አብሮ ሄደ ፤ አብርሃምም ተመልሶ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ ። ሮሜ ፲፭ ፡ ፳፬ ። ፫ ዮሐ ፭ ፡ ፮ ።

፲፯ ወይቤሎ እግዚአብሔር ኢየኀብእ እምቍልዔየ አብርሃም ዘእገብር አነ ።

ጌታም እንዲህ አለ እኔ የምሠራውን ከወዳጄ ከአብርሃም አልሠውርም ። መዝ. ፳፭ ፡ ፲፬ ። አሞ. ፫ ፡ ፯ ። ዮሐ. ፲፭ ፡ ፲፭ ።

፲፰ እስመ ሕዝበ ዓቢየ ወብዙኀ ይከውን ወይትባረኩ ቦቱ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ።

አብርሃም ታላቅና ብዙ ሕዝብ ይሆናልና በእሱም የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ። ዘፍ. ፲፪ ፡ ፫ ። ፳፪ ፡ ፲፰ ። ፳፮ ፡ ፬ ። ግብ. ሐ. ፫ ፡ ፳፭ ። ገላ. ፫ ፡ ፳፭ ።

፲፱ እስመ አአምር ከመ ሀለዎ ለአብርሃም የአዝዞሙ ለደቂቁ ወለቤቱ ወያዕቅቦሙ ፍናዊሁ ለእግዚአብሔር ከመ ይግበሩ ምጽዋተ ወፍትሐ ፤ ከመ ይግበር ሎሙ እግዚአብሔር ኵሎ ዘይቤሎ ለአብርሃም ።

እግዚአብሔር ለአብርሃም የነገረውን ሁሉ ያደርግላቸው ዘንድ ምጽዋትን ፤ ፍርድንም ፤ ያደርጉ ዘንድ የእግዚአብሔር ሕጉን ጠብቁ ብሎ ልጆቹን ቤተ ሰቦቹን እንዲያዝዛቸው አውቃለሁና ። ዘፍ. ፯ ፡ ፯ ። ዘዳ. ፬ ፡ ፱ - ፲ ። ፮ ፡ ፯ ። ኢያ. ፳ ፡ ፲፭ ። ኤፌ. ፮ ፡ ፬ ።

፳ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ጽራሖሙ ለሰዶም ወለገሞራ በጽሐ ኀቤየ ወኀጢአቶሙኒ በዝኀት ጥቀ ።

እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤ የገሞራና የሰዶም ጩኸታቸው ከፊቴ ደረሰ ፤ ኃጢአታቸውም እጅግ በዛች ። ዘፍ. ፬ ፡ ፲ ። ፲፱ ፡ ፲፫ ። ያዕ. ፭ ፬ ።

፳፩ እወርድ እንከሰ ወእርአይ ለእመ በከመ ጽራሖሙ እንተ ትመጽእ ኀቤየ ይፈጽምዋ ወእመ አኮሰ አአምር ።

እንግዲህስ እወርዳለሁ ፤ ወደ እኔ እንደምትመጣ እንደ ድንፋታቸው ያደርጉ እንደሆነ አያለሁ ፤ አለዚያም አውቃለሁ ። ዘፍ. ፲፩ ፡ ፭ ። ዘፀ. ፫ ፡ ፰ ። ዘዳ. ፰ ፡ ፪ ። ፲፫ ፡ ፫ ።

፳፪ ወሰበ ተመይጡ እምህየ እልክቱ እደው መጽኡ ውስተ ሰዶም ፤ ወአብርሃምሰ ሀሎ ዓዲ ይቀውም ቅድመ እግዚአብሔር ።

እነዚያ ሰዎች ከዚያ እንደ ተመለሱ ወደ ሰዶም መጡ ፤ አብርሃም ግን ገና በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ነበር ። ዘፍ. ፲፱ ፡ ፩ ። ፲፰ ፡ ፩ ።

፳፫ ወቀርበ አብርሃም ወይቤ ኢታማስን እግዚኦ ጻድቃነ ምስለ ኃጥአን ፤ ወኢይኩን ጻድቅ ከመ ኃጥእ ።

አብርሃምም ቀርቦ አቤቱ ! ጻድቃንን ከኃጥአን ጋር አታጥፋ ፤ ጻድቁም እንደ ኃጢአተኛው አይሁን ። ዘፍ. ፳ ፡ ፬ ። ፲፯ ፡ ፳፪ ። መዝ. ፻፴፯ ። ዕብ. ፳ ፡ ፪ ።

፳፬ ለእመ ሀለዉ ኀምሳ ጻድቃን በውስተ ሀገር ታማስኖሙኑ ወኢታሐይኖ በእንተ ፶ ጻድቃን ኵሎ ብሔረ ።

በአገር ፶ ደጋጎች ሰዎች ቢኖሩ ታጠፋቸዋለህን ! ስለ ፶ ደጋግ ሰዎችስ አገርን ሁሉ አታድንምን ! ዘዳግ. ፲፫ ፡ ፫ ።

፳፭ ሐሰ ለከ እግዚኦ ኢትግበር ዘንተ ነገረ ወኢትቅትል ጻድቃነ ምስለ ኃጥአን ፤ ሐሰ ዘይኴንና ለኵላ ምድር ኢትግበር ዘንተ ደይነ ።

አቤቱ ! ለአንተ አይገባም ይህን ነገር አታድርግ ፤ ጻድቃንንም ከኃጥአን ጋር አታጥፋ ፤ ዓለምን ሁሉ ፈጥሮ የሚገዛ አይገባም ፤ ይህን ቍርጥ ፍርድ አታድርግ ። ኢዮ. ፰ ፡ ፫ ። ፳ ፡ ፳ ። ሮሜ ፫ ፡ ፮ ።

፳፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለእመ ረከብኩ ውስተ ሀገረ ሰዶም ፶ ጻድቃነ አድኅን ኵሎ ሀገረ በእን ቲአሆሙ ።

በሰዶም ፶ ጻድቃን ካገኘሁ ስለእነሱ አገሪቱን በመላ አድናለሁ አለው ። ኤር ፭ ፣ ፩ ። ሕዝ. ፳፪ ፣ ፴ ።

፳፯ ወአውሥአ አብርሃም ወይቤ ይእዜ አኀዝኩ እትናገር ምስለ እግዚእየ እግዚአብሔር፣ ወአንሰ መሬት ወሐመድ አነ ።

አብርሃምም መልሶ እንዲህ አለ፤ እኔ አፈር ትቢያ ስሆ ን ከጌታዬ ከእግዚአብሔር ጋር እነጋገር ጀመር ። ዘፍ. ፪ ፣ ፯ ። ፫ ፣ ፲፱ ። ኢዮ. ፬ ፣ ፲፱ ። ሉቃ. ፲፰ ፣ ፩ ።

፳፰ ወእመሰኬ ውኅዱ እምእልክቱ ጻድቃን ፭ቱ ታማስንኑ ኵሎ ሀገረ በእንተ እለ ውኅዱ፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለእመ ረከብኩ በህየ ፵ወ፭ተ ኢያማስን በእንቲአሆሙ ።

ከነዚያ ከደጋጎች ሰዎች ፭ቱ ቢጐድሉስ ስለ አም ስቱ ሰዎች አገርን ሁሉ ታጠፋለህን፤ እግዚአብሔርም በዚያ ፵፭ ደጋጎች ሰዎች ካገኘሁ፣ ስለ እነሳቸው አላጠ ፋም አለው ።

፳፱ ወይቤሎ አብርሃም ለእመኬ ተረክቡ በህየ ፵፣ ወይ ቤሎ እግዚአብሔር፣ ኢያማስን በእንተ ፵ ።

አብርሃምም በዚያ ፵ ቢገኙስ፤ አለው፣ እግዚአብሔ ርም ስለ ፵ው አላጠፋም አለው ።

፴ ወደገመ ዓዲ ብሂሎቶ አብርሃም ወይቤሎ እመሰኬ ተረ ክቡ በህየ ፴፣ ወይቤሎ ኢያማስን በእንተ ፴ ።

አብርሃም ነገሩን እንደገና መለሰና በዚያ ፴ ቢገኙስ፤ አለው፣ ስለ ፴ውም አላጠፋትም አለው ።

፴፩ ወይቤሎ አብርሃም እስመ ተበዋሕኩ እትናገር ምስለ እግዚእየ እግዚአብሔር፣ ለእመኬ ተረክቡ በህየ ፳፣ ወይቤሎ ኢያማስን በእንተ ፳ ።

አብርሃምም ከጌታዬ ከእግዚአብሔር ጋራ እናገር ዘን ድ መብት አግኝቻለሁና፣ በዚያ ፳ ቢገኙስ፤ አለው፣ ስለ ፳ውም አላጠፋም አለው ።

፴፪ ወይቤሎ አብርሃም አብሐኒ እግዚኦ እንብብ ዓዲ ለእ መኬ ተረክቡ በህየ ፲ቱ፣ ወይቤሎ ኢያማስን በእንተ ፲ቱ።

አብርሃምም አሁን ልናገር ፍቀድልኝ በዚያ ፲ ቢገኙስ፤ አለው፣ ስለ ፲ሩም አላጠፋም አለው ። መሳ ፮ ፣ ፴፱ ።

፴፫ ወሰበ አኅለቀ ተናግሮቶ ለአብርሃም ኀለፈ እግዚአብ ሔር፣ ወአብርሃምኒ ገብአ ኀበ ምንባሪሁ ።

እግዚአብሔርም አብርሃምን ማነጋገሩን ከፈጸመ በኋላ ተሠወረው፣ አብርሃም ወደ ቦታው ተመለሰ ።

## ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወበጽሑ እልክቱ ፪ቱ መላእክት ውስተ ሰዶም ፍና ሰርክ፣ ወሎጥኒ ሀሎ ይነብር ውስተ አንቀጸ ሀገረ ሰዶም፣ ወሰበ ርእዮሙ ተንሥአ ወተቀበሎሙ ወሰገደ ሎሙ ።

እነዚያ ፪ቱ መልእክተኞችም ማታ ጊዜ ወደ ሰዶም ደረሱ፣ ሎጥም በሰዶም አገር በር ተቀምጦ ነበር፣ በያቸ ውም ጊዜ ተነሥቶ ተቀበላቸው፣ ሰገደላቸው ። ዘፍ. ፲፰ ፣ ፳፪ ። ፲፰ ፣ ፪ ።

፪ ወይቤሎሙ አጋእዝትየ ገኀሡ ኀበ ቤተ ገብርክሙ ወኅ ድሩ ወተሐፀቡ እገሪክሙ ወትጌሡ ወትሐሩ ፍኖተክሙ፣ ወይቤልዎ አልቦ፣ አላ ነኀድር ውስተ መርኅብ ።

ጌቶቼ! ወደ ብርያችሁ ቤት ገብታችሁ እደሩ እግራች ሁንም ታጠቡ፣ በጧትም ማልዳችሁ ጐዳናችሁን ሂዱ አላቸው፣ አይሆንም በአደባባይ እናድራለን እንጂ አሉት። ዘፍ. ፵፫ ፣ ፳፬ ። ሉቃ. ፳፬ ፣ ፳፰ ።

፫ ወአገበሮሙ ወግኅሡ ኀቤሁ ወቦኡ ውስተ ቤቱ ወገብረ ሎሙ ዳፍንተ ናእተ ወበልዑ ።

ግድ ግቡልኝ አላቸው፣ ከሱ ዘንድም ወደ ቤቱ ገቡ፣ ቂጣ ድፎም አዘጋጀላቸው እነሱም በሉ ።

፬ ወእንበለ ይስክቡ ሰብአ ለይእቲ ሀገር ዐገትዎ ለቤቶሙ ኵሉ ሰብአሙ ኅቡረ ንኡሶሙ ወዐቢዮሙ ።

ከመተኛት በፊትም የዚያች አገር ሰዎች ቤታቸውን ከበቡት ሰዎቻቸው ሁሉ ታላቁም ታናሹም በአንድነት ።

፭ ወጸውዕዎ ለሎጥ ወይቤልዎ አይቴ እሙንቱ እደው እለ በኡ ኀቤከ ሌሊተ፣ አውጽኦሙ ኀቤነ ከመ ንሕሮሙ ።

ሎጥም ጠርተው እነዚያ ማታ ወደ አንተ የገቡ ሰዎች የት አሉ፤ ወደኛ አውጣቸውና እንወቃቸው አሉት ። ዘፍ. ፲፫ ፣ ፲፫ ። መሳ. ፲፱ ፣ ፳፪ ። ኢሳ. ፫ ፣ ፱ ። ሮሜ ፩ ፣ ፳፬ - ፳፯ ። ይሁ. ፩ ፣ ፯ ።

፮ ወወፅአ ኀቤሆሙ ሎጥ ኀበ ኆኅት ቅድሚሆሙ ወዐ ፀወ ኆኅተ ድኅሬሁ ።

ሎጥም ወደ እነርሱ ወደ ደጅ ፊት ለፊት ወጣ፣ በሩ ንም በስተኋላው ዘጋ ። መሳ. ፲፱ ፣ ፳፫ ።

፯ ወይቤሎሙ ሐሰ ለክሙ አኀውየ፣ ኢታኅሥሙ ላዕለ እሉ ።

ወንድሞቼ! አይገባም በእነዚህ ሰዎች ላይ ክፉ ነገር አታድርጉ ።

፰ ወናሁ ብየ ፪ አዋልድ ዘኢየአምራ ብእሴ፣ ወአወ ፅኦን ለክሙ ወግበርዎን ዘከመ ይኤድመክሙ፣ ወበሕቱ ላዕለ እሉ እደው ኢትግበሩ ምንተኒ በመፃ እለ በኡ ታሕ ተ ጽላሎተ ቤትየ ።

እነሆ ባል ያላገቡ ፪ት ሴቶች ልጆች አሉኝ፣ ላውጣ ላችሁና እንደወደዳችሁ አድርጓቸው፣ ነገር ግን ወደ ቤቱ በገቡ በእነዚህ ሰዎች ላይ ምንም ምን ክፉ ነገር አታድ ርጉ አላቸው ። ዘፍ. ፲፱ ፣ ፳፬ ። ፲፰ ፣ ፭ ። ፴፫ ፣ ፫ - ፲ ።

፱ ወይቤልዎ ሑር ከሐከ፣ በእከ ከመ ትኅድር ምስሌነ ወአኮ ከመ ትኰንነነ፣ ወይእዜኒ ኪያከ ንሣቂ ፈድፋደ

ወዲያ ሂድ ከእኛ ጋር ልትኖር መጣህ እንጂ ልትገዛን አይደለም! አሁንም ከእነሱ ይበልጥ አንተን እናሠቃ

| | | |
|---|---|---|
| እምኔሆሙ፤ ወተኀየልዎ ለሎጥ ፈድፋደ ወቀርቡ ከመ ይስብርዎ ለኆኅት ። | | ይሃለን አሉት፤ እጅግ በረቱበት በሩንም ሊሰብሩት ቀረቡ ። ዘፍ. ፲፫ ፥ ፲፱ ። ፪ ጴጥ. ፪ ፥ ፯ - ፰ ። ዘፀ. ፪ ፥ ፲፬ ። |
| ወአውፅኡ እደዊሆሙ እልክቱ እደው ወሰሐብዎ ለሎጥ ወአብእዎ ኀቤሆሙ ውስተ ቤት ወዐፀዉ ኆኅተ ። | ፲ | እነዚያም ሰዎች እጃቸውን አውጥተው ሎጥን ጐትተው ወደ እነሱ ወደ ቤት ውስጥ አገቡት ፥ ደጃፉንም ዘጉ ። |
| ወለእልክቱሰ እደው እለ ሀለዉ ቅድመ ኆኅቱ ለውእቱ ቤት አፆርዎሙ አዕይንቲሆሙ ለንኡሶሙ ወለዐቢዮሙ ፤ ወሠርሑ እንዘ የኀሥሥዎ ለውእቱ ኆኅት ወኀጥእዎ ። | ፲፩ | በዚያ ቤት በር ፊት ለፊት ያሉትን ሰዎች ግን ዓይናቸውን አሣወሯቸው ፤ ትንሹንም ትልቁንም በሩን በመፈለግ ደከሙ አላገኙትም ። ግ፡ ሐዋ. ፲፫ ፥ ፲፩ ። |
| ወይቤልዎ ለሎጥ እልክቱ መላእክት ቦኑ ዘብከ በዝየ ታእኅ፤ አው ታሕማ፤ ወእመሂ ደቂቅ ወአዋልድ፤ ወለእመቦ ዘብከ ዐርክ፤ ዘተአምር ውስተዝ ሀገር አውፅኦሙ እምነ ዝንቱ መካን ። | ፲፪ | እነዚያ መልእክተኞችም ሎጥን እንዲህ አሉት ፤ በዚህ ያለህ ዘመድ፤ አማች፤ ይኖርህ ይሆን፤ ወንዶች ልጆች ሴቶች ልጆች እንዳሉ፤ የምትወደው ወዳጅም በዚች አገር እንዳለ ከዚች በታ አውጣቸው ። ፪ ጴጥ. ፪ ፥ ፯ - ፱ ። |
| እስመ ናማስና ንሕነ ለዝቲ መካን እስመ ዐብየ ገዐሮሙ በቅድመ እግዚአብሔር ወፈነወነ ከመ ንደምስሳ ። | ፲፫ | እኛ ይህቺን በታ እናጠፋታለንና ጩኸታቸው በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ ብሏልና ልናጠፋት ልኮናል ። |
| ወወፅአ ሎጥ ኀበ ታሕማሁ እለ ይነሥእዎን ለአዋልዲሁ ወይቤሎሙ ተንሥኡ ወፃኡ እምዝቲ ሀገር፤ እስመ ይደመስሳ እግዚአብሔር ለዛቲ ሀገር፤ ወመሰሎሙ ለታሕማሁ ከመ ዘበሥላቅ ይቤሎሙ ። | ፲፬ | ሎጥም ወጥቶ ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን የሚያገቡት አማቾቹን ተነሡ ከዚች አገር ውጡ፤ እግዚአብሔር ይህቺን አገር ያጠፋታልና አላቸው፤ ለአማቾቹ ግን በቀልድ የሚነግራቸው ይመስላቸው ነበር ። ዘፍ. ፲፱ ፥ ፰ ። ዘኍ. ፲፮ ፥ ፳፩ ። ፳፬ ፥ ፳፮ - ፵፭ ። ኤር. ፶፩ ፥ ፮ ፡ ራእ. ፲፰ ፥ ፬ ። |
| ወሶበ ጸብሐ አጉጕእዎ መላእክት ለሎጥ ወይቤልዎ ተንሥእ ወንሣእ ክልኤሆን አዋልዲከ ወብእሲተከ፤ ወፃእ ከመ ኢትሙት በኃጢአቶሙ ለሰብአ ዛቲ ሀገር ። | ፲፭ | ጎሕም በቀደደ ጊዜ መልእክተኞች ሎጥን ተነሥ ሁለቱ ልጆችህንና ሚስትህን ይዘህ ውጣ፤ አንተም በዚህች ሀገር ሰዎች ኃጢአት እንዳትጠፋ እያሉ ያስቸኩሉት ጀመር ። ዘፍ. ፬ ፥ ፲፫ ። |
| ወሶበ ጐንደየ አኀዝዎ እዴሁ እልክቱ እደው ወእደ ብእሲቱ ወክልኤሆን አዋልዲሁ ወአውፅእዎሙ እስመ ምህከሙ እግዚአብሔር ። | ፲፮ | በዘገየ ጊዜም እነዚያ ሰዎች እሱንና ሚስቱን ሁለቱን ልጆቹንም እጅ እጃቸውን ይዘው አወጧቸው፤ እግዚአብሔር ራርቶላቸዋልና ። |
| ወይቤልዎ ሶበ አውፅእዎ አፍኅእ አድኅን ነፍሰከ ወኢትንጽር ድኅሬከ ወኢትቁም ውስተ አድያሚሃ፤ ወውስተ ደብራ ለዛቲ ሀገር ከመ ኢትርከብከ ለከኒ እኪት ። | ፲፯ | ወደ ውጭም በወጡት ጊዜ ነፍስህን አድን ወደ ኋላህም አትይ፤ አንተንም መከራ እንዳታገኝህ በዳርቻዋ በዚያችም አገር ተራራ አትቁም አሉት ። ዘፍ ፲፱ ፥ ፳፮ ። |
| ወይቤሎሙ ሎጥ ብቍዑኒ እጋእዝትየ ። | ፲፰ | ሎጥም እንዲህ አላቸው፤ ጌቶቼ! በጀ በሉኝ ። ግ፡ ሐዋ. ፲ ፥ ፲፬ ። |
| እመ ረከብኩ ምሕረተ በቅድሜክሙ ወአዕበይክ ለምሕረትከ ምስሌየ ከመ ታሕይዎ ለነፍስየ፤ አንሰ ኢይክል አድኅኖ ርእስየ ውስተ ደብር ከመ ኢትርከበኒ እኪት ወኢይሙት ። | ፲፱ | በፊትህ ምሕረትን አግኝቼ እንደሆነ ሰውነቴንም ታድናት ዘንድ፤ ቸርነትህን አብዝተህልኝ እንደሆነም መከራ አግኝቶኝ እንዳልጠፋ እኔ ወደ ተራራ ሸሽቼ ራሴን ማዳን አልችልም ። |
| ወናሁ ዛቲ ሀገር ቅርብት ይእቲ ወንስቲት እሩጽ ህየ ወአድኅን ርእስየ፤ ወኢኮነት ንስቲተ እምከመ ድኅነት ነፍስየ ። | ፳ | እነሆ ይህች አገር ቅርብ ናት ትንሽ ናት፤ ወደዚያች ሩጬ ራሴን ላድን፤ ግን ሰውነቴ ከዳነች ትንሽ አይደለችም ። |
| ወይቤሎ ናሁ አድኀንኩዎ ለገጽከ ወበከመ ትቤ ኢይገፍትኣ ለዛቲ ሀገር እንተ በእንቲአሃ ነበብከኒ ። | ፳፩ | እንዲህ አለው እነሆ ፊትህን አልመለስኩትም (ልመናህን ተቀብያለሁ) ስለ እሷ የነገርኸኝን ይቺን አገርም አላጠፋትም ። ኢዮ. ፵፪ ፥ ፰ - ፱ ። |
| ሶፍጥን እንከ ወአድኅን ርእሰከ ህየ፤ እስመ ኢይክል ገቢረ ምንተኒ እስከ ትበጽሕ፤ በእንተ ዝንቱ ተሰምየት ይእቲ ሀገር ሴጎር ። | ፳፪ | እንግዲህ አፍጥን ወደዚያም ድረስህ ራስህን አድን፤ ወደዚያም እስክትደርስ ምንም ምን አላደርግምና፤ ስለዚህም ያቺ አገር ሴጎር ተባለች ። |
| ሠረቀ ፀሐይ በዲበ ምድር ወሎጥኒ ቦአ ውስተ ሴጎር ። | ፳፫ | ፀሐይ በምድር ላይ ወጣ፤ ሎጥም ወደ ሴጎር ገባ ። |
| ወአዝነመ እግዚአብሔር ላዕለ ሰዶም ወገሞራ እሳተ ወተየ እምኀበ እግዚአብሔር እምሰማይ ። | ፳፬ | እግዚአብሔርም ከሱ ዘንድ ከሰማይ በገሞራና በሰዶም እሳትና ዲን አዘነመ ። ዘዳ ፳፱ ፥ ፳፫ ። ኢሳ ፲፫ ፥ ፲፱ ። ኤር. ፳ ፥ ፲፮ ። ፶ ፥ ፵ ። ሕዝ ፲፮ ፥ ፵፱ - ፶ ። አሞ. ፬ ፥ ፲፩ ። |
| ወገፍትአን ለእማንቱ አህጉር ወለአድያሚሆን ምስለ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴቶን ወለኵሉ ዘርአ ምድሮሙ ። | ፳፭ | እነዚያን አገሮች አውራጃቸውንም ከሚኖሩባቸው ሰዎች ሁሉ ጋራ አጠፋቸው፤ የምድራቸውንም አዝመራ ሁሉ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወነጸረት ብእሲተ ሎጥ ድኅሬሃ ወኮነት ሐውልተ ጼው። | ፳፮ | የሎጥ ሚስትም ወደ ኋላዋ ተመልሳ አይታ የጨው ደንጊያ ሆነች ። ሉቃ. ፲፯ ፣ ፴፪ ። |
| ወጌሠ አብርሃም ውስተ ዝኩ መከን ኀበ ቆመ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፳፯ | አብርሃምም በእግዚአብሔር ፊት ወደ ቆመበት ወደ ዚያ ቦታ ገሥግሦ ሄደ ። ዘፍ. ፲፰ ፣ ፳፪ ። |
| ወነጸረ ላዕለ ገጸ ሰዶም ወገሞራ ወላዕለ አድያሚሃ ፣ ወሰበ ርእየ ናሁ የዐርግ ነድ እምድር ከመ ጢሰ እቶን ። | ፳፰ | ወደ ገሞራና ወደ ሰዶም አየ አውራጃዋንም ሁሉ ፣ በየም ጊዜ እነሆ እንደ ምድጃ ጢስ ከምድርም እሳት ሲወጣ አየ ። ራእ. ፲፰ ፣ ፱ ። |
| ወከነ ሰበ ደምሰሶን እግዚአብሔር ለአህጉር ወለኵሉ አድያሚሆን አለ ውስቴቶን የኀድር ሎጥ ተዘ ከሮ ለአብርሃም ፣ ወአውፅአ ለሎጥ እማእከለ ሙስና ። | ፳፱ | እግዚአብሔርም ሎጥ የሚኖርባቸውን እነዚያን አገሮ ችና አውራጃቸውንም ሁሉ በአጠፋ ጊዜ እንዲህ ሆነ ፣ እግዚአብሔር አብርሃምን አሰበው ፣ ሎጥም ከጥፋት አዳ ነው ። ዘፍ. ፰ ፣ ፩ ። |
| ወዐርገ ሎጥ እምነ ሴጎር ወኀደረ ውስተ ደብር ወክል ኤቲ አዋልዲሁ ምስሌሁ እስመ ፈርሀ ነቢረ ውስተ ሴጎር ወነበረ ውስተ በዓት ውእቱ ወክልኤሆን አዋልዲሁ ። | ፴ | ሎጥ ከሴጎር ወጥቶ በተራራ ተቀመጠ ፣ ሁለቱም ሴቶች ልጆች አብረዉት ነበር ፣ በሴጎር መቀመጥን ፈርቷልና በዋሻ ውስጥም ተቀመጠ ፣ እሱም ሁለት ሴቶች ልጆቹም ። ዘፍ. ፲፱ ፣ ፲፯ - ፲፱ ። |
| ወትቤላ እንተ ትልኅቅ ለእንተ ትንእስ ናሁ አቡነ አረጋዊ ውእቱ ፣ ወአልቦ ሰብእ ዘይበውእ ኀቤነ ከመ ይትዋ ለድ ውስተ ኵሉ ምድር ። | ፴፩ | ታላቂቱ ታናሺቱን እንዲህ አለቻት ፣ እነሆ አባታችን አርጅቷል ፣ በምድር ሁሉ እንደሚባዘው ለማድረግ ወደ እኛ የሚገባ ሰው የለም ። |
| ንዒ ናስትዮ ወይነ ለአቡነ ወንስክብ ምስሌሁ ወናቅም ዘርአ እምአቡነ ። | ፴፪ | ነዪ ወይን እናጠጣውና ከእሱ ጋር እንተኛ ፣ ከአባታች ንም ዘር እናስቀር ። |
| ወአስተያሁ ወይነ ለአቡሆን ወበይእቲ ሌሊት ቦአት እንተ ትልኅቅ ወሰከበት ምስለ አቡሃ ፣ ወኢያእመረ በሰ ኪቦታ ወበተንሥአታ ። | ፴፫ | ለአባታቸውም ወይን አጠጡት ፣ በዚያችም ሌሊት ታላ ቂቱ ገብታ ከባቷ ጋር ተኛች ፣ እሱ ግን ስትተኛም ስትነ ሣም አላወቀም ። |
| ወእምዝ ትቤላ እንተ ትልኅቅ ለእንተ ትንእስ ናሁ ሰከ ብኩ ትማልም ምስለ አቡነ ፣ ከዕበ ናስትዮ ወይነ ወስከቢ ምስሌሁ በዛቲ ሌሊት ወናቅም ዘርአ እምአቡነ ። | ፴፬ | ከዚህም በኋላ ታላቂቱ ታናሺቱን እንዲህ አለቻት ፣ እነሆ ትናንትና እኔ ከአባታችን ጋራ ተኛሁ ፣ ዳግመኛም ወይን እናጠጣው አንቺም በዚች ሌሊት ከእሱ ጋራ ተኚ ፣ ከአባታችንም ዘር እናስቀር ። |
| ወአስተያሁ ወይነ በይእቲ ሌሊት ወቦአት እንተ ትን እስ ወሰከበት ምስለ አቡሃ ፣ ወኢያእመረ በሰኪቦታ ወበ ተንሥአታ ። | ፴፭ | በዚያችም ሌሊት ወይን አጠጡት ፣ ታናሺቱ ገብታ ከአ ባቷ ጋራ ተኛች ፣ እሱ ግን ስትተኛም ስትነሣም አላወቀም ። |
| ወፀንሳ ክልኤሆን አዋልዲሁ ለሎጥ እምአቡሆን ። | ፴፮ | የሎጥ ሁለቱ ልጆቹም ከአባታቸው ፀነሱ ። |
| ወወለደት እንተ ትልኅቅ ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ሞአብ ዘእምአቡየ ብሂል ፣ ወውእቱ አቡሆሙ ለሞአባውያን ። | ፴፯ | ታላቂቱም ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ሞአብ አለ ችው ፣ ይኸውም ከአባቴ የወለድኩት ማለት ነው ፣ እሱም እስከ ዛሬ የሞአባውያን አባት ነው ። ዘዳ. ፪ ፣ ፱ ። |
| ወወለደት ወልደ እንተ ትንእስኒ ወሰመየቶ ስሞ አሞን እንዘ ትብል ዘእምዘመድየ ፣ ወውእቱ አቡሆሙ ለአሞና ውያን እስከ ዮም ። | ፴፰ | ታናሺቱም ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ስሙንም አሞን አለ ችው ፣ ከወገኔ ወለድኩት ስትል ፣ እሱም እስከ ዛሬ የአሞ ናውያን አባት ነው ። ዘዳ. ፪ ፣ ፲፱ ። |
| ምዕራፍ ፳ ። | | ምዕራፍ ፳ ። |
| ወተንሥአ አብርሃም እምህየ ወሖረ መንገለ ምድረ አዜብ ፣ ወኀደረ ማእከለ ቃዴስ ወማእከለ ሱሬ ወነበረ ውስተ ጌራራ ። | ፩ | አብርሃምም ከዚያ ተነሥቶ ወደ አዜብ ምድር ሄደ ፣ በሱሬና በቃዴስ መካከል ኖረ ፣ በጌራራም ተቀመጠ ። ዘፍ. ፲፰ ፣ ፩ - ፴፫ ። ፲፯ ፣ ፯ - ፲፬ ። ፳፮ ፣ ፫ ። ፲ ፣ ፲፱ ። |
| ወይቤሎሙ አብርሃም በእንተ ሳራ ብእሲቱ እኅትየ ይእቲ ፣ ወለአከ አቤሜሌክ ንጉሠ ጌራራ ወነሥአ ለሳራ ። | ፪ | አብርሃም ሳራ ሚስቱን እኅቴ ናት አላቸው ፣ የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክም ልኮ ሳራን ወሰዳት ። ዘፍ. ፲፪ ፣ ፲፫ - ፳ ። ፳፮ ፣ ፯ - ፲፩ ። |
| ወቦአ እግዚአብሔር ኀበ አቤሜሌክ በይእቲ ሌሊት እንዘ ይነውም ወይቤሎ በሕልም ናሁ ትመውት አንተ በእንተ ዛቲ ብእሲት እንተ ነሣእከ እስመ ብእሲተ ብእሲ ይእቲ ። | ፫ | በዚያች ሌሊት አቤሜሌክ ተኝቶ ሳለ እግዚአብሔር ወደ አቤሜሌክ ገባ በሕልም እሷ የጉልማስ ሚስት ናትና ስለዚች ስለ ወሰድካት ሴት አንተ እነሆ ትሞታለህ አለው ። መዝ. ፻፭ ፣ ፲፬ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወአቤሜሌክሰ ኢለከፋ ፣ ወይቤ አቤሜሌክ ሕዝበኑ ዘኢያእመረ በጽድቅ ትቀትል ። | ፬ | አቤሜሌክ ግን አልነካትም ነበር ፣ አቤሜሌክም እንዲህ አለ በእውነት ያላወቀ ሰውን ታጠፋለህን፣ ዘፍ. ፲፰ ፣ ፳፫። |
| ለሊሁ ይቤለኒ እኅትየ ይእቲ ፣ ወይእቲኒ ትቤለኒ እኅቱ አነ፣ ወበንጹሕ ልብ ወበጽድቀ እደውየ ገበርክዎ ለዝንቱ። | ፭ | እሱ እኅቴ ናት አለኝ ፣ እሷም እኅቱ ነኝ አለችኝ ፣ ይህ ንንም ሥራ በንጹሕ ልቤ በንጹሕ እጄ አደረግሁት አለ ው ። ዘፍ. ፲፯ ፣ ፩ ። ፪ ሳሙ. ፲፭ ፣ ፲፩ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር በሕልም አነኒ አእመርኩ ከመ በንጹሕ ልብ ገበርከ ለዝንቱ ወምህኩከ ወዐቀብኩከ ከመ ኢተአብስ፣ ወበእንተ ዝንቱ ኢኅደጉከ ትቅረብ ። | ፮ | እግዚአብሔርም በሕልም እንዲህ አለው ፣ እኔም በየዋ ህነትህ እንዳደረግኸው አውቄአለሁና ራራሁልህ ኃጢአ ትም እንዳትሠራ ጠበቅሁህ፣ ስለዚህም እንድትቀርብት አልፈቀድኩልህም ። ዘፍ. ፴፱ ፣ ፱ ። መዝ. ፶፩ ፣ ፬ ። |
| ወይእዜኒ አግብእ ለብእሲ ብእሲቶ እስመ ነቢይ ውእቱ ወይጼሊ በእንቲአከ ወተሐዩ፣ ወእመሰ ኢያግባእከ እአ ምር ከመ ሞተ ትመውት አንተ ወኵሉ ዘዚአከ ። | ፯ | አሁንም ለዚያ ሰው ሚስቱን መልስለት ፣ ደግ ሰው ነውና ስለ አንተም ይጸልይልሃል አንተም ትድናለህ፣ በትመልስለት ግን አንተ ሞትን እንድትሞት ፣ ያንተ የሆ ነውም ሁሉ እንዲጠፋ ዕወቅ አለው። ዘፀ. ፯ ፣ ፩። ዘኍ. ፲፯ ፣ ፴፪ - ፴፫ ። ፩ ሳሙ. ፯ ፣ ፭ ። ኢዮ. ፵፪ ፣ ፰ ። |
| ወተንሥአ አቤሜሌክ በጽባሕ ወጸውዐ ኵሎ ደቀ ወን ሮሙ ዘንተ ነገረ ፣ ወፈርህዎ ለእግዚአብሔር ኵሉ ሰብአ ቤቱ ጥቀ ። | ፰ | አቤሜሌክም በጧት ተነሥቶ አሽከሮቹን ጠራቸው ይህንንም ነገር ነገራቸው ፣ ቤተ ሰቦቹም ሁሉ ፈጽመው እግዚአብሔርን ፈሩት ። |
| ወጸውዖ አቤሜሌክ ለአብርሃም ወይቤሎ ምትኑ ዝ ዘገ በርከ ላዕሌየ ወላዕለ መንግሥትየ ፣ ኀጢአት ዐቢይ ዘኢገ ብሮ መኑሂ ። | ፱ | አቤሜሌክም አብርሃምን ጠርቶ ይህ በእኔና በመንግ ሥቴ ላይ ያደረግኸው ምንድር ነው ፣ ማንም የማይሠ ራው ታላቅ ኃጢአት ነው አለው ። ዘፍ. ፳፱ ፣ ፳፯ ። |
| ወይቤሎ አቤሜሌክ ለአብርሃም ምንተ ርእየከ ዘገበር ከሁ ለዝንቱ ነገር ። | ፲ | አቤሜሌክም አብርሃምን ይህን ያደረግኸው ምን አይ ተህ ነው ፣ አለው ። |
| ወይቤሎ አብርሃም እስመ እቤ ዮጊ አልቦ ፍርሃተ እግዚ አብሔር ውስተዝ መከን፣ ወይቀትሉኒ በእንተ ብእሲትየ። | ፲፩ | አብርሃምም እንዲህ አለ ምናልባት በዚህ ቦታ እግዚ አብርሔርን መፍራት የለምና ስለ ሚስቴ ይገድሉኛል ብዬ ነው ። ምሳ. ፲፯ ፣ ፯ ። |
| ወካዕበ አማን እኅትየ ወይእቲ እመንገለ አቡየ ፣ ወአከ እመንገለ እምየ ወኮነተኒ ብእሲተ ። | ፲፪ | ዳግመኛም በእውነቱ እኅቴ የአባቴ ወገን ናት ፣ ከእናቴ በኩል አይደለችም ፣ ሚስትም ሆነችኝ ። ዘፍ. ፲፩ ፣ ፳፱ ። |
| ወአመ አውፅአኒ እግዚአብሔር እምቤተ አቡየ እቤላ ዘንተ ጽድቀ ግበሪ ሊተ ውስተ ኵሉ መከን ኀበ በእነ በሊ እኅትየ ውእቱ ። | ፲፫ | እግዚአብሔርም ከባቴ ቤት በወጣኝ ጊዜ ይህንን በጎ ሥራ አድርጊልኝ፣ በገባንበትም ቦታ ሁሉ ወንድሜ ነው በዪ አልኋት ። ዘፍ. ፲፪ ፣ ፩ ። |
| ወነሥአ አቤሜሌክ ዐሠርተ ምእተ ጠፋልሐ ብሩር ወአግብርተ ወአእማተ ወአባግዐ ወአልሕምተ ወወሀበ ለአብርሃም ወአግብአ ሎቱ ብእሲቶ ሳራሃ ። | ፲፬ | አቤሜሌክም ሺሕ ምዝምዝ ብርን፣ ሴቶች አገልጋዮ ችንና ወንዶች አገልጋዮችን ላሞችንና በጎችንም አም ጥቶ ለአብርሃም ሰጠው ፣ ሚስቱ ሳራንም መለሰለት ። ዘፍ. ፲፪ ፣ ፲፯ ። |
| ወይቤሎ አቤሜሌክ ለአብርሃም ናሁ ምድርየ ቅድ ሜከ ኀበ ፈቀድከ ንበር ። | ፲፭ | አቤሜሌክም አብርሃምን እነሆ አገሬ በፊትህ ናት በወ ደድከው ኑር አለው ። ዘፍ. ፲፫ ፣ ፱ ። ፴፬ ፣ ፲ ። ፲፯ ፣ ፯ ። |
| ወይቤላ ለሳራሂ ፣ ናሁ ወሀብክዎ ለእኁኪ ዐሠርተ ምእ ተ ጠፋልሐ ብሩር ፣ ወዝንቱ ይኩንኪ ለኪ ለክብረ ገጽኪ ወበኵሉ ጽድቀ ተናገሪ ። | ፲፮ | ሳራንም እነሆ ለወንድምሽ ሺሕ ምዝምዝ ብር ሰጠ ሁት ፣ ይህም ለፊትሽ ጌጥ ይሁንሽ አላት ፣ በሁሉም በጎ ነገር ተናገራት ። ዘፍ. ፳፭ ፣ ፳፬ - ፳፭ ። |
| ወጸለየ አብርሃም ኀበ እግዚአብሔር ወፈወሶ እግዚአብ ሔር ለአቤሜሌክ ወለብእሲቱ ወለአዋልዲሁ ወለአእማ ቲሁ እለ ውስተ ቤቱ ወወለዳ ። | ፲፯ | አብርሃምም ወደ እግዚአብሔር ለመነ፣ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ፈወሰው ፣ ሚስቱንም ባሮቹንና ልጆቹን ቤተ ሰቦቹንም ልጆቹንም ወለዱ ። |
| እስመ ዐጊወ ዐፀዋ እግዚአብሔር ለማኅፀን እምአፍአሃ በእንተ ሳራ ብእሲተ አብርሃም ። | ፲፰ | ስለ አብርሃም ሚስት ስለ ሳራ እግዚአብሔር ማኅፀንን ሁሉ ፈጽሞ ዘግቶ ነበርና ። ዘፍ. ፲፪ ፣ ፲፯ ። |

ምዕራፍ ፳፩ ። ምዕራፍ ፳፩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወሐወፃ እግዚአብሔር ለሳራ ወበከመ ይቤ ገብረ ላቲ እግዚአብሔር ። | ፩ | እግዚአብሔርም ሳራን ጐበኛት ፣ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው አደረገላት ። ዘፍ. ፲፯ ፣ ፲፱ ። ፩ ሳሙ. ፪ ፣ ፳፩ ። ፲፰ ፣ ፲ - ፲፬ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወፀንሰት ሳራ ወወለደት ወልደ ለአብርሃም በርስዐቲሁ በመዋዕል ዘይቤሎ እግዚአብሔር ። | ፪ | ሳራም እግዚአብሔር በነገረው ቀን በርጅናዋ ፀንሳ ለአብርሃም ወንድ ልጅ ወለደችለት ። ዘፍ. ፲፯፡ ፳፩ ። ዕብ. ፲፩፡ ፲፩ ። ገላ. ፬፡ ፳፪ ። |
| ወሰመዮ አብርሃም ለውእቱ ሕፃን ዘወለደት ሎቱ ሳራ ይስሐቅ ። | ፫ | አብርሃምም ሳራ የወለደችለትን ያንን ሕፃን ይስሐቅ ብሎ ጠራው ። ዘፍ. ፲፯፡ ፲፱ ። |
| ወገዘሮ በሳምንት ዕለት በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ። | ፬ | እግዚአብሔር እንዳዘዘውም በ፰ኛው ቀን ገዘረው ። ዘፍ. ፲፯፡ ፲-፲፪ ። ግ፡ ሐዋ ፯፡ ፰ ። |
| ወለአብርሃም ፻ት ዓመቱ አመ ተወልደ ሎቱ ይስሐቅ። | ፭ | ይስሐቅም በተወለደለት ጊዜ ለአብርሃም ፻ ዓመት ሆኖት ነበር ። ዘፍ. ፲፯፡ ፩-፲፯ ። |
| ወትቤ ሳራ ሰሐቀ ረሰየኒ እግዚአብሔር ወኵሉ ዘይሰምዕ ይትፌሣሕ ሊተ ። | ፮ | ሳራም እግዚአብሔር ደስ አሰኘኝ፤ የሰማውም ሁሉ ስለኔ ደስ ይሰኛል አለች ። ኢሳ. ፶፬፡ ፩ ። ገላ. ፬፡ ፳፯ ። |
| ወትቤ መኑ እምዜነዎ ለአብርሃም ከመ ትሐፅን ሳራ ሕፃነ ዘወለደት በርስዓቲሁ ። | ፯ | በርጅናዋ የወለደችውን ልጅ ሳራ እንድታሳድግ ለአብርሃም ማን በነገረው! አለች ። ዘፍ. ፲፰፡ ፲፩-፲፪ ። |
| ወልሀቀ ሕፃን ወአኅደግዎ ጥበ፤ ወገብረ አብርሃም ማእደ ዐቢየ በዕለተ አኅደግዎ ጥበ ለይስሐቅ ። | ፰ | ልጁ አደገ ጡትንም አስጣሉት፤ ይስሐቅን ጡት በስጣሉት ቀንም አብርሃም ታላቅ ምሳ አደረገ ። |
| ወርእየቶ ሳራ ለይስማኤል እንዘ ይትዌነይ ምስለ ይስሐቅ ወልዳ ። | ፱ | ሳራም ይስማኤልን ከልጅዋ ከይስሐቅ ጋራ ሲጫወት አየችው ። ዘፍ ፲፯፡ ፩ ። ፲፡ ፯ ። ገላ. ፬፡ ፳፱ ። |
| ወትቤሎ ሳራ ለአብርሃም ስድዳ ለዛቲ ዓመት ምስለ ወልዳ፡ እስመ ኢይወርስ ወልዳ ለዓመት ምስለ ወልድየ ይስሐቅ ። | ፲ | ሳራም አብርሃምን ይህቺን ባርያ ከነልጅዋ አባርራት፤ የባርያ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አይወርስምና አለችው ። |
| ወዕፁበ ክዋ ዝንቱ ነገር በቅድሜሁ ለአብርሃም ጥቀ በእንተ ወልዱ ። | ፲፩ | ይህም ነገር ለአብርሃም እጅግ ጭንቅ ሆነበት ስለ ልጁ። ዘፍ. ፲፯፡ ፲፰ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ኢይኩን ዕፁበ ቅድሜከ በእንተ ዝንቱ ሕፃን ወበእንተ ዛቲ ዓመት ኵሎ ዘትቤለከ ስምዓ ለሳራ፤ እስመ እምይስሐቅ ይሰመይ ለከ ዘርእ ። | ፲፪ | እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው የዚህ ልጅ፡ የዚችም ባርያ ነገር በፊትህ ጭንቅ አይሁንብህ፤ የምትልህን ሁሉ ሳራን ስማት ከይስሐቅ ዘር ይትከልሃልና አለው ። ሮሜ ፱፡ ፯ ። ዕብ. ፲፩፡ ፲፰ ። |
| ወለወልዳኒ ለዛቲ ዓመት ዐቢየ ሕዝበ እሬስዮ እስመ ዘርእ ዚአከ ውእቱ ። | ፲፫ | የዚችን የባርያ ልጅም ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ ያንተ ዘር ነውና ። ዘፍ. ፲፯፡ ፳ ። ፳፩፡ ፲፰ ። |
| ወተንሥአ አብርሃም በጽባሕ ወነሥአ ኅብስተ ወማዕረ ማይ ወሀበ ለአጋር ወአንበረ ዲበ መትከፍታ ወሕፃንኒ ወፈነዋ ወሖረት፤ ወስከወየት ውስተ ገዳም መንገለ ዐዘቅተ መሐላ ። | ፲፬ | አብርሃምም በጧት ተነሥቶ እንጀራና ጮጮ ወስዶ ለአጋር ሰጣት፤ በጫንቃውም አሸከማት ልጁንም ሠጥቶ አሰናበታት፤ በመሐላ ጉድጓድ በኩልም ባለ በምድረ በዳ ተቅበዘበዘች ። ዘፍ. ፳፩፡ ፴፩ ። |
| ወኀልቀ ማይሂ ዘውስተ ማዕረ ወገደፈቶ ለሕፃን ታሕተ አሐቲ ዕፅ ወሖረት ። | ፲፭ | ውኃውም ከጮጮዋ አለቀ፤ ሕፃኑንም ከአንዲት ዛፍ ሥር ጥላው ሄደች ። |
| ወነበረት ትኔጽሮ እምርኁቅ ከመ ምንዳፈ ሐጽ እስመ ትቤ ኢይርአይ ሞቶ ለሕፃንየ ወበከየት ። | ፲፮ | የጦር መወርወርያ ያህል ርቃ እየተመለከተችው ተቀመጠች፤ የልጄን ሞት አልይ ብላለችና ምርር ብላም አለቀሰች ። |
| ወሰምዐ እግዚአብሔር እውያቶ ለውእቱ ሕፃን፤ ወጸውዓ መልአከ እግዚአብሔር ለአጋር እምሰማይ ወይቤላ ምንተ ኮንኪ አጋር፤ ኢትኅዝኒ እስመ ሰምዐ እግዚአብሔር ቃሎ ለሕፃንኪ እምውስተ መካን ኀበ ሀሎ ተንሥኢ ወንሥኢ ሕፃንኪ ። | ፲፯ | እግዚአብሔርም የዚያን ልጅ ልቅሶ ሰማ፤ የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ወርዶ አጋርን ጠርቶ እንዲህ አላት፤ አጋር ምን ሁነሻል፤ አትዘኚ፤ እግዚአብሔር የልጅሽን ልቅሶ ካለበት ቦታ ሰምቷልና ተነሺ ልጅሽን ያዥው። |
| ወአፅንዒዮ በእዴኪ እስመ ሕዝበ ዐቢየ እሬስዮ ። | ፲፰ | በክንድሽ አቅፈው ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁና ። |
| ወፈትሐ እግዚአብሔር አዕይንቲሃ ለአጋር ወርእየት ዐዘቅተ ማይ፤ ወሖረት ወመልአት ማዕረ ማየ ወአስተየቶ ለሕፃን ። | ፲፱ | እግዚአብሔርም የአጋርን ዓይኖቿን ከፈተ የውኃ ጉድጓድን አየች፤ ሄዳ ውኃውንም በጮጮዋ መላች ለልጅዋም አጠጣችው ። |
| ወሀሎ እግዚአብሔር ምስለ ውእቱ ሕፃን፤ ወልሀቀ ወኀደረ ውስተ ውእቱ ገዳም ወኮነ ነዳፌ ። | ፳ | እግዚአብሔርም ከዚያ ልጅ ጋራ ነበር፤ አደገና በዚያም በምድረ በዳ ኖረ አዳኝም ሆነ ። ዘፍ. ፴፱፡ ፪ ። ፫፡ ፳፩ ። ፲፯፡ ፲፪ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወእምዝ ኃደረ ውስተ ሐቅለ ፋራን፡ ወነሥአት ሎቱ እሙ ብእሲተ እምድረ ግብጽ ። | ፳፩ | ከዚያም በኋላ በፋራን ምድረ በዳ ኖረ፡ እናቱም ከግብጽ አገር ሚስት አጋባችው ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፬ ። |
| ወኮነ በእማንቱ መዋዕል ሖሩ አቤሜሌክ ወአኮዘት መጋቤ መራዕይሁ ወፋኮል መልአከ ሠራዊቱ ኀበ አብርሃም ወይቤልዎ እግዚአብሔር ምስሌከ በኵሉ ዘገበርከ ። | ፳፪ | በነዚያ ወራት እንዲህ ሆነ አቤሜሌክ የመንጋው ሹም አኮዘትና የሠራዊቱ አለቃ ፋኮል ወደ አብርሃም ሄዱና በአደረግኸውም ሁሉ እግዚአብሔር ከንተ ጋር አለ አሉት ። ዘፍ. ፳ ፡ ፪ ። ፳፯ ፡ ፩ - ፳፯ ። ፳፯ ፡ ፳፰ ። |
| ወይቤ አቤሜሌክ ይእዜኒ መሐል ሊተ በእግዚአብሔር ከመ ኢትዐምፀኒ ኢ. ለዘርእየ ወኢ. ለሥጋየ ወኢ. ለዘምስሌየ፡ አላ በከመ መጻእከ አንተ ወገበርኩ ለከ ትግበር ሊተ ወለምድርየኒ እንተ ሀሎከ ውስቴታ ። | ፳፫ | አቤሜሌክም አሁንም በእግዚአብሔር ማልልኝ በእኔ ክፉ እንዳታደርግብኝ፡ በልጄም ፡ በወገኔ ከእኔ ጋር ባለው ሁሉ አንተ ወደኔ እንደመጣህ እኔም እንደተቀበልኩህ እንድታደርግልኝ ላለህበት ምድርም እንዲሁ እንድታደርግ ። ዘፍ. ፳፯ ፡ ፳፱ ። ኢያ. ፲፪ ። ፩ ሳሙ. ፳፬ ፡ ፳፩ ። |
| ወይቤ አብርሃም እሆ፡ እምሕል አንሰ ። | ፳፬ | አብርሃምም እሺ እምላለሁ አለ ። |
| ወተዛለፎ አብርሃም ለአቤሜሌክ በእንተ ዐዘቅተ ማይ ዘሄድዎ ደቁ ። | ፳፭ | ግን አብርሃም አሽከሮቹ ስለቀሙት ስለውኃው ጉድጓድ አቤሜሌክን ወቀሰው ። |
| ወይቤ አቤሜሌክ ኢያእመርኩ መኑ ገብሮ ለዝንቱ ግብር፡ ወአንተኒ ኢያይዳዕከኒ፡ ወአንኒ ኢሰማዕኩ ዘእንበለ ዮም ። | ፳፮ | አቤሜሌክም ይህን ሥራ ማን እንዳደረገው አላወቅሁም፡ አንተም አልነገርከኝ፡ እኔም ያለ ዛሬ አልሰማሁም አለ ። |
| ወነሥአ አብርሃም አልሕምተ ወአባግዐ ወወሀበ ለአቤሜሌክ፡ ወተማሐሉ በበይናቲሆሙ ። | ፳፯ | አብርሃምም በጎችንና ላሞችን አምጥቶ ለአቤሜሌክ ሰጠው፡ እርስ በርሳቸውም ተማማሉ ። ዘፍ. ፳፯ ፡ ፴፩ ። |
| ወአቀመ አብርሃም ፯ አባግዐ እንተ ባሕቲቶን ። | ፳፰ | አብርሃምም ፯ በጎችን ለብቻቸው አቆመ ። |
| ወይቤሎ አቤሜሌክ ለአብርሃም፡ ምንትኑ እላ ፯ አባግዕ እለ አቀምከን እንተ ባሕቲቶን ። | ፳፱ | አቤሜሌክም አብርሃምን እሊህ ለብቻቸው ያቆምካቸው ፯ በጎች ምንድር ናቸው፤ አለው ። ዘፍ. ፴፫ ፡ ፰ ። |
| ወይቤሎ አብርሃም፡ እላንተ ፯ አባግዐ ንሣእ እምእዴየ ከመ ይኩናኒ ስምዐ ከመ ከረይክዋ ለዛቲ ዓዘቅት ። | ፴ | አብርሃምም ይህችን ጉድጓድ እንደቈፈርኋት ምስክር ይሆኑኝ ዘንድ፡ እሊህን ፯ በጎች ከእጄ ተቀበል አለው ። |
| ወበእንተዝ ሰመዮ ለውእቱ ዐዘቅት ቤርሳቤህ፡ እስመ በህየ ተማሐሉ በበይናቲሆሙ ። | ፴፩ | ስለዚህም ያን ጉድጓድ ቤርሳቤህ ብሎ ጠራው፡ በዚያ እርስ በርሳቸው ተማምለዋልና ። ዘፍ. ፳፩ ፡ ፲፬ ። ፳፯ ፡ ፴፫ ። |
| ወተካየዱ ኪዳነ በኀበ ዐዘቅተ መሐላ፡ ወተንሥአ አቤሜሌክ ወአኮዘት መጋቤ መራዕይሁ፡ ወፋኮል መልአከ ሠራዊቱ ወተመይጡ ውስተ ምድረ ፍልስጥኤም ። | ፴፪ | በመሐላ ጉድጓድ አጠገብም መሐላን ተማማሉ፡ አቤሜሌክም ተነሣ፡ የመንጋው ሹም አኮዘትም የሠራዊቱ አለቃ ፋኮልም ወደ ፍልስጥኤም ምድር ተመለሱ ። |
| ወተከለ አብርሃም ዕፀወ በቀልት ኀበ ዐዘቅተ መሐላ፡ ወጸውዐ አብርሃም በህየ ስመ እግዚአብሔር ዘለዓለም ። | ፴፫ | አብርሃምም በመሐላ ጉድጓድ አጠገብ የዘንባባ ዛፍ ተከለ፡ አብርሃምም በዚያ ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር የእግዚአብሔርን ስም ጠራ ። ዘፍ. ፬ ፡ ፳፮ ። ፩ ሳሙ. ፳፪ ፡ ፮ ። |
| ወነበረ አብርሃም ውስተ ምድረ ፍልስጥኤም ብዙኀ መዋዕለ ። | ፴፬ | አብርሃምም በፍልስጥኤም ምድር ብዙ ዘመን ኖረ ። ዘፍ. ፲ ፡ ፲፬ ። ፳፮ ፡ ፩ ። |

## ምዕራፍ ፳፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ አመከሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም ወይቤሎ አብርሃም አብርሃም፡ ወይቤ ነየ አነ ። | ፩ | ከዚህም በኋላ እንዲህ ሆነ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፡ አብርሃም አብርሃም ብሎ ጠራው፡ እሱም አቤት አለ ። ፩ ቆሮ. ፲ ፡ ፲፫ ። ዕብ. ፲፩ ፡ ፲፯ ። ያዕ. ፩ ፡ ፲፪ - ፲፫ ። |
| ወይቤሎ ንሥአ ለወልድከ ዘታፈቅር ይስሐቅሃ፡ ወሑር ውስተ ደብር ላዕላይ ወአዕርጎ ህየ ወሡዖ ላዕለ አሐዱ ደብር ዘእቤለከ ። | ፪ | የምትወደው ልጅህ ይስሐቅንም ይዘኸው ወደ ላይኛው የተራራ አገር ሂድ፡ ወደዚያም አውጥተህ እኔ በዘዝኩህ በአንዱ ተራራ ላይ ሠዋው አለው ። ፪ ዜና መ. ፫ ፡ ፩ ። |
| ወተንሥአ አብርሃም በጽባሕ ወረሐነ አድጎ ወነሥአ ፪ ደቆ፡ ወይስሐቅሃኒ ወልዶ፡ ወሠፀረ ዕፀወ ለመሥዋዕት ወእፆረ ወሖረ ። | ፫ | አብርሃምም በጧት ተነሥቶ አህያውን ጫነ፡ ልጁ ይስሐቅንና፡ ሁለቱ ብላቴኖቹንም ወሰደ፡ ለመሥዋዕትም ዕንጨቶችን ፈልጦ አሸክሞ ሄደ ። |
| ወበጽሐ ውስተ ውእቱ መካን ኀበ ይቤሎ እግዚአብሔር በሣልስት ዕለት፡ ወነጸረ አብርሃም በአዕይንቲሁ ወርእየ መካነ እምርሑቅ ። | ፬ | በ፫ኛውም ቀን እግዚአብሔር ወዳለው ወደዚያ ቦታ ደረሰ፡ አብርሃምም በዓይኑ ቃኘ በቦታውንም ከሩቅ አየ ። |
| ወይቤሎሙ አብርሃም ለደቂቀ ንበሩ ዝየ ምስለ አድግ፡ | ፭ | አብርሃምም ብላቴኖቹን እናንተ አህያውን ይዛችሁ ከዚ |

| | | |
|---|---|---|
| አነ ወወልድየ ነሐውር እስከ ደብር ወሰጊደነ ንገብእ ኀቤክሙ ዝየ ፡፡ | | ህ ቱዩ ፡ እኔና ልጄ ግን ወደ ተራራ እንሄዳለን ፡ ሰግደንም ወደ እናንተ እንመለሳለን አላቸው ፡፡ |
| ወነሥአ አብርሃም ዕፀወ ዘመሥዋዕት ወአፆሮ ለይስሐቅ ወልዱ ወነሥአ እሳተኒ ውስተ እዴሁ ወመጥባሕተኒ ወሖሩ ፪ሆሙ ኅቡረ ፡፡ | ፮ | አብርሃም መሥዋዕት የሚቃጠልበትን ዕንጨት አምጥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው ፡ እሱም ወቅለምቱንና እሳቱን በጁ ያዘ ፡ ሁለቱም በአንድነት ሄዱ ፡፡ ዮሐ ፲፱ ፡ ፲፯ ፡፡ |
| ወይቤሎ ይስሐቅ ለአብርሃም አቡሁ አባ ፡ ወይቤሎ ምንት ውእቱ ወልድየ ፡ ወይቤሎ ናሁ ዕፅ ወእሳትኒ ፡ አይቴ ሀሎ በግዑ ለመሥዋዕት ፡፡ | ፯ | ይስሐቅም አባቱ አብርሃምን አባ አለው ፡ እሱም ልጄ ምንው ! አለው እነሆ እሳትና ዕንጨት አለ ፡ መሥዋዕት የሚሆነው በጉ ወዴት ነው ! አለው ፡፡ ዘፍ. ፳፪ ፡ ፰፡ ዘፀ. ፲፪ ፡ ፫ - ፭ ፡፡ ኢሳ. ፶፫ ፡ ፳፫ ፡፡ |
| ወይቤሎ አብርሃም እግዚአብሔር ይሬኢ ሎቱ በግዐ ለመሥዋዕት ወልድየ ፡፡ | ፰ | አብርሃምም ልጄ ! መሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ያሰባል አለው ፡፡ |
| ወሖሩ ኅቡረ ወበጽሑ ውስተ ውእቱ መከን ዘይቤሎ እግዚአብሔር ወነደቀ አብርሃም ምሥዋዐ በህየ ወወደየ ዕፀወ ፡ ወአሠሮ ወአዕቀፆ ለይስሐቅ ወልዱ ወአስከቦ በከብዱ ላዕለ ምሥዋዕ መልዕልተ ዕፀው ፡፡ | ፱ | አብረውም ሄዱና እግዚአብሔር ወደ አለው ወደዚያ ቦታ ደረሱ ፡ አብርሃምም በዚያ መሠዊያ ሠራ ዕንጨቱን ደረደረ ፡ ልጁ ይስሐቅንም አሥሮ ጠልፎ በመሠውያው በዕንጨቱ ላይ በልቡ አስተኛው ፡፡ ያዕ ፪ ፡ ፳፩ - ፳፪ ፡፡ |
| ወአልዓለ እዴሁ አብርሃም ወነሥአ መጥባሕተ ከመ ይሕርዶ ለወልዱ ፡፡ | ፲ | አብርሃምም ልጁን ያርደው ዘንድ እጁን ዘርግቶ ወቅለምቱን አነሣ ፡፡ |
| ወጸውዖ እግዚአብሔር ለአብርሃም ወይቤሎ አብርሃም አብርሃም ፡ ወይቤ ነየ አነ ፡፡ | ፲፩ | እግዚአብሔርም አብርሃምን ፡ አብርሃም አብርሃም ፡ ብሎ ጠራው ፡ እሱም አቤት ! አለው ፡፡ |
| ወይቤሎ ኢትደይ እዴከ ላዕለ ወልድከ ወኢትግበር ቦቱ ምንተኒ ይእዜ አእመርኩ ከመ አንተ ትፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኢመሐከ እምኔየ ለወልድከ ዘታፈቅር ፡፡ | ፲፪ | በልጅህ ላይ እጅህን አትዘርጋ ምንም ምን አታድርግበት ፡ አንተ እግዚአብሔርን እንድትፈራው አሁን አወቅሁ ፡ ለምትወደው ለልጅህ አልራራህለትምና ፡፡ ዘፍ. ፳፯ ፡ ፭፡ ሚክ. ፯ ፡ ፯ ፡፡ |
| ወሶበ ነጸረ አብርሃም ርእየ ናሁ ፩ዱ በግዕ ወእኁዝ አቅርንቲሁ በዕፀ ሳቤቅ ፡ ወሖረ አብርሃም ወነሥኦ ወሦዖ ህየንተ ይስሐቅ ወልዱ ፡፡ | ፲፫ | አብርሃምም በተመለከተ ጊዜ ቀንድና ቀንዱ በዕፀ ሳቤቅ የተያዘ አንድ በግ አየ ፡ አብርሃምም ሄደና ወስዶ በልጁ በይስሐቅ ፈንታ ሠዋው ፡፡ |
| ወሰመዮ አብርሃም ለውእቱ መከን ራእየ እግዚአብሔር እንዘ ይብል ዮም አስተርአዮ አስተርአየኒ እግዚአብሔር በዝ ደብር ፡፡ | ፲፬ | አብርሃምም አሁን በዚህ ተራራ እግዚአብሔር ፈጽሞ ታየኝ ሲል ፡ የዚያን ቦታ ስሙን እግዚአብሔርን ያየሁበት አለው ፡፡ ዘፍ. ፳፪ ፡ ፰ ፡፡ |
| ወጸውዖ መልአከ እግዚአብሔር ለአብርሃም ዳግመ እምሰማይ ፡፡ | ፲፭ | የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ አብርሃምን ዳግመኛ ጠራው ፡፡ |
| ወይቤሎ መሐልኩ በርእስየ ይቤ እግዚአብሔር እስመ ገበርከ ለዝንቱ ነገር ወኢመሐከከ እምኔየ ወልድከ ዘታፈቅር ፡፡ | ፲፮ | እንዲህ አለው ይህንን ነገር አድርገኸዋልና ለምትወደው ልጅህም ከኔ አልራራህለትምና በራሴ ማልኩ አለ እግዚአብሔር ፡፡ መዝ. ፻፭ ፡ ፱ ፡፡ ሉቃ. ፩ ፡ ፸ ፡፡ ዕብ. ፮ ፡ ፲ ፡፡ |
| ከመ ባርኮ እባርከከ ወአብዝኆ አስተበዝኆ ለዘርእከ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ወከመ ኆፃ ዘድንጋገ ባሕር ወይወርሱ ዘርእከ አህጉረ ፀር ፡፡ | ፲፯ | መባረከን እባርክሀለሁ ዘርህንም የብዙ ብዙ አደርገዋለሁ በሰማይ እንዳሉ ከዋክብት በባሕር እንዳለ አሸዋ አደርገዋለሁ ፡ ልጆችህ የጠላት አገሮችን ይወርሳሉ ፡፡ መዝ. ፻፭ ፡ ፱ ፡፡ ሉቃ. ፩ ፡ ፸፫ ፡፡ ዕብ. ፯ ፡ ፲፫ ፡፡ |
| ወይትባረኩ በዘርእከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር እስመ ሰማዕከ ቃልየ ፡፡ | ፲፰ | ቃሌን ሰምተሃልና የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይከብራሉ አለው ፡፡ ዘፍ. ፲፰ ፡ ፰ ፡፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ፡፡ ኤር. ፴፫ ፡ ፰ ፡፡ ፪ ሳሙ. ፲፯ ፡ ፲፩ ፡፡ ፩ ነገ. ፱ ፡ ፰ ፡፡ ኢሳ. ፵፰ ፡ ፲፱ ፡፡ መዝ. ፻፳፯ ፡ ፰ ፡፡ |
| ወገብአ አብርሃም ኀበ ደቁ ወተንሥኡ ወሖሩ ኅቡረ ወበጽሑ ኀበ ዐዘቅተ መሐላ ፡፡ | ፲፱ | አብርሃምም ወደ አሽከሮቹ ተመለሰ ፡ ተነሥተውም አብረው ሄዱ ወደ መሐላ ጕድጓድም ደረሱ ፡፡ ዘፍ. ፲፪ ፡ ፫ ፡፡ ፲፰ ፡ ፲፰ ፡፡ ፳፪ ፡ ፱ ፡፡ ፳፯ ፡ ፰ ፡፡ ግብ. ሐዋ. ፫ ፡ ፳፭ ፡፡ |
| ወከነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር ዜነውዎ ለአብርሃም ወይቤልዎ ወለደት ወልደ ፡ ሚልካ ለናኮር እኁከ ፡፡ | ፳ | ከዚህም ነገር በኋላ እንዲህ ሆነ ሚልካ ለወንድምህ ለናኮር ወንድ ልጅ ወለደችለት ብለው ለአብርሃም ነገሩት ፡፡ ዘፍ. ፳፩ ፡ ፴፩ ፡፡ |
| ሆክስ በኵሩ ፡ ወመዋክሴን እኁሁ ፡ ወቀማኤል አቡሁ ለአራን ፡፡ | ፳፩ | በኵሩ ሆክስ ፡ ወንድሙ መዋክሴን ፡ የአራን አባት ቀማኤል ፡፡ ዘዝ. ፲፩ ፡ ፳፱ ፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ወአክዘት ፤ ወኤዝራው ፤ ወፌሉር ፤ ወዮፋት ፤ ወበቱ ኤል አቡሃ ለርብቃ ። | ፳፪ | አክዘት ፤ ኤዝራው ፤ ፌሉር ፤ ዮፋት ፤ የርብቃ አባት በቱኤል ። ኢዮ. ፩ ፩ ። ፴፪ ፥ ፪ ። |
| እሉ እሙንቱ ፰ ደቂቅ ዘወለደቶሙ ሚልካ ለናኮር እኁሁ ለአብርሃም ። | ፳፫ | ሚልካ ለአብርሃም ወንድም ለናኮር የወለደችለት ፰ቱ ወንዶች ልጆች እነዚህ ናቸው ። |
| ወሂማ ዕቅብቱ ወለደቶሙ ለቀዓት ወለቢካ፥ ወለማክ ወለሚከ ። | ፳፬ | ዕቅብቱ ሂማም ፤ ቢካንና ቀዓትን ፤ ሚከንና ማክን ፤ ወለደቻቸው ። ዘፍ. ፳፩ ፥ ፲፩ ። ሮሜ ፱ ፥ ፲ ። |
| ምዕራፍ ፳፫ ። | | ምዕራፍ ፳፫ ። |
| ወኮነ ሕይወታ ለሳራ ፻፳ወ፯ ዓመተ ። | ፩ | የሳራ ዕድሜዋ ፻፳፯ ዓመት ሆነ ። |
| ወሞተት ሳራ በሀገረ አርበቅ እንተ ውስተ ቈላት እንተ ይእቲ ኬብሮን እንተ ውስተ ከነአን ፤ ወቆመ አብርሃም ከመ ይላሀዋ ለሳራ ወይብክያ ። | ፪ | ሳራም በቈላው ውስጥ አርባቅ በምትባል አገር ሞተች፤ ይህችውም በከነአን መከከል ያለች ኬብሮን ናት ፤ አብርሃምም ለሳራ ፈጽሞ ያለቅስላት ዘንድ ተቀመጠ ። ፲፫ ፥ ፲፰ ። ፳፫ ፥ ፲፱ ። መሳ. ፩ ፥ ፲ ። ኢያ. ፲፬ ፥ ፲፭ ። |
| ወተንሥአ አብርሃም እምኀበ በድና ወይቤሎሙ ለደቂቀ ኬጢ ። | ፫ | አብርሃም ከሬሳዋ አጠገብ ተነሥቶ የኬጢን ልጆች አላቸው ። |
| ነግድ ወፈላሲ አነ ማእከሌክሙ ሀቡኒ ሊተ ከመ እሣየጥ መቃብረ ወእቅብር በድንየ ከማክሙ ። | ፬ | እኔ በእናንተ ዘንድ እንግዳና ስደተኛ ነኝ፤ መቃብር እንድገዛ ፍቀዱልኝ፤ እንደ እናንተም ሬሳዬን ልቅበር። ዘፍ. ፲፯ ፥ ፰ ። ፩ ዜና ፳፱ ፥ ፲፭ ። መዝ. ፻፭ ፥ ፲፪ ። |
| ወአውሥእዎ ደቂቀ ኬጢ ለአብርሃም ወይቤልዎ አልቦ። | ፭ | የኬጢም ልጆች መልሰው አብርሃምን እንዲህ አሉት ፤ አይሆንም ። |
| እግዚኦ ስምዐነ እስመ ንጉሥ አንተ ለነ እምኀበ እግዚአብሔር ውስተ መቃብሪነ ዘኀረይከ ቅብር በድነከ እስመ አልቦ እምኔነ ዘይከልአከ መቃብረ ከመ ትቅብር ብድነከ በህየ ። | ፮ | ጌታ! እኛን ስማን አንተ ለእኛ ከእግዚአብሔር የተሾምክ ንጉሥ ነህና ፤ ከመቃብራችን በታ በመረጥከው ሬሳህን በዚያ ትቀብር ዘንድ መቃብሩን የሚከለክልህ የለምና ። ዘፍ. ፴ ፥ ፰። ዘፀ. ፱ ፥ ፳፰። መዝ. ፴፯ ፥ ፯። ፺ ፥ ፲። |
| ወተንሥአ አብርሃም ወሰገደ ቅድመ ሕዝብ ዘደቂቀ ኬጢ ። | ፯ | አብርሃምም ተነሥቶ በኬጢ ልጆች ወገኖች ፊት እጅ ነሣ ። |
| ወይቤሎሙ እመ ፈቀድክሙ ታቅብሩኒ በድንየ ንግርዎ በእንቲአየ ለኤፍሮን ወልደ ሰአር ። | ፰ | እንዲህም አላቸው ፤ ሬሳዬን ታስቀብሩኝ ዘንድ ከወደዳችሁ ስለ እኔ ለሰአር ልጅ ለኤፍሮን ንገሩት ። |
| የሀበኒ በዓተ ክዕበት እንቲአሁ እንተ ሀለወት ውስተ ገራህቱ በወርቅየ በሤጥ በመጠነ ከነ ወእሣየጥ እምኔሁ ። | ፱ | በዋሻው መከከል ያለችውን የግቡን ድርብ ዋሻ ይስጠኝ ፤ በገንዘቤ በሆነው ዋጋ ከእርሱ ልግዛ ። |
| ወሀሎ ኤፍሮን ይነብር ማእከሌሆሙ ለደቂቀ ኬጢ ፤ ወይቤሎ ኤፍሮን ኬጥያዊ ለአብርሃም እንዘ ይሰምዑ ደቂቀ ኬጢ ወኵሎሙ እለ ይበውኡ ውስተ ሀገር ። | ፲ | ኤፍሮንም በኬጢ ልጆች መከከል ተቀምጦ ነበር ፤ ኬጥያዊው ኤፍሮንም የኬጢ ልጆች ወደ ሸንጎም የሚገቡትም ሁሉ እየሰሙ አብርሃምን እንዲህ አለው ። |
| ቅረበኒ እግዚእየ ወስምዐኒ ! ገራህቶ ወበዐቶሂ ዘውስቴቱ ለከ ወሀብኩከ በቅድመ ኵሉ ሰብአ ሀገርየ ፤ ወናሁ ወሀብኩከ ቅብር በድነከ ። | ፲፩ | ጌታዬ ሆይ! ቀረብ በልና ቃሌን ስማኝ ፤ እርሻውንም በውስጡ ያለውን ዋሻውንም በገሬ ሰዎች ሁሉ ፊት ለአንተ ሰጥቼሃለሁ ፤ እነሆ ሰጥቼሃለሁ ሬሳህን ቅበር ። ዘፍ. ፳፫ ፥ ፲፫ - ፲፯ ። ፴፬ ፥ ፰ - ፳፬ ። ሩት ፬ ፥ ፩ ። |
| ወሰገደ አብርሃም ቅድመ ኵሉ ሕዝብ ። | ፲፪ | አብርሃምም በሕዝቡ ሁሉ ፊት እጅ ነሣ ። |
| ወይቤሎ ለኤፍሮን እንዘ ይሰምዑ ኵሎሙ ስምዓኒ ሤጦ ለገራህትከ ንሣእ እምኔየ ወእቅብር በድንየ በህየ ። | ፲፫ | ኤፍሮንንም ሰዎች ሁሉ እየሰሙ ነገሬን ስማኝ የእርሻህን ዋጋ ከኔ ተቀበል፤ እኔም በዚያ ሬሳዬን ልቅበር አለው። |
| ወአውሥአ ኤፍሮን ለአብርሃም ወይቤሎ ። | ፲፬ | ኤፍሮንም መልሶ አብርሃምን እንዲህ አለው ። |
| አልቦ እግዚኦ ! ስምዐኒ ምንት ውእቱ ዝንቱ ምድር ወምንትኑ ውእቱ ፬፻ ጠፋልሕ ማእከሌየ ወማእከሌከ እንከሰ ቅብር በድነከ በህየ ። | ፲፭ | ጌታ ! አይሆንም ስማኝ ፤ ይህ ምድር ምንድር ነው ፤ ፬፻ ምዝምዝ ብርስ ምንድር ነው፤ በአንተና በኔ መከከል ! እንግዲህስ ሬሳህን በዚያ ቅበር። ዘፍ. ፲፯ ፥ ፲፪ ። ፳ ፥ ፲፯። ዘፀ. ፴ ፥ ፲፫ ። ሕዝ. ፵፭ ፥ ፲፪ ። |
| ወሰምዖ አብርሃም ለኤፍሮን ዘይቤሎ በቅድመ ደቂቀ ኬጢ ወደለወ ሎቱ ፬፻ ጠፋልሐ ብሩር መፍዴ ዘኢኮነ ተምያነ ። | ፲፯ | አብርሃምም በኬጢ ልጆች ፊት ኤፍሮንን ሰምቶ ግብዝ ያይደለ ለዕዳ የማያልፍ ፬፻ ምዝምዝ ብርን መዝኖ ሰጠው። ፩ ዜና ፳፩ ፥ ፳፭ ። ኤር. ፴፪ ፥ ፱ ። |

፲፯ ወገራህቱ ለኤፍሮን ወበዐቱኒ ወኵሉ ዕፀው እንተ ውስ
ቴታ ከነ ለአብርሃም ።
፲፰ ወተሰየጠ በቅድመ ኵሎሙ ደቂቀ ኬጢ ።
፲፱ ወእምዝ ቀበራ ለሳራ ብእሲቱ ውስተ በዐተ ከዐበት
እንተ ተሰየጠ እምኤፍሮን ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

፩ ወልኅቀ አብርሃም ወኀለፈ መዋዕሊሁ ወባረኮ እግዚአ
ብሔር ለአብርሃም በኵሉ ።

፪ ወይቤሎ አብርሃም ለገብሩ ዘይልኅቅ ዘውእቱ መጋቢሁ
ላዕለ ኵሉ ንዋዩ ደይ እዴከ ላዕለ እዴየ ።

፫ ወአምሕለከ በአምላከ ሰማይ ወምድር ከመ ኢትንሣእ
ብእሲተ ለወልድየ ይስሐቅ እምአዋልደ ከነአን እለ ምስ
ሌሆሙ አኀድር አነ ።
፬ ዳእሙ ሖር ውስተ ብሔር ኀበ ተወለድኩ ወንሣእ
ብእሲተ ለወልድየ ይስሐቅ በህየ ።
፭ ወይቤሎ ገብሩ ለእመኬ ኢፈቀደት ይእቲ ብእሲት
ትምጻእ ምስሌየ ዘንተ ብሔረ እግብኦኑ ለወልድከ ውስተ
ውእቱ ምድር እምኀበ ወፃእከ ።
፮ ወይቤሎ አብርሃም ዑቅ ኢታግብኦ ለወልድየ ህየ ።

፯ እግዚአብሔር አምላከ ሰማይ ወምድር ዘአውፅአኒ እም
ቤተ አቡየ ወ፡ምድር እንተ ተወለድኩ በውስቴታ ወዘ
መሐለ ሊተ ወይቤለኒ ለከ እሁበከ ዘንተ ምድረ ወለዘር
እከ፣ ውእቱ ይፌኑ መልአኮ ቅድሜከ ወትነሥእ ብእሲተ
ለወልድየ እምህየ ።
፰ ወእመሰ ኢፈቀደት ብሕቱ ይእቲ ብእሲት ትምጻእ
ምስሌከ ውስተ ዛቲ ምድር ንጹሕ አንተ እመሐላ ወዘ
ንተ ዑቅ ከመ ኢታግብአ ለወልድየ ።
፱ ወወደየ እዴሁ ውእቱ ገብር ላዕለ እዴ አብርሃም እግ
ዚኡ ወመሐለ ሎቱ በእንተዝ ነገር ።
፲ ወነሥአ ውእቱ ገብር ፲ተ አግማለ እምአግማለ እግ
ዚኡ ወኵሎ ሠናየ ዘእግዚኡ ምስሌሁ ነሥአ፣ ወተንሥአ
ወሖረ ኀበ አፍላገ አራም ሀገረ ናኮር ።

፲፩ ወአዕረፈ አግማሊሁ አፍአ እምሀገር ኀበ ዓዘቅተ ማይ
ፍና ሠርክ ጊዜ ይወጽአ ሐዋርያት ማይ ከመ ይቅድሑ ።

፲፪ ወይቤ እግዚአየ አምላኩ ለአብርሃም አስተበቍዐከ
ሠርሕ ሊተ ዮም ወግበር ምሕረተ ምስለ እግዚእየ
አብርሃም ።
፲፫ ናሁ ቆምኩ ኀበ ዐዘቅተ ማይ ወአዋልዲሆሙ ለሰብአ
ሀገር ይወፅአ ይቅድሐ ማየ ።

፲፬ ወትኩን ይእቲ ድንግል እንተ እብላ አኒ አጽንኒ ቀሱ
ተኪ ወአስትዪኒ ማየ፣ ወትቤለኒ ይእቲ ድንግል ስተይ
አንተኒ ወአግማሊከኒ አስቲ እስከ ይረውዩ፣ ወኪያሃ አስ

የኤፍሮን እርሻ ዋሻውም በውስጧም ያለው ተክል
ሁሉ ለአብርሃም ሆነ። ዘፍ. ፳፭፣ ፱። ፴፩፣ ፴፩። ፵፱፣ ፴።
አብርሃምም በኬጢ ልጆች ሁሉ ፊት ገዛት ።
ከዚህም በኋላ ሚስቱ ሳራን ከኤፍሮን በገዛት ዕጥፍነት
ባላት ዋሻ ቀበራት ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

አብርሃምም አረጀ ዘመኑም አለፈ፣ እግዚአብሔርም
አብርሃምን በሁሉ ባረከው ። ዘፍ. ፲፰፣ ፲፩። ፲፫፣ ፪።
፲፱፣ ፲፱። ፳፱፣ ፵፭ ።
አብርሃምም በገንዘቡ ሁሉ ላይ አዛዥ የነበረውን ሽማ
ግሌ ሎሌውን እንዲህ አለው፣ እጅህን በእጄ ላይ ጫን
አለው ። ዘፍ. ፲፭፣ ፪። ፳፫፣ ፲። ፵፯፣ ፳፱ ።
እኔ አብሬአቸው ከምኖረው ከከነአን ሴቶች ልጆች
ለልጄ ሚስት እንዳትወስድለት በሰማይና በምድር አም
ላክ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ ።
ወደ ተወለድኩበት አገር ሂደህ ለልጄ ለይስሐቅ ከዚያ
ሚስት አምጣለት እንጂ ። ዘፍ. ፳፰፣ ፪። ፲፩፣ ፴፩ ።
አገልጋዩም ያች ሴት ከኔ ጋራ ወደዚህ አገር ትመጣ
ዘንድ ባትወድስ፣ ልጅህን ወደ ወጣህበት አገር ልመልሰ
ውን፣ አለው ።
አብርሃምም እንዲህ አለው፣ ልጄን ወደዚያ እንዳትመ
ልሰው ዕወቅ ።
ከአባቴ ቤት ከተወለድኩበትም አገር ያወጣኝ ይህችንም
አገር ላንተ እሰጥሃለሁ፣ ለልጆችህም እሰጣቸዋለሁ ብሎ
የማለልኝ እግዚአብሔር እርሱ መልአኩን ይሰድልሃል፣
ለልጄም ከዚያ ሚስት ታመጣለታለህ ። ዘፍ. ፲፪፣ ፩ ።

ነገር ግን ያች ሴት ከንተ ጋራ ወደዚያች አገር ትመጣ
ዘንድ ካልወደደች አንተ ከመሐላው ንጹሕ ነህ፣ ግን
ልጄን ወደዚያ አገር እንዳትመልሰው ዕወቅ። ኢሳ ፪፣ ፳።
ያም አገልጋይ እጁን በጌታው በአብርሃም ጕልበት ላይ
ጭኖ ስለዚህ ነገር ማለለት ።
ያም አገልጋይ ከጌታው ግመሎች ፲ ግመሎች ወሰደ፣
ከጌታውም ገንዘብ ያማረ ያማረውን ሁሉ መርጦ ያዘ፣
ተነሥቶም ወደ ናኮር አገር ወደ አራም ወንዞች ሄደ።
ዘፍ. ፲፪፣ ፲፯። ፳፱፣ ፳፱። ፳፯፣ ፵፫።
ግመሎቹንም ውኃ ቀጂዎች በሚወጡበት ጊዜ ወደ
ማታ በውኃው ጕድጓድ አጠገብ ከከተማው ውጭ አስ
ረፈ። ዘፍ. ፳፱፣ ፱። ዘፀ. ፪፣ ፲፯። ፩ ሳሙ. ፱፣ ፲፩።
እንዲህም አለ ጌታዬ የአብርሃም አምላክ፣ እለምንሃ
ለሁ፣ ዛሬ መንገዴን አቅናልኝ ለጌታዬ ለአብርሃምም
ምሕረትን አድርግ።
እነሆ እኔ በውኃው ምንጭ አጠገብ ቆሜአለሁ የአገሩ
ሰዎች ሴቶች ልጆችም ውኃ ሊቀዱ ይወጣሉ። ዘፍ. ፳፱፣
፳፯ - ፴፪። ፲፯፣ ፯። ዘፀ. ፫፣ ፮ - ፲፭። መዝ. ፴፣ ፯ - ፰።
እኔ ማድጋሽን አዘንብለሽ ውኃ አጠጪኝ የምላት ድን
ግል እሷም አንተም ጠጣ ግመሎችህንም እስኪጠግቡ
ድረስ አጠጣልሃለሁ የምትለኝ ድንግል እሷ ትሁን፣ እሷን

| | | |
|---|---|---|
| ተዳሎከ ለገብርከ ይስሐቅ እግዚእ ፡ ወበዝንቱ አአምር ከመ ገበርከ ምሕረተ ለእግዚእየ አብርሃም ። | | ለባርያህ ለይስሐቅ አዘጋጅተሃል ፡ ለጌታዬ ለአብርሃምም ቸርነትን እንዳደረግህ በዚህ ዐውቃለሁ ። ዘፍ. ፲፫ ፡ ፲፰ ። |
| ወኮነ ዘእንበለ ያኅልቅ ተናግሮ ከመዝ በልቡ ወነያ ወፅአት ርብቃ እንተ ተወልደት ለባቱኤል ወልደ ሚልካ ብእሲተ ናኮር እኁሁ ለአብርሃም ፡ ወትጸውር ቀሡታ ላዕለ መትከፍታ ። | ፲፭ | በልቡም እንዲህ ብሎ አሰላስሎ ሳይጨርስ እንዲህ ሆነ ፡ የአብርሃም ወንድም የናኮር ሚስት ሚልካ ለወለደችው ለባቱኤል የተወለደችለት ርብቃ እነሆ ወጣች ፡ ማድጋዋንም በጫንቃዋ ላይ ተሸክማ ነበር ። ዘፍ ፲፩ ፡ ፳፱ ። ፳፪ ፡ ፳፫ ። |
| ወሠናይ ገጻ ጥቀ ለይእቲ ወለት ወድንግል ይእቲ ወኢተአምር ብእሴ ወወረደት ውስተ ዐዘቅት ወቀድሐት ማየ ወመልዐት ቀሡታ ወዐርገት ። | ፲፮ | የዚያችም ልጅ መልክ እጅግ ያማረ ነበረ ፡ ይህችውም ድንግል ነበረች ባልም አላገባችም ነበር ፡ ወደ ምንጭም ወርዳ ውኃ ቀዳች ማድጋዋንም መልታ ወጣች ። ዘፍ ፳፮ ፡ ፯ ። |
| ወሮጸ ውእቱ ብእሲ ወይቤላ አስትይኒ ሕቀ ማየ እምቀሡትኪ ። | ፲፯ | ያ ሰውም ሩጦ ከማድጋሽ ጥቂት ውኃ አጠጪኝ አላት ። |
| ወትቤሎ ስተይ እግዚእየ! ወአውረደት ቀሡታ ፍጡነ እምዲበ መትከፍታ ወአስተየቶ እስከ ይረዊ ። | ፲፰ | እሷም ጌታዬ! ጠጣ አለችው ፈጥኖ ማድጋዋንም ከጫንቃዋ አውርዳ እስኪረካ አጠጣችው ። |
| ወትቤሎ ለአግማሊከኒ እቀድሕ ወይስተዩ ኵሎሙ ። | ፲፱ | ለግመሎችህም ልቀዳ ሁሉም ይጠጡ አለችው ። |
| ወሦጠት ማየ እምቀሡታ ፍጡነ ውስተ ምስታይ ወሮጸት ወቀድሐት ዳግመ ለአግማሊሁ ኵሎሙ ። | ፳ | ውኃውንም ፈጥና ከማድጋዋ በማጠጫው ገለበጠች ፡ ዳግመኛም ፈጥና ለግመሎቹ ሁሉ ቀዳች ። |
| ወውእቱሰ ብእሲ ይሬእያ ከመ ወያረምም ከመ ይርአይ እመ ይሴርሕ እግዚአብሔር ፍኖቶ ወለእመሂ አልቦ ። | ፳፩ | ያ ሰው ግን ፀጥ ብሎ እተኵሮ ይመለከታት ነበር ፡ እግዚአብሔር ጐዳናውን ያቀናለት እንደሆነ አያቀናለትም እንደሆነ ያይ ዘንድ ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፲፪ ። ፵ ፡ ፵፪ - ፶፯ ። |
| ወእምዘረወዩ አግማሊሁ ነሥአ ውእቱ ብእሲ አዕኑገ ዘወርቅ ዘዘሕልቅ ድልወቱ ወአውቃፈ ለእእዳዊሃ ዘዘዐሥሩ ሕልቀ ድልወቱ ። | ፳፪ | ግመሎቹ ከጠጡ በኋላ ያ ሰው ሚዛኑ አንዳንድ ወቄት የሚሆን የወርቅ ጉትቻ ለእጆቿም ሚዛኑ ፲ ወቄት የሚሆን አምባር አመጣላት ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፴ - ፵፯ ። ዘፀ ፴፫ ፡ ፳፪ ። መሳ ፰ ፡ ፳፬ ። ፳ ፡ ፳፯ ። ኢዮ. ፵፪ ፡ ፲፩ ። |
| ወተስእላ ወይቤላ ወለተ መኑ አንቲ ንግርኒ እስኩ ለእመ ቦቱ ማኅደር ውስተ ቤተ አቡኪ ለነ ። | ፳፫ | እሷንም አንቺ የማነሽ ልጅ ፡ እስኪ ንገሪኝ ፡ በአባትሽ ቤት ለኛ ማደርያ እንዳለ ብሎ ጠየቃት ። |
| ወትቤሎ አነ ወለተ ባቱኤል ወልደ ናኮር ። | ፳፬ | እሷም እንዲህ አለችው እኔ የናኮር ልጅ የሚሆን የባቱኤል ልጅ ነኝ ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፲፭ ። |
| ወቦ ኀቤነ ማዕርኒ ወኀሠር ወማኅደርኒ ለአግማሊከ ። | ፳፭ | በእኛ ዘንድ ሣርም ገለባም ለግመሎችህም ማደርያ አለ አለችው ። |
| ወአደሞ ለውእቱ ብእሲ ወሰገደ ለእግዚአብሔር ። | ፳፮ | ያንንም ሰው ደስ አለው ለእግዚአብሔርም ሰገደ ። |
| ወይቤ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ለእግዚእየ አብርሃም ዘኢያውፅአ ለጽድቁ ወለርትዑ እምእግዚእየ ወሊተኒ ሠርሐኒ ፍኖትየ ውስተ ቤተ እኁሁ ለእግዚእየ አብርሃም ። | ፳፯ | እሱም ረድኤቱንና ቸርነቱን ከጌታዬ ያላራቀ ለእኔም ወደ ጌታዬ ወደ አብርሃም ወንድም ቤት እሄድ ዘንድ ጐዳናዬን ያቃናልኝ የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን አለ ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፵፰ - ፶፪ ። ዘፀ. ፩ ፡ ፵፩ ። |
| ወሖረት ይእቲ ወለት ወነገረት ለቤተ እማ ዘንተ ነገረ ። | ፳፰ | ያችም ልጅ ሂዳ ለናቷ ቤት ይህን ነገር ነገረች ። ዘፍ. ፵፪ ፡ ፲ ። ፳፬ ፡ ፵፰ ። መዝ. ፰ ፡ ፫ ። |
| ወባቲ ለርብቃ እኁው ዘስሙ ላባ ወሮጸ ላባ ኀበ ዝኩ ብእሲ አፍአ ኀበ ዐዘቅት ። | ፳፱ | ለርብቃም ስሙ ላባ የሚባል ወንድም ነበራት ፡ ላባም ወደዚያ ሰው ከሠፈር ውጭ ወደ ጕድጓድ አደባበይ ሮጠ ። |
| ወሰበ ርእየ አዕኑጊሃ ወአውቃፊሃ ለእኅቱ ርብቃ ወትቤ ከመዝ ይቤለኒ ውእቱ ብእሲ ወበጽሐ ኀበ ውእቱ ብእሲ እንዘ ይቀውም ኀበ ዓዘቅት ምስለ አግማሊሁ ። | ፴ | የእኅቱ የርብቃንም አምባሯንና ጉትቻዋን ባየ ጊዜ ያ ሰው እንዲህ አለኝ ባለችውም ጊዜ በውኃው ጕድጓድ አጠገብ ከግመሎቹ ጋር ቆሞ ሳለ ሮጦ ወደዚያ ሰው ደረሰ ። ዘፍ ፳፭ ፡ ፳ ። ፳፰ ፡ ፪ ። ፳፱ ፡ ፭ ። |
| ወይቤሎ ነዓ ባእ ውስተ ቤት ፡ ይትባረክ እግዚአብሔር ምንት ያቀውመከ አፍአ ወናሁ አስተዳሎነ ለከ ማኅደረ ወቤተ ለአግማሊከ ። | ፴፩ | ና ፡ ወደ ቤት ግባ አንተ እግዚአብሔር የባረከህ ሰው ከውጭ ምን ያቆምሃል ፡ ላንተ ማደሪያ ለግመሎችህም ቤት አዘጋጅተናል አለው ። |
| ወቦአ ውእቱ ብእሲ ወአግብአ አግማሊሁ ወአቅረቡ | ፴፪ | ያም ሰው ገባ ግመሎችንም አስገባ ለግመሎቹም ሣርና |

ሎሙ ኀሠረ ወማዕረ ለአግማሊሁ ወአምጽኡ ሎቱ ማየ ለአግሩ ወለእደው እለ ምስሌሁ ።

ገለባ አቀረቡላቸው ፤ ለእግሩም ውኃ አመጡለት ፤ ከሱ ጋራ ላሉ ሰዎችም ። ዘፍ. ፳፯ ፡ ፳፬ ። መሳ. ፲፯ ፡ ፪ ። ሩት ፫ ፡ ፲ ።

፴፫ ወአምጽኡ ሎቱ ኅብስተ ይብላዕ ወይቤሎሙ ኢይበልዕ እስከ እነግር ቃልየ ወይቤልዎ ንግር ።

ይበላም ዘንድ እንጀራን አቀረቡለት ፤ እሱም መልእክቱን ሳልናገር አልበላም አላቸው ፤ ተናገር አሉት ። ዘፍ. ፴፱ ፡ ፴፫ ። ፲ ፡ ፰ - ፱ ። ፲፱ ፡ ፪ ። መሳ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

፴፬ ወይቤሎሙ ገብረ አብርሃም አነ ።

እንዲህም አላቸው ፤ እኔ የአብርሃም አገልጋይ ነኝ ።

፴፭ ወእግዚአብሔር ባረከ ለእግዚእየ ጥቀ ወአዕበዮ ወወሀበ አልሕምተ ወአባግዐ ወርቀ ወብሩረ አግብርተ ወአእማተ ወአግማለ ወአእዱገ ።

እግዚአብሔርም ጌታዬን እጅግ ባረከው ከፍ ከፍ አደረገው ፤ በጎችንና ላሞችን ፤ ብርንና ወርቅን ፤ ሴቶች አገልጋዮችንና ወንዶች አገልጋዮችን ፤ አህዮችንና ግመሎችን ሰጠው ።

፴፮ ወወለደት ሎቱ ሳራ ብእሲቱ ለእግዚእየ አብርሃም ፩ደ ወልደ በርስዓኒ ፤ ወወሀበ ኵሎ ዘቦቱ ሎቱ ።

ሚስቱ ሳራም ለጌታዬ ለአብርሃም በእርጅና አንድ ልጅ ወልዳለታለች ፤ ለእርሱ ያለውን ገንዘቡን ሁሉ ሰጥቶታል ። ዘፍ. ፳፩ ፡ ፩ ።

፴፯ ወአምሐለኒ እግዚእየ ወይቤለኒ ኢትንሣእ ለወልድየ ብእሲተ እምአዋልደ ከናኔን እለ አኀድር አነ ምስሌሆሙ ።

ጌታዬ አምሎኛል እንዲህ ብሎ ፤ እኔ አብሬአቸው ከምኖር ከከነአን ሰዎች ለልጄ ሚስት አታምጣ ።

፴፰ ዳእሙ ሑር ውስተ ቤተ አቡየ ፤ ወውስተ ነገድየ ፤ ወንሣእ ሎቱ ብእሲተ ለወልድየ እምህየ ።

ነገር ግን ወደ አባቴ ቤት ፤ ወደ ወገኔ ሂድ ፤ ከዚያም ለልጄ ሚስት አምጣለት ። ዘፍ. ፳ ፡ ፪ ። ፳፰ ፡ ፪ ።

፴፱ ወእቤሎ ለእግዚእየ ዮጊ ለእመ ኢፈቀደት ይእቲ ብእሲት መጺአ ምስሌየ ።

ጌታዬንም ያች ሴት ከኔ ጋራ መምጣት ባትወድስ ፤ አልኩት ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፭ ።

፵ ወይቤለኒ እግዚእየ እግዚአብሔር ዘአሥመርኩ በቅድሜሁ ውእቱ ይፌኑ መልአኮ ቅድሜከ ወያሤኒ ፍኖተከ ።

ጌታዬም እንዲህ አለኝ ፤ በፊቱ ያገለገልሁት እግዚአብሔር ፤ መልአኩን ልኮ መንገድህን ያቃናልሃል ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፯ ።

፵፩ ወትንሣእ ብእሲተ ለወልድየ እምህየ እምነገድየ ወእምቤተ አቡየ ።

ከዚያም ከወገኔ ከአባቴ ቤትም ልጄን ሚስት ታጋባዋለህ ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፯ ። ፲፯ ፡ ፩ ። ፳፬ ፡ ፳፭ ።

፵፪ ወይእተ አሚረ ንጹሐ ትከውን እመሐላየ ፤ ወእመኒ አበዩከ ውሂበ ፤ ንጹሐ አንተ እመሐላየ ፤ ወሶበ በጻሕኩ ዝየ ኀበ ዐዘቅት ወናሁ ቆምኩ መልዕልተ ዓዘቅት ማይ ወአዋልደ ሰብአ ሀገር ይወጽኣ ይቅድሓ ማየ ።

የዚያን ጊዜ ከመሐላዬ ንጹሕ ትሆናለህ ፤ አንሰጥም ቢሉህም አንተ ከመሐላዬ ንጹሕ ነህ ፤ እዚህ በደረስኩ ጊዜ ከውኃ ምንጭ አጠገብ ቆምኩ ፤ የሀገሩ ሰዎች ሴቶች ልጆችም ውኃ ሊቀዱ ይወጡ ነበር ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፰ ።

፵፫ ወእቤ እግዚኦ አምላከ እግዚእየ አብርሃም ለእመ አንተ አሠናእከኒ ዮም በዛቲ ፍኖትየ ።

እንዲህም አልኩ ፤ አቤቱ የጌታዬ የአብርሃም ፈጣሪ ፤ ዛሬ እኔ በምሄድበት በዚች መንገዴ አንተ ከመራኸኝ ። ዘፍ ፳፬ ፡ ፲፪ ። ፳፬ ፡ ፳፮ ።

፵፬ ለትኩን ይእቲ ድንግል እንተ አነ እብላ አስትይኒ ማየ ሐቅ እምቀሱትኪ ፤ ወዘትቤለኒ ስተይ አንተኒ ወለአግማሊከኒ እቀድሕ ወይእቲ ብእሲት አስተዳሎከ ለገብርከ ይስሐቅ እግዚኦ ወቦቱ አአምር ከመ ገበርከ ምሕረተ ለእግዚእየ አብርሃም ።

ውኃ አጠጪኝ የምላት ድንግል እሷ አንተም ጠጣ ፤ ለግመሎችህም እቀዳለሁ የምትለኝ ትሁን ፤ ያችን ሴት ለባርያህ ለይስሐቅ አዘጋጀህ ማለት ነው ፤ ለጌታዬ ለአብርሃምም ይቅርታን እንዳደረግህ በዚህ አውቃለሁ ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፲፬ - ፲፭ ። ፳ ፡ ፲፯ ።

፵፭ ወከነ ዘእንበለ አኅልቅ ሐልዮ በልብየ በጊዜ ወጽአት ርብቃ ወትፀውር ቀሡታ ፤ ወወረደት ውስተ ዓዘቅት ወቀድሐት ።

በልቤ ያሰብኩትንም ሳልናገር እንዲህ ሆነ ፤ የዚያን ጊዜ ርብቃ ማድጋዋን ተሸክማ ወጣች ፤ ወደ ጉድጓዱም ወርዳ ውኃን ቀዳች ። ፩ ሳሙ. ፩ ፡ ፲፫ ።

፵፮ ወእቤላ አስትይኒ ማየ ወአውረደት ቀሡታ ፍጡነ ወትቤለኒ ስተይ አንተኒ ወአግማሊከኒ እስቲ ወሰተይኩ ወአግማልየኒ ሰትዩ ።

ውኃ አጠጪኝ አልኳት ፤ እሷም ማድጋዋን ፈጥና አውርዳ አንተም ጠጣ ግመሎችህንም አጠጣለሁ አለችኝ ፤ እኔም ጠጣሁ ግመሎቼም ጠጡ ።

፵፯ ወተስእልክዋ ወእቤላ ወለተ መኑ አንቲ ንግርኒ ወትቤለኒ አነ ወለተ ባቱኤል ወልደ ናኮር ዘወለደት ሎቱ ሚልካ ፤ ወይእተ ጊዜ ሶበ ሰማዕኩ ዘንተ እምአፉሃ አደመተኒ ጥቀ ወአሠርገውክዋ አዕኑገ ውስተ አዕዛኒሃ ፤ ወአውቃፈ ውስተ እእዳዊሃ ።

አንቺ የማነሽ ልጅ ንገርኝ ብዬ ጠየቅኋት ፤ እሷም ሚልካ ለናኮር የወለደችለት የባቱኤል ልጅ ነኝ አለችኝ ፤ ያን ጊዜም ይህንንም ነገር ከአንደበቷ በሰማሁ ጊዜ እጅግ ደስ አለችኝ ፤ ለጆሮዋ ጉትቻውን ፤ ለእጅዋ አምባሩን አስጌጥኋት አለ ። ዘፍ. ፳፬ ፡ ፳፪ ። ሕዝ. ፲፮ ፡ ፲፩ - ፲፪ ።

፵፰ ወሶበ አደመተኒ ሰገድኩ ለእግዚአብሔር ወአእኰትክዎ

ደስም ባሰኘቺኝ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰገድኩ ፤ የጌታ

ለእግዚአብሔር አምላኩ ለአብርሃም ዘአውዐአኒ ውስተ ፍኖተ ጽድቅ ከመ እንሣእ ወለተ እኁሁ ለእግዚእየ ለወልዱ ።

፵፱ ወይእዜኒ ለእመ ትገብሩ ምሕረተ ወጽድቀ ለእግዚ እየ ንግሩኒ ወእመ አኮ አትመየጥ እመ አኮ የማነ ወእመ አኮ ጸጋመ ።

፶ ወአውሥእዎ ባቱኤል ወላባ ወይቤልዎ እምኀበ እግ ዚአብሔር ኮነ ዝ ነገር ወኢንክል ተናግሮ ኢ ሠናየ ወኢ እኩየ ።

፶፩ ነያ ርብቃ ንሥኣ ወሑር ትኩን ብእሲተ ለወልደ እግ ዚእከ በከመ ይቤለከ እግዚእከ ።

፶፪ ወሰበ ሰምዐ ዘንተ ነገረ ሰገደ ዲበ ምድር ።

፶፫ ወአውፅአ ውእቱ ገብር ሠርጕ ወርቅ ወብሩር ወአ ልባሰ ሠናያተ ወወሀበ ለርብቃ ፣ ወዓዲ ወሀቦሙ አምኃ ለአኀዊሃኒ ወለእማኒ ።

፶፬ ወእምዝ በልዑ ወሰትዩ ውእቶኒ ወእለ ምስሌሁ ወቤ ቱ ፣ ወተንሥአ በጽባሕ ወይቤ ፣ ፈንዉኒ ከመ እሑር ኀበ እግዚእየ ።

፶፭ ወይቤሉ አኀዊሃ ወእማ ወአኁሃ ትንበር ወለትን ዐ ሡረ መዋዕለ ምስሌነ ወእምዝ ተሐውር ።

፶፮ ወይቤሎሙ ኢታስተጽንዑኒ ፣ እንዘ እግዚአብሔር ሠርሐኒ ፍኖትየ ፈንዉኒ ከመ እሑር ኀበ እግዚእየ ።

፶፯ ወይቤልዎ ንጸውዓ ለርብቃ ወንስማዕ እምአፉሃ ።

፶፰ ወጸውዕዋ ለርብቃ ወይቤልዋ ተሐውሪኑ ምስለ ዝ ብእሲ ወትቤ እወ አሐውር ።

፶፱ ወፈነውዋ ለርብቃ ምስለ ንዋያ ወለሐፀኒታ ወለገብረ አብርሃምኒ ፈነውዎ ምስለ አሊአሁ ።

፷ ወባረክዋ ለርብቃ እኅቶሙ ወይቤልዋ እኅትነ አንቲ ኩኒ አልፈ ወአእላፈ አእላፋት ወይረስ ዘርእኪ አህጉረ ፀር ።

፷፩ ወተንሥአት ርብቃ ወሐፀኒታኒ ወተጽዕና አግማሊ ሆን ወሖራ ምስለ ውእቱ ብእሲ ፣ ወተወፈያ ውእቱ ብእሲ ለርብቃ ወሖረ ።

፷፪ ወይስሐቅሰ ይዋሒ ውስተ ገዳም መንገለ ዐዘቅት ወሀ ሰዉ ኀዱራን ውስተ ምድር እንተ መንገለ መስዕ ።

፷፫ ወወፅአ ይስሐቅ ይዛዋዕ ውስተ ገዳም ፍና ሠርክ ወ ሰበ ነጸረ ርእየ አግማለ እንዘ ይመጽኡ ።

፷፬ ወሰበ ትኔጽር ርእየቶ ርብቃ ለይስሐቅ ወወረደት እምላዕለ ገመል ።

፷፭ ወተስእለቶ ለውእቱ ወልድ ወትቤሎ መኑ ውእቱ ዝ ኩቱ ብእሲ ዘያንሶሱ ውስተ ገዳም ወይትቄበለነ ወይቤላ ዝንቱ ውእቱ እግዚእየ ፣ ወነሥአት ሞጣሕታ ወተከድ ነት ገጻ ።

ዩን የወንድሙን ልጅ ለልጁ አመጣ ዘንድ ወደ እውነት ጐዳና የመራኝን የጌታዬን የአብርሃምን ፈጣሪ አመሰገ ንሁት ። ዘፍ፡ ፳፬ ፳፯ - ፶፪ ። ፳፱ ፳፫ ። ፩ ነገ፡ ፳ ፳፯ ።

አሁንም ለጌታዬ እውነተኛ ቸርነትን ታደርጉ እንደ ሆነ ንገሩኝ ፣ ይህ ካልሆነ ግን ወደ ቀኝ ወደ ግራ ብዬ እሬ ልጋለሁ አላቸው ። ዘፍ፡ ፵፯ ፳፱ ። ኢያ፡ ፪ ፲፬ ።

ባቱኤልና ላባም እንዲህ አሉት ፤ ይህ ነገር ከእግዚአ ብሔር ዘንድ ሁኗል ፣ ክፉውንም ሆነ በጎ መናገር አንች ልም ። ዘፍ፡ ፴፩ ፳፬ ። ፪ ሳሙ፡ ፲፫ ፳፬ ።

ርብቃ ያቻትልህ ጌታህ እንዳዘዘህ ለጌታህ ልጅ ሚስት ትሆነው ዘንድ ይዘሃት ሂድ ። ዘፍ፡ ፲፫ ፲፬ - ፲፰ ።

ይህንም ነገር በሰማ ጊዜ በምድር ላይ ሰገደ ። ዘፍ፡ ፳፬ ፳፯ - ፶፫ ።

ያም አገልጋይ የብሩንና የወርቁን ጌጥ ያማረ ያማረው ንም ልብስ አውጥቶ ለርብቃ ሰጣት ፣ ዳግመኛም ለእናቷና ለአባቷ እጅ መንሻ ሰጣቸው ። ዘፀ፡ ፫ ፳፪ ። ፲፩ ፪ ። ፲፪ ፴፭ ። ፪ ዜና መ፡ ፳፩ ፫ ። ዕዝ፡ ፩ ፮ ።

ከዚህ በኋላ እሱም ከሱ ጋራ ያሉትም በልተው ጠጥ ተው አደሩ ፣ በጧትም ተነሥቶ ወደ ጌታዬ ዘንድ ልሂድ አሰናብቱኝ አላቸው ። ዘፍ፡ ፳፬ ፭ - ፮ ። ፴፬ ፶፮ ፶፱ ።

እናቷና አባቷ ወንድሟም ልጃችን ፲ ቀን ከእኛ ጋራ ትቀመጥ ፣ ከዚህ በኋላ ትሄዳለች አሉት ። ዘሌ፡ ፳፭ ፴፱ ።

እሱም እግዚአብሔር ጐዳናዬን አቅንቶልኝ ሳለ አታስ ናክሉኝ ወደ ጌታዬም እሄድ ዘንድ አሰናብቱኝ አላቸው ።

ርብቃን እንጥራትና የምትናገረውን ከአንደበቷ እን ስማ አሉት ።

ርብቃንም ጠርተው ከዚህ ሰው ጋራ ትሄጂን ፤ አሏት እሷም አዎን እሄዳለሁ አለች ።

ርብቃንም ገንዘብ ሰጥተው ሰደዷት ፣ ሞግዚቷንም ጨምረው ሰደዷት ፣ የአብርሃምንም መልእክተኛ ከወገ ኖቹ ጋራ አሰናበቱት ። ዘፍ፡ ፴፭ ፰ ።

እኅታቸው ርብቃንም አንቺ እኅታችን የብዙ ብዙ ሁኚ ፤ ዘርሽም የጠላቱን አገር ይግዛ ይውረስ ብለው መረ ቋት ። ዘፍ፡ ፲፯ ፲፯ ። ፳፪ ፲፯ ። ሩት ፬ ፲፩ ።

ርብቃ ተነሣች ሞግዚቷም በግመሎቻቸው ተቀም ጠው ከዚያ ሰው ጋራ ሄዱ ፣ ያም ሰው ርብቃን ተረክ ቧት ሄደ ።

ይስሐቅ ግን በምድረ በዳ የራእይ ጕድጓድ በምትባ ለው በኩል እያሸገረ ይመለከት ነበር ፣ በዚያ በአዜብ በኩል ባለችው ምድር ይኖር ነበርና ። ዘፍ፡ ፲፮ ፲፬ ።

ይስሐቅም ሊዝናና ማታ ጊዜ ወደ ምድረ በዳ ወጣ ፣ አንገቱንም ቀና አድርጎ በተመለከተ ጊዜ እነሆ ግመሎ ችን ሲመጡ አየ ። መዝ፡ ፺፭ ፲፯ ። ፸፯ ፯ ። ፻፲፱ ፲፭ ።

ርብቃም አሻግራ በተመለከተች ጊዜ ይስሐቅን አየ ችው ከግመልም ላይ ወረደች ። ኢያ፡ ፲፭ ፲፰ ።

እኛን ሊቀበለን በምድረ በዳ የሚዘዋወረው ይህ ሰው ማነው ፤ ብላ ያንን ባላቴና ጠየቀችው ፣ እሱም ጌታዬ ይህ ነው አላት ፣ እሷም መጐናጸፊያዋን አንሥታ ፊቷን ተከ ናነበች ። ፩ ቆሮ፡ ፲፩ ፫ ፣ ፮ ፲ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወዜነዎ ለይስሐቅ ውእቱ ወልድ ኵሎ ዘገብረ ። | ፷፮ | ያም ብላቴና ያደረገውን ሁሉ ለይስሐቅ ነገረው ። |
| ወቦአ ይስሐቅ ውስተ ቤተ እሙ ፣ ወእምዝ ነሥኣ ለርብቃ ወኮነቶ ብእሲተ ወአፍቀራ ፣ ወአንገፍዎ ላሀ ለይስሐቅ በእንተ እሙ ። | ፷፯ | ይስሐቅም ወደ እናቱ ቤት ገባ ከዚህ በኋላ ርብቃን አገባት ሚስትም ሆነችው ወደዳትም ፣ ይስሐቅንም ስለ እናቱ ሞት ልቅሶን አስተዉት ። ዘፍ፣ ፴፯ ፴፭ ። |
| ምዕራፍ ፳፭ ። | | ምዕራፍ ፳፭ ። |
| ወደገመ አብርሃም አውሰበ ብእሲተ እንተ ስማ ኬጡራ። | ፩ | አብርሃምም ስሟ ኬጡራ የምትባል ሚስትን ዳግመኛ አገባ ። |
| ወወለደት ሎቱ ወልደ ዘስሙ ዘንበሬ ወዮቃጤንሃ ወሚዶንሃ ወዮብቅሃ ወምድያምሃ ወሴሔሃ ። | ፪ | ስሙ ዘንበሬ የሚባል ልጅ ወለደች ፣ ዮቃጤንን ፣ ሚዶንን ፣ ዮብቅን ፣ ምድያምን ፣ ሴሔን ወለደች ። ፩ ዜና መዋ፣ ፩ ፴፪ - ፴፫ ። |
| ወዮቃጤንሂ ወለዶሙ ለሳቤቅ ወለቴማን ወለዱዳን ፣ ወዱዳን ወለዶሙ ለራጉኤል ወለንበብዝ ወለአስራኤም ወለሎኤም ። | ፫ | ዮቃጤንም ሳቤቅንና ፣ ቴማንን ፣ ዱዳንንም ፣ ወለዳቸው ፣ ዱዳንም እንበብዝንና ራጉኤልን ፣ ሎኤምንና አሰራኤምን ወለዳቸው ። |
| ወደቂቀ ምድያም ጌፌር ወኤፋር ወሄኖኅ ወአቤሮን ወቲያሬስ ፣ እሉ ኵሎሙ ደቂቀ ኬጡራ ። | ፬ | የምድያምም ልጆች ጌፌር ፣ ኤፋር ሄኖኅንና ፣ አቤሮን ፣ ቲያሬስም ናቸው ፤ እሊህ ሁሉ የኬጡራ ልጆች ናቸው ። |
| ወወሀበ አብርሃም ኵሎ ንዋዮ ለይስሐቅ ወልዱ በሕይወቱ ። | ፭ | አብርሃምም ገንዘቡን ሁሉ ለልጁ ለይስሐቅ በሕይወቱ ሳለ ሰጠው ። ዘፍ፣ ፳፬ ፴፮ ። |
| ወለደቂቀ ዕቁባቲሁ ወሀቦሙ አብርሃም ሀብተ ወፈነዎሙ እምኀበ ይስሐቅ ወልዱ ውስተ ምድር ዘመንገለ ምሥራቅ ። | ፮ | ለዕቁባቶቹ ልጆች ግን አብርሃም ፈንታ ፈንታቸውን ሰጥቶ ከልጁ ከይስሐቅ ፊት በምሥራቅ በኩል ወዳለች አገር አሰናበታቸው ። ዘፍ፣ ፳፩ ፲፬ ። መሳ፣ ፮ ፫ ። |
| ወዝንቱ ውእቱ ሕይወቱ ለአብርሃም ወዓመታቲሁኒ ምእት ወሰብዓ ወኀምስቱ ። | ፯ | የአብርሃም ዘመኑ ይህ ነው ፣ ዕድሜውም ፻፸፭ ዓመት ነው ። |
| ወረሲዮ ጥቀ ሠናየ ርስአ ወፈጺሞ መዋዕሊሁ ሞተ አብርሃም ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ ። | ፰ | አብርሃምም እጅግ በጎ እርጅናን አርጅቶ ዘመኑንም ጨርሶ ሞተ ፣ ወደ ወገኖቹም ተጨመረ ። ዘፍ፣ ፲፭ ፲፭ ። |
| ወቀበርዎ ይስሐቅ ወይስማኤል ደቂቁ ውስተ በዐተ ክዕበት ዘገራህተ ኤፍሮን ዘሰዓር ኬጥያዊ ዘአንጻረ ምንባሬ ዘተሣየጠ አብርሃም እምደቂቀ ኬጢ ። | ፱ | ልጆቹ ይስሐቅና ይስማኤልም በወርቁ በገዛት በመምሬ ፊት አንፃር በምትገኘው በኬጥያዊው ሰዓር ልጅ በኤፍሮን እርሻ ባለችው ድርብ ዋሻ ቀበሩት ። ዘፍ፣ ፱፣ ፲፫ ። |
| ወህየ ቀበርዎ ለአብርሃም ፣ ወለሣራ ብእሲቱ ። | ፲ | አብርሃምን በዚያ ቀበሩት ፣ ሚስቱን ሳራንም ። ዘፍ፣ ፳፫ ፲፯ ። ፵፱ ፴፩ ። መዝ፣ ፱ ፲፫ ። |
| ወኮነ እምድኅረ ሞተ አብርሃም ባረከ እግዚአብሔር ለይስሐቅ ወልዱ ወኀደረ ይስሐቅ መንገለ ዐዘቅተ ራእይ። | ፲፩ | አብርሃምም ከሞተ በኋላ እንዲህ ሆነ ፣ እግዚአብሔር ልጁን ይስሐቅን ባረከው ፣ ይስሐቅም አብርሃም እግዚአብሔርን ባየበት ጉድጓድ አጠገብ ኖረ ። ዘፍ፣ ፲፮ ፲፬ ። |
| ወከመዝ ውእቱ ልደቱ ለይስማኤል ወልዱ ለአብርሃም ዘወለደት ሎቱ አጋር አመተ ሳራ ። | ፲፪ | የሳራ አገልጋይ አጋር የወለደችለት የአብርሃም ልጅ ይስማኤልም ትውልዱ እንዲህ ነው ። ዘፍ፣ ፲፮ ፲፭ ። |
| ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ይስማኤል በኵሩ ናቡአት ወቄዳር ወናብዳሄል ወመብሳን ። | ፲፫ | የይስማኤልም ልጆች ስማቸው ይህ ነው ፤ የበኵር ልጁ ስሙ ናቡዓት ነው ፣ ቄዳር ፣ ናብዳሄል ፣ መብሳን ። ፩ ዜና መዋ፣ ፩ ፳፱ ። ፴ ፳፩ ። |
| ወማሴማ ወዱማ ወማሴን ። | ፲፬ | ማሴማ ፣ ዱማ ፣ ማሴን ። |
| ወኩዳ ወቴማን ወኢያጤር ወናፌስ ወቄዳን ። | ፲፭ | ኩዳ ፣ ቴማን ፣ ኢያጤር ፣ ናፌስ ፣ ቄዳን ። ፩ ዜና ፩ ፴ ። |
| እሉ እሙንቱ ደቂቀ ይስማኤል ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ፣ በበሀገሮሙ ወበበማኅበሮሙ ወበበብሔሮሙ ወበበሕዘቢሆሙ ፣ ዐሠርቱ ወክልኤቱ መላፍንት ። | ፲፮ | የይስማኤል ልጆች እሊህ ናቸው ፣ በየአገራቸው በየሸንጓቸው ፣ በየመንደራቸው ፣ በየወገናቸው የሚጠሩበት ስማቸው ይህ ነው ፣ እነዚህም ፲፪ አለቆች ናቸው ። ዘፍ፣ ፲፯ ፳ ። |
| ወኀደረ እምኤዊላጥ እስከ ሴይር እንተ ውስተ ግብጽ ወበጽሐ ውስተ አሶርዮን ወኀደረ ቅድመ ገጸ ኵሉ አኀዊሁ። | ፲፯ | ከኤዊላጥ ጀምሮ በግብጽ እስካለች እስከ ሴይር ድረስ ተስፋፋ ወደ አሶርዮንም ደረሰ ፣ በወንድሞቹም መካከል ኖረ ። ዘፍ፣ ፳፭ ፳ ። |
| ወዝንቱ ውእቱ ዓመተ ሕይወቱ ለይስማኤል ፻ወ፴ወ፯ | ፲፰ | ይስማኤል በሕይወት የኖረው ዘመን ፻፴፯ ዓመት ነው |

| | | |
|---|---|---|
| ዓመት፡ ወሞተ ረሲዖ ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ ። | | አርጅቶ ሞተ፡ ወደ ወገኖቹም ተጨመረ ። ዘፍ፡ ፲፮ ፯ ። |
| ወከመዝ ውእቱ ልደቱ ለይስሐቅ ወልደ አብርሃም ። | ፲፱ | የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ትውልድም እንዲህ ነው ። ማቴ፡ ፩ ፪ ። |
| አርብዓ ዓመቱ ለይስሐቅ አመ ነሥአ እማእከለ አፍላግ ዘሰርያ ለርብቃ ወለተ ባቱኤል ሶርያዊ እኅቱ ለላባ ከመ ትኩኖ ብእሲተ ። | ፳ | ለይስሐቅም ሚስት ትሆነው ዘንድ የላባን እኅት የሶርያዊውን ሰው የባቱኤልን ልጅ ርብቃን ከሶርያ ወንዞች መካከል በመጣት ጊዜ ፵ ዘመን ሆኖት ነበር ። |
| ወሰአለ ይስሐቅ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ርብቃ ብእሲቱ እስመ መካን ይእቲ ወሰምዖ እግዚአብሔር ወፀንሰት ርብቃ ። | ፳፩ | ይስሐቅም ስለ ሚስቱ ስለ ርብቃ ወደ እግዚአብሔር ለመነ ሚስቱ መካን ነበረችና፡ እግዚአብሔርም ልመናውን ሰማው ርብቃም ፀነሰች ። ፩ ሳሙ፡ ፩ ፲፩ ። |
| ወይትሐወሱ ደቂቃ በውስተ ከርሣ ወትቤ እመሰ ሀለወኒ እኩን ከመዝ ለምንት ሊተ ዝንቱ፡ ወሖረት ትሰአል ኀበ እግዚአብሔር ። | ፳፪ | ልጆቿም በማኅፀኗ ይራገጡ ነበር፡ እንዲህ የምሆን ከሆነማ ይህ መውለድ ለምኔ ነው አለች፡ ትጠይቅም ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ሄደች ። ፩ ሳሙ፡ ፱ ፱ ። |
| ወይቤላ እግዚአብሔር ክልኤቱ ሕዝብ ሀለዉ ውስተ ከርሥኪ ወክልኤቱ ሕዝብ ይወፅኡ እምከርሥኪ፡ ወሕዝብ እምሕዝብ ይኄይስ ወዘየዐቢ ይትቀነይ ለዘይንእስ ። | ፳፫ | እግዚአብሔርም ፪ት ሕዝብ በማኅፀንሽ አሉ፡ ፪ቱም ሕዝብ ከማኅፀንሽ ይወጣሉ፡ ሕዝብ ከሕዝብ ይበልጣል፡ ታላቁም ለታናሹ ይገዛል አላት ። ዘፍ፡ ፲፯ ፲፯ ። ፳፬ ፰ ። |
| ወተፈጸመ መዋዕለ ወሊዶታ ወክልኤቱ ሀለዉ ውስተ ከርሣ ። | ፳፬ | የምትወልድበት ወራት ደረሰ፡ ፪ት ልጆችም በማኅፀኗ ነበሩ ። |
| ወወፅአ ወልዳ ዘበኵራ ወቀይሕ ኵለንታሁ ከመ ጽጌረዳ ወጸጕር፡ ወሰመዮቶ ስሞ ዔሳው፡ ወእምድኅሬሁ ወፅአ እኁሁ ወይእኅዝ በእዴሁ ሰኰና ዔሳው፡ ወበእንተዝ ሰመዮቶ ስሞ ያዕቆብ ። | ፳፭ | የበኵር ልጅዋ ወጣ እንደ ጽጌረዳ ቀይ፡ ሁለንትናውም ጠጕር ነበር ስሙንም ኤሳው አለችው፡ ተከትሎትም ወንድሙ ወጣ፡ የኤሳውንም ሰኰናውን በእጁ ጨብጦ ነበር፡ ስለዚህም ስሙን ያዕቆብ አለችው ። ዘፍ፡ ፳፯ ፲፩ ። ፲፯ ፳፫ ። |
| ወስሳ ዓመቱ ለይስሐቅ አመ ወለደቶሙ ርብቃ ለዔሳው ወለያዕቆብ ። | ፳፮ | ርብቃ ያዕቆብና ኤሳውን በወለደቻቸው ጊዜ ለይስሐቅ ፷ ዓመት ሆኖት ነበር ። ዘፍ፡ ፳፯ ፴፯ ። ሆሴ ፲፪ ፫ ። |
| ወልሀቁ ወኮኑ ወራዙተ ወኮነ ዔሳው ብእሴ ሐቅል ነዓዊ፡ ወያዕቆብሰ ንጹሕ ውእቱ ወይነብር ውስተ ቤት ። | ፳፯ | እነሱም አደጉ ጐለመሱም፡ ኤሳው በረኸኛ አዳኝ ሆነ፡ ያዕቆብ ግን ቅምጥል ነበር፡ ከቤትም አይወጣም ነበር ። ዘፍ፡ ፳፯ ፫ - ፭ ። ፯ ፱ ። ኢዮብ ፩ ፩ - ፰ ። ፪ ፫ ። |
| ወያፈቅሮ ይስሐቅ ለዔሳው እስመ ዘውእቱ ነዐወ ይሴሰይ፡ ወርብቃሰ ታፈቅሮ ለያዕቆብ ። | ፳፰ | ይስሐቅ ዔሳውን ይወድ ነበር እሱ ያደነውን ይመገብ ነበርና፡ ርብቃ ግን ያዕቆብን ትወድ ነበር ። ዘፍ፡ ፳፯ ፬ - ፯ ። |
| ወአብሰለት ሎቱ ለያዕቆብ ተብሲለ ወመጽአ ዔሳው እምሐቅል እንዘ ይደክም ። | ፳፱ | ምስር ንፍሮም ቀቀለችለት ዔሳውም ከበረኻ ገባ ። |
| ወይቤሎ ዔሳው ለያዕቆብ፡ አብልዐኒ እምተብሲልከ እስመ ደከምኩ ጥቀ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስሙ ኤዶም ። | ፴ | ዔሳውም ያዕቆብን እጅግ ደክሚያለሁና ከንፍሮህ አብላኝ አለው፡ ስለዚህም ስሙ ኤዶም (ጉጉ) ተባለ ። |
| ወይቤሎ ያዕቆብ ለዔሳው፡ አግብእኬ ሊተ ብኵርናከ ። | ፴፩ | ያዕቆብም ዔሳውን ብኵርናህን ስጠኝ አለው ። |
| ወይቤሎ ዔሳው፡ ናሁ እመውት ለምንት እንከ ሊተ ከዊነ በኵር ። | ፴፪ | ዔሳውም እነሆ እኔ መሞቴ ነው፡ እንግዲህ በኵርነት ምን ያደርግልኛል አለው ። |
| ወይቤሎ ያዕቆብ፡ መሐልኬ ሊተ ዮም ከመ ታግብእ ሊተ ብኵርናከ፡ ወመሐለ ሎቱ ዔሳው፡ ወአግብአ ሎቱ ለያዕቆብ ከዊነ በኵር ። | ፴፫ | ያዕቆብም ብኵርናህን ልትሰጠኝ አሁን ማልልኝ አለው፡ ዔሳውም ማለለት ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሰጠው ። ዕብ፡ ፲፪ ፲፮ ። |
| ወወሀበ ያዕቆብ ለዔሳው ኅብስተ ወተብሲለ ብርስን ወበልዐ ወሰትየ፡ ወተንሥአ ወሖረ ። | ፴፬ | ያዕቆብም ለዔሳው ምስር ዳቦና ንፍሮ ሰጠው፡ በልቶ ጠጥቶም ተነሥቶ ሄደ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፳፮ ። | | ምዕራፍ ፳፮ ። |
| ወኮነ ኀልእ ረኃብ ውስተ ብሔር ዘእንበለ ረኃብ ዘኮነ በመዋዕለ አብርሃም ወሖረ ይስሐቅ ኀበ አቤሜሌክ ንጉሠ ፍልስጥኤም ውስተ ጌራራ ። | ፩ | በአብርሃም ዘመን ከሆነው ረኀብ ሌላ በአገር ሁለተኛ ረኀብ ሆነ፡ ይስሐቅም ከፍልስጥኤም ንጉሥ ከአቤሜሌክ ዘንድ ወደ ጌራራ ሄደ ። ዘፍ፡ ፰ ፪ ። ፲፪ ፲ ። ፳፩ ፴፪ ። |
| ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ወይቤሎ ኢትረድ ውስተ ግብጽ ወኅድር ውስተ ምድር እንተ አነ እቤለከ ። | ፪ | እግዚአብሔርም ተገለጠለትና እንዲህ አለው ወደ ግብጽ አትውረድ እኔ በፈቀድኩልህ ምድር ኑር ። ዘፍ፡ ፲፪ ፩ ። |

፫ ወንበር ውስተ ይእቲ ምድር ወአሐውር ምስሌከ ወእባርከከ፡ እስመ ለከ ወለዘርእከ እሁብ ለዛቲ ምድር፡ ወአቀውም ምስሌከ መሐላየ ዘመሐልኩ ለአብርሃም አቡከ ።

በዚያችም አገር ተቀመጥ እኔም ከንተ ጋራ እኖራለሁ እባርክሃለሁ፡ ይህችን አገር ለአንተ ለልጆችህም እሰጣታለሁና፡ ለአበትህ ለአብርሃም የማልኩለት መሐላዬንም ከአንተ ጋር አፀናለሁ ። ዘፍ፡ ፳ ፩ ። ዕብ፡ ፲፩ ፱ ።

፬ ወአበዝኆ ለዘርእከ ከመ ከከበ ሰማይ፡ ወእሁብ ለዘርእከ ኵላ ዛተ ምድረ፡ ወይትባረኩ በዘርእከ ኵሉ አሕዛበ ምድር ።

ዘርህንም እንደ ሰማይ ከከብ አበዛዋለሁ፡ ይህችንም አገር በሙላዋ ለልጆችህ እሰጣታለሁ፡ የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ። ዘፍ፡ ፲፪ ፫ ።

፭ እስመ ሰምዐ አብርሃም ቃለ ዚአየ ወዐቀበ ትእዛዝየ ወኵነኔየ ወሕግየ ።

አብርሃም ቃሌን እንደሰማ ትእዛዜን ፍርዴን ሕጌን እንደጠበቀ ። ዘፍ፡ ፳፪ ፲፮ - ፲፰ ።

፮ ወነበረ ይስሐቅ ውስተ ጌራራ ።

ይስሐቅም በጌራራ ኖረ ።

፯ ወተስእልዎ ሰብአ ብሔር ለይስሐቅ በእንተ ርብቃ ብእሲቱ፡ ወይቤሎሙ እኅትየ ይእቲ፡ እስመ ፈርሀ አይድሆቶሙ ከመ ብእሲቱ ይእቲ ከመ ኢይቅትልዎ ሰብአ ውእቱ ብሔር በእንተ ርብቃ ብእሲቱ እስመ ሠናይ ገጻ ።

የአገር ሰዎችም ይስሐቅን የሚስቱን የርብቃን ነገር ጠየቁት እሱም እኅቴ ናት አላቸው፡ ስለ ሚስቱ ስለ ርብቃ የዚያ አገር ሰዎች እንዳይገድሉት ሚስቴ ናት ብሎ መናገሩን ፈርቷልና መልከ መልክም ነበረችና ። ዘፍ፡ ፲፪ ፲፫ ። ፳፬ ፲፯ ። ምሳ፡ ፳፱ ፳፭ ።

፰ ወነበረ ህየ ብዙኀ መዋዕለ ወሶበ ሐወጸ አቤሜሌክ እንተ መስኮት ርእዮ ለይስሐቅ እንዘ ይትዋነይ ምስለ ርብቃ ብእሲቱ ።

በዚያም ብዙ ዘመን ኖረ፡ አቤሜሌክም በመስኮት በተመለከተ ጊዜ ይስሐቅን ከርብቃ ጋራ ሲጫወት አየው።

፱ ወጸውዖ አቤሜሌክ ለይስሐቅ ወይቤሎ ናሁ ብእሲትከ ይእቲ፡ ወትቤለኒ እኅትየ ይእቲ፡ ወይቤሎ ይስሐቅ፡ እስመ እቤ ይቀትሉኒ በእንቲአሃ ።

አቤሜሌክም ይስሐቅን ጠርቶ እኅቴ ናት አልከኝ እንጂ እነሆ ሚስትህ ናት አለው፡ ይስሐቅም በእሷ ምክንያት ይገድሉኛል ብየ ነው አለው ።

፲ ወይቤሎ አቤሜሌክ፡ ምንትኑ ዝንቱ ዘረሰይከኒ ሕቀ ከመ ዘእምሰከበ ምስለ ብእሲትከ ብእሲ ዘእምአዝማድየ ወእምአምጻእከ ላዕሌየ ኃጢአተ በኢያእምሮ ።

አቤሜሌክም ይህ ያደረግኽብኝ ነገር ምንድር ነው፡ ከዘመዶቼ የሚሆን አንድ ሰው ከሚስትህ ሊተኛ ጥቂት ቀርቶት ነበር፡ ባለማወቅም ኃጢአት ታመጣብኝ ነበር ። ዘፍ፡ ፳፡ ፱ ።

፲፩ ወአዘዞሙ ንጉሥ ለኵሎሙ ሕዝቢሁ፡ ወይቤሎሙ ኵሉ ዘለሐጠ ለዝንቱ ብእሲ ወለብእሲቱ ሞተ አኩይ ኵነኔሁ ።

ንጉሡም ይህን ሰው ሚስቱንም የነካ ሁሉ ፍርዱ ይሙት በቃ ነው ብሎ ሕዝቡን አዘዛቸው ። መዝ፡ ፻፭ ፲፭ ።

፲፪ ወዘርአ ይስሐቅ ውስተ ይእቲ ምድር ወከነ ምእተ ምክዕቢተ፡ ወባረኮ እግዚአብሔር ።

ይስሐቅም በዚያች ምድር ዘርን ዘራ፡ መቶ ዕዕፍም ሆነለት እግዚአብሔር ባረከው። ማቴ፡ ፲፫ ፰። መዝ፡ ፻፲፪ ፫።

፲፫ ወተለዐለ ወዐብየ ጥቀ ።

ከፍ ከፍ አለ እጅግም ገነነ ። ምሳ፡ ፲ ፳፪ ።

፲፬ ወአጥረየ አግብርተ ወእእማተ አባግዐ ወአልሕምተ ብዙኀ ወቀንኡ ላዕሌሁ ሰብአ ፍልስጥኤም ።

ወንድ ባርያን ሴት ባርያን ላምን በግን አብዝቶ ገዛ፡ የፍልስጥኤም ሰዎችም ቀኑበት ። ዘፍ፡ ፴፯ ፲፩። መክ፡ ፬ ፬።

፲፭ ወለኵሎሙ ዐዘቃት ዘከረዩ ደቀ አብርሃም በመዋዕለ አቡሁ ደፈንዎሙ ሰብአ ፍልስጥኤም ወመልእዎሙ መሬተ ።

በበቱም ዘመን የአብርሃምን ብላቴኖች የቈፈሩዋቸውን ጕድጓዶች ሁሉ የፍልስጥኤም ሰዎች ደፈኑዋቸው፡ መሬትንም መሉዋቸው ። ዘፍ፡ ፳፩ ፴ ።

፲፮ ወይቤሎ አቤሜሌክ ለይስሐቅ ሑር እምኔነ እስመ ጸናዕከነ ጥቀ ።

አቤሜሌክም ይስሐቅን ፈጽመህ በርትተህብናልና ከኛ ተለይተህ ሂድ አለው ።

፲፯ ወሖረ እምህየ ይስሐቅ ወኀደረ ውስተ ቈላተ ጌራራ ወነበረ ህየ ።

ይስሐቅም ከዚያ ተነሥቶ በጌራራ ሸለቆ ሰፍሮ በዚያ ተቀመጠ ። ዘፀ፡ ፩ ፱ ።

፲፰ ወከዐበ ከረዮን ይስሐቅ ለዐዘቃተ ማይ እለ ከረዩ አግብርተ አቡሁ አብርሃም ዘደፈንዎን ሰብአ ፍልስጥኤም እምድኅረ ሞተ አብርሃም አቡሁ፡ ወሰመዮን በበአስማቲሆን በከመ ሰመዮን አብርሃም ።

ይስሐቅም ያባቱ የአብርሃም አገልጋዮች የቈፈሩዋቸው አባቱ አብርሃም ከሞተም በኋላ የፍልስጥኤም ሰዎች የደፈኑዋቸውን የውኃ ጕድጓዶች እንደገና ቈፈራቸው፡ አብርሃም እንደ ጠራቸውም በየስማቸው ጠራቸው ።

፲፱ ወከረዩ አግብርተ ይስሐቅ ዐዘቅተ በቈላተ ጌራራ ወረከቡ ነቅዐ ማይ ጥዑመ ።

የይስሐቅም አገልጋዮች በጌራራ ቈላ ጕድጓድ ቈፍረው የሚጣፍጥ የውኃ ምንጭ አገኙ ።

፳ ወተበአሱ ኖሎተ ይስሐቅ ወኖሎተ ጌራራ ወይቤሉ ዚአነ ውእቱ ማይ፡ ወሰመያ ስማ ለይእቲ ዐዘቅት ዐዘ

የይስሐቅ እረኞችና የጌራራ እረኞችም ይህ ውኃ የኛ ነው የኛ ነው በማለት ተጣሉ፡ ያችንም የወኃ ጕድ

| | | |
|---|---|---|
| ቀተ ዐመፃ እስመ ዐመፅዎ ። | | ጓድ የዓመፅ-ጕድጓድ ብሎ ጠራት ዐምፀዉታልና ። |
| ወገዐዘ እምህየ ይስሐቅ ወከረየ ካልእተ ዐዘቅተ በህየ፣ ወተባሰንዎ በእንቲአሃ ወሰመያ ስማ ጽልእ ። | ፳፩ | ይስሐቅም ከዚያ ተጕዞ ሂዶ በዚያ ሌላ ጕድጓድ ቈፈረ፣ በርሷም ምክንያት ተጣሉት፣ ስሟንም ጠብ ብሎ ጠራት። |
| ወገዐዘ እምህየ ወከረየ ዐዘቅተ፣ ወኢተባአስዎ በእንቲአሁ ወሰመዮ ስሞ መርኅብ እንዘ ይብል እስመ አርኀበ ለነ እግዚአብሔር ይእዜ ወአብዝኀነ ውስተ ምድር ። | ፳፪ | ከዚያም ተጕዞ ሌላ ጕድጓድ ቈፈረ፣ በርሱ ምክንያት ግን አልተጣሉትም ስሙንም ሰፊ አሉት፣ ዛሬ እግዚአብሔር አሰፋልን በምድርም አበዛን እኮ ሲሉ ። ዘፀ፣ ፩ ፯ ። |
| ወገዐዘ እምህየ ኀበ ዐዘቅተ መሐላ ። | ፳፫ | ከዚያም ተነሥቶ ወደ መሐላው ምንጭ ተጓዘ ። |
| ወአስተርአዮ እግዚአብሔር በይእቲ ሌሊት ወይቤሎ ነየ አነ ውእቱ አምላኩ ለአብርሃም አቡከ ኢትፍራህ ሀለውኩ ምስሌከ ወእባርከከ ወአበዝኆ ለዘርእከ በእንተ አብርሃም አቡከ ። | ፳፬ | እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት ታየው፣ የአባትህ የአብርሃም ፈጣሪ እኔ ነኝ አትፍራ፣ እነሆ ካንተ ጋር አለሁና ስለ አባትህ ስለ አብርሃም ብየ አከብርሃለሁ፣ ዘርህንም አበዛዋለሁ አለው ። ዘፍ፣ ፲፭.፩ ። ሮሜ ፰ ፴፩ ። |
| ወነደቀ በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላኩ ወጸውዐ ስመ እግዚአብሔር፣ ወተከለ በህየ ዐፀደ ወከረዩ በህየ ደቀ ይስሐቅ ዐዘቅተ ። | ፳፭ | በዚያም ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠራ፣ የእግዚአብሔርንም ስም ጠራ፣ በዚያም ድንኳን ተከለ፣ የይስሐቅም ብላቴኖች ከዚያ የውኃን ጕድጓድ ቈፈሩ ። ዘፍ፣ ፲፫ ፲፰ ። መዝ፣ ፻፲፯ ፲፯ ። |
| ወሖሩ ኀቤሁ እምን ጌራራ አቤሜሌክ ወአኮዘት መጋቤ መራዕይሁ ወፋኮል መልአከ ሠራዊቱ ። | ፳፮ | ንጉሡ አቤሜሌክ ላምራሡ አኮዘትና የሠራዊቱ አለቃ ፋኮልም ከጌራራ ተነሥተው ወደርሱ ሄዱ ። |
| ወይቤሎሙ ይስሐቅ ለምንት መጻእክሙ ኀቤየ እምድኅረ ጸላእክሙኒ ወአስቈረርክሙኒ ወሰደድክሙኒ እምኀቤክሙ ። | ፳፯ | ይስሐቅም ጠልታችሁኝ ተመቅኝታችሁኝ ከናንተ ሰይታችሁ ከሰደዳችሁኝ በኋላ ለምን ወደኔ መጣችሁ፣ አላቸው ። መሳ፣ ፲፩ ፯ ። |
| ወይቤልዎ እስመ አኮ ንሕነ ዘአስቈረርናከ፣ አላ አንበርናከ ሠናየ ወፈነውናከ በሠናይ ወይእዜኒ ቡሩክ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክ ። | ፳፰ | እኛ የጠላንህ የተመቀኘንህ አይደለንም፣ አክብረን አኑረን ደስ አሰኝተን ሸኝተን ሰደድንህ እንጂ አሉት አሁንም ለፈጣሪህ እግዚአብሔር የምትገዛ ቡሩክ ነህ ። ዘፍ፣ ፳፬ ፳፪-፳፫ ። |
| ወሰበ ርኢነ ከመ ሀሎ እግዚአብሔር አምላክ ምስሌከ ንቤ ከመ ይኩን ማእከሌከ ወማእከሌነ መሐላ፣ ወንትማሐል ከመ ኢትግበር እኩየ ላዕሌነ ወኢንግበር እኩየ ላዕሌከ ። | ፳፱ | ፈጣሪ እግዚአብሔር ካንተ ጋራ እንዳለ ባየን ጊዜ በኛና በአንተ መካከል መሐላ ይደረግ እንላለን፣ አሁንም አንተ በኛ ላይ ክፉ እንዳታደርግ እኛም በንተ ላይ ክፉ እንዳናደርግ እንማማል አሉት ። ዘፍ፣ ፳፬ ፴፩ ።መዝ፣ ፻፲፭ ፲፭ ። |
| ወገብረ ሎሙ ማእደ ወበልዑ ወሰትዩ ። | ፴ | ማእድ አቅርበላቸው በሉም ጠጡም ። ዘፍ፣ ፲፱ ፫ ። |
| ወተንሥኡ ጸብሐ ወተማሐሉ በበይናቲሆሙ፣ ወፈነዎሙ ይስሐቅ ወሖሩ በዳኅን ። | ፴፩ | ማልደውም ተነሥተው እርስ በርሳቸው ተማማሉ፣ ይስሐቅ አሰናብቶአቸው በደኅና ሄዱ ። ዘፍ፣ ፳፩ ፴፩ ። |
| ወኮነ በይእቲ ዕለት በጽሑ አግብርቲሁ ለይስሐቅ ወነገርዎ በእንተ ዐዘቅት ዘከረዩ ወረከቡ ማየ በውስቴታ ። | ፴፪ | በዚያች ሌሊት እንዲህ ሆነ፣ የይስሐቅ አገልጋዮች ደርሰው የውኃ ጕድጓድ እንደቈፈሩና በውስጧም ውኃ እንዳገኙ ነገሩት ። |
| ወሰመያ ስማ ቤርሳቤህ፣ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየት ቤርሳቤህ ይእቲ ሀገር እስከ ዮም ። | ፴፫ | ስምዋንም ቤርሳቤህ ብሎ ጠራት፣ ስለዚህም ያች አገር ቤርሳቤህ ትባላለች፣ እስከ ዛሬ ድረስ ። |
| ወኮኖ ለዔሳው አርብዓ ዓመተ ወነሥአ ብእሲተ እንተ ስማ ይድን ወለተ ቤኤል ኬጥያዊ ወቤሴሞት ወለተ ኤሎን ኤውያዊ ። | ፴፬ | ለኤሳውም ፵ ዓመት ሲሆነው ስሟ ይድን የምትባል የኬጢያዊው የቤኤል ልጅንና የኤውያዊው ኤሎን ልጅ ቤሴሞትን አገባ ። ዘፍ፣ ፴፮ ፪ ። |
| ወይትቃነዋሆሙ ለይስሐቅ ወለርብቃ ። | ፴፭ | እነርሱም ይስሐቅንና ርብቃን ያሳዝኑዋቸው ነበር ። ዘፍ፣ ፳፯፣ ፵፮ ። ፳፰ ፩፣ ፰ ። |

## ምዕራፍ ፳፯ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወኮነ እምድኅረ ልህቀ ይስሐቅ ወረስዐ ተሐምጋ አዕይንቲሁ ወኢይሬኢ ። | ፩ | ይስሐቅ አርጅቶ ዓይኖቹ ፈዝዘው የማያይ ከሆነ በኋላ እንዲህ ሆነ ። ዘፍ፣ ፵፰ ፲ ። ፩ ሳሙ፣ ፫ ፪ ። |
| ወጸውዖ ለዔሳው ወልዱ ዘይልህቅ ወይቤሎ ናሁ ረሳዕኩ ወኢየአምር ዕለተ ሞትየ ። | ፪ | ታላቁ ልጁ ኤሳውን ጠርቶ እነሆ አረጀሁ ዕለተ ሞቴንም አላውቅም ። ምሳ፣ ፳፯ ፩ ። ያዕ፣ ፬ ፲፬ ። |
| ወይእዜኒ ንሣእ ንዋየ ሐቅልከ ወምጕንጳከ ወቀስትከ ወፃእ ሐቅለ ወነዐው ። | ፫ | አሁንም ማዳኛህንና አፎትህን ቀስትህንም ይዘህ በረሃ ሂደህ አድነህ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወግበር ሊተ መብልዐ ዘከመ አፈቅር ወአምጽእ ሊተ እብላዕ ከመ ትባርከ ነፍስየ ዘእንበለ እሙት ። | ፬ | ሳልሞት ነፍሴ እንድትመርቅህ እንደምወደው አድርገህ አበላ ዘንድ የምበላውን አምጣልኝ። ዘፍ፡ ፳፭ ፳፯-፳፰። |
| ወሰምዐቶ ርብቃ ለይስሐቅ እንዘ ይብሎ ከመዝ ለዔሳው ወልዱ ፡ ወሖረ ዔሳው ሐቅለ ይንዐው ለአቡሁ ። | ፭ | ርብቃም ይስሐቅ ለልጁ ለኤሳው እንዲህ ሲለው ሰማችው ኤሳውም ሊያድን በረሃ ሄደ ። |
| ወትቤሎ ርብቃ ለያዕቆብ ወልዳ ዘይንእስ ፡ ናሁ አን ሰማዕክዎ ለአቡከ እንዘ ይብሎ ለዔሳው እኁከ ። | ፮ | ርብቃ ታናሹ ልጅዋ ያዕቆብን እንዲህ አለችው ፡ እነሆ አባትህ ወንድምህ ኤሳውን ። |
| ሖር አምጽእ ሊተ እምዘነዐውከ ወግበር ሊተ መብልዐ ወእባርከ ቅድመ እግዚአብሔር ዘእንበለ እሙት ። | ፯ | ሳልሞት በእግዚአብሔር ፊት እንድመርቅህ ከአደንከው አዘጋጅተህ የምበላውን አምጣልኝ ሲለው ሰምቼዋለሁ ። |
| ወይእዜኒ ወልድየ ስምዐኒ ዘከመ እቤለከ ። | ፰ | አሁንም ልጄ ሆይ እሺ በለኝ በማዝህ ነገር ። |
| ወሑር ኀበ አባግዒነ ወአምጽእ ሊተ ክልኤተ መሐስአ ሠናያነ ወእግበሮሙ መብልዐ ለአቡከ ዘከመ ያፈቅር። | ፱ | ወደ በጎቻችን ሂደህ ያማሩ ሁለት ጠቦቶች አምጣልኝና አባትህ እንደሚወደው ምግብ አዘጋጃቸው ዘንድ ። |
| ወትሰድ ለአቡከ ወይብላዕ ወይባርከ ዘእንበለ ይሙት። | ፲ | ሳይሞት በልቶ እንዲመርቅህ ወስደህ ለአባትህ እንድትሰጠው አለችው ። ዘፍ፡ ፵፰ ፲፭ ። |
| ወይቤላ ያዕቆብ ለርብቃ እሙ ናሁ ዔሳው እኁየ ጸጓር ውእቱ ወአንሰ ኢኮንኩ ጸጓረ ። | ፲፩ | ያዕቆብም እናቱ ርብቃን እንዲህ አላት ፤ እነሆ ወንድሜ ኤሳው ጠጉራም ነው ፡ እኔ ግን ጠጉራም አይደለሁም ። ዘፍ፡ ፳፭ ፳፭ ። |
| ወዮጊ እመ ገሠሠኒ አቡየ አከውን በቅድሜሁ ከመ ዘአስተሐቅሮ ወአመጽእ ላዕሌየ መርገመ ወአኮ በረከተ ። | ፲፪ | ምናልባት አባቴ ቢዳስሰኝ በፊቱ እንደምዘብትበት እሆናለሁና ምረቃን ያይደለ በላዬ ላይ መርገምን አመጣለሁ። ዘፍ፡ ፱ ፳፭ ። ዘዳ፡ ፳፯ ፲፰ ። |
| ወትቤሎ እሙ ላዕሌየ ይኩን መርገምከ ወልድየ ፡ ዳእሙ ስምዐኒ ወሑር ወአምጽእ ሊተ ዘእቤለከ ። | ፲፫ | እናቱም ልጄ መርገምህ በኔ ላይ ይሁን ቃሌን ብቻ ስማኝ ፡ ሂድና የምልህን አምጣልኝ አለችው ። ዘፍ፡ ፵፫ ፱ ። |
| ወሖረ ወአምጽአ ላቲ ለእሙ ወገብረት መብልዐ ዘከመ ያፈቅር አቡሁ ። | ፲፬ | ሂዶም ለእናቱ አመጣላትና አባቱ እንደሚወደው አድርጋ መብሉን አዘጋጀች ። |
| ወነሥአት ርብቃ አልባሲሁ ለዔሳው ወልዳ ዘይልህቅ ወዘይሤኒ ዘሀሎ ኀቤሃ ወአልበሰቶ ለያዕቆብ ወልዳ ዘይንእስ ። | ፲፭ | ርብቃ ከርሷ ዘንድ የነበረ ያማረውን የታላቅ ልጅዋ የኤሳውን ልብስ አምጥታ ለታናሹ ልጅዋ ለያዕቆብ አለበሰችው ። ቊ፡ ፳፯ ። |
| ወዝክተሂ አምእስቲሆሙ ለእልክቱ ክልኤቱ መሐስእ ወደየት ላዕለ መታክፍቲሁ ወላዕለ ክሳዱ ። | ፲፮ | ያንን የሁለቱን ጠቦቶች ለምድ በትከሻውና በአንገቱ ላይ አደረገች ። |
| ወወሀበቶ ዝኩ መብልዐ ወኅብስተኒ ዘገብረት በእደዊሁ ለያዕቆብ ወልዳ ። | ፲፯ | ያን ያዘጋጀችውን እንጀራንና ጣፋጭ መብልን ለያዕቆብ በእጁ ሰጠችው ። |
| ወአብአ ለአቡሁ ወይቤሎ አባ ፡ ወይቤሎ አቡሁ ነየ አነ ፡ መኑ አንተ ወልድየ ። | ፲፰ | ወደ አባቱም ገብቶ አባቴ ሆይ! አለው ፡ አባቱም እነሆኝ ልጄ ሆይ አንተ ማነህ! አለው ። |
| ወይቤሎ ያዕቆብ አነ ውእቱ ዔሳው ወልድከ ዘበኵርከ ገበርኩ ዘትቤለኒ ተንሥእ ወንበር ወብላዕ እምዘነዓውኩ ለከ ከመ ትባርከኒ ነፍስከ ። | ፲፱ | ያዕቆብም እኔ የበኩር ልጅህ ዔሳው ነኝ ያልከኝን አድርጌ አለሁ ተነሥና ተቀመጥ ፡ ከአደንኩልህም ብላና ነፍስህ ትመርቀኝ ዘንድ አለው ። |
| ወይቤሎ ይስሐቅ ለወልዱ ምንትኑ ውእቱ ዝንቱ ዘአፍጠንከ ረኪበ ወልድየ ፡ ወይቤሎ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር አምላክከ ቅድሜየ ። | ፳ | ይስሐቅም ለልጁ ልጄ ፈጥነህ ያገኘህ ይህ ምንድር ነው፤ አለው ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በፊቴ የሰጠኝ ነው አለው ። |
| ወይቤሎ ይስሐቅ ቅረበኒ ወልድየ ወእግሥሥከ ለእመ አንተሁ ውእቱ ዔሳው ወለእመ ኢኮንከ ። | ፳፩ | ይስሐቅም ልጄ! ቅረበኝ ልዳሥሥህ አንተ ዔሳው እንደሆንክ ወይም ያይደለህ እንደሆነ አለው ። |
| ወቀርበ ያዕቆብ ኀበ ይስሐቅ አቡሁ ወገሠሦ ወይቤሎ ቃልሰ ቃለ ያዕቆብ ወእደውሰ ዘዔሳው ። | ፳፪ | ያዕቆብም ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ ቀረበ ፡ ዳሠሠውም ቃልህ የያዕቆብ ነው ፡ እጆችህ ግን የዔሳው ናቸው አለው። |
| ወኢያእመሮ እስመ እደዊሁ ጸጓራት ከመ እደወ ዔሳው ፡ ወባረከ ይስሐቅ ። | ፳፫ | ነገር ግን አላወቀውም እጆቹ እንደ ዔሳው እጆች ጠጉራሞች ነበሩና ፡ ይስሐቅም መረቀው ። ቊ፡ ፲፮ ። |
| ወይቤሎ አንተ ውእቱ ወልድየ ዔሳው ፡ ወይቤሎ ነየ አነ ። | ፳፬ | አንተ ልጄ ዔሳው ነህን አለው ፡ እነሆ እኔ ልጅህ ነኝ አለው ። ሮሜ ፫ ፯-፰ ። ኤፌ፡ ፬ ፳፭ ። |
| ወይቤሎ አምጽእ ሊተ እምዘነዐውከ ወልድየ ከመ እብላዕ ወትባርከ ነፍስየ ፡ ወአቅረበ ሎቱ ወበልዐ ወአም | ፳፭ | ልጄ አድነህ ያመጣህልኝን በልቼ ሰውነቴ ትመርቅህ ዘንድ አምጣልኝ አለው ፡ አቅርበለት በላም ወይንም አመ |

| | | |
|---|---|---|
| ጽአ ሎቱ ወይነ ወሰትየ ። | | ጣለት ጠጣ ። |
| ወይቤሎ ይስሐቅ ቅረበኒ ወሰዐመኒ ወልድየ ። | ፳፮ | ይስሐቅም ልጄ ! ቅረበኝና ሳመኝ አለው ። |
| ወቀርበ ወሰዐሞ ወአጼነዎ ወጼነዎ ጼና አልባሲሁ ወይቤ ናሁ ጼናሁ ለወልድየ ከመ ጼና ገዳም ጥቀ ጥንቁቀ ዘባረኮ እግዚአብሔር ። | ፳፯ | ቀርቦም ሳመው ፡ የልብሱንም ሽታ አሸተተው ፡ እነሆ የልጄ ልብስ ሽታው እግዚአብሔር እንደባረከው እንደ ዱር አበባ ሽታ ነው አለ ። |
| ወይቤሎ የሀብከ እግዚአብሔር እምጠለ ሰማይ ወእምጠለ ምድር ፡ ወያብዝኅ ሥርናየከ ወወይነከ ወቅብዐከ ። | ፳፰ | እግዚአብሔር ከሰማይ ጠል ፡ ከምድር ስብ ይስጥህ ፡ ሥንዴህን ወይንህንና ዘይትህን ያብዛልህ አለው ። ዮሴ፡ ፲፩ ፯ ። መኃ፡ ፪ ፲፫ ። |
| ወይትቀነዩ ለከ አሕዛብ ወይስግዱ ለከ መላእክት ወኩን እግዚአ ለእኁከ ወይስግዱ ለከ ደቂቀ አቡከ ፡ ዘይባርከከ ቡሩከ ይኩን ፡ ወዘይረግመከ ርጉመ ለይኩን ። | ፳፱ | አሕዛብ ይገዙልህ ፡ አለቆችም ይስገዱልህ ፡ ለወንድሞችህም ጌታ ሁን ፡ የአባቶችህ ልጆች ይስገዱልህ አንተን የሚመርቅህ የተመረቀ ይሁን ፡ አንተን የሚረግምህም የተረገመ ይሁን ። |
| ወእምድኅረ እኅለቀ ባርኮቶ ይስሐቅ ለያዕቆብ ፡ ወዕአ ያዕቆብ እምቅድመ ገጸ ይስሐቅ አቡሁ ወመጽአ ዔሳው እምንዒው ። | ፴ | ይስሐቅ መርቆ ከጨረሰ በኋላ ያዕቆብ ከባቱ ከይስሐቅ ፊት ወጣ ፡ ዔሳውም ከአደን ተመልሶ መጣ ። |
| ወገብረ ውእቱሂ መብልዐ ወአምጽአ ለአቡሁ ወይቤሎ ተንሥእ አባ ወብላዕ እምዘነዐወ ለከ ወልድከ ከመ ትባርከኒ ነፍስከ ። | ፴፩ | እርሱም አድኖ ያመጣውን ምግብ አዘጋጅቶ ወደ አባቱ አመጣ ፡ አባቴ ሰውነትህ ትመርቀኝ ዘንድ እኔ ልጅህ አድኜ ከመጣሁት ተነሥተህ ብላ አለው ። |
| ወይቤሎ ይስሐቅ መኑ አንተ ፡ ወይቤሎ ዔሳው አነ ውእቱ ዔሳው ወልድከ ዘበኵርከ ። | ፴፪ | ይስሐቅም አንተ ማን ነህ አለው ፡ ዔሳውም እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ አለው ። |
| ወደንገፀ ይስሐቅ ዐቢየ ድንጋፄ ጥቀ ወይቤሎ መኑመ ዘአምጽአ ሊተ ዘነዐወ ወበላዕኩ ወባረክዎ ወቡሩከ ውእቱ። | ፴፫ | ይስሐቅም እጅግ ደነገጠ ፡ ያደነውን ሠርቶ አዘጋጅቶ በልቼ የመረቅሁት ማን ነው ፣ እሱም የተባረከ ነው አለው ። ዘፍ፡ ፳፰ ፫ ፡ ፬ ። ኤፌ፡ ፩ ፫ ። |
| ወኮነ ሶበ ሰምዐ ዔሳው ቃለ አቡሁ ጸርሐ በዐቢይ ቃል ወአምረረ ጥቀ ወይቤ ፡ ባርከኒ ኪያየኒ አባ ። | ፴፬ | ዔሳውም ያባቱን ነገር በሰማ ጊዜ በታላቅ ቃል ጮኸ ምርር ብሎም አለቀሰ ፡ አባቴ እኔንም መርቀኝ አለው ። |
| ወይቤሎ ይስሐቅ ለዔሳው መጽአ እኁከ በጕሕሉት ወነሥአ በረከተከ ። | ፴፭ | ይስሐቅም ወንድምህ በተንኰል መጥቶ በረከትህን ወሰደው አለው ። |
| ወይቤ ዔሳው በጽድቅ ተሰምየ ያዕቆብ እስመ አዕቀጸኒ ክልኤተ ጊዜ ፡ ቀዳሚ ብኵርናየ ነሥአኒ ወናሁ ዮምኒ በረከትየ ነሥአኒ ፡ ወይቤሎ ዔሳው አልቦኑ አባ ዘአትረፍከ ሊተ በረከተ ። | ፴፮ | ዔሳውም በእውነት ያዕቆብ ተባለ ሁለት ጊዜ አሰናክሎኛልና ፡ አስቀድሞ ብኵርናዬን ወሰደብኝ ፡ እነሆ ዳግመኛም በረከቴን ወሰደብኝ አለ ፡ ዔሳውም አባቴ ለእኔስ ያስቀረህልኝ በረከት የለምን ፤ አለው ። ዘፍ፡ ፳፭ ፳፱-፴፫ ። |
| ወአውሥአ ይስሐቅ ወይቤሎ ለዔሳው እግዚአከ ረሰይክዎ ወለኵሎሙ አኃዊሁ አግብርቲሁ ረሰይክዎሙ ወአብዛኅኩ ሎቱ ወይነ ወሥርናየ ወቅብዐ ፡ ወለከ ምንተ እሬሲ ወልድየ ። | ፴፯ | ይስሐቅም መልሶ ዔሳውን እንዲህ አለው ፤ ጌታህ አደረግሁት ወንድሞቹንም ሁሉ ተገዥዎቹ አደረግኋቸው ፡ ሥንዴውን ወይኑን ዘይቱን አበዛሁለት ፡ ልጄ ! ላንተስ ምን ላድርግልህ ፤ ፪ ሳሙ፡ ፰ ፲፬ ። ቍ፡ ፳፫ ። |
| ወይቤሎ ዔሳው ለይስሐቅ አቡሁ አሐቲኑ ከመ በረከትከ ለከ አባ ፡ ወአምዝ ጸርሐ ዔሳው ወበከየ ። | ፴፰ | ዔሳውም ይስሐቅን እንዲህ አለው ፤ አባቴ በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን ፤ አባቴ እኔንም መርቀኝ እንጂ አለው ፡ ከዚህ በኋላ ድምፁን አሰምቶ አለቀሰ ። ዕብ፡ ፲፪ ፲፯ ። |
| ወይቤ ይስሐቅ ናሁ እምጠለ ሰማይ እምላዕሉ ወእምጠለ ምድር ይኩን ሕይወትከ ። | ፴፱ | ይስሐቅም እንዲህ አለ ፤ እነሆ መኖሪያህ ከምድር በላይ ካለ ከሰማይ በወረደ ጠል ከምድር በተገኘ ስብ ይሁን ። |
| ወበመጥባሕትከ ሕየው ወተቀነይ ለእኁከ ፡ ወባሕቱ እመ ትፈቅድ ትግድፍ ያሮ እምላዕለ ክሳድከ ተጋነይ ሎቱ ። | ፵ | በሰይፍህ አድነህ ኑር ፡ ለወንድምህም ተገዛ ፡ ነገር ግን አገዛዙን ከአንገትህ ሊቀልልህ ብትወድ ተለማመጥ ። |
| ወተበቀሎ ዔሳው ለያዕቆብ በእንተ በረከቱ ዘባረኮ አቡሁ ፡ ወይቤ ዔሳው በልቡ ለትቅረብ መዋዕለ ላሁ ለአቡየ ከመ እቅትሎ ለያዕቆብ እኁየ ። | ፵፩ | ዔሳውም አባቱ ስለ መረቀው ምረቃ በያዕቆብ ቂም ያዘበት ፡ ዔሳው በልቡ ወንድሜ ያዕቆብን እገድለው ዘንድ የአባቴ የልቅሶው ቀን ትድረስ አለ ። |
| ወአይድዕዋ ለርብቃ ዘይቤ ወልዳ ዘይልህቅ ወለኤክት መጸውዐቶ ለያዕቆብ ወልዳ ዘይንእስ ፡ ወትቤሎ ናሁ ዔሳው እኁከ ይንዕወከ ወይፈቅድ ይቅትልከ ። | ፵፪ | ታላቁ ልጅዋ ዔሳው የተናገረውን ለርብቃ ነገሩዋት ፡ እሷም ታናሹ ልጅዋ ያዕቆብን ልካ አስጠርታ እነሆ ወንድምህ ዔሳው ያድንሃል ሊገድልህም ይፈልጋል ። |

፵፫ ወይእዜኒ ወልድየ ስምዐኒ ቃልየ ዘእብለከ ተንሥእ ወሑር ማእከለ አፍላግ ዘሶርያ ኀበ ላባ እኁየ ውስተ ካራን ።

፵፬ ወንበር ኀቤሁ ኅዳጠ መዋዕለ እስከ ይቀርር መዓቱ ለእኁከ ።

፵፭ ወይረስዕ ዘገበርከሉ ወእልእከ ወእነሥአከ እምህየ ከመ ኢይሕጐል ክልኤክሙ በአሐቲ ዕለት ።

፵፮ ወትቤሎ ርብቃ ለይስሐቅ ጸላእኩ ሕይወትየ እምአዋልደ ከነአን ወእመሰ ይነሥእ ያዕቆብ ብእሲተ እምአዋልደ ዝንቱ ብሔር ለምንት እንከ አሐዩ ።

## ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ ወጸውዖ ይስሐቅ ለያዕቆብ ወባረኮ ፡ ወይቤሎ ኢትንሣእ ብእሲተ እምአዋልደ ከናዓን ።

፪ ተንሥእ ወሑር ማእከለ አፍላግ ውስተ ቤተ ባቱኤል አቡሃ ለእምከ ወንሣእ ለከ ብእሲተ እምአዋልዲሁ ለላባ እኁሃ ለርብቃ እምከ ።

፫ ወአምላኪየ ይሑር ምስሌከ ወያዕቢከ ወይባርከ ወያብዝኅከ ወኩን ብዙኀ አሕዛበ ።

፬ ወየሀብከ በረከተ አብርሃም አቡየ ለከ ወለዘርእከ እምድኅሬከ ከመ ትረስ ለይእቲ ምድር እንተ ወሀበ ለአብርሃም ።

፭ ወፈነዎ ይስሐቅ ለያዕቆብ ወልዶ ማእከለ አፍላግ ዘሶርያ ኀበ ላባ ወልደ ባቱኤል ሶርያዊ እኁሃ ለርብቃ ።

፮ ወሰበ ርእየ ዔሳው ከመ ባረኮ አቡሁ ለያዕቆብ ወከመ ሖረ ማእከለ አፍላግ ዘሶርያ ከመ ይንሣእ ብእሲተ እምህየ አመ ባረኮ ወከመ አዘዞ ወይቤሎ ኢትንሣእ ብእሲተ እምአዋልደ ከናዓን ።

፯ ወሰምዖሙ ያዕቆብ ለአቡሁ ወለእሙ ወሖረ ።

፰ ወሰበ ርእየ ዔሳው ከመ እኩያት እማንቱ አዋልደ ከናዓን በኀበ አቡሁ ይስሐቅ ሖረ ኀበ ይስማኤል ።

፱ ወነሥአ ለቤሴሞት ወለተ ይስማኤል ወልደ አብርሃም እኅቶ ለናኮር ከመ ትኩኖ ብእሲተ ምስለ አንስቲያሁ ።

፲ ወወፅአ ያዕቆብ እምዐዘቅተ መሐላ ወሖረ ኀበ ካራን ።

፲፩ ወረከበ መካነ ወቤተ ህየ ፡ እስመ ዐርበት ፀሐይ ወነሥአ እምውእቱ እብን ዘውስተ ውእቱ ብሔር ወወደየ ውስተ ትርአሲሁ ወሰከበ በውእቱ መካን ።

፲፪ ወሐለመ ወይሬኢ ሰዋስወ ዘወርቅ ውስተ ምድር ወርእሱ ይጐድእ ሰማየ ፡ ወመላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወርዱ ቦቱ ወእግዚአብሔር ይቀውም ላዕሌሁ ።

፲፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ አቡከ ፡ ኢትፍራህ ዘተኒ ምድረ እንተ ውስቴታ ትሰክብ ለከ እሁበከ ወለዘርእከ ።

፲፬ ወይከውን ዘርእከ ከመ ኖፃ ባሕር ወይበዝኅ ወይመ

---

፵፫ አሁንም ልጄ የምልህን ነገር ስማኝ፤ ተነሥና በሶርያ ወንዞች መካከል ወዳለ ወደ ወንድሜ ላባ ወደ ካራን ሂድ አለችው ። ዘፍ፤ ፲፩ ፴፩ ።

፵፬ የወንድምህ የቊጣው ቀን እስኪበርድለት ድረስ ጥቂት ቀን ከርሱ ዘንድ ተቀመጥ ።

፵፭ ያደረግኸውን ነገር እስኪረሳው ድረስ፤ ከዚያም ልኬ አስመጣሃለሁ፤ በአንድ ቀን ሁለታችሁን እንዳላጣ ።

፵፮ ርብቃ ይስሐቅን እንዲህ አለችው ፤ ከከነዓን ሴቶች (ከዔሳው ሚስቶች) የተነሣ ኑሮዬን ጠላሁ፤ ያዕቆብ ከዚህ አገር ልጆች ወገን ሚስት ያገባ እንደሆነ እንግዲህ በሕይወት መኖር ለምኔ ነው ! ። ዘፍ፤ ፳፰ ፰ ።

## ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ ይስሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ ባረከው፤ እንዲህም አለው ፤ ከከነዓን ልጆች ወገን ሚስት አታግባ ።

፪ ተነሥና በወንዞች መካከል ወዳለው ወደናትህ አባት ወደ ባቱኤል ቤት ሂደህ ከናትህ ርብቃ ወንድም ከላባ ልጆች ሚስት አግባ ።

፫ ፈጣሪዬም ከንተ ጋር ይኑር፤ ያክብርህ፤ ይባርክህ ያብዛህ፤ ብዙ ሕዝብ ሁን ።

፬ የአባቴ የአብርሃምን በረከት ላንተ ይስጥህ፤ ካንተም በኋላ ለዘርህ ለአብርሃም የሰጠው ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ ። ዘፍ፤ ፲፪ ፪ ።

፭ ይስሐቅም ልጁ ያዕቆብን የርብቃ ወንድም የሶርያ ሰው የሚሆን የባቱኤል ልጅ ወዳለበት በሶርያ ወንዞች መካከል ወዳለው አገር አሰናበተው ።

፮ ዔሳውም አባቱ ያዕቆብን እንደ መረቀው በየ ጊዜ በባረከውም ጊዜ ከዚያ ሚስት ያጭ ዘንድ በሶርያ ወንዞች መካከል ወዳለው አገር እንደሄደ በየ ጊዜ፤ ከከነዓንም ልጆች ወገን ሚስት አታግባ ብሎ እንደ አዘዘው በየ ጊዜ ።

፯ ያዕቆብም የአባቱንና የናቱን ሰምቶ ወደ ሶርያ እንደ ሄደ በየ ጊዜ ።

፰ ዔሳው የከነዓን ልጆች በአባቱ በይስሐቅ ዘንድ ክፉዎች እንደ ሆኑ በየ ጊዜ ወደ ይስማኤል ሄደ ።

፱ ከሚስቶቹ ጋር ሚስት ትሆነው ዘንድ የናኮር ወንድም የአብርሃም ልጅ የሚሆን የይስማኤል ልጅ ቤሴሞትን አገባ ።

፲ ያዕቆብም ከተማማሉበት የውኃ ጕድጓድ ወጥቶ ወደ ካራን ሄደ ። ግብ፤ ሐዋ፤ ፯ ፪ ።

፲፩ ፀሐይ ገብቶ መሽቶ ነበርና ቦታ አግኝቶ ከዚያ አደረ፤ በቦታው ካለ ደንጊያ አንሥቶ ያንን ተንተርሶ በዚያ ቦታ ተኝቶ አደረ ።

፲፪ በዚያም ሌሊት በራእይ የወርቅ መሰላል ተተክሎ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሶ አየ፤ መላእክትም ይወጡበት ይወርዱበት ነበር፤ በላዩም ላይ እግዚአብሔር ተቀምጦ አየ ። ዘፍ፤ ፵፩ ፩ ።

፲፫ የአብርሃም ፈጣሪ የአባትህም የይስሐቅ ፈጣሪ እኔ እግዚአብሔር ነኝና አትፍራ አለው፤ የተኛህበትንም ምድር ላንተም ለልጆችህም እሰጣታለሁ ። ዘፍ፤ ፲፫ ፤ ፲፯ ።

፲፬ ዘርህም እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል፤ ይበዛል በአራት

ልእ እስከ ባሕር ወውስተ አዜብ ወመስዕ፣ ወውስተ ጽባሕ ወይትባረኩ ብከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ወበዘርእከ።
፲፭ ወናሁ አሐውር ምስሌከ ወአዐቅበከ በኵሉ ፍኖትከ እንተ ትሐውር ወአገብአከ ውስተ ውእቱ ምድር ወኢየኀድገከ እስከ እገብር ለከ ኵሎ ዘእቤለከ።
፲፮ ወነቅሐ ያዕቆብ እምንዋሙ ወይቤ እግዚአብሔር ሀሎ ውስተ ዛቲ ምድር ወአንሰ ኢያእመርኩ።
፲፯ ወፈርሀ ወይቤ ግሩም ውእቱ ዝንቱ ምድር ወይከውን ዝየ ቤተ እግዚአብሔር ወዛቲ ይእቲ ኆኅት ለሰማይ።

፲፰ ወተንሥአ ያዕቆብ በጽባሕ ወነሥአ ሰይእቲ እብን እንተ ወደየ ውስተ ትርአሲሁ ወአቀማ ከመ ሐውልት ወሦጠ ቅብዐ ላዕለ ርእሳ።
፲፱ ወሰመየ ስሞ ለውእቱ መከን ቤተ ኤል፣ ወስሙሰ ለውእቱ መከን ትካቲሁ ወለምሐሳ።
፳ ወበፅዐ ያዕቆብ ወይቤ ለእመ ሀሎ እግዚአብሔር ምስሌየ ወዐቀበኒ በዛቲ ፍኖት እንተ አሐውር ወወሀበኒ እክለ ዘእበልዕ ወልብሰ ዘእለብስ።
፳፩ ወእግብአኒ በዳኅን ቤተ አቡየ ይከውነኒ እግዚአብሔር አምላኪየ።

፳፪ ወዛቲ እብን እንተ አቀምኩ ትከውነኒ ቤተ እግዚአብሔር ወኵሎ ዘወሀብከኒ ዓሥራተ እዴሁ እዔሥር ለከ።

ምዕራፍ ፳፱።

፩ ወተንሥአ ያዕቆብ ወሖረ በጽባሕ ኀበ ላባ ወልደ ባቱኤል ሶርያዊ እኁሃ ለርብቃ እሞሙ ለያዕቆብ ወለዔሳው።

፪ ወሶበ ይኔጽር ወይሬኢ ናሁ ዐዘቅት ውስተ ገዳም፣ ወሀለዋ ህየ ሠላሳ አባግዐ ወይሰክባ ላዕሌሃ፡ እስመ እምነ ይእቲ ዐዘቅት ያስትዩዎን ለውእቶን አባግዐ ወዐቢ አፉሃ ለይእቲ ዐዘቅት እብን ዐቢይ።
፫ ወይትጋብኡ ህየ ኵሎሙ ኖሎት ወያሴስልዋ ለይእቲ እብን እምአፈ ዐዘቅት ወያሰትዩ አባግዒሆሙ ወያገብእዋ ለይእቲ እብን ውስተ አፈ ዐዘቅት።

፬ ወይቤሎሙ ያዕቆብ፣ አንትሙ አኀውየ እምአይቴ አንትሙ፣ ወይቤልዎ እምነ ካራን ንሕነ።
፭ ወይቤሎሙ ተአምርዎኑ ለላባ ወልደ ናኮር፤ ወይቤልዎ ነአምሮ።
፮ ወይቤሎሙ ዳኅንኑ ውእቱ፣ ወይቤልዎ እወ ዳኅን፣ ወናሁ ራኄል ወለቱ ትመጽእ ምስለ አባግዐ አቡሃ።
፯ ወይቤሎሙ ዓዲኑ ኢበጽሐ ሰዓት ከመ ይትጋብኡ እንስሳክሙ ወይስተዩ ወይሑሩ ወይትረዐዩ።
፰ ወይቤልዎ ኢንክል ለእመ ኢተጋብኡ ኵሎሙ ኖሎት፣ ወያሴስልዋ ለዛቲ እብን እምአፈ ዐዘቅት ወናስቲ አባግዒነ።
፱ ወእንዘ ዘንተ ይትናገሩ በጽሐት ራኄል ምስለ አባ

መንግሥትን ሁሉ ይመላል፣ በምድር ያሉ አሕዛብም ሁንተም በልጅህም ይከብራሉ።
እኔም ከንተ ጋራ እሄዳለሁ፣ በምትሄድበት መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፣ ወደዚህም ምድር እመልስሃለሁ ያል ኩህን ሁሉ እስክደርግልህ ድረስ አልለይህም ብሎ ነገረው።
ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቅቶ እግዚአብሔር በዚህች ምድር አለ እኔ ግን አላወቅሁም ነበር አለ። ዘፀ፡ ፫ ፭።
ፈራ እንዲህም አለ፤ ይህ ቦታ የሚያስፈራ ነው፣ ከዚህ ቤተ እግዚአብሔር ይሠራል የሰማይም ደጃፍ ይህች ናት አለ። ዮሐ፡ ፩ ፲፭።
ያዕቆብ ሲነጋ ተነሥቶ ትራስ ያደረጋትን ያችን ድንጊያ አንሥቶ እንደ ሐውልት አድርጎ አቆማት፣ በላይዋም ዘይት አፈሰሰባት።
ያንንም ቦታ ስሙን ቤቴል ብሎ ጠራው፣ የዚያ ቦታ ጥንተ ስሙ ግን ወለምሐሳ ይባል ነበር። መሳ፡ ፩፡ ፳፫።
ያዕቆብም እንዲህ ብሎ ተሳለ እግዚአብሔር ከእኔ ጋራ ከሆነ በዚች በምሄድበትም መንገድ ከጠበቀኝ የምበላውን እህል የምለብሰውን ልብስ ከሰጠኝ።
ወዳባቴም ወገኖች በደኅና ከመለሰኝ፣ ፈጣሪዬ እግዚአብሔር የሚሰጠኝ ይህ ይበቃኛል። መሳ፡ ፲፩ ፴፩። ፪ ሳሙ፡ ፲፭ ፰።
ይህችም ያቆምኋዋት ድንጊያ የእግዚአብሔር ቤት ትሆንልኛለች፣ ከሰጠኸኝም ሁሉ "ከሥር አንድ„ አውጥቼ ላንተ እሰጣለሁ ብሎ ተሳለ። ዘፍ፡ ፴፭ ፯።

ምዕራፍ ፳፱።

ያዕቆብ ሲነጋ ተነሥቶ የያዕቆብና የዔሳው እናታቸው የርብቃ ወንድም የሶርያ ሰው ከሚሆን ከባቱኤል ልጅ ከላባ ዘንድ ሄደ። ዘኍ፡ ፳፫ ፯። ሆሴ፡ ፲፪ ፲፪።
አሻግሮ በተመለከተ ጊዜ እነሆ በምድረ በዳ ያለውን የውኃ ጕድጓድ አየ፣ በዚያም ፴ በጎች ተኝተው ነበር፣ እነዚያን በጎች ከዚያች የጕድጓድ ውኃ ያጠጡዋቸው ነበርና በዚያችም ጕድጓድ አፍ ታላቅ ድንጊያ ተጋጥሞ ነበር።
እረኞቹም ሁሉ ተሰብስበው ድንጊያውን ከምንጩ አፍ አንሥተው በጎቻቸውን ያጠጡ ነበር፣ በጎቻቸውንም ካጠጡ በኋላ ድንጊያይቱን ከጕድጓዱ አፍ መልሰው ይገጥሙዋት ነበር።
ያዕቆብም እናንተ ወንድሞቼ ከወዴት ናችሁ፤ አላቸው፣ ከወደ ካራን ነን አሉት።
የናኮር ልጅ ላባን ታውቁታላችሁን፤ አላቸው፣ አዎን እናውቀዋለን አሉት።
ደኅና ነውን አላቸው፣ አዎን ደኅና ነው አሁንም ልጁ ራኄል ያባቷን በጎች ይዛ ትመጣለች አሉት።
ከብቶቻችሁ ውኃ ለመጠጣት የሚሰበሰቡበት ጠጥተውም የሚሠማሩበት ሰዓት አልደረሰምን አላቸው።
እነሱም እረኞቹ ሁሉ ተሰብስበው ድንጊያዋን ከጕድጓዱ አፍ ላይ ካላነሥዋት በጎቻችንን ለማጠጣት አንችልም አሉት።
ይህንም ተናግረው ሳይጨርሱ ራኄል የአባቷን በጎች

ግበ አቡሃ እስመ ይእቲ ትሬዒ አባግዐ ።

ይዛ ደረሰች፥ እርሷ በጎች ትጠብቅ ነበርና ።

፲ ወሶበ ርእያ ያዕቆብ ለራኄል ወለተ ላባ እኁሁ ለእሙ ሰዓማ ለራኄል ወጸርሐ በቃሉ ወበከየ ወአይድዓ ለራኄል ከመ ወልደ ርብቃ እኁቱ ለአቡሃ ውእቱ ።

ያዕቆብም የናቱ ወንድም የላባ ልጅ ራኄልን የላባን በጎች ይዛ ስትመጣ ባየ ጊዜ ራኄልን ሳማት፥ ቃሉንም ከፍ አድርጎ አለቀሰ፥ የአባቱ እኅት የርብቃ ልጅ መሆኑንም ለራኄል ነገራት ።

፲፩ ወአሰሰላ ለእብን እምአፈ ዐዘቅት ወአስተየ አባግዒሃ ለራኄል ።

ድንጊያይቱንም ከጉድጓዱ አፍ ላይ አንሥቶ የራኄልን በጎች አጠጣ ። ዘፀ፥ ፪ ፲፯ ።

፲፪ ወሮጸት ራኄል ወሐረት ወአይድአቶ ለአቡሃ ዘንተ ነገረ ።

ራኄልም እየሮጠች ሄዳ ይህን ነገር ለአባቷ ነገረችው።

፲፫ ወሶበ ሰምዐ ላባ ከመ ያዕቆብ ወልደ ርብቃ እኁቱ ሮጸ ወተቀበሎ ወሐቀፎ ወሰዐሞ ወወሰዶ ቤቶ፥ ወነገሮ ለላባ ኵሎ ነገሮ ።

ላባም የእኅቱ የርብቃን ልጅ ስም በሰማ ጊዜ ፈጥኖ ሄዶ አቅፎ ስሞ ወደ ቤቱ ወሰደው፥ ያዕቆብ የመጣበትንም ሁሉ ነገር ለላባ ነገረው ።

፲፬ ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ ዐፅምየ ወሥጋየ አንተ ንበር ምስሌየ፥ ወነበረ ምስሌሁ ሠላሳ መዋዕለ ።

ላባም ያዕቆብን አንተ አጥንቴ ሥጋዬ ነህና ከኔ ጋር ተቀመጥ አለው፥ ከሱም ጋር ፴ ቀን ተቀመጠ። መክ፥ ፬ ፩።

፲፭ ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ እስመ እኁየ አንተ ኢትትቀነይ ሊተ በከ፥ ንግረኒ ምንት ውእቱ ዐስብከ ።

ላባም ያዕቆብን አንተ ወንድሜ ነህና በከንቱ ለኔ አትገዛም ደመወዝህ ምን እንደሆነ ንገረኝ አለው ።

፲፮ ወበቱ ለላባ ክልኤቲ አዋልድ፥ ስማ ለእንተ ትልህቅ ልያ፥ ወለእንተ ትንእስ ራኄል ።

ለላባም ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት፥ የትልቂቱ ስም ልያ ነው፥ የትንሺቱም ስምዋ ራኄል ነው ።

፲፯ ወልያሰ ትደዊ አዕይንቲሃ፥ ወሰራኄልሰ ሠናይ ራእያ ወላህይ ገጻ ።

ልያ ዓይኑ ታማሚ ነበረች፥ ራኄል ግን መልከ መልካም ነበረች፥ ፊቷም ውብ ነበር ።

፲፰ ወአፍቀራ ያዕቆብ ለራኄል፥ ወይቤሎ ያዕቆብ ለላባ እትቀነይ ለከ ሰብዓተ ዓመተ በእንተ ራኄል ወለትከ እንተ ትንእስ ወሀበኒ ኪያሃ ከመ ትኩነኒ ብእሲተ ።

ያዕቆብም ራኄልን ወደዳት፥ ያዕቆብ ስለ ትንሺቱ ልጅህ ፯ት ዓመት እገዛልሃለሁና ሚስት ትሆነኝ ዘንድ እሷን ስጠኝ አለው ። ዘፍ፥ ፴፩ ፵፩ ።

፲፱ ወይቤሎ ላባ ይኄይሰኒ ለከ አሀብከ ለማእምርየ ወለሥጋየ እምአሀ፤ ለካልእ ብእሲ ነኪር፥ ንበር እንከሰ ።

ላባም ለሌላ ባዕድ ሰው ከምሰጣት ይልቅ ለማውቅህ ላንተ ለዘመዴ ብሰጣት ይሻለኛል እንግዲያውስ ተቀመጥ አለው ።

፳ ወተቀንየ ያዕቆብ ሰብዓተ ዓመተ በእንተ ራኄል ወኮኖ በቅድሜሁ ከመ ኅዳጥ መዋዕል እስመ አፍቀራ ።

ያዕቆብም ስለ ራኄል ፯ት ዓመት ተገዛ፥ ራኄልን ስለ ወደዳት ፯ቱ ዓመት ለያዕቆብ እንደ ጥቂት ቀን ሆነለት ። ዘፍ፥ ፴ ፳፮ ። መኃ፥ ፰ ፯ ።

፳፩ ወይቤሎ ያዕቆብ ለላባ ሀበኒ እንከሰ ብእሲትየ ከመ እበእ ኅቤሃ እስመ ፈጸምኩ መዋዕሊሁ ።

ያዕቆብም ላባን ዘመኑን ፈጽሜ አለሁና እንግዲህስ እገናኛት ዘንድ ሚስቴን ስጠኝ አለው ። መሳ፥ ፲፭ ፩ ።

፳፪ ወአስተጋብአሙ ላባ ለኵሎሙ ሰብአ ብሔሩ ወገብረ ከብካበ ።

ላባም የአገሩን ሰዎች ሁሉ ሰብስቦ ሠርግ አደረገ ።

፳፫ ወሶበ መስየ ነሥአ ላባ ለልያ ወለቱ ወአብአ ኅበ ያዕቆብ ።

በመሸም ጊዜ ላባ ልጁ ልያን ወስዶ ለያዕቆብ አገባለት።

፳፬ ወወሀባ ላባ ለልያ ወለቱ ዘለፋሃ ትኩና አመተ፥ ወሶበ ጸብሐ ነያ ልያ ።

ላባም ለልጁ ልያ አገልጋይ ትሆናት ዘንድ ዘለፋን ሰጣት፥ ሲነጋም እነሆ ልያ ሆና ተገኘች ።

፳፭ ወይቤሎ ያዕቆብ ለላባ ለምንት ረሰይከኒ ከመዝ እኮኑ በእንተ ራኄል ተቀነይኩ ለከ ወለምንት አስተሐቀርከኒ ።

ያዕቆብም ላባን ለምን እንዲህ አደረግኸኝ ያገለገልሁህ ስለ ራኄል አልነበረምን ለምንስ አታለልከኝ አለው ።

፳፮ ወይቤሎ ላባ ኢኮነ ከመዝ በብሔርነሰ ኢይቀድሙ ውሂበ እንተ ትንእስ እንዘ ሀለወት እንተ ትልህቅ ።

ላባም ነገሩ እንዲህ አይደለም፥ በአገራችን ታላቂቱ ሳለች ትንሺቱን አይድሩም አለው ።

፳፯ ፈጽም ለዛቲኒ ሰብዓተ ዓመተ ወእሁበከ ኪያሃኒ በእንተ ዘትትቀነይ ሊተ ካልአ ሰብዓተ ዓመተ ።

ለዚችም ፯ቱን ዓመት ፈጽምና እርሷንም እሰጥሃለሁ ሁለተኛ ሰባት ዓመት የምትገዛልኝ ስለሆነ አለው ።

፳፰ ወገብረ ያዕቆብ ከማሁ ወፈጸመ ላቲኒ ሰብዓተ ዓመተ ወወሀበ ላባ ለያዕቆብ ራኄልሃ ።

ያዕቆብም እንዲህ አደረገ ለርሷም ፯ት ዓመት ተገዛለት፥ ላባም ለያዕቆብ ራኄልን ሰጠው ።

፳፱ ወወሀባ ለራኄል ባላሃ ትኩና አመተ ።

ላባ ለራኄል አገልጋይ ትሆናት ዘንድ ባላን ሰጣት ።

፴ ወቦአ ያዕቆብ ኀበ ራኄል ወአፍቀራ ፈድፋደ እምልያ ወተቀንየ ሎቱ ለላባ ካልአ ሰብዓተ ዓመተ በእንቲአሃ ።

ያዕቆብም ወደ ራኄል ገባ፥ ከልያም ይልቅ ፈጽሞ ወደዳት፥ ያዕቆብ ራኄልን ካገባም በኋላ ዳግመኛ ስለርሷ ፯ት ዓመት አገለገለው ። ሆሴ፥ ፲፪ ፲፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፴፩ | ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ ትጸላእ ልያ ፈትሐ ማኅፀና ፣ ወራሔልሰ ከነት መካነ ። | እግዚአብሔር ልያ በያዕቆብ ዘንድ እንደ ተጠላች ባየ ጊዜ ማኅፀኗን ከፈተላት ፣ ራሔል ግን መካን ሆነች ። |
| ፴፪ | ወፀንሰት ልያ ወወለደት ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ሮቤል እንዘ ትብል እስመ ርእየ እግዚአብሔር ትሕትናየ ፣ ወእምይእዜሰ ያፈቅረኒ ምትየ ። | ልያም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ስሙንም ሮቤል አለችው ፣ እግዚአብሔር መዋረዴን ስላየ ከእንግዲህስ ወዲህ ባሌ ይወደኛል ስትል ። ዘፀ፣ ፫ ፯ ። ዘዳ፣ ፳፮ ፯ ። |
| ፴፫ | ወዳግመ ፀንሰት ልያ ወወለደት ካልአ ወልደ ለያዕቆብ ወትቤ እስመ ሰምዐኒ እግዚአብሔር በእለትየ ከመ እጸላእ ወሰከኒ ዘንተ ፣ ወሰመየቶ ስሞ ስምዖን ። | ዳግመኛም ልያ ፀንሳ ለያዕቆብ ሌላ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፣ እግዚአብሔር እንደ ተጠላሁ አይቶ ለመናዬንም ሰምቶ ይህን ጨመረልኝ ስትል ስሙን ስምዖን አለችው ። |
| ፴፬ | ወፀንሰት ዳግመ ወወለደት ወልደ ወትቤ እምይእዜሰ ኀቤየ ውእቱ ምትየ እስመ ወለድኩ ሎቱ ሠለስተ ደቂቀ ፣ ወሰመየቶ ስሞ ሌዊ ። | ሦስተኛም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ሦስት ልጆች ወልጄለታለሁና እንግዲህስ ወዲህ ባሌ ወዳጄ ነው ስትል ስሙን ሌዊ አለችው ። |
| ፴፭ | ወፀንሰት ዳግመ ወወለደት ወልደ ወትቤ ይእዜ በእንተዝ አአምኖ ለእግዚአብሔር አምላክ ፣ ወበእንተዝ ሰመየቶ ስሞ ይሁዳ ፣ ወአቀመት ወሊደ ። | ደግሞም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ አራተኛ ልጅ ሰጥቶኛልና ስለዚህ ፈጣሪዬ እግዚአብሔርን አምነዋለሁ ስትል ስሙን ይሁዳ አለችው ፣ ከዚህ በኋላ መውለድን አቋረጠች ። |
| | **ምዕራፍ ፴ ።** | **ምዕራፍ ፴ ።** |
| ፩ | ወሶበ ርእየት ራሔል ከመ ኢወለደት ለያዕቆብ ቀንአት ላዕለ ልያ እኅታ ወትቤሎ ለያዕቆብ ሀበኒ ወልደ ወእመ አኮ እመውት ። | ራሔል ለያዕቆብ ልጅ እንዳልወለደችለት በየች ጊዜ በእኅቷ በልያ ላይ ቀናች ፣ ያዕቆብንም ወንድ ልጅ ስጠኝ አለበለዚያ እሞታለሁ አለችው ። ኢዮብ ፭ ፪ ። |
| ፪ | ወተምዓ ያዕቆብ ለራሔል ወይቤላ ከመ እግዚአብሔር ኑ አከውን አነ ዘአክልአኪ ፍሬ ከርሥኪ ። | ያዕቆብም የማኅፀንሽን ፍሬ የምነሣሽ እኔ እንደ እግዚአብሔር ነኝን ብሎ ራሔልን ተቈጣት ። ፩ ሳሙ፣ ፩ ፭ ። |
| ፫ | ወትቤሎ ራሔል ነያ አመትየ ባላ ሑር ባእ ኀቤሃ ወትለድ ዲበ አብራክየ ወእትወለድ አነሂ እምኔሃ ፣ ወወሀበቶ ባላሃ ትኩኖ ብእሲተ ። | ራሔልም ያዕቆብን እንዲህ አለችው ፤ እነሆ አገልጋዬ ባላ አለች ፣ ድረስባት በኔ ጭን ላይ ትውለድ ፣ እኔም ከርሷ በተወለደው ልጅ እዘመዳለሁ ብላ ሚስት ትሆነው ዘንድ ባላን ሰጠችው ። ዘፍ፣ ፲፮ ፪ ። |
| ፬ | ወቦአ ያዕቆብ ኀቤሃ ወፀንሰት ባላ ወወለደት ወልደ ለያዕቆብ ። | ያዕቆብም ባላን ቢደርስባት ፀንሳ ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት ። |
| ፭ | ወትቤ ራሔል ፈትሐ ሊተ እግዚአብሔር ወሰምዐኒ ቃልየ ወወሀበኒ ወልደ ፣ ወበእንተዝ ሰመየቶ ስሞ ዳን ። | ራሔልም እግዚአብሔር ፈረደልኝ ፣ ለመናዬንም ሰምቶ ወንድ ልጅ ሰጠኝ አለች ፣ ስለዚህም ስሙን ዳን አለችው ። መዝ፣ ፵፫ ፩ ። |
| ፮ | ወፀንሰት ዳግመ ባላ አመተ ራሔል ወወለደት ካልአ ወልደ ለያዕቆብ ። | የራሔል ገረድ ባላም ፀንሳ ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደችለት ። |
| ፯ | ወትቤ መጠቀኒ እግዚአብሔር ወመሰልክዋ ለእኅትየ ወኀየልክዋ ፣ ወሰመየቶ ስሞ ንፍታሌም ። | እግዚአብሔርም ከፍ ከፍ አደረገኝ እኅቴንም ተበራትቼ መሰልኋት ስትል ስሙን ንፍታሌም አለችው ። ማቴ፣ ፬ ፲፫ ። |
| ፰ | ወሶበ ርእየት ልያ ከመ ኢወለደት ወኀደገት ወሊደ ነሥአታ ለዘለፋ አመታ ወወሀበቶ ለያዕቆብ ትኩኖ ብእሲተ ። | ልያም እንዳልወለደች መውለድንም እንዳቆመች በየች ጊዜ ፣ አገልጋይዋ ዘለፋን ወስዳ ሚስት ትሆነው ዘንድ ለያዕቆብ ሰጠችው ። |
| ፱ | ወፀንሰት ዘለፋ ለያዕቆብ ወወለደት ወልደ ። | ዘለፋም ፀንሳ ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደች ። |
| ፲ | ወትቤ ልያ አብፃዕኩ አነኒ ፣ ወሰመየቶ ስሞ ጋድ ። | ልያም እኔም ብፅዕት ተባልኩ ስትል ስሙን ጋድ አለችው ። |
| ፲፩ | ወፀንሰት ዳግመ ዘለፋ ወወለደት ለያዕቆብ ። | ዳግመኛም ዘለፋ ፀነሰች ፣ ለያዕቆብም ወንድ ልጅ ወለደች ። |
| ፲፪ | ወትቤ ልያ ብፅዕት አነ ወያስተበፅዓኒ አንስት ፣ ወሰመየቶ ስሞ አሴር ። | ልያ እኔ ንእድት ክብርት ነኝ ፣ ሴቶችም ያከብሩኛል ስትል ስሙን አሴር አለችው ። ምሳ፣ ፴፩ ፳፰ ፣ ሉቃ፣ ፩ ፵፰ ። |
| ፲፫ | ወሖረ ሮቤል በመዋዕለ ማእረረ ሥርናይ ወረከበ ኮለ በሐቅል ወአምጽአ ላቲ ለእሙ ፣ ወትቤላ ራሔል ለልያ ሀብኒ ኮለ ዘወልድኪ ። | ሮቤልም የሥንዴ አዝመራ በሚታጨድበት ወራት ሂዶ ከበረኻ እንኮይን አግኝቶ ለናቱ አመጣላት ፣ ራሔልም ልያን የልጅሽን እንኮይ ስጪኝ አለቻት ። ዘፍ፣ ፳፭ ፴ ። |
| ፲፬ | ወትቤላ ልያ ኢአክለኪኑ ዘነሣእከኒ ምትየ ዳግመ ትፈ | ልያም ራሔልን ባሌ የወሰድሽብኝ አልበቃሽምን ደግ |

| | | |
|---|---|---|
| ቅዲ ትንሥእኒ ክለዘ ዘወልድየ ወትቤላ ራሔል ለልያ አኮ ከማሁ ለይቢት ዮም ኀቤኪ በእንተ ክሉ ዘወልድኪ ወወሀበታ ። | | ም ልጇ ያመጣውን እንኮይ ልትወስጂብኝ ትፈልጊያለሽን አለቻት፡ ራሔልም ልያን እንዲህ አይደለም ልጅሽ ያመጣውን እንኮይ ስለ ሰጠሽኝ ዛሬ ከንቺ ጋር ይደር ብላ ሰጠቻት ። ዘኍ፡ ፲፯ ፱ ። |
| ወአተወ ያዕቆብ እምሐቅል ፍና ሠርክ ወተቀበለቶ ልያ ፍና ሠርክ ወትቤሎ ኀቤየ ትበይት ዮም እስመ ተሣየጥኩከ በክል ዘወልድየ፡ ወቤተ ኀቤሃ በይእቲ ሌሊት ። | ፲፮ | ያዕቆብም ሲመሽ ከበረኻ ገባ፡ ልያም ማታ ሲመጣ ተቀበለችው፡ በልጄ እንኮይ ገዝቼሃለሁና ዛሬ ከኔ ጋር ታድራለህ አለችው፡ በዚያችም ሌሊት ከርሷ ጋር አደረ። |
| ወሰምዓ እግዚአብሔር ለልያ ወፀንሰት ወወለደት ወልደ ኃምሰ ። | ፲፯ | እግዚአብሔር የልያን ልመና ሰምቶ ፀንሳ አምስተኛ ወንድ ልጅ ወለደች ። |
| ወትቤ ልያ ወሀበኒ እግዚአብሔር ዐስብየ እስመ ወሀብክዋ ክለ ሐቅል ዘወልድየ፡ ወሰየመቶ ስሞ ይሳኮር፡ ዐስብ ብሂል ። | ፲፰ | ልያም ልጇ ያመጣውን የበረኻ እንኮይ ስለ ሰጠሁት እግዚአብሔር ዋጋዬን ሰጠኝ አለች፡ ስሙንም ይሳኮር አለችው ። |
| ወፀንሰት ዓዲ ልያ ወወለደት ወልደ ሳድሰ ለያዕቆብ። | ፲፱ | ልያም ዳግመኛ ፀንሳ ለያዕቆብ ስድስተኛ ወንድ ልጅ ወለደችለት ። |
| ወትቤ ልያ ፈትሐ ሊተ እግዚአብሔር ሠናየ ፍትሐ እምዮምሰ እንከ ያፈቅረኒ ምትየ እስመ ወለድኩ ሎቱ ስድስተ ደቂቀ፡ ወሰመየቶ ስሞ ዛብሎን ። | ፳ | ልያም እግዚአብሔር መልካም ፍርድ ፈረደልኝ ስድስት ልጆች ስለ ወለድኩለት እንግዲህስ ወዲህ ባሌ ይወደኛል ስትል ስሙን ዛብሎን አለችው ። |
| ወእምዝ ወለደት ወለተ ወሰመየታ ስማ ዲና ። | ፳፩ | ከዚህ በኋላ ሴት ልጅ ወለደች ስሚንም ዲና ብላ ጠራቻት ። |
| ወተዘከራ እግዚአብሔር ለራሔል ወፈትሐ ማኅፀና ። | ፳፪ | እግዚአብሔርም ራሔልን አሰበት ማኅፀኗንም ከፈተላት ። ፩ ሳሙ፡ ፩ ፲፱ ። ዘፍ፡ ፳፱ ፴፩ ። |
| ወፀንሰት ወወለደት ወልደ ለያዕቆብ ወትቤ አውፅአ እግዚአብሔር እምላዕሌየ ዝንጓጌየ ። | ፳፫ | ፀንሳም ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት፡ እግዚአብሔርም ስድቤን አስወገደልኝ አለች ። |
| ወሰመየቶ ስሞ ዮሴፍ፡ ወትቤ ይወስከኒ እግዚአብሔር ወልደ ካልአ ። | ፳፬ | ስሙንም ዮሴፍ አለችው፡ እግዚአብሔር ሁለተኛ ወንድ ልጅ ይጨምርልኝ ስትል ። ዘፍ፡ ፴፭ ፲፯ ። |
| ወሶበ ወለደት ራሔል ዮሴፍሃ ይቤሎ ያዕቆብ ለላባ ፈንወኒ ከመ እሖር ብሔርየ ወውስተ ምድርየ ። | ፳፭ | ራሔል ዮሴፍን በወለደች ጊዜ ያዕቆብ ላባን ወደ አገሬ ወደ ርስቴ እመለስ ዘንድ አሰናብተኝ አለው ። |
| ወሀበኒ ደቂቅየ ወአንስቲያየ ዘበእንቲአሆን ተቀነይኩ ለከ ወለሊከ ተአምር ዘከመ ተቀነይኩ ለከ ። | ፳፮ | ስለ እርሳቸው የተገዛሁልህ ልጆቼንና ሚስቶቼን ስጠኝ እንደተገዛሁልህም አንተ ታውቃለህ አለው። ዘፍ፡ ፳፱ ፳። |
| ወይቤሎ ላባ ለእመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ እስመ አእመርኩ ከመ ባረከኒ እግዚአብሔር በእንቲአከ ። | ፳፯ | ላባም በፊትህ በለሟልነትን ከገኘሁ በንተ ምክንያት እግዚአብሔር እንዳከበረኝ አውቃለሁና። ዘፍ፡ ፴፱ ፫ ፭። |
| ፍልጥ ሊተ ዐስበከ ዘእሁበከ ። | ፳፰ | የምሰጥህን ዋጋ ለይልኝ ። |
| ወይቤሎ ያዕቆብ ኢተአምርኑ ከመ ተቀነይኩ ለከ፡ ወሚመጠን እማንቱ እንስሳከ ዘኀቤየ ። | ፳፱ | ያዕቆብም የተገዛሁልህን አታውቅምን? ከኔ ዘንድ ያሉ ከብቶችህ ምን ያህል ነበሩ? ዘፍ፡ ፴፩ ፮። ማቴ፡ ፳፬ ፵፭። |
| እስመ ረከብከምን ኅዳጠ ወመልአ ወበዝኀ ወባረከ እግዚአብሔር በእግረ ዚአየ፡ ወይእዜኒ ማእዜኑመ እገብር አንሰ ቤተ ለርእስየ ። | ፴ | ጥቂቶች አልነበሩምን፡ አሁን ግን ፈጽመው በዝተዋል፡ በኔ መምጣት እግዚአብሔር አበዛቸው አሁንም እኔ ለራሴ ቤት ሠርቼ ጎጆ የምወጣ መቼ ነው? አለው ። |
| ወይቤሎ ላባ ምንተኑመ አሁበከ፡ ወይቤሎ ያዕቆብ አልቦ ዘትሁበኒ ወኢምንተኒ፡ ለእመ ገበርከ ሊተ ዘንተ ነገረ እርዒ ከዐበ አባግዒከ ወአዐቅብ ። | ፴፩ | ላባም የምሰጥህ ምንድር ነው? አለው፡ ያዕቆብም ምንም የምትሰጠኝ ነገር የለም፡ አሁን ወደ ፊት የምነግርህን ነገር ከደረግህልኝ ዳግመኛ በጎችህን ፈጽሜ እጠብቃለሁ ። ዘፍ፡ ፴፩ ፰ ። |
| ወይኅልፉ ኵሉን አባግዒከ ዮም ወፍልጥ ሊተ እምውስቴቶን ኵሉ በግዐ ዘፀዐዳ ጸጕሩ ወዘኰሳኵስ ኅብሩ ወፍጥረቱ ይኩነኒ ዐስብየ ። | ፴፪ | አሁን በጎችህ በፊት ይለፉና ከበጎችህ ሁሉ ጠጉራቸው ነጭ የሆኑትንና መልካቸው ዝንጕርጕር የሆነውንም ስለ ዋጋዬ ለይልኝ አለው ። |
| ወኵሉ ዘኢኮነ ኰሳኵስ ወዘኢኮነ ፀዐዳ ፍጥረቱ ለከ ይኩንከ ውእቱ ። | ፴፫ | ዓይነቱ ዝንጕርጕር ያልሆነውና መልኩ ነጭ ያልሆነው ሁሉ ግን ላንተ ይሁን አለው ። |
| ወይቤሎ ላባ ይኩን በከመ ትቤ ። | ፴፬ | ላባም እንዳልከው ይሁን አለው ። |
| ወፈለጠ በይእቲ ዕለት አብሓኰ አባግዕ ዘኰሳኵስ ወዘፀዐዳ ወኵሉ አብሓኰ አጣሊ ዘኰሳኵስ ወዘፀዐዳ ወዘ | ፴፭ | በዚያችም ቀን ነጩንም ቀዩንም ዝንጕርጕሩንም መልኩ ዳንግሌ የሆነውንም የፍየሉን አውራ ለይቶ |

ቀይሕ ኅብሩ ወወሀቦሙ ለደቂቁ ።
፴፮ ወርኀቀ ምሕዋረ ሠሉስ መዋዕል ማእከሎሙ ወማእከለ ያዕቆብ፣ ወያዕቆብሰ ይርዒ አባግዐ ላባ ዘተርፋ ።

፴፯ ወነሥአ ሎቱ ያዕቆብ በትረ ዘልብን ሐመልሚለ ወዘከርከዕ ዐቢየ ወለሐጸ ያዕቆብ ወአሰሰለ ቅርፍቶ ወአስተርአየ ፀዐዳሆን ለእማንቱ፤አብትር እለ ለሐጸ ።
፴፰ ወወደዮን ለእማንቱ አብትር ውስተ ገብላት ዘምስታየ ማይ ከመ ሶበ መጽአ እማንቱ አባግዕ ይስተያ ማየ ይኩና ቅድሜሆን እማንቱ አብትር ።
፴፱ ወሶበ መጽአ እማንቱ፤አባግዕ ወሰትያ ፀንሳ በአርአያሆን ለእማንቱ አብትር፣ ወወለዳ አባግዐ ፀዐዳ ወዘኅብረ ሐመድ ወኲሰኰስ ።
፵ ወቤጸ ያዕቆብ ተባዕተ አባግዒሁ ወፈለጠ አባግዐ ወአቀሞን ቅድመ አብሐኰ ፀዐዳ ወዘኅብረ ሐመድ ወፈለጠ መራዕየ እንተ ባሕቲቶን ወኢደመሮን ምስለ አባግዐ ላባ።

፵፩ ወእምዝ እንከ አመ መዋዕል በዘበቱ ይፀንሳ እማንቱ አባግዕ ይሠይሞን ያዕቆብ ለእማንቱ አብትር ቅድመ አባግዕ ውስተ ገብላት ከመ ይዕንሳ በአርአያሆን ለእማንቱ አብትር ።
፵፪ ወእምከመ ወለዳ እማንቱ አባግዕ ኢይሠይሞን እንከ ወከነ ኵሉ ዘበቱ ትእምርት ለያዕቆብ፣ ወዘአልቦ ትእምርት ለላባ ።
፵፫ ወብዕለ ያዕቆብ ጥቀ ፈድፋደ ወአጥረየ አግብርተ ወአእማተ ወብዙኀ እንስሳ አልሕምተ ወአባግዐ፣ አግማለ ወአእዱገ ።

ምዕራፍ ፴፩ ።

፩ ወሰምዐ ያዕቆብ ነገሮሙ ለደቂቀ ላባ ዘይቤሉ ነሥአ ያዕቆብ ኵሎ ንዋየ አቡነ ወእምንዋየ አቡነ አጥረዮ ለዝንቱ ኵሉ ክብር ።
፪ ወርእዮ ያዕቆብ ለላባ ከመ ኢኮነ ከመ ትካት ገጹ ምስሌሁ ።
፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ሑር ወግባእ ብሔረ አቡከ ወእዝማዲከ ወአነ እሄሉ ምስሌከ ።
፬ ወጸውዖን ያዕቆብ ለልያ ወለራኄል ውስተ ሐቅል ኀበ መርዓይ ።
፭ ወይቤሎን ናሁ አነ እሬኢ ገጾ ለአቡክን ከመ ኢኮነ ምስሌየ ከመ ትካት ወአምላኩ ለአቡየ ሀሎ ምስሌየ ።

፮ ተአምራ ከመ በኵሉ ኀይልየ ተቀነይኩ ለአቡክን ።

፯ ወአቡክንሰ አኅዘነኒ ወወለጠ ዐስብየ ዓሥርተ ጊዜ፣ ወኢያብሖ እግዚአብሔር ያኅሥም ላዕሌየ ።

፰ ወለእመ ይቤለኒ ዘኅብር ይኩን ዐስብከ ይወልዳ ኵሎን አባግዕ ዘኅብር፣ ወለእመ ይቤለኒ ፀዐዳ ይኩን ዐስብከ

ለልጆቹ ሰጣቸው ።
በነሱና በያዕቆብ መካከል ሦስት ቀን የሚያስኬድ ጉዳና ርቀው ሄዱ፣ ያዕቆብ ግን የቀሩትን የላባ በጎች ይጠብቅ ነበር ። ዘፍ፡ ፴፩ ፱ ።
ያዕቆብ የልምጭ በትርና ታላቅ የሎሚ በትር ወስዶ ቅርፍቱን ልጦ ጣለው፣ ያዕቆብ የላጣቸው በትሮች ነጫጭ ሁነው ታዩ ።
እነዚያንም በትሮች በጎች ከሚጠጡበት ገንዳ ላይ ጣላቸው፣ በጎቹ ውኃ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ እነኛ በትሮች በፊታቸው ሆነው ይታዩ ዘንድ ።
መጥተውም በጠጡ ጊዜ እነዚያን በትሮች አስመስለው ፀንሰው ነጩንና ሐመደ ክበውን ዝንጕርጕሩን ወለዱ ።

ያዕቆብም አውራ አውራዎቹን በጎች ለየ አውራ አውራውን ከለየ በኋላ እንስት እንስቲቱን በጎች ለይቶ ዝንጕርጕር ሐመደ ክበና ነጭ በሚሆኑ አውራዎች ፊት አቆማቸው፣ የራሱንም በጎች ለብቻቸው ለየ እንጂ ከላባ በጎች ጋር አልጨመራቸውም ።
ከዚህ በኋላ በጎቹ በሚፀንሱበት ወራት ያዕቆብ እሊያን በትሮች በበጎቹ ፊት ለፊት በገንዳው ውስጥ ያኖራቸው ነበር፣ እሊያን በትሮች አስመስለው ይፀንሱ ዘንድ።

በጎቹ ከወለዱ በኋላ ግን እሊያን በትሮች በገንዳው ላይ አያኖራቸውም ነበር፣ ምልክት ያለው ሁሉ ለያዕቆብ፣ ምልክት የሌለው ለላባ ሆነ ።
ያዕቆብ እጅግ ፈጽሞ በለጸጋ ሆነ ሴቶችም ወንዶችንም አገልጋይዎች ገዛ፣ ብዙ ከብት ላሞችንም በጎችንም ግመሎችንና አህዮችን ገዛ ። ኢዮብ ፩ ፫ ። መክ፡ ፪ ፯ ።

ምዕራፍ ፴፩ ።

ያዕቆብ የላባ ልጆች፣ የአባታችን የላባን ገንዘብ ሁሉ ወሰደው ከአባታችን ገንዘብ የተነሣ ይህን ሁሉ ክብር አገኘ ያሉትን ሰማ ። ኢዮብ ፳ ፱ ። ምሳ፡ ፲፬ ፴ ።
ያዕቆብ የላባ ፊቱ እንደ ቀድሞው ከሱ ጋር እንዳ ይደለ አየው ።
እግዚአብሔርም ያዕቆብን እኔ ከንተ ጋር አለሁና ወደ አባትህና ወደ ዘመዶችህ አገር ተመልሰህ ግባ አለው ።
ያዕቆብ ልያንና ራኄልን በጎቹን ወደ ሚያሠማራበት በረኻ ጠራቸው ። ዘፍ፡ ፳፰ ፲፭ ።
እነሆ እኔ የአባታችሁ ፊት እንደ ቀድሞው ከኔ ጋር እንዳልሆነ አያለሁ የአባቴ ፈጣሪ ግን ከኔ ጋር አለ አላቸው ። ኢሳ፡ ፵፩ ፣ ። ዕብ፡ ፲፫ ፭ ።
እኔ በሙሉ ጉልበቴ ለአባታችሁ እንዳገለገልኩ ታውቃላችሁ ። ዘፍ፡ ፴ ፳፱ ።
አባታችሁ ግን አሥር ጊዜ ያገለግሎቴን ዋጋ እየለዋወጠ አሳዘነኝ፣ እግዚአብሔር ግን በኔ ላይ ክፉ እንዲያደርግ አላሠለጠነውም ። ኢዮብ ፲፱ ፫ ። ምሳ፡ ፴ ፭ ።
ዝንጕርጕር ሲወለድ ዋጋህ ይሁን ቢለኝ በጎቹ ሁሉ ዝንጕርጕር ይወልዳሉ፣ ዋጋህ ነጭ ይሁን ቢለኝ ሁሉም

ይወልዳ ኵሉን ዐበዳ ።
፱ ወነሥአ እግዚአብሔር ኵሎ አበግዒሁ ለአቡክን ወወ
ሀበኒዮን ሊተ ።
፲ ወእምዝ አመ ይፀንሳ እሬኢ በአዕይንትየ በሕልም
መናሁ አብሐኦ ዘአበግዕ ወዘአጣሊ የዐርጉ ዲበ አበግዕ
ወዲበ አጣሊ ዐበዳ ወዘኅብረ ሐመድ ወዘኰሳኵስ ።

፲፩ ወይቤለኒ እግዚአብሔር በሕልም "ያዕቆብ ያዕቆብ"
ወእቤ ነየ አነ ምንትኑ ።
፲፪ ወይቤለኒ ነጽር በአዕይንቲከ ወርኢ አብሐኦ ዘአበ
ግዕ ወዘአጣሊ የዐርጉ ዲበ አበግዕ ወዲበ አጣሊ ዐበዳ
ወዘኅብረ ሐመድ ወዘኰሳኵስ እስመ ርኢኩ ኵሎ ዘይገ
ብር ላዕሌከ ላባ ።
፲፫ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአስተርአይኩከ
በብሔር በኀበ ቀባእከ ሊተ ሐውልተ ወበሀየ በፃዕከ ሊተ
ብፅዓተ ፤ ወይእዜኒ ተንሥእ ወሑር ውስተ ብሔር ኀበ
ተወለድከ ወአነ እሄሉ ምስሌከ ።
፲፬ ወአውሥኦሁ ወይቤልዎ ቦኑ እንከ ዘብነ ርስት ውስተ
ቤተ አቡነ ።
፲፭ አኮኑ ከመ ነኪር ንሕነ በኀቤሁ ወሤጠነ ወበልዐ
ሤጠነ ።
፲፮ ወዝ ኵሉ ክብር ዘነሥአ እግዚአብሔር እምአቡነ ለነ
ውእቱ ወለውሉድነ ፤ ወይእዜኒ ግበር ኵሎ ዘይቤለከ
እግዚአብሔር ።
፲፯ ወተንሥአ ያዕቆብ ወነሥአ አንስቲያሁ ወደቂቆ ወጸ
ዐኖሙ ዲበ አግማል ።
፲፰ ወነሥአ ኵሎ መራዕይሁ ወቍሳቍሳቲሁኒ ዘአጥረየ
በማእከለ አፍላግ ወኵሎ ዘዚአሁ ወሖረ ኀበ አቡሁ ይስ
ሐቅ ውስተ ምድረ ከነአን ።
፲፱ ወላባሰ ሖረ ኀበ ይቀርፅ አበግዒሁ ወሰረቀት ራሔል
አማልክተ አቡሃ ።
፳ ወያዕቆብሰ ኀብአ ለላባ ሶርያዊ ወኢያይድዖ ከመ
የሐውር ።
፳፩ ወሖረ ውእቱ ወኵሉ ዘዚአሁ ወዐደወ ፈለገ ወኀደረ
በደብረ ገለዓድ ።
፳፪ ወዜነውዎ ለላባ ሶርያዊ ከመ ሖረ ያዕቆብ ።
፳፫ ወነሥአሙ ላባ ለኵሎሙ አኀዊሁ ወዴገኖሙ ምሕ
ዋረ ሠሉስ መዋዕል ወረከቦሙ በደብረ ገለዓድ ።
፳፬ ወመጽአ እግዚአብሔር ኀበ ላባ ሶርያዊ በሕልም ሌሊ
ተ ወይቤሎ ዑቅ ኢትንብብ ኅሡመ ላዕለ ያዕቆብ ገብርየ ።

፳፭ ወረከበ ላባ ለያዕቆብ ፤ ወያዕቆብሰ ይተክል ሐይመቶ
ውስተ ደብር ወአቀሞሙ ላባ ለአኃዊሁ ውስተ ደብረ
ገለአድ ።
፳፮ ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ ምንተ ገበርከ ጽሚተ ዘትትኀ
ጥአኒ ወትሰርቀኒ አዋልድየ ከመ ዘበኵናት ፄዉወ ።

፳፯ ወሶበ ነገርከኒ እምፈነውኩከ በትፍሥሕት ወበኃሤት
ወበማኅሌት ወበከበሮ ወበመሰንቆ ።

ነጭ ይወልዳሉ ። ዘፍ፣ ፴ ፴፪ ።
እግዚአብሔር ያባታችሁን በጎች ሁሉ ለይቶ ለኔ
ሰጠኝ ።
ከዚህም በኋላ በሚፀንሱበት ጊዜ እነሆ የበጎቹ አውራ
ዎች ከበጎቹ የፍየሎቹም አውራዎች ከፍየሎቹ በነጩም
በሐመዱ ከበውም በዝንጕርጕሩም ላይ ሲንጠላጠሉ በሕ
ልም በዓይኔ አያለሁ ።
እግዚአብሔር በሕልም "ያዕቆብ ያዕቆብ" ብሎ ጠ
ራኝ ፤ እኔም እነሆ እኔ አለሁ ፤ ምንድር ነው ፤ አልኩ ።
የበጎቹ አውራዎች ከበጎቹ የፍየሎቹ አውራዎች ከፍ
የሎቹ በነጩም በዝንጕርጕሩም በሐመዱ ከበውም ላይ
ሲንጠላጠሉ በዓይንህ ተመልከት ፤ ላባ በአንተ ላይ የሚያ
ደርገውን ሁሉ አይቻለሁና አለኝ። ዘፀ፣ ፫ ፯። መዝ፣ ፲፪ ፭።
ዘይት ያፈሰስክበትን ድንጊያ ባቆምክበት ለኔም ስለ
ትን በተሳልክበት በታ የታየሁህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር
እኔ ነኝ ፤ አሁንም ከዚህ ተነሥተህ ወደ ተወለድክበት
አገር ሂድ ፤ እኔም ካንተ ጋር እኖራለሁ አለኝ አላቸው ።
እነሱም እንዲህ ብለው መለሱለት ፤ እንግዲህ ወዲህ
በአባታችን ቤት የምናገኘው ርስት በውኑ አለን ?
በርሱ ዘንድ እንደ ባዕድ አይደለንምን ፤ እኛንስ ሸጠ
ዋጋችንን የበላ አይደለምን ! ።
ይህ ሁሉ ሃብት እግዚአብሔር ከአባታችን ነሥቶ የሰ
ጠህ ለኛም ለልጆቻችንም ነው ፤ አሁንም እግዚአብሔር
ያለህን አድርግ አሉት ።
ያዕቆብም ሚስቶቹን ይዞ ልጆቹን በግመሎች ጭኖ
ተነሣ ።
በሁለቱ ወንዞች መካከል ባለው በሶርያ ያፈራቸው
መንጋዎቹን ታላላቁንና ታናናሹን ገንዘቡን ሁሉ ይዞ ወደ
አባቱ ወደ ይስሐቅ ወደ ከነናን አገር ሄደ ። ዘፍ፣ ፴፭ ፱ ።
ላባ ግን በጎቹ ወደሚሸልትበት በታ ሂዶ ነበር ፤ ራኄ
ልም ያባቷን ጣኦቶች ሰረቀች ።
ያዕቆብም ለሶርያው ሰው ለላባ ሠወረው እንጂ እንደ
ሚሄድ አልነገረውም ነበር ።
እሱም የሱንም ወገኖች ሁሉ ይዞ ሄደ ፤ ወንዙንም
ተሻግሮ በገለአድ ተራራ አደረ ።
ለሶርያዊው ላባም ያዕቆብ እንደ ሄደ ነገሩት ።
ላባም ወንድሞቹን ሁሉ ይዞ የሦስት ቀን ጐዳና ተከ
ትሎ በገለአድ ተራራ አገኛቸው ።
እግዚአብሔርም ሌሊት በሕልም ወደ ሶርያዊው ሰው
ወደ ላባ መጥቶ ፤ በወዳጄ በያዕቆብ ላይ ክፉ ነገር እንዳት
ናገር ተጠንቀቅ አለው ። ዘፍ፣ ፳ ፫ ። ማቴ፣ ፩ ፳ ።
ላባም ያዕቆብን አገኘው ፤ ያዕቆብ ግን ድንኳኑን በተ
ራራው ላይ ተክሎ ሰፍሮ ነበር ፤ ላባም ወንድሞቹን በገለ
አድ ተራራ ላይ አቁሟቸው ሄደ ።
ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው ፤ ተሠውረኸኝ ኰብልለህ
የመጣህ ምን አደረግሁህ በጦር እንደ ማረከ ሰው ፤ ልጆቼ
ንስ ለምን ሰረቅኸኝ ? አለው ። ፩ ሳሙ፣ ፴ ፪ ።
ነግረኸኝስ ቢሆን በፍጹም ደስታ በዘፈን በጩዋታ
ከበሮውን መሰንቆውን እያስመታሁ በሸኘሁህ ነበር ።

| | | |
|---|---|---|
| ወሚመ ኢይደልወኒኑ ከመ እስዐም ደቂቅየ ወአዋልድየ፣ ወይእዜሰ ከመ ዐብድ ገበርከ። | ፳፰ | ወይስ ወንዶች ልጆቼን ሴቶች ልጆቼን ስሜ ሸኝቼ መሰናበት አይገባኝም ነበርን፣ አሁንም እንደ አላዋቂ ሰው ሥራ ሠርተሃል ። ፩ ነገ፣ ፲፱ ፳ ። |
| ወይእዜኒ እምክህልኩ ገቢረ እከይ ላዕሌከ ወባሕቱ አምላከ አቡከ ይቤለኒ ትማልም ዑቅ ርእሰከ ኢትግበር ጎሡመ ላዕለ ያዕቆብ ። | ፳፱ | አሁንም ባንተ ላይ ክፉ ነገር ላደርግ በተቻለኝ ነበር፣ ነገር ግን ያባትህ ፈጣሪ ትናንት በያዕቆብ ላይ ክፉ እንዳ ትሠራ ስራስህ ተጠንቀቅ ብሎ ቢነግረኝ ነው እንጂ ። |
| ወይእዜኒ ሑር እመ ፈተውከ ከመ ትሑር ቤተ አቡከ ወለምንት ትሰርቀኒ አማልክትየ ። | ፴ | አሁን ግን ወደ አባትህ ቤት መሄድን ከወደድክ ሂድ አለው፣ በዚያውስ ላይ አማልክቶቼን ለምን ሰረቅኸኝ፣ አለው ። |
| ወአውሥአ ያዕቆብ ወይቤሎ ለላባ እስመ መሰለኒ ዘተኀይደኒ አዋልዲከ ወኵሎ ንዋይየ፣ ወይእዜኒ ርኢ ለእመ ቦ ንዋይከ ኀቤየ ወንሣእ፣ ወበኀበ ዘረከብከ አማልክቲከ ኢይሕየው ። | ፴፩ | ያዕቆብም ለላባ እንዲህ ሲል መለሰለት ፤ ልጆችህን ገንዘቤንም ሁሉ የምትቀማኝ ስለ መሰለኝ ነው፣ አሁንም ገንዘብህ ከኔ ዘንድ እንዳለ አይተህ ውሰድ አለው፣ ጣኦቶችህን ያገኘህበትም ሰው አይዳን ። መሳ፣ ፲፰ ፳፬ ። |
| ወኖሁ አሰምዐ ለከ በቅድመ አኀዊነ ወኢያእመረ ያዕቆብ ከመ ሰረቀት ራኄል ። | ፴፪ | እነሆ ያንተ የሆነው ገንዘብ ከኔ ዘንድ ቢገኝ በነዚህ ወንድሞቻችን ፊት አዳኝብሃለሁ ያዕቆብ ግን ራኄል እንደ ሰረቀች አላወቀም ነበር ። ዘፍ፣ ፵፬ ፱ ። |
| ወቦአ ላባ ቤተ ያዕቆብ ወኢረከበ፣ ወወፅአ ወቦአ ቤተ ልያ ወፈተነ ወኢረከበ፣ ወቦአ ቤተ ክልኤሆን ዕቁባቲሁ ወኢረከበ፣ ወቦአ ቤተ ራኄል ። | ፴፫ | ላባም ከያዕቆብ ቤት ገብቶ አላገኘም፣ ከዚያም ወጥቶ ወደ ልያ ቤት ገብቶ ቢበረብር ምንም አላገኘም፣ ከሁለቱ ዕቁባቶቹም ቤት ገብቶ በረበረ ነገር ግን ምንም አላገኘም፣ ራኄል ከለችበትም ቤት ገባ ። |
| ወራኄልሰ ነሥአቶሙ ለአማልክተ አቡሃ ወወደየቶሙ ውስተ ሕንባለ ገመል ወነበረት ላዕሌሆሙ ። | ፴፬ | ራኄል ግን ያባቷን ጣኦቶች ሠርቃ ከግመል ኮርቻ ውስጥ አግብታ በላዩ ላይ ተቀምጣ ነበር ። ቊ፣ ፲፱ ። |
| ወትቤሎ ለአቡሃ ኢይምሰልከ ዘአስተሐቀርኩከ እግዚእየ እስመ ኢይክል ተንሥኦ ቅድሜከ እስመ ትክት አነ ወፈተነ ላባ ኵሎ ቤታ ለራኄል ወኢረከበ አማልክቲሁ ። | ፴፭ | አባቴ ከግዳጄ ስላልነሳሁ በፊትህ መነሣት አልቻልምና ነው እንጂ ያቃለልኩህ አይምሰልህ አለችው፣ ላባም የራኄልን ቤት ሁሉ በረበረ፣ ነገር ግን ጣኦቶቹን አላገኘም ። |
| ወተምዐ ያዕቆብ ወተባከዮ ለላባ ወይቤሎ ምንትኑ አበሳየ ወምንትኑ ጌጋይየ ዘዴገንከኒ ወፈተንከኒ ኵሎ ንዋይየ ። | ፴፮ | ያዕቆብም ተቈጥቶ ላባን እንዲህ ሲል ተከራከረው፣ ገንዘቤን ሁሉ የበረበርክብኝና የተከተልከኝ በደሌ ዕዳዬ ምንድር ነው፤። ፩ ሳሙ፣ ፲፱ ፫ ። ፩ ቆሮ፣ ፯ ፭ ። |
| ወምንተ ረከብከ እምነ ቊሳቊስ ቤትከ ናስተአኀዝኑ ቅድመ እሉ አኀዊነ ወይግዝልፉ ማእከሌነ ። | ፴፯ | ከቤትህስ ቊሳቊስ ዕቃ ምን አገኘህ፤ በነዚህ ወንድሞቻችን ፊት እንዋቀስና በመካከላችን ይፍረዱን ። |
| ዕሥራ ወክልኤ ዓመት ሊተ እንዘ እፀቅብ አባግዒከ ወአጣሊከ ወኢመሐስአ በግዐ ኢበላዕኩ እምአባግዒከ ። | ፴፰ | ሃያ አንድ ዓመት በጎችህንና ፍየሎችህን ስጠብቅ ኖርኩ ከበጎችህም ጠቦት እንኳ አልበላሁም ። ዘፀ፣ ፳፪ ፲፱። |
| ወብላዐ አርዌኒ ኢያምጻእኩ ለከ፣ ወእፈድየከ እምኀቤየ እመኒ ቦ ዘተሰርቀ፣ እመኒ መዓልተ ወእመኒ ሌሊተ በጠል እበይት፣ ወነፍጸ ንዋም እምአዕይንትየ ። | ፴፱ | አውሬ የነከሰውንም ትራፊ አላመጣሁልህም፣ የተሰረቀም ቢኖር ከኔ እከፍልህ ነበር፣ በቀንም በሌሊትም በጤዛ ተነክሬ እኖር ነበር፣ እንቅልፍ ከዓይኖቼ ጠፍቶ ይኖር ነበር ። |
| ዕሥራ ወክልኤ ዓመት ሊተ ዮም ውስተ ቤትከ ዘተቀነይኩ ለከ ። | ፵ | በቤትህ የተገዛሁልህ ዛሬ ሃያ አንድ ዓመት ነው ። ዘፍ፣ ፴፩ ፵፩ ። |
| ዓሥርተ ወአርባዕተ ዓመተ ተቀነይኩ ለከ በእንተ ክልኤሆን አዋልዲከ፣ ወሰብዓተ ዓመተ በእንተ አባግዒከ ወአኅለፍከ ብየ ዐሥብየ ዓሥርተ ጊዜ ። | ፵፩ | ስለ ሁለቱ ልጆችህ ዓሥራ አራት ዓመት ተገዛሁልህ፣ ስለ በጎችህም ፯ት ዓመት ተገዛሁልህ ዋጋዬንም ዓሥር ጊዜ ለዋወጥክብኝ ። ዘፍ፣ ፳፱ ፳፯ ። መዝ፣ ፻፳፱ ፩ ። |
| ወሰበ አኮ አምላከ አብርሃም አቡየ ዘሀሎ ምስሌየ ወሰበ አኮ በፍርሀተ ይስሐቅ ዕሩቅየ እምፈነውከኒ ወርእየ እግዚአብሔር የማሆን ለእደውየ ወገሠፀከ ትማልም ። | ፵፪ | ያባቴ የአብርሃም ፈጣሪ ከኔ ጋር ባይኖር፣ በአባቴ ይስሐቅ አምልኮት ጸንቼ ባልኖር ባዶዬን በሰደድኸኝ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን የእጆቼን ድካም አይቶ ትናንት በሕልም ገሠፀህ ። |
| ወአውሥአ ላባ ለያዕቆብ ወይቤሎ ደቂቅከኒ ደቂቅየ ወአዋልዲከኒ አዋልድየ፣ ወእንስሳከኒ እንስሳየ ወዝ ኵሉ ዘትሬኢ ዚኣየ ውእቱ ለአላ አዋልድየ ምንተ እንከ እሬስዮን ሎቶን ዮም ወለውሉዶንሂ ዘወለዳ ። | ፵፫ | ላባም ለያዕቆብ እንዲህ ሲል መለሰለት ፤ ወንዶቹም ሴቶቹም ልጆችህ ልጆቼ፣ ከብቶችህም ከብቶቼ ናቸው፣ ይህ የምታየው ሁሉ የኔ ገንዘብ ነው፣ እንግዲህ እሊህ ልጆቼን አሁን ምን አደርጋቸዋለሁ ፤ የወለዱዋቸው ልጆ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ቻቸውንስ ምን አደርጋቸዋለሁ ፤ |
| ወይእዜኒ ነዓ ንትማሐል አነ ወአንተ ወይኩን ሰላም ማእከሌየ ወማእከሌከ ። | ፵፬ | አሁንም እኔና አንተ እንማማል ፣ በኔና በንተ መካከል ሰላም ይሁን አለው ። ዘፍ፡ ፳፮ ፳ ። ኢያሱ ፳፬ ፳፯ ። |
| ወነሥአ ያዕቆብ እብነ ወአቀመ ሐውልተ ። | ፵፭ | ያዕቆብም ድንጊያን አንሥቶ ሐውልት አቆመ ። |
| ወይቤሎሙ ያዕቆብ ለአኀዊሁ አልዱ አእባነ ፣ ወአለዱ ወገብሩ ወግረ ወበልዑ ወሰትዩ ዲበ ይእቲ እብነ ወግር ፣ ወይቤሎ ላባ ዛቲ ወግር ስምዕ ማእከሌየ ወማእከሌከ ። | ፵፮ | ያዕቆብ ወንድሞቹን ድንጊያ ሰብስቡ ብሎአቸው ሰብስበው ክረብታን ያህል ከመሩ ፣ ሰብስበው በክምሩትም ድንጊያ ላይ ተቀምጠው በሉ ጠጡ ፣ ላባም ይህች ክረብታ በኔና በአንተ መከከል ምስክር ናት አለው ። |
| ወሰመያ ላባ "ወግረ ስምዕ" ወያዕቆብኒ ሰመያ ከማሁ ። | ፵፯ | ክረብታይቱንም "የምስክር ተራራ" ብሎ ጠራት ያዕቆብም እንዲሁ የምስክር ተራራ ብሎ ጠራት ። ኢያ፡ ፳፬ ፳፯፥ |
| ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ ነያ ዛቲ ወግር እንተ አቀውም ስምዕ ማእከሌየ ወማእከሌከ ፣ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስማ "ወግረ ስምዕ" ። | ፵፰ | ላባም ያዕቆብን ይህች ያቆምኳት ሐውልት በኔና በንተ መከከል የምስክር ሐውልት ትሁን አለው ፣ ስለዚህም ስሟ "የምስክር ክረብታ" ተባለች ። ኢያሱ፡ ፳፬ ፳፯ ። |
| ወይቤሎ ላባ ራእየ ዘአስተርአየኒ እግዚአብሔር ይርአይ ማእከሌየ ወማእከሌከ ዮም እስመ ንትራኃቅ አሐዱ እምካልኡ ። | ፵፱ | ላባ ያዕቆብን በራእይ የተነጋገረኝ እግዚአብሔር ዛሬ በኔና በንተ መካከል ምስክር ነው ፣ እርስ በርሳችን አንዱ ከንዱ ተራርቀን እንኖራለንና ። መሳ፡ ፲፩ ፳፱ ። |
| ከመ ኢትሣቅዮን ለአዋልድየ ወከመ ኢትንሣእ ብእሲተ ላዕሌሆን ። | ፶ | በላያቸው ላይ ሴት አግብተህ ልጆቼን እንዳታሳዝናቸው በኔና በንተ መከከል እግዚአብሔር ይፍረድ አለው ። |
| ወርኢ ናሁ አልቦ ዘሀሎ ምስሌነ ። | ፶፩ | አሁን ከኛ ጋር ሌላ ሰው እንደሌለ አስተውል ። |
| አመኒ ዐዶኩ ኀቤከ ዛቲ ወግር ወዛቲ ሐውልት ትትልወኒ በእኪት ። | ፶፪ | እኔ መሐላዬን አፍርሼ በክፋት ወዳንተ ብሻገር ይህች ተራራና ሐውልት በክፋት ትከተለኝ ። |
| ወአንተኒ ለእመ ዐዶከ ኀቤየ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ናኮር ይፍታሕ ማእከሌየ ወማእከሌከ ፣ ወመሐለ ሎቱ ያዕቆብ በፍርሀተ ይስሐቅ አቡሁ ። | ፶፫ | አንተም መሐላህን አፍርሰህ በክፋት ወደኔ ብትመጣ የአብርሃምና የናኮር ፈጣሪ በኔና በንተ መከከል ይፍረድ አለው ፣ ያዕቆብም አባቱ ይስሐቅ በሚያመልከው በእግዚአብሔር ስም ማለ ። ዘፍ፡ ፲፯ ፰ ። |
| ወሦዐ ያዕቆብ መሥዋዕተ በውስተ ደብር ወጸውዖሙ ለአኀዊሁ ወበልዑ ወሰትዩ በቤቱ ፣ ወቤቱ ውስተ ውእቱ ደብር ። | ፶፬ | ያዕቆብ በተራራው ላይ መሥዋዕትን ሠውቶ ወንድሞቹን በቤቱ ጠርቶ በልተው ጠጥተው በዚያው ተራራ ላይ አደሩ ። |
| ወተንሥአ ላባ በጽባሕ ወሰዐመ አዋልዲሁ ወደቂቆን ወባረኮሙ ፤ ወተመይጠ ላባ ብሔሮ ወሖረ ። | ፶፭ | ላባም ማለዳ ተነሥቶ ልጆቹን የልጅ ልጆቹን ስሞና መርቆ ተመልሶ ወደ አገሩ ሄደ ። |

ምዕራፍ ፴፪ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወያዕቆብኒ ገብአ ውስተ ፍኖቱ ፣ ወነጸረ በአዕይንቲሁ ያዕቆብ ወርእየ ተዐይነ እግዚአብሔር ኀዱራነ ወተራከብዎ መላእክተ እግዚአብሔር ። | ፩ | ያዕቆብም ወደ መንገዱ ተመለሰ ፣ ያዕቆብ በዓይኖቹ ተመልክቶ የእግዚአብሔርን ሠራዊት ከትመው አየ ፣ የእግዚአብሔር መላእክትም ተገናኙት ። መዝ፡ ፺፩ ፲፩ ። |
| ወይቤ ያዕቆብ ሶበ ርእየ ተዐይነ እግዚአብሔር ይእቲ ዛቲ ፣ ወሰመየ ስሞ ለውእቱ ብሔር ተዐይን ። | ፪ | ያዕቆብም ይህን በየ ጊዜ ይህች የእግዚአብሔር ከተማ ናት አለ ፣ የዚያን ቦታ ስም የእግዚአብሔር ከተማ ብሎ ጠራ ። መዝ፡ ፺፫ ፳፩ ። |
| ወፈነወ ያዕቆብ ሐዋርያተ ኀበ ዔሳው እኁሁ ብሔረ ሴይር ውስተ ምድረ ኤዶም ። | ፫ | ያዕቆብ በኤዶም ውስጥ ወዳለች ወደ ሴይር ከወንድሙ ዘንድ መልእክተኛ ላከ ። ዘዳ፡ ፪ ፭ ። ኢያሱ፡ ፳፬ ፬ ። |
| ወአዘዞሙ ወይቤሎሙ ከመዝ በልዎ ለዔሳው እግዚእየ ፣ ከመዝ ይቤ ገብርከ ያዕቆብ ኀበ ላባ ነበርኩ ወጐንደይኩ እስከ ዮም ። | ፬ | ጌታዬ ዔሳውን አገልጋይህ ያዕቆብ ከላባ ዘንድ እኖር ነበር ፣ እስከ ዛሬ ድረስም ዘገየሁ በሉት ብሎ አዘዛቸው ። ምሳ፡ ፲፭ ፩ ። |
| ወአጥረይኩ አግብርተ ወአእማተ ወአልሕምተ ወአባግዐ ፣ አግማለ ወአእዱገ ወፈነውኩ ይዜንውዎ ለእግዚእየ ዔሳው ከመ እርከብ ሞገሰ በቅድሜከ አነ ገብርከ ። | ፭ | ወንዶችም ሴቶችም አገልጋዮች ፣ ላሞችም አህዮችም ግመሎችም አገኘሁ ፣ እኔ አገልጋይህ በፊትህ ባለሟልነትን አገኝ ዘንድ ለጌታየ ለዔሳው ሊነግሩት ዘንድ ላክሁ ። |
| ወገብኡ ኀቤሁ ለያዕቆብ እሙንቱ ሐዋርያት እለ ፈነወ ወይቤልዎ ሖርነ ኀበ ዔሳው እኁከ ወናሁ መጽአ ይትቀበልከ ወአርባዕቱ ምእት እደው ምስሌሁ ። | ፮ | የላካቸውም መልእክተኞች ተልእኳቸውን አድርሰው ወደ ያዕቆብ ተመለሱ ፣ ወደ ወንድምህ ወደ ዔሳው ሂደን የላክኸንን ነገርነው ፣ እሱም አሁን አራት መቶ ሰው |

| | | |
|---|---|---|
| | | አስከትሎ ሊቀበልህ መጥቷል። ዘፍ፣ ፴፫ ፩። |
| ወፈርሀ ጥቀ ያዕቆብ ወኀጥአ ዘይገብር ወነፈቆሙ ለሕዝብ እለ ምስሌሁ ወለአባግዕኒ ወለአልሕምትኒ ወለአግማልኒ ወገብሮሙ ክልኤተ ትዕይንተ። | ፯ | ያዕቆብም እጅግ ፈርቶ ተጨንቀ የሚያደርገውን አጣ ከሱ ጋር ያሉትን ከሁለት ከፈላቸው፣ ላሞችንም በጎችንም ግመሎችንም ሁለት ሁለት ወገን አድርጎ ከፈላቸው። |
| ወይቤ ያዕቆብ ለእመ መጽአ ዔሳው ውስተ አሐቲ ትዕይንት ወቀተላ ትድኅን ክልእት ትዕይንት። | ፰ | ያዕቆብ ዔሳው መጥቶ አንዲቱ ሰፈር ቢያጠፋ አንዲቱ ሰፈር ትድናለች ብሎ ከሁለት ወገን ከፈላቸው። |
| ወይቤ ያዕቆብ ውእቱ አምላክ አቡየ አምላክ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ዘይቤለኒ ሑር ውስተ ብሔር ኀበ ተወለድኩ ወአነ አሤኒ ላዕሌከ ያሤኒ እንከሰ ላዕሌየ። | ፱ | ወደ ተወለድክበት አገር ሂድ ላንተ በጎ ነገርን አደርግልሃለሁ ያለኝ ያባቶቼ የአብርሃም የይስሐቅ ፈጣሪ እግዚአብሔር እሱ በጎ ነገርን ያደርግልኛል አለ። መዝ፣ ፶ ፲፩። |
| ወበኵሉ ጽድቅ ወርትዕ ዘገበርከ ለገብርከ ረከብኩ፣ እስመ በበትርየ ዐደውክዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ወይእዜሰ ክነኩ ክልኤተ ተዐይነ። | ፲ | ከዚህም በፊት ለኔ ላገልጋይህ በደረግኸው ቸርነትና ቅንነት ሁሉ በለሟልነትን አግኝቻለሁ፣ ይህን ዮርዳኖስን ከበትሬ ጋር ተሻግሬው ነበርና ዛሬ ግን ሁለት ጭፍራ ለመሆን በቃሁ። ፪ ሳሙ፣ ፱ ፰። ዘፍ፣ ፳፱ ፳፯። |
| ወአድኅነኒ እግዚኦ እምእዴሁ ለዔሳው እኁየ፣ እስመ እፈርሀ አነ እምኔሁ ላዕለ ርእስየ ከመ ኢይምጻእ ወኢይቅትለኒ ወኢይቅትል እመ ምስለ ውሉዳ። | ፲፩ | አሁንም ከወንድሜ ከዔሳው እጅ አድነኝ መጥቶ እንዳይገድለኝ ከሱ የተነሣ ለራሴ እፈራለሁና፣ እናትን ከልጆቿ ጋር እንዳይገድል አለ። መዝ፣ ፶፱ ፩-፪። |
| እስመ ትቤለኒ አሤኒ ላዕሌከ ወእሬሲ ዘርአከ ከመ ኆፃ በሕር ዘኢይትኌለቍ እምብዝኁ። | ፲፪ | በጎ ነገርን አደርግሃለሁ ብለኸኛልና፣ ከብዛቱም የተነሣ የልጅ ልጅህን እንደማይቈጠር አሸዋ አደርገዋለሁ ብለኸኝ ነበርና። ዘፍ፣ ፳፰ ፲፫ ፲፬። |
| ወቤተ ህየ በይእቲ ሌሊት ወአውዐአ አምኃ ዘይወስድ ለዔሳው እኁሁ። | ፲፫ | በዚያችም ሌሊት ከዚያ አደረ፣ ለወንድሙ ለዔሳው የሚወስደውን እጅ መንሻ ሁለት መቶ እናት ፍየል፣ ሃያ የፍየል አውራ አወጣ። ዘፍ፣ ፵፫ ፲፩። |
| ክልኤተ ምእተ አጣሌ፣ ወዕሥራ አብሓኰ አጣሊ፣ ወክልኤተ ምእተ አባግዐ፣ ወስሳ አብሓኰ አባግዕ። | ፲፬ | ሁለት መቶ ፍየሎች፣ ሃያ የፍየል አውራዎች ሁለት መቶ እናት በጎች፣ ስድሳ የበጎች አውራዎች አወጣ። |
| ኃምሳ ናቃተ ምስለ እጐሊሆን፣ ወአርብዐ ዕጐልተ፣ ወዐሠርተ አሥዋረ፣ ወዕሥራ አእዱገ ወዐሠርተ ዕዋለ። | ፲፭ | አምሳ ግመሎች ከነጥጆቻቸው፣ አርባ ጊደ፣ ዓሥር ገቦች፣ ሃያ አህዮች፣ ዓሥር የአህያ ግልገሎች አወጣቶ። |
| ወወሀቦሙ ለደቂቁ መራዕየ እንተ ባሕቲቶሙ ወይቤሎሙ ሑሩ ቅድመ ወአስተራኅቁ መራዕየ እመራዕይ። | ፲፮ | ለብላቴኖቹ ሰጣቸው መንጋውን ከመንጋ ለይታችሁ እያራራቃችሁ በፊት በፊቴ ሂዱ አላቸው። |
| ወአዘዞ ለቀዳማዊ ወይቤሎ ለእመ ረከበከ ለዔሳው እኁየ ወተስእለከ ወይቤለከ ዘመኑ ዝንቱ ወአይቴ ተሐውር ወዘመኑ ዝ ዘየሐውር ቅድሜከ። | ፲፯ | ፊተኛውንም እንዲህ ብሎ አዘዘው፣ ወንድሜ ዔሳው አግኝተኸው ይህ መንጋ የማን ነው፤ ብሎ የጠየቀህ እንደሆነ የት ትሄዳለህ ያለህም እንደሆነ በፊትህስ የሚሄደው ይህ መንጋ የማነው፤ ብሎ ቢጠይቅህ። |
| በሎ ዘገብርከ ያዕቆብ አምኃ ዘፈነወ ለእግዚኡ ዔሳው ወናሁ ውእቱኒ ይተልወነ ድኅሬነ። | ፲፰ | አገልጋይህ ያዕቆብ ለጌታው ለዔሳው የላከው እጅ መንሻ ነው፣ እሱም አሁን በኋላችን ይከተለናል በለው አለው። |
| ወአዘዞ ለካልኡኒ ወለሣልሱኒ ወለኵሎሙ እለ የሐውሩ ቅድሜሁ ወይነድኡ መራዕየ ወይቤሎሙ ለእመ ረከብክምዎ ለዔሳው እኁየ ከመዝ በልዎ ናሁ ገብርከ ያዕቆብ ይበጽሕ ድኅሬነ። | ፲፱ | ሁለተኛውንና ሦስተኛውንም አከች በፊት በፊቱ መንጋ እየነዱ የሚሄዱትንም ሁሉ ወንድሜ ዔሳውን ያገኛችሁት እንደሆነ፣ እነሆ አገልጋይህ ያዕቆብ በኋላችን ይመጣል በሉት ብሎ አዘዛቸው። |
| እስመ ይቤ እድኅን እምገጹ በዝንቱ አምኃ ዘይወስዱ ደቅ ቅድሜሁ ወእምዝ እሬኢ ገጾ ቅድመ ከመ ይትቀበሎ ለገጽየ በዳኅን። | ፳ | በፊቱ በሚወስዱት በዚህ እጅ መንሻ ከወንድሜ ከፊቱ ቍጣ እድናለሁ ብሏልና፣ ከዚህ በኋላ ፊቱን ደስ ብሎት አያለሁ፤ እኔንም በደኅና ይቀበለኛል ብሎ ነው። |
| ወእምዝ ፈነወ አምኃ ወውእቱሰ ቤተ ውስተ ትዕይንት በይእቲ ሌሊት። | ፳፩ | ከዚህ በኋላ እጅ መንሻውን ላከ፣ እርሱ ግን በዚያች ሌሊት በሰፈር አደረ። |
| ወተንሥአ ያዕቆብ ወነሥአን ለክልኤሆን አንስቲያሁ ወለክልኤሆን ዕቁባቲሁ ወዐሠርተ ወአሐደ ደቂቀ ወዐደወ ማዕዶተ ያቦቅ። | ፳፪ | ያዕቆብ ተነሥቶ ሁለቱ ሚስቶቹን ሁለቱ ዕቁባቶቹንና ዓሥራ አንድ ልጆቹን ይዞ የያቦቅን ወንዝ ተሻገረ፣ ዘዳግ፣ ፫ ፲፮። |
| ወነሥአሙ ወዐደወ ውኂዘ ወአዕደወ ኵሎ ንዋያቲሁ። | ፳፫ | ይዞአቸውም ወንዙን ተሻገረ ጓዙንም ሁሉ አሻገረ። |

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



| | | |
|---|---|---|
| ወተርፈ ያዕቆብ ባሕቲቱ ወተጋደሎ ብእሲ እስከ ጽባሕ። | ፳፬ | ያዕቆብ ብቻውን ቀረ እስከንጋት ድረስ አንድ ሰው ሲታገለው አደረ ፤ ፪ ቆሮ. ፲፪ ፯ ። |
| ወሰበ ርእየ ከመ ኢክህሎ አኀዘ ሥርዐ ሕሩመ እንዘ ይትጋደል፣ ምስሌሁ ። | ፳፭ | ከርሱም ጋር ሲታገል እንዳልቻለው በየ ጊዜ ፤ ከርሙ የሚሆንበት ቸልዳውን ያዘው ። |
| ወይቤሎ ፈንወኒ እስመ ኀየ ጽባሕ ፤ ወይቤሎ ኢይፌንወከ ለእመ ኢባረከኒ ። | ፳፮ | ጎህ ቀድዷልና ልቀቀኝ አለው ፤ ካልመረቅከኝ አልለ ቅህም አለው ፤ ሉቃ. ፳፬ ፳፰ ። |
| ወይቤሎ መኑ ስምከ ወይቤሎ ያዕቆብ ስምየ ። | ፳፯ | ስምህ ማን ይባላል ፤ ቢለው ፤ ስሜ ያዕቆብ ነው አለው። |
| ወይቤሎ ኢይኩን እንከ ስምከ ያዕቆብ ፤ ዳዕሙ ይኩን ስምከ "እስራኤል„ እስመ ክህልከ ምስለ እግዚአብሔር ወምስለ እጓለ እመሕያው ። | ፳፰ | እንግዲህ ወዲህ ስምህ ያዕቆብ አይባል ፤ "እስራኤል„ ይባል እንጂ አለው ፤ ከእግዚአብሔርና ከሰውም ጋር መታገልን ችለሃልና ፤ ሆሴ. ፲፪ ፬ ። |
| ወይቤሎ ያዕቆብ አይድዐኒ ስመከ ፤ ወይቤሎ ለምንት ለከ ትሴአል ስምየ እስመ መድምም ውእቱ ወባረኮ በህየ። | ፳፱ | ያዕቆብም ስምህን ንገረኝ አለው ፤ ስሜን ለምን ትጠይቃለህ ፤ ስሜ መድምም (ድንቅ) ነውና ፤ በዚያም ቦታ ባረከው። |
| ወሰመዮ ያዕቆብ ስሞ ለውእቱ ብሔር ፤ "ራእየ እግዚአብሔር„ እስመ ይቤ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር ገጸ በገጽ ወድኅነት ነፍስየ ወገጽየ ። | ፴ | ያዕቆብ የዚያን ቦታ ስም "የእግዚአብሔር መገለጫ„ ብሎ ጠራው እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አይቼዋለሁና ፤ ከዚህም የተነሣ ሰውነቴም ፊቴም ድናለችና ፤ ዘፍ. ፲፮ ፲፫ ። |
| ወሠረቀ ፀሐይ ሰበ ኀደጎ ራእየ እግዚአብሔር ወሎቱሰ ያሰአክዝ እግሩ ። | ፴፩ | ፀሐይም በወጣ ጊዜ የእግዚአብሔር መገለጥ ተወው እሱንም ቸልዳው ያደነዝዘው ነበር ። |
| ወበእንተዝ ኢይበልዑ ደቂቀ እስራኤል እስከ ዛቲ ዕለት ውእተ ሥርወ ዘአስአዘዘ ዘሀሎ ውስተ ዓወ እግሩ እስመ አኀዘ ሥርዐ ሕሩመ ለያዕቆብ ውስተ ሥርው ገቦም። | ፴፪ | ስለዚህም የእስራኤል ልጆች በእግሩ መካከል ያለ የደነዘዘውን ቸልዳ እስከ ዛሬ ድረስ አይበሉም የያዕቆብ ቸልዳው ደንዝዞበት ነበርና ፤ ይህ ቸልዳ ለእስራኤል ልጆች እርም ነው ። |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፴፫ ። | | ምዕራፍ ፴፫ ። |
| ወአንሥአ ያዕቆብ አዕይንቲሁ ወርእየ ወናሁ ኤሳው እኁሁ መጽአ ወአርባዕቱ ምእት እደው ምስሌሁ፣ ወነፈቆሙ ያዕቆብ ለደቂቁ ኀበ ልያ ወኀበ ራኄል ወኀበ ክልኤሆን ዕቁባቲሁ ። | ፩ | ያዕቆብም ዓይኖቹን አቅንቶ አየ ፤ እነሆም ወንድሙ ዔሳው አራት መቶ ሰዎችን ይዞ ሲመጣ ተመለከተ ፤ ልጆቹንም የልያ ልጆች ከልያ ፤ የራኄልን ልጆች ከራኄል ፤ የባላን ልጆች ከባላ ፤ የዘለፋን ልጆች ከዘለፋ አድርጎ ከፋፈላቸው ፤ ዘፍ፣ ፴፪ ፮ ። |
| ወረሰዮን ለዕቁባቲሁ ምስለ ደቂቆን ቅድመ ፤ ወለልያ ወለደቂቃ ድኅሬሆን ወለራኄልሰ ወለዮሴፍ ድኅሬሃ ። | ፪ | ዕቁባቶቹን ከልጆቻቸው ጋር በፊት ፤ ልያን ከልጆቿ ጋር ወደኋላ አደረጋቸው ፤ ራኄልንና ዮሴፍን ግን ከሁሉ በኋላ አደረጋቸው ። |
| ወውእቱሰ ሖረ ቅድሜሆሙ ወሰገደ ውስተ ምድር ስብዐ እስከ ይበጽሐ ኀበ እኁሁ ኤሳው ። | ፫ | እሱ ግን በፊት በፊታቸው ሄደ ፤ ከወንድሙ ከዔሳው እስኪደርስ ድረስ ግምባሩን ምድር እያስነካ ሰባት ጊዜ ሰገደ ። |
| ወአቅደመ ረዊጸ ዔሳው ወተቀበሎ ወሐቀፎ ክሳዶ ወሰዓሞ ወበከዩ ክልኤሆሙ ኅቡረ ። | ፬ | ዔሳውም በየው ጊዜ እየሮጠ ሄዶ አንገቱን አቅፎ ሳመው ፤ ሁለቱም ተያይዘው አለቀሱ ፤ ዘፍ. ፵፭ ፲፬ ። |
| ወሰበ ነጸረ ኤሳው ወርእዮን ለአንስት ወለደቂቆን ይቤሎ ምንትከ እሉ ፤ ወይቤሎ ያዕቆብ ደቂቀየ እሙንቱ ዘመሐሮ እግዚአብሔር ለገብርከ ። | ፭ | ዔሳውም ሁለቱ ሚስቶቹንና ልጆቻቸውን በየ ጊዜ እነ ዚህ ምኖችህ ናቸው ፤ አለው ያዕቆብም እግዚአብሔር ለኔ ለአገልጋይህ የመጸወተኝ ልጆቼ ናቸው አለው ። |
| ወመጽአ ዕቁባቲሁ ወደቂቆን ምስሌሆን ወሰገዳ ። | ፮ | ዕቁባቶቹም ከልጆቻቸው ጋር መጥተው እጅ ነሡት ። |
| ወመጽአት ልያ ወደቂቃ ወሰገዱ ሎቱ ወእምዝ መጽአት ራኄል ወሰገደት ። | ፯ | ልያም ከልጆቿ ጋር መጥታ እጅ ነሣችው ፤ ከሁሉ በኋላም ራኄል መጥታ እጅ ነሣች ። |
| ወይቤሎ ኤሳው ለያዕቆብ ምንትከ ውእቱ ዝንቱ ኵሉ ትአይን ዘረከብኩ ወይቤሎ ያዕቆብ ለኤሳው ዘገበርኩ ለከ እግዚኦ ከመ እርከብ ሞገሰ በቅድሜከ ። | ፰ | ዔሳውም ያዕቆብን ይህ ሁሉ ያገኘሁት ሠራዊት ምንህ ነው ፤ አለው ፤ ያዕቆብም ዔሳውን አቤቱ በፊትህ በለሟልነትን አገኝ ዘንድ ያደረግሁት ነው አለው ፤ ዘፍ፣ ፴፪ ፭ ። |
| ወይቤሎ ኤሳው ብየ እንስሳ ብዙኀ እኁየ ወይኩንከ ለከ ዘዚአከ ። | ፱ | ወንድሜ ለኔ ብዙ ከብት አለኝ ፤ ያንተ ገንዘብ ላንተ ይሁንልህ አለው ። |
| ወይቤሎ ያዕቆብ እኮ ከመዝ ለእመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ተመጠው አምኃየ እምእዴየ ፤ እስመ በእንተ | ፲ | ያዕቆብም እንዲህ አይደለም በፊትህስ በለሟልነትን ካገኘሁ ያመጣሁትን እጅ መንሻዬን ተቀበለኝ አለው። ስለ |

www.ethiopianorthodox.org

ዝንቱ እሬኢ ገጸከ ከመ ዘይሬኢ ገጸ እግዚአብሔር ።

፲፩ ወእመሰ ታፈቅረኒ ንሣእ አምኃየ ዘአምጻእኩ ለከ እስመ መሐረኒ እግዚአብሔር ወብየ ኵሉ ፡ ወአገበሮ ወነሥአ ።

፲፪ ወይቤሎ ኤሳው ተንሥአ ንሑር አንተ መንጸር ።

፲፫ ወይቤሎ ያዕቆብ ለሊከ ተአምር እግዚእየ ከመ ድኩማን ደቂቅ ወአልሕምት ወአባግዕ ወእጕላትኒ የሐርሳ ላዕሌየ ፡ ወለእመሰ መረድኩ ላዕሌሆሙ አሐተ ዕለተ ወእመ አከ በኵየ ይመውቱ ኵሉ እንስሳነ ።

፲፬ ሑር አንተሰ እግዚእየ ቅድመ ገብርከ ወንሕነሰ በከመ ንክል ንሖውር ወንወዕልሂ ውስተ ፍኖት እንዘ ንሐውር ፡ ወዕበሂ ንሖውር በእግረ ደቂቅ ንሐውር ፡ እስከ ንበጽሕ ኀበ እግዚእነ ውስተ ሴይር ።

፲፭ ወይቤሎ ኤሳው እኅድግኑ ለከ እምዝንቱ ሕዝብ ዘምስሌየ ፡ ወይቤሎ ያዕቆብ ለምንትኑ ዝንቱ የአክለኒ ዘምስሌየ ወዘረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ እግዚኦ ።

፲፮ ወገብአ ኤሳው ፍኖቶ በይእቲ ዕለት ውስተ ሴይር ።

፲፯ ወያዕቆብሰ ኀደረ ውስተ ተአይን ወገብረ ሎቱ ሐጹረ በህየ ሎቱኒ ወለእንስሳሁኒ ፡ ወበእንተዝ ሰመዮ ለውእቱ ብሔር ማኅደር ።

፲፰ ወበጽሐ ያዕቆብ ውስተ ሴሎም ውስተ ሀገረ ሰቂሞን እንተ ሀለወት ውስተ ምድረ ከነአን እምድኅረ መጽአ እምእፍላግ ዘሶርያ ወበጽሐ አንጻረ ሀገር ።

፲፱ ወተሣየጠ ደወለ ገራህት ወተከለ ህየ ማኅደረ ፡ ወገራህትሰ እንተ ተሣየጠ እምኤሞር አቡሁ ለሴኬም በምእት አባግዕ ።

፳ ወአቀመ በህየ ምሥዋዐ ወጸውዖ ለአምላከ እስራኤል ።

## ምዕራፍ ፴፬ ።

፩ ወወፅአት ዲና ወለተ ልያ እንተ ተወልደት ለያዕቆብ ከመ ትርአይ አዋልደ ውእቱ ብሔር ።

፪ ወርእያ ሴኬም ወልደ ኤሞር ኤውያዊ መልአከ ብሔር ወነሥኣ ወሰከበ ምስሌሃ ወአኅሠራ ።

፫ ወርእየ ነፍሳ ለዲና ወለተ ያዕቆብ ወአፍቀራ ለይእቲ ወለት ወተናገራ በእንተ ግእዛ ።

፬ ወይቤሎ ሴኬም ለኤሞር አቡሁ ንሥኣ ሊተ ለዛቲ ወለት ትኩነኒ ብእሲተ ።

፭ ወሰምዐ ያዕቆብ ከመ አርኰሳ ለዲና ወለቱ ወልደ ኤሞር ወደቂቁሰ ሐቅለ ሀለዉ ምስለ እንስሳሁ ፡ ወአርመመ ያዕቆብ እስከ ይመጽኡ ደቂቁ ።

፮ ወመጽአ ኤሞር አቡሁ ለሴኬም ኀበ ያዕቆብ ከመ ይትናገሮ ።

፯ ወመጽኡ ደቂቁ እምሐቅል ፡ ወሰበ ሰምዑ ዘከመ ሰከበ ሴኬም ምስለ ወለተ ያዕቆብ ደንገፁ ጥቀ ወተከዙ እስመ ኀፍረተ ገብረ ላዕለ እስራኤል ወኢከነ ከማሁ ሕጉ ።

ዚህም የእግዚአብሔርን ፊት እንደሚያይ ሰው ደስ ብሎኝ ፊትህን አያለሁ ፡ ፪ ሳሙ ፡ ፫ ፲፫ ።

የምትወደኝስ ከሆነ ያመጣሁልህን እጅ መንሻዬን ተቀበለኝ አለው ፡ እግዚአብሔር ሰጥቶኛ ሁሉም አለኝና ፡ ግድ ቢለውም ተቀበለው ፡ ፪ ነገ. ፭ ፳፫ ።

ዔሳውም ተነሥ በፊታችን ወዳለው አገር እንሂድ አለው ።

ያዕቆብም ጌታዬ ልጆቹም ከብቶቹም በጎቹም እንደ ደከሙ አንተ ታውቃለህ ፡ ላሞቹም እየወለዱ ያጠቡሉ ፡ አንድ ቀን ወይም ሁለተኛ ቀን በችኰላ የነዳናቸው እንደ ሆነ ከብቶቻችን ሁሉ ይሞታሉ ።

ጌታዬ አንተ ቀድመህ ሂድ እኛ ግን እንደቻልን ቀስ እያልን እናዘግማለን ፡ ስንጓዝም በመንገድ እንውላለን ፡ በምንሄድበትም ጊዜ ጌታችን ካለህበት እስከ ሴይር እስክንደርስ ድረስ በሕፃናቱ ርምጃ መጠን ነው የምንሄደው ፡ አለው ዘፍ. ፴፪ ፫ ።

ዔሳውም ከኔ ጋር ካሉት ሰዎች ልተውልህን አለው ፡ ያዕቆብም ይህ ለምንድ ነው አቤቱ ከኔ ጋር ያለውና በፊትህ ያገኘሁት በሏሏልነት ይበቃኛል አለው ።

ዔሳውም በዚያች ቀን ተነሥቶ ወደ ሴይር ገባ ።

ያዕቆብ ግን በዚያው በሰፈሩ አደረ ፡ በዚያም ቦታ ለሱም ለከብቶቹም ዳሳን ጣለ ፡ ስለዚህም ያን አገር ማኅደር ብሎ ጠራው ፡ ኢያሱ ፲፫ ፳፯ ። ዘኁል. ፳ ፱ ።

ያዕቆብ የሶርያውን ወንዝ ተሻግሮ ከመጣ በኋላ በከነዓን ውስጥ ወዳለች የሰቂሞን አውራጃ ወደምትሆን ሴሎም ወደ ምትባል አገር ደረሰ ፡ ዮሐ. ፫ ፳፫ ።

ከከተማውም አፍዛግ በደረሰ ጊዜ የእርሻ አውራጃ ገዛ ፡ በዚያው በገዛውም እርሻ ድንኳኑን ተከለ ፡ እርሻውግን ከሰኬም አባት ከኤሞር በመቶ በግ የገዛው ነው ።

በዚያም መሠውያ ሠርቶ ፡ የእስራኤልን አምላክ ጠራው (አመሰገነው) ፡ ዘፍ፡ ፴፭ ፯ ።

## ምዕራፍ ፴፬ ።

ከያዕቆብ የተወለደች የልያ ልጅ ዲናም የዚያን አገር ሴቶች ለማየት ወጣች ፡ ዘፍ፡ ፴ ፳፩ ።

የአገር አለቃ የሚሆን ኤውያው ሰው የኤሞር ልጅ ሴኬም አያት ነጥቆ ወስዶም ደረሰባት ከክብርም አሳነሣት።

የያዕቆብ ልጅ ዲናን መልኳን አይቶ ያችን ልጅ ወደዳት ፡ የጠባይዋንም ነገር ተናገረ ።

ሴኬምም አባቱ ኤሞርን ለኔ ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ይህችን ልጅ አጋባኝ አለው ፡ ዘሖሳ፡ ፲፬ ፪ ።

ያዕቆብም የኤሞር ልጅ ልጁ ዲናን ከክብር እንዳሳነሣት ሰማ ፡ ልጆቹ ግን ከከብት ጋር በረኻ ነበሩና ፡ ልጆቹ እስኪመጡ ድረስ ዝም አለ ።

የሴኬም አባት ኤሞር (ልጅህን ለልጄ ስጥልኝ ብሎ) ሊነጋገረው ወደ ያዕቆብ መጣ ።

ልጆቹም ከበረኻ መጡ ፡ ሰኬም (እኅታቸውን) የያዕቆብ ልጅ ዲናን እንደደረሰበት በሰሙ ጊዜ እጅግ ደንግጠው አዘኑ ፡ በእስራኤል ላይ የሚያሳፍር ሥራ ሠርቶዋ

ልና ፡ ሥርዓቱም እንዲህ አይደለምና ፡ ፪ ሳሙ፡ ፲፫ ፲፪-፳፪ ፡

፰ ወተናገርሙ ወይቤሎሙ ኤሞር ፡ ሴኬም ወልድየ አፍቀራ ለወለትክሙ ሀብዎ ትኩኖ ብእሲተ ።

ኤሞርም ልጄ ሴኬም ልጃችሁን ወዷታልና ሚስት ትሆነው ዘንድ ስጡት ብሎ ተናገራቸው ።

፱ ወትትሐመዉነ ሀቡነ አዋልዲክሙ ወአዋልዲነኒ ንሥኡ ለደቂቅክሙ ።

(በጋብቻም) ከኛ ጋር ትዛመዱ ዘንድ ወንዶች ልጆቻችሁን ለኛ ስጡን ፡ ሴቶች ልጆቻችንንም ለወንዶች ልጆቻችሁ ውሰዱ (በጋብቻ) ከኛ ጋራ ኑሩ አላቸው ፡ ዘፀ፡ ፴፬ ፲፮ ፡

፲ ወንበሩ ምስሌነ ፡ ወምድርነሂ ናሁ ረኃብ ቅድሜክሙ ንድሩ ውስቴታ ወተገበሩ ።

መሬታችንም እነሆ በፊታችሁ ሰፊ ናት ፡ በውስጧ ሁናችሁ ቤት ሠርታችሁ እረሱ ቁፍሩ አላቸው ዘፍ፡ ፲፫ ፱ ።

፲፩ ወይቤሎሙ ሴኬም ለአቡሃ ወለአኀዊሃ ረከቡ ሊተ ዘንተ ፍትሐ በቅድሜክሙ ወኵሎ ዘትብሉ እሁብ ።

ሴኬምም ለአባቷና ለወንድሞቿ ይህን ነገር መዳችሁ አድርጉልኝ (በጅ በሉኝ) ያላችሁትም ሁሉ እሰጣለሁ ።

፲፪ ወመጠነ አብዛኅክሙ ጥቀ ሕዩሃ እሁበክሙ ሀቡኒያ ለዛቲ ወለት ትኩነኒ ብእሲተ ።

ያላችሁትን ማጫዋንም እጅግ ያበዛችሁትን ያህል እሰጣችኋለሁ ፡ ይህችን ብላቴና ሚስት ልትሆነኝ ስጡኝ አላቸው ።

፲፫ ወአውሥእዎሙ ደቂቀ ያዕቆብ ስምዖን ወሌዊ ለሴኬም ወለኤሞር አቡሁ በጕሕሉት እስመ አርኰሰዋ ለዲና እኅቶሙ ።

የያዕቆብ ልጆች ስምዖንና ሌዊም ለሴኬምና ለአባቱ ለኤሞር በተንኰል መለሱላቸው ፡ እኅታቸው ዲናን አዋርደዋታልና ።

፲፬ ወይቤልዎሙ ኢንክል ገቢሮቶ ለዝንቱ ነገር ከመ ንሁብ እኅተነ ለብእሲ ዘኢኮነ ግዙረ እስመ ፅዕለት ውእቱ ለነ ።

እንዲህም አሏቸው ላልተገዘረ ሰው እኅታችንን ልንሰጥ ይህን ነገር ልናደርገው አንችልም ፡ ይህ ለኛ ስድባችን ነውና ። ኢያሱ ፭ ፱ ።

፲፭ ወበሕቱ በዝንቱ ትከውኑ ከማነ ወንነብር ምስሌክሙ ለእመ ገዘርክሙ ኵሎ ተባዕተክሙ ።

ነገር ግን ወንድ ወንዱን ብትገዝሩ በዚህም እኛን ከመሰላችሁ ፡ እኛም እናንተን መስለን እንኖራለን ።

፲፮ ወንሁበክሙ አዋልዲነ ወንነሥእ አዋልዲክሙ ለነ አንስቲያ ፡ ወንነብር ምስሌክሙ ወንከውን አሐደ ዘመደ ።

ሴቶች ልጆቻችንን እንሰጣችኋለን ፡ እኛም የናንተን ሴቶች ልጆች ሚስት አድርገን እንወስዳለን ፡ በግቢ አንድ ወገን ሆነን ተዛምደን ተዋልደን እንኖራለን ፡ አንድ ዘመድም እንሆናለን ።

፲፯ ወለእመሰ ኢሰማዕክሙነ ንነሥእ ወለተነ ወነሐውር ።

ካልሰማችሁን ግን ልጃችንን ይዘን እንሄዳለን ።

፲፰ ወአደሞሙ ለኤሞር ወለሴኬም ዝንቱ ነገር ።

ይህ ነገር ለኤሞርና ለሴኬም ደስ አሰኛቸው ።

፲፱ ወኢጐንደየ ገቢሮቶ ውእቱ ወልድ ለዝንቱ ነገር እስመ ያፈቅራ ለወለተ ያዕቆብ ፡ ወውእቱ ይከብር እምኵሉ ቤተ አቡሁ ።

ያም ልጅ የያዕቆብን ልጅ ስለወደዳት ይህን ነገር ከመፈጸም አልዘገየም ፡ ከቤቱ ወገኖች ሁሉ ይልቅ እሱ ይከብር ነበርና ፡ ፪ ሳሙ፡ ፲፭ ፱ ። ሩት ፬ ፩ ።

፳ ወሖሩ ኤሞር ወሴኬም ወበጽሑ ውስተ አንቀጸ ሀገሮሙ ወነገሩ ለኵሉ አደወ ሀገሮሙ ።

ኤሞርና ሴኬም ሄደው ከአገራቸው አደባባይ ደርሰው ለአገራቸው ሰዎች ሁሉ ይህን ነገር ነገሩዋቸው ።

፳፩ ወይቤልዎሙ እሉ አደው ሰንዕ እሙንቱ ምስሌነ ወይንበሩ ውስተ ምድርነ ወይትገበርዋ እስመ ረኀብ ይእቲ ምድር ቅድሜሆሙ ወአዋልዲሆሙ ንነሥእ ለነ አንስቲያ ወአዋልዲነኒ ንሁቦሙ ።

እሊህ ሰዎች ከኛ ጋር ስምም ናቸውና ምድራችንን እያረሱ እየቈፈሩ በአገራችን ይኑሩ አሉዋቸው ይህች ምድርም በፊታቸው ሰፊ ናትና ፡ ሴቶች ልጆቻቸውን ለኛ ሚስት እናደርጋለን ፡ ሴቶች ልጆቻችንንም እንሰጣቸዋለን ።

፳፪ ወበዝ ባሕቲቱ ንትመሰሎሙ ከመ እሙንቱሂ ይኩኑ ከማነ ወንኩን አሐደ ዘመደ ፡ ወንግዝር ኵሎ ተባዕተነ በከመ እሙንቱ ይገዝሩ ።

እነሱ እኛን መስለው አንድ ወገን ሆነን እንኖር ዘንድ በዚህ ብቻ እንምሰላቸው ፡ አንድ ዘመድ አንድ ወገን እንሁን ፡ እነሱ ወንድ ወንዱን እንዲገዝሩ ፡ እኛም ወንድ ወንዱን ሁሉ እንግዘር ።

፳፫ ወመራዕይሆሙኒ ወእንስሳሆሙኒ ወንዋዮሙኒ አኮኑ ለነ ውእቱ ፡ ወባሕቱ በዝንቱ ከመ ንኩን ከማሆሙ ወይንበሩ ማእከሌነ ።

እንዲህ ከሆነ መንጋቸውም ፡ ከብታቸውም ገንዘባቸውም ለኛ አይደለምን ፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ ከመሰልናቸው በኛ መካከል (ተዛምደውን) ይኑሩ ።

፳፬ ወይቤልዎሙ ለኤሞር ወለሴኬም ወልዱ ኵሎሙ እለ ይበውኡ ውስተ አንቀጸ ሀገር እሆ ፡ ወተገዝሩ ከተማ ሥጋ ነፍስቶሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ።

በአገሩ አደባባይ የሚገቡ ሰዎች ሁሉ ለኤሞርና ለልጁ ለሴኬም እሺ (እንገዘራለን) አሉዋቸው ወንድ ወንዶቹ ሁሉ የሰውነታቸውን ብልት (ሰንኮፍ) ተገዘሩ ።

፳፭ ወእምዝ አመ ሣልስት ዕለት እንዘ ሀለዉ ውስተ ሕማም ወጽሉአን እሙንቱ ነሥኡ ክልኤሆሙ ደቂቀ ያዕቆብ ስምዖን ወሌዊ አኀዊሃ ለዲና መጣብሒሆሙ ዘዚአሆሙ

ከዚህም በኋላ በሦስተኛው ቀን እነሱ ቈስለው በሕመም ላይ ሳሉ ፡ የዲና ወንድሞች የያዕቆብ ልጆች ስምዖንና ሌዊ ሁለቱ የየራሳቸውን አፋ ይዘው ተነሥተው አይ

ወበኡ ውስተ ሀገር ተታቢዖሙ ወቀተሉ ኵሎ ተባዕቶሙ ።

ዘሀ አይዘሀ ተበብለው ወደ መንደር ገብተው ወንድ ወንዱን ሁሉ ገደሉ፤ ዘፍ፡ ፵፱ ፭-፯ ።

፳፮ ለኤሞርሂ ወለሴኬም ቀተልዎሙ ወነሥእዋ ለዲና እኅቶሙ ወአውፅእዋ እምነ ቤተ ሴኬም ።

ኤሞርንና ሴኬምንም ገደሉዋቸው፤ እኅታቸው ዲናንም ከሴኬም ቤት አውጥተው ወሰዱዋት ።

፳፯ ወቦኡ ደቂቀ ያዕቆብ ኀበ ቅቱላን ወበርበርዋ ለይእቲ ሀገር እንተ ውስቴታ አርኰስዋ ለዲና እኅቶሙ ።

የያዕቆብ ልጆች ወደ ሞቱት ሰዎች ገብተው እኅታቸው ዲናን ክብሯን ያሳነሱባት ሰዎች ያሉባት ያችን አገር በረበሩዋት ።

፳፰ ወነሥእዎሙ አልሕምቲሆሙ ወአባግዒሆሙኒ ወአእዱጊሆሙኒ ወኵሎ ዘሀሎ ውስተ ሐቅል ወውስተ ሀገር ።

በጎቻቸውንም ላሞቻቸውንም አህዮቻቸውንም፤ በበረኻና በአገር ያለውን ሁሉ (ዘረፉ) ።

፳፱ ወነብረሆሙኒ ወአንስቲያሆሙኒ ወኵሎ ቁሳቍሶሙ ፄወዉ ወበርበሩ ኵሎ ዘውስተ ሀገር ወዘውስተ አብያት ።

ቤተ ሰቦቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ጥቃቅን የቤታቸውን ዕቃ ሁሉ ማረኩ፤ በመንደሮቻቸውና በበረኻ ያለውንም ሁሉ በረበሩ ።

፴ ወይቤሎሙ ያዕቆብ ለስምዖን ወለሌዊ እኩየ ረሰይክሙኒ ወአጽላእክሙኒ በኀበ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ኵሉ ምድር በኀበ ከናኔዎን ወፌርዜዎን፡ ወአንሰ ውኁድ አነ በኍልቍየ ወይትጋብኡ ላዕሌየ ወይቀትሉኒ ወእትቀጠቀጥ አነ ወቤትየ ።

ያዕቆብም ስምዖንና ሌዊን ክፉ አደረጋችሁብኝ፤ በከናኔዎን፤ በፌርዜዎን ምድር ሁሉ በሚኖሩ ሁሉም ዘንድ አስጠላችሁኝ አላቸው፤ እኔ በቍጥሬ ጥቂት ነኝ፤ በኔ ላይ ተሰብስበው ይወጉኛል እኔም ከወገኔ ጋር እቀጠቀጣለሁ ።

፴፩ ወይቤልዎ ለምንትኑ ከመ ዘማ ረሰይዋ ለእኅትነ ወአኅሠርዋ ።

እነሱም እኅታችንን ለምን እንደ አመንዝራ አዋረዱዋት አሉት ።

## ምዕራፍ ፴፭ ።

፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ተንሥእ ወሑር ውስተ ቤቴል ወንበር ህየ ወግበር መሥዋዕተ ሊተ ዘአስተርአይኩከ አመ ጐየይከ እምገጸ ኤሳው እኁከ ።

እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዲህ አለው፤ ተነሥተህ ወደ ቤቴል ሂደህ በዚያ ኑር፤ ከወንድምህ ከዔሳው ፊት ሸሽተህ በሄድህ ጊዜ ለታየሁህ ለኔ መሥዋዕት ሠዋልኝ።

፪ ወይቤሎሙ ያዕቆብ ለሰብአ ቤቱ ወለኵሎሙ እለ ምስሌሁ አሰስሉ እምኔክሙ አማልክተ ነኪር ወአውፅኡ እማእከሌክሙ ወንጽሑ ወሕፅቡ አልባሲክሙ ።

ያዕቆብም ቤተ ሰቡንና ከርሱ ጋር ያሉትን ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ ከናንተ ዘንድ ያሉ ልዩ ጣዖታትን ከናንተ አስወግዱ፤ ከመካከላችሁም አውጡ፤ ንጹሐን ሁኑ፤ ልብሶቻችሁንም እጠቡ ። ዘፍ፡ ፲፰ ፲፱ ። ኢያሱ ፳፬ ፲፭ ።

፫ ወተንሥኡ ንዕርግ ውስተ ቤቴል ወንግበር በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ዘሰምዐኒ በዕለተ ምንዳቤየ ወዘሀሎ ምስሌየ ወአድኀነኒ በፍኖትየ ወአዕደወኒ ።

ተነሡ ወደ ቤቴል እንውጣ፤ በዚያም በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ አሁንም ከኔ ጋር ላለ፤ በሄድኩበትም ሁሉ ከመከራ አድኖ ላሻገረኝ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንሠዋ አላቸው ። ዘፍ፡ ፴፪ ፳፬ ። መዝ፡ ፻፯ ፮ ።

፬ ወወሀብዎ ለያዕቆብ ኵሎ አማልክተ ነኪራነ ወኵሎ ዘሀሎ ኀቤሆሙ ወአእኑጊ ዘውስተ ዕዘኒሆሙ፤ ወኀብአ ያዕቆብ ውስተ ዕፀ ዘሰቂሞን ወአኅጐሎሙ እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ።

ልዩ የሆኑ ጣዖታትንና ከነሱ ዘንድ ያለውንም ለያዕቆብ ሁሉ ሰጡት፤ በጆሮአቸው ያለውን ጉትቾችንም (አውጥተው) ሰጡት፤ ያዕቆብም በሰቂሞን ባለችው ዕንጨት ሥር ቀበረው እስከ ዛሬ እስከዚች ቀን ድረስ እንደ ቀበራቸው ይኖራሉ ። ሆሴ፡ ፪ ፲፫ ። ኢያሱ ፳፬ ፳፮ ።

፭ ወግዕዘ እስራኤል እምሴቄም፤ ወኮነ ፍርሀተ እግዚአብሔር ላዕለ እግንቲ አህጉር እለ ዐውዶሙ ወኢተለውዎሙ ድኅሬሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

እስራኤልም ከሴቄም ተነሣ፤ በዙርያቸው ባሉት በነዚያ አገሮች ላይ እግዚአብሔርን መፍራት ሆነ፤ የአገሩም ሰዎች የእስራኤልን ልጆች አልተከተሉዋቸውም ።

፮ ወበጽሐ ያዕቆብ ኀበ ሎዛ እንተ ውስተ ምድረ ከነአን እንተ ይእቲ ቤቴል፤ ውእቱ ወኵሉ ሕዝብ ዘምስሌሁ ።

ያዕቆብም ከሱም ጋር ካሉ ሕዝብ ሁሉ በከነዓን አውራጃ ወዳለች ወደ ሎዛ ደረሰ፤ እርሷም ቤቴል ናት ።

፯ ወነደቀ በህየ ምሥዋዐ ወሰመየ ስሞ ለውእቱ መከን ቤቴል፤ እስመ በህየ አስተርአዮ እግዚአብሔር አመ ተኀጥአ እምገጸ ኤሳው እኁሁ ።

በዚያም መሠውያን ሠራ፤ የዚያንም በታ ስሙን ቤቴል ብሎ ጠራው፤ ከወንድሙ ከዔሳው ፊት ሸሽቶ በሄደ ጊዜ በዚያ ታይቶት ነበርና ። ዘፍ፡ ፳፰ ፲፫ ። መክ፡ ፭ ፬ ።

፰ ወሞተት ዲቦራ ሐፃኒታ ለርብቃ ወተቀብረት እምታሕቱ ለቤቴል ኀበ ዕፀ በላን ወሰመይዎ አመ ላህ ።

የርብቃ ሞግዚት (የነበረች) ዲቦራም ሞተች፤ ከቤቴል በታች በላን ከሚባል ዕንጨት (ግራር ወይራ) ሥር ተቀበረች፤ የልቅሶም ዛፍ አሉት ። ዘፍ፡ ፳፬ ፶፱ ።

፱ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለያዕቆብ አመ ወፅአ እማእከለ አፍላግ ዘሶርያ ።

እግዚአብሔርም ከሶርያ ወንዞች መካከል በወጣ ጊዜ ለያዕቆብ ታየው ።

| | | |
|---|---|---|
| ወባረኮ እግዚአብሔር ወይቤሎ ኢይሰመይ ስምከ ያዕቆብ ዳእሙ እስራኤል ። | ፲ | እግዚአብሔርም ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ብሎ ባረከው ። ዘፍ፡ ፴፪ ፳፰ ። |
| ወይቤሎ አነ ውእቱ አምላክከ ብዛኅ ወተባዛኅ ፡ ወይኩን እምኔከ ሕዝብ ወማኅበረ አሕዛብ ወነገሥት ይፃኡ እምኔከ ። | ፲፩ | ፈጣሪህ እኔ ነኝና ብዛ ተባዛም ሕዝብ አሕዛብም ከአንተ ይወለዱ ፡ የአሕዛብ ማኅበርና ነገሥታትም ከአንተ ይወጡ አለው ። ዘፍ፡ ፲፯ ፩ ። ማቴ ፫ - ፱ ። |
| ወለዛቲ ምድር እንተ ወሀብኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ለከ እሁብ ወለዘርእከ እምድኅሬከ ። | ፲፪ | ለአብርሃም ለይስሐቅ የሰጠኋት ይህችን ምድር ላንተ ካንተ በኋላም ለልጆችህ እሰጣታለሁ ። ዘፀ፡ ፴፪ ፲፫ ። |
| ወዐርገ እግዚአብሔር እምኅቤሁ እምውእቱ ብሔር ኀበ ተናገሮ ። | ፲፫ | እግዚአብሔርም ከተነጋገረበት ከዚያ አገር ከሱ ተለይቶ ዐረገ (ተሠወረ) ። ዘፍ፡ ፲፯ ፳፪ ። |
| ወአቀመ ያዕቆብ ሐውልተ ውስተ ውእቱ ብሔር ኀበ ተናገሮ ወአውጽሐ ሞጻሕተ ላዕሌሃ ወከዐወ ላዕሌሃ ቅብዐ ። | ፲፬ | ያዕቆብም ከርሱ ጋር በተነጋገረበት በዚያ ቦታ ሐውልትን አቆመ ፡ በላዩም ላይ ዘይት አፈሰሰበት ። |
| ወሰመዮ ስሞ ያዕቆብ ለውእቱ መካን ቤቴል ። | ፲፭ | ያዕቆብ ያን ቦታ ቤቴል ብሎ ጠራው ። |
| ወግዕዘ እምነ ቤቴል ወተከለ ማኅደረ ኀበ ማኅፈድ ዘጋዴር ፡ ወእምዝ ሶበ በጽሐ ውስተ ምድረ ኤፍራታ ወለደት ራሔል ወዐጸበት በወሊድ ። | ፲፮ | ከቤቴልም ተጉዞ ሂዶ በጋዴር ግንብ አጠገብ ድንኳን ተከለ ፡ ከዚህም በኋላ ከኤፍራታ ምድር በደረሰ ጊዜ ራሔል ወለደች ፡ በወሊድም ተጨነቀች ። ዘፍ፡ ፴፰ ፲፱ ። |
| ወእምዝ እንዘ ሀለወት ውስተ ሕማመ ወሊድ ትቤላ መወልዲት ኢትፍርሂ እስመ ዝኒ ይከውነኪ ወልደ ። | ፲፯ | ከዚህ በኋላ በምጥ ተይዛ ሳለች አዋላጂቱ ይህም ወንድ ልጅ ይሆንልሻልና አትፍሪ አለቻት ። ዘፍ፡ ፴ ፳፬ ። |
| ወእምዝ አልጸቀት ከመ ትፃእ ነፍሳ እስመ በቱ ከነ ሙተታ ፡ ወሰመየቶ ስሞ ወልደ ፃዕርየ ወአቡሁሰ ሰመዮ ብንያም ። | ፲፰ | ሞቷ በሱ ምክንያት ነውና ከዚህ በኋላ ነፍሷ ከሥጋዋ ልትለይ ቀረበች ፡ ስሙንም የፃር ጋር ልጄ አለችው አባቱ ግን ብንያም አለው ። |
| ወሞተት ራሔል ወተቀብረት ውስተ ፍኖት ዘኤፍራታ እንተ ይእቲ ቤተ ልሔም ። | ፲፱ | ራሔልም ሞተች በኤፍራታ ጐዳና ተቀበረች ፡ ይህችውም ቤተ ልሔም ናት ። ዘፍ፡ ፵፰ ፯ ። ሩት ፩ ፪ ። |
| ወአቀመ ያዕቆብ ሐውልተ ላዕለ መቃብራ ወይእቲ ተሰምየት ሐውልተ መቃብረ ራሔል እስከ ዮም ። | ፳ | ያዕቆብም በራሔል መቃብር ላይ (ለምልክት) ሐውልትን አቆመ ፡ ያችም ሐውልት እስከ ዛሬ ድረስ የራሔል መቃብር ሐውልት ተባለች ። ፩ ሳሙ፡ ፲ ፪ ። |
| ወእምዝ እንዘ ሀሎ እስራኤል ውስተ ይእቲ ምድር ሖረ ሮቤል ወሰከበ ምስለ ዕቅብተ ያዕቆብ አቡሁ ምስለ ባላ ፡ ወሰምዐ እስራኤል ወኮነ እኩየ በቅድሜሁ ። | ፳፩ | ከዚህ በኋላ እስራኤል በዚያች ምድር ሳለ ሮቤል ሂዶ ከአባቱ ከያዕቆብ ዕቅብት ከባላ ደረሰ (ተኛ) እስራኤልም በሰማ ጊዜ በፊቱ ክፉ ነገር ሆነ። (ከፋው) ፩ ዜ፡ መዋ፡ ፭ ፩። |
| ወዐሠርቱ ወክልኤቱ እሙንቱ ደቂቀ ያዕቆብ ። | ፳፪ | የያዕቆብም ልጆች ዓሥራ ሁለት ናቸው ። |
| ደቂቀ ልያ ፡ ሮቤል በኵሩ ፡ ወስምዖን ፡ ወሌዊ ፡ ወይሁዳ ፡ ወይሳኮር ፡ ወዛብሎን ። | ፳፫ | የልያ ልጆች በኩሩ ሮቤል ፡ ስምዖን ፡ ሌዊ ፡ ይሁዳ ፡ ይሳኮር ፡ ዛብሎን ናቸው ። ዘፍ፡ ፵፮ ፰ ። ዘፀአ፡ ፩ ፪ ። |
| ወደቂቀ ራሔል ፡ ዮሴፍ ፡ ወብንያም ። | ፳፬ | የራሔል ልጆች ዮሴፍ ፡ ብንያም ፡ ናቸው ። |
| ወደቂቀ ባላ ፡ እመተ ራሔል ዳን ፡ ወንፍታሌም ። | ፳፭ | የራሔል አገልጋይ የባላ ልጆች ዳን ፡ ንፍታሌም ፡ ናቸው ። |
| ወደቂቀ ዘለፋ አመተ ልያ ጋድ ፡ ወአሴር ፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ያዕቆብ እለ ተወልዱ ሎቱ በማእከለ አፍላግ ዘሶርያ ። | ፳፮ | የልያ ገረድ የዘለፋ ልጆች ጋድ ፡ አሴር ፡ ናቸው በሶርያ ወንዞች መካከል የተወለዱለት የያዕቆብ ልጆች እሊህ ናቸው ። |
| ወበጽሐ ያዕቆብ ኀበ ይስሐቅ አቡሁ ውስተ ምንባሬ እንተ ውስተ ሐቅል እንተ ይእቲ ኬብሮን በምድረ ከነአን ኀበ ነበሩ አብርሃም ወይስሐቅ ። | ፳፯ | ያዕቆብም በምድረ በዳ አቅራቢያ ባለች አብርሃምና ይስሐቅ ይቀመጡባት በነበረች አገር እሷም ኬብሮን ናት ከአባቱ ከይስሐቅ ዘንድ ደረሰ ። ኢያሱ ፲፬ ፲፭ ። |
| ወኮነ መዋዕሊሁ ለይስሐቅ ምእተ ወሰማንያ ዓመተ ወልህቀ ይስሐቅ ። | ፳፰ | (ያን ጊዜም) የይስሐቅ ዕድሜው መቶ ሰማንያ ነበር ፡ ይስሐቅም አረጀ ። |
| ወረሢአ ወፈጺሞ መዋዕሊሁ ሞተ ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ ወቀበርዎ ኤሳው ወያዕቆብ ደቂቁ ። | ፳፱ | አርጅቶም ዕድሜውን ጨርሶ ሞተ ፡ ከወገኖቹም ተጨመረ (ተቀበረ) ልጆቹ ዔሳውና ያዕቆብ ቀበሩት ። |
| **ምዕራፍ ፴፮ ።** | | **ምዕራፍ ፴፮ ።** |
| ወከመዝ ውእቱ ልደቱ ለኤሳው ወውእቱ ኤዶም ። | ፩ | የዔሳው ትውልዱ እንዲህ ነው ! እርሱም ኤዶም (ጉጉ ፈታዊ) ነው ። ዘፍ፡ ፳፭ ፴ ። |
| ወነሥአ ሎቱ አንስቲያ እምአዋልደ ከነአን ሐዳሰ ወ | ፪ | ዔሳው ከከነዓን ልጆች መራርጦ ሚስቶችን አገባ ፡ እነ |

ለተ ኤሎን ኬጥያዊ ወኤሌማ ወለተ ሐና ወልደ ሴቤዖ ኤውያዊ ።

፫ ወቤሴሞት ወለተ ይስማኤል እኅቱ ለናቡአት ።

፬ ወወለደቶ ሐዳሰ ለኤልፋዝ፥ ወቤሴሞት ወለደቶ ለራጉኤል ።

፭ ወኤሌማ ወለደቶሙ ለዮሔል ወለይጉሚል ወለቆሬ፣ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ለኤሳው እለ ተወልዱ ሎቱ በምድረ ከነአን ።

፮ ወነሥአ ኤሳው አንስቲያሁ ወደቂቆ ወአዋልዲሁ ወኵሎ ነበሬ ቤቱ ወኵሎ እንስሳሁ ወኵሎ ንዋዮ ዘአጥረየ በምድረ ከነአን፣ ወሖረ እምድረ ከነአን እምገጸ ያዕቆብ እኁሁ ።

፯ እስመ ብዙኅ ንዋዮሙ ወኢክህሉ ነቢረ ኅቡረ በእንተ ብዝኀ ንዋዮሙ ።

፰ ወኀደረ ኤሳው ውስተ ደብረ ሴይር፣ ወስሊሁ ኤሳው ኤዶም ውእቱ ።

፱ ወከመዝ ውእቱ ፍጥረቱ ለኤሳው አቡሆሙ ለኤዶም በደብረ ሴይር ።

፲ ወዝ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ኤሳው ኤልፋዝ ወልደ ሐዳሰ ብእሲተ ኤሳው፣ ወራጉኤል ወልደ ቤሴሞት ብእሲተ ኤሳው ።

፲፩ ወኮኑ ደቂቀ ኤልፋዝ ወልደ ኤሳው ቴማን፣ ወኤሞር፣ ወሰፍር፣ ወጎቶን፣ ወቄኔዝ ።

፲፪ ወቲምናሕ ዕቅብቱ ለኤልፋዝ ወልደ ኤሳው፣ ወለደት ሎቱ አማሌቅሃ፣ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ሐዳሰ ብእሲተ ኤሳው ።

፲፫ ወደቂቀ ራጉኤል ወልደ ኤሳው ፡ ናሖት ወዛራ ወሴን ወሞዛኅ፣ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ቤሴሞት ብእሲተ ኤሳው ።

፲፬ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሌማ ወለተ ሐና ብእሲተ ኤሳው ዘወለደት ለኤሳው ዮሔል ወይጉሚል ወቆሬ ።

፲፭ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሳው ።

፲፮ መሳፍንት ደቂቀ ኤልፋዝ በኵሩ ለኤሳው፣ ቴማን መስፍን፣ ወኤሞር መስፍን፣ ወሰፍር መስፍን፣ ወቀኔዝ መስፍን ።

፲፯ ወቆሬ መስፍን፣ ወጎቶን መስፍን፣ ወአማሌቅ መስፍን፣ እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ኤልፋዝ በምድረ ኤዶም እለ ተወልዱ እምነ ሐዳሰ ።

፲፰ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ራጉኤል ወልደ ኤሳው መሳፍንት፣ ናሖት መስፍን፣ ወዛራ መስፍን፣ ወሴን መስፍን፣ ወሞዛኅ መስፍን፣ እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ራጉኤል በምድረ ኤዶም እለ ተወልዱ እምነ ቤሴሞት ብእሲተ ኤሳው ።

፲፱ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሌማ ብእሲተ ኤሳው መሳፍንት፣ ዮሔል መስፍን፣ ወይጉሚል መስፍን፣ ወቆሬ መስፍን ።

፳ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሳው መሳፍንተ ኤዶም ።

፳፩ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ሴን ሖርያዊ እለ ይነብሩ ዲበ ምድር ።

ዚሁም የኬጥያዊው ሰው የኤሎን ልጅ ሐዳስ የኤውያው ሰው የሴቤስ ልጅ የሐና ልጅ ኤሌማ ።

የናቡዓት እኅት የይስማኤል ልጅ ቤሴሞት ናቸው ።

ሐዳስ ኤልፋዝን ወለደችው፣ ቤሴሞትም ራጉኤልን ወለደችው ። ዘፍ ፳፰ ፱ ። ፩ መዋ፣ ፯ ፴፭ ።

ኤሌማም ዮሔልን፣ ይጉሚልንና ቆሬን ወለደቻቸው በከነዓን አገር የተወለዱለት የዔሳው ልጆች እነዚህ ናቸው ።

ዔሳውም ሚስቶቹን፣ ወንዶቹንም ሴቶቹንም ልጆቹን ቤተ ሰቦቹን ሁሉ ከብቶቹንም ሁሉ፣ በከነዓን ያፈራውን ገንዘቡን ሁሉ ይዞ ከወንድሙ ከያዕቆብ ፊት ተለይቶ ከከነዓን አገር ተነሥቶ ሄደ ። ዘዳ፡ ፳፫ ፯ ። መዝ፡ ፴፱ ፲፪ ።

ገንዘባቸው ብዙ ስለሆነ ከገንዘባቸው ብዛት የተነሣ አንድነት መኖር አልቻሉምና ። ዘፍ፣ ፲፫ ፮፣ ፲፩ ።

ዔሳው (ከከነዓን ሄዶ) ሴይር በሚባል ተራራ ተቀመጠ፣ ይኸውም ዔሳው (ማለት) ጉምጁ ነው ። ዘፍ፣ ፴፪ ፫ ።

በሴይር ተራራ ያሉ የኤዶምያስ ሰዎች ያባቻቸው የዔሳው ትውልድ እንዲህ ነው ።

የዔሳው ልጆች ስማቸው ይህ ነው፤ የዔሳው ሚስት የሐዳስ ልጅ ኤልፋዝ፣ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት ልጅ ራጉኤል ናቸው ።

የዔሳው ልጅ የኤልፋዝ ልጆች ቴማን፣ ኤሞር፣ ሰፍር፣ ጎቶንና ቄኔዝ ናቸው ።

የዔሳው ልጅ የኤልፋዝ ዕቅብት ተምናህ አማሌቅን ወለደችለት ፤ የዔሳው ሚስት የሐዳስ ልጆች እነዚህ ናቸው ። ዘፀአ፡ ፲፯ ፰ ። ፩ ሳሙ፣ ፲፭ ፪ - ፫ ።

የዔሳው ልጅ የኤልፋዝ ልጆች ናሆት፣ ዛራ፣ ሴን፣ ሞዛህ ናቸው፣ የዔሳው ሚስት ቤሴሞት የወለደቻቸው ልጆች እሊህ ናቸው ።

ለዔሳው የወለደችለት የዔሳው ሚስት የሐና ልጅ ኤሌማ የወለደቻቸው ልጆች እሊህ ናቸው፤ ዮሔል፣ ይጉሚል፣ ቆሬ፣ ናቸው ።

የዔሳው ልጆች መሳፍንት እሊህ ናቸው ።

የዔሳው የበኩር ልጁ ኤልፋዝ የወለዳቸው ቴማን መስፍን፣ ኤሞር መስፍን፣ ሳፍር መስፍን፣ ቄኔዝ መስፍን፣ ናቸው ።

ቆሬ መስፍን፣ ጎቶን መስፍን፣ አማሌቅ መስፍን፣ በኤዶምያስ አገር ከሐዳስ የተወለዱ የኤልፋዝ መሳፍንት እሊህ ናቸው ።

የዔሳው ልጅ ራጉኤል የወለዳቸው መሳፍንት እሊህ ናቸው፤ ናሖት መስፍን፣ ዛራ መስፍን፣ ሴን መስፍን፣ ሞዛኅ መስፍን፣ ናቸው ፣ በኤዶም ምድር ከዔሳው ሚስት ከቤሴሞት የተወለዱ የራጉኤል መሳፍንት እሊህ ናቸው ።

የዔሳው ሚስት ኤሌማ የወለደቻቸው መሳፍንትም እሊህ ናቸው፤ ዮሔል መስፍን፣ ይጉሚል መስፍን፣ ቆሬ መስፍን ።

በኤዶምያስ መስፍንነት የተሾሙ የዔሳው ልጆች እሊህ ናቸው ።

በኤዶምያስ የሚኖሩ የሖርያ ወገን የሚሆኑ የሴን ልጆች እነዚህ ናቸው ።

| | | |
|---|---|---|
| ሎጣን፣ ወሶባን፣ ወሳበቅ፣ ወአናም፣ ወዲሶን ወኢሶር፣ ወእሉ እሙንቱ መሳፍንተ ሆርያዊ ደቂቀ ሴን ። | ፳፪ | ሎጣን፣ ሶባን፣ ሳበቅ፣ አናም፣ ዲሶንና ኢሶር ናቸው፣ የሆርያዊ መሳፍንት የሴን ልጆች እነዚህ ናቸው ። |
| እሉ እሙንቱ ደቂቀ ሎጣን ሐሪ፣ ወሐማን፣ ወእኅተ ሎጣን ትምናእ ። | ፳፫ | የሎጣንም ልጆች ሐሪ፣ ሐማን፣ የሎጣን እኅት ትምናእ ናቸው ። |
| ወደቂቀ ሶባን፣ አልዋን፣ ወማኔሐት፣ ወአቤል፣ ወሶፉ፣ ወአውናም ። | ፳፬ | የሶባንም ልጆች አልዋን፣ ማኔሐት፣ አቤል፣ ሶፉና አውናም ናቸው ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ሳበቅ ኢአ፣ ወአናን፣ ወውእቱ አናን ዘረከበ ለያሚን በገዳም (ወቀተሎ ለአንበሳ) እንዘ ይርዒ አእዱገ ለሳበቅ አቡሁ ። | ፳፭ | የሳበቅም ልጅ ኢአ፣ አናን፣ ናቸው፣ ይኸውም አናን በምድረ በዳ ያባቱን የሳበቅ አህዮች ሲጠብቅ ፍል ውኃን ያገኘ (አንበሳንም የገደለ) እሱ ነው ። ዘሌዋ፣ ፲፱ ፲፱ ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ አናን፣ ዲሳን፣ ወኤሌማ ወለተ አናን ። | ፳፮ | የአናንም ልጆች ዲሳን፣ የአናን ልጅ የምትሆን ኤሌማ ናቸው ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ዲሶን ሕምዳን፣ ወአስባን፣ ወቤያር፣ ወይትራን ወክራን ። | ፳፯ | የዲሶንም ልጆች ሕምዳን፣ አስባን፣ ቤያር፣ ይትራን ክራን፣ ናቸው ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሶር ብልሐን ወዛአን ወኢቃን ። | ፳፰ | የኤሶርም ልጆች ብልሐን፣ ዛአን፣ ኢቃን ናቸው ። |
| ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ዲሳን ዑስ፣ ወአራን ። | ፳፱ | የዲሳንም ልጆች ዑስ፣ አራን ናቸው ። |
| ወእሉ እሙንቱ መሳፍንተ ሆሪ፣ ሎጣን መስፍን፣ ወሶባን መስፍን፣ ወሳበቅ መስፍን፣ ወአናን መስፍን፣ ወዲሶን መስፍን፣ ወኢሶር መስፍን ። | ፴ | የሆሪም መሳፍንት፣ ሎጣን መስፍን፣ ሶባን መስፍን፣ ሳበቅ መስፍን፣ አናን መስፍን፣ ዲሶን መስፍን፣ ኢሶር መስፍን ናቸው ። |
| እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ሆሪ በበመሳፍንቲሆሙ ውስተ ምድረ ሴይር ። | ፴፩ | (አባታቸው) ሆሪ በሴይር አገር በየሹመት በየሹመታቸው መስፍን አድርጎ የሾማቸው የሆሪ መሳፍንት እነዚህ ናቸው ። |
| ወእሉ እሙንቱ ነገሥት እለ ነግሡ በኤዶም ዘእንበለ ይንግሥ ንጉሥ ለእስራኤል ። | ፴፪ | ለእስራኤል ንጉሥ ሳይነግሥ፣ በኤዶም የነገሡ ነገሥታት እነዚህ ናቸው ። |
| ወነግሠ በኤዶም ባላቅ ወልደ ቤያር ወስመ ሀገሩ ዲናባ ። | ፴፫ | የቤያር ልጅ ባላቅም በኤዶም ነገሠ፣ የአገሩም ስም ዲናባ ይባላል ። ፩ ዜና መዋ፣ ፩ ፵፫ ። ፩ ሳሙ፣ ፲ ፳፬ ። |
| ወሞተ ባላቅ ወነግሠ ህየንቴሁ ኢዮባብ ወልደ ዛራ ዘእምነ ባሱራ ። | ፴፬ | ባላቅም ሞተ፣ በሱም ፈንታ ከባሱራስ ወገን የሆነ የዛራ ልጅ ኢዮባብ ነገሠ ። |
| ወሞተ ኢዮባብ ወነግሠ ህየንቴሁ ሑሳም ዘእምነ ምድረ ቴማኒ ። | ፴፭ | ኢዮባብም ሞተ፣ በሱም ፈንታ የቴማን ተወላጅ የሆነ ሑሳም ነገሠ ። |
| ወሞተ ሑሳም ወነግሠ ህየንቴሁ አዳድ ወልደ ብዳድ ዘቀተሎሙ ለምድያም በሐቅለ ሞአብ ወስመ ሀገሩ ዐዊት ። | ፴፮ | ሑሳምም ሞተ፣ በሱም ፈንታ በሞዓብ አውራጃ የኤዶምያስን ሰዎች የወጋቸው የብዳድ ልጅ አዳድ ነገሠ፤ የአገሩም ስም ዐዊት ይባላል ። |
| ወሞተ አዳድ ወነግሠ ህየንቴሁ ሰምላ ዘእምነ መሥርቃ ። | ፴፯ | አዳድም ሞተ፣ በሱም ፈንታ ተተክቶ ከመሥርቃ ወገን የተወለደ ሰምላ ነገሠ ። |
| ወሞተ ሰምላ ወነግሠ ህየንቴሁ ሳኦል ዘእምነ ርአቦት እንተ ፈለግ ። | ፴፰ | ሰምላም ሞተ፣ በሱም ፈንታ ተተክቶ በወንዝ አጠገብ ያለች የርአቦት ተወላጅ የሆነ ሳኦል ነገሠ ። |
| ወሞተ ሳኦል ወነግሠ ህየንቴሁ በአለናን ወልደ አክቦር ። | ፴፱ | ሳኦልም ሞተ፣ በሱም ፈንታ የአክቦር ልጅ በአለናን ነገሠ ። |
| ወሞተ በአለናን ወልደ አክቦር ወነግሠ ህየንቴሁ አዳር ወስመ ሀገሩ ፍጉ ወስመ ብእሲቱ ምኤጠብኤል ወለተ መጥሬድ ወለተ ሚዘአብ ። | ፵ | የአክቦር ልጅ በአለናንም ሞተ የፍጉ አገር ተወላጅ የሆነ አዳር ነገሠ፣ የሚስቱም ስም የሚዘአብ ልጅ የመጥሬድ ልጅ ምኤጠብኤል ይባላል ። |
| ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለመሳፍንተ ዔሳው በበ ነገዶሙ ወበበብሔሮሙ ወበበአስማቲሆሙ ትምናእ መስፍን፣ ዐልዋ መስፍን፣ ኢቴት መስፍን ። | ፵፩ | በየነገዳቸው በየአገራቸውና በየስማቸው የዔሳው መሳፍንት ስማቸው ይህ ነው፤ ትምናእ መስፍን፣ ዓልዋ መስፍን፣ ኢቴት መስፍን ። ፩ ዜና መዋ፣ ፩ ፶፩ ። |
| ኤሌማ መስፍን፣ ኢላ መስፍን፣ ፊኖን መስፍን ። | ፵፪ | ኤሌማ መስፍን፣ ኢላ መስፍን፣ ፊኖን መስፍን ። |
| ቄኔዝ መስፍን፣ ቴማን መስፍን፣ ሚብሳር መስፍን ። | ፵፫ | ቄኔዝ መስፍን፣ ቴማን መስፍን፣ ሚብሳር መስፍን ። |
| መግዲኤል መስፍን፣ ዒራም መስፍን ። | ፵፬ | መግዲኤል መስፍን፣ ዒራም መስፍን ። |
| እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ኤዶም በበማኅደሮሙ ዘበምድሮሙ፣ ወለሊሁ ዔሳው አቡሆሙ ውእቱ ለኤዶም ። | ፵፭ | በአገራቸው በየማደሪያቸው የተሾሙ የኤዶም መሳፍንት እሊህ ናቸው፤ እሱ ዔሳውም ለኤዶምያስ ሰዎች አባታቸው ነው ። |

## ምዕራፍ ፴፯።

፩ ወነበረ ያዕቆብ ውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ነበረ አቡሁ ውስተ ምድረ ከነአን።

፪ ወከመዝ ውእቱ ፍጥረቱ ለያዕቆብ፡ ወኮኖ ለዮሴፍ ዐሠርቱ ወሰብዓቱ ዓመት ወይርዒ ምስለ አኀዊሁ አባግዐ አቡሁ ወወሬዛ ውእቱ ምስለ ደቂቀ ባላ ወምስለ ዘለፋ አንስትያ አቡሁ ወአምጽኡ ላዕለ ዮሴፍ ውዴተ እኪተ ኀበ አቡሆሙ እስራኤል።

፫ ወያዕቆብሰ ያፈቅሮ ለዮሴፍ እምኵሎሙ ደቂቁ እስመ በርስዓኑ ወለዶ ወገብረ ሎቱ ክዳነ ዘኅብረ ዐሥቅ።

፬ ወሰበ ርእዩ አኀዊሁ ከመ ኪያሁ ያፈቅር አቡሆሙ እምኵሎሙ ጸልእዎ ወኢክህሉ ተናግሮቶ ሠናየ።

፭ ወሐለመ ዮሴፍ ሕልመ ወነገሮሙ ለአኀዊሁ።

፮ ወይቤሎሙ ስምዕዎ ለዝንቱ ሕልም ዘሐለምኩ።

፯ እሬኢ ከላስስቲክሙ ዘዘኢአክሙ ማእከለ ገዳም ወተንሥአ ክልስስት ዘዚአየ ወቆመ ወተመይጡ ከላስስት ዘዚአክሙ ወሰገዱ ለዘዚአየ ክልስስት።

፰ ወይቤልዎ ነጊሠኑ ትነግሥ ላዕሌነ ወሚመ እግዚእኑ ትከውነነ ወአፈድፈዱ ዓዲ ጸሊአቶ በእንተ ሕልሙ ወበእንተ ነገሩ።

፱ ወደገመ ዓዲ ወርእየ ሕልመ ወነገሮ ለአቡሁ ወይቤሎሙ ናሁ ሐለምኩ ካልአ ሕልመ ወከመዝ ሕልሙ ፀሐይ ወወርኅ ወዐሠርቱ ወአሐዱ ከዋክብት ይሰግዱ ሊተ።

፲ ወገሠፆ አቡሁ ወይቤሎ ምንት ውእቱ ዝንቱ ሕልምከ ዘሐለምከ ወሶበ አሐዝብ ንመጽእ አነ ወእምከ ወአኀዊከ ወንሰግድ ለከ ዲበ ምድር።

፲፩ ወቀንኡ ላዕሌሁ አኀዊሁ፡ ወአቡሁሰ ዐቀበ ለዝንቱ ነገር በልቡ።

፲፪ ወሖሩ አኀዊሁ ይርዐዩ አባግዐ አቡሆሙ ውስተ ሴኬም።

፲፫ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ አኮኑ አኀዊከ ውስተ ሴኬም፡ ነዓ እልአከ ኀቤሆሙ፡ ወይቤሎ አሆ ነየ።

፲፬ ወይቤሎ ሑር ርኢ ለእመ ዳኅንኑ አኀዊከ ወአባግዒሆሙኒ ወዜንወኒ፡ ወፈነዎ እምነ ቈላተ ኬብሮን ወበጽሐ ውስተ ሴኬም።

፲፭ ወረከቦ አሐዱ ብእሲ እንዘ የዓይል ወይሰክዕ ውስተ ገዳም ወተስእሎ ወይቤሎ መነ ተኀሥሥ።

፲፮ ወይቤሎ ዮሴፍ አይድዐኒ አይቴ ይርዕዩ አኀውየ።

፲፯ ወይቤሎ ውእቱ ብእሲ ግዕዙ እምዝየሰ ወሰማዕክዎሙ ባሕቱ ይብሉ ንሑር ዶታዮን፡ ወሖረ ዮሴፍ ወተለዎሙ ለአኀዊሁ ወረከቦሙ በዶታዮን።

፲፰ ወቀደሙ ርእዮቶ እምርኁቅ ዘእንበለ ይቅርብ ኀቤሆሙ ወመከሩ ለቀቲሎቱ።

## ምዕራፍ ፴፯።

ያዕቆብ በከነዓን ውስጥ አባቱ ይኖርባት በነበረች አገር ኖረ።

የያዕቆብም ትውልዱ እንዲህ ነው፤ ለዮሴፍ (ያን ጊዜ) ዓሥራ ሰባት ዓመት ሆኖት ነበር፡ ከወንድሞቹም ጋር ያባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር፡ እንደ አባቱ ሚስቶች እንደ ባላና እንደዘለፋ ልጆችም ወጣት ነበር፡ (በዚያ ወራት ወንድሞቹ) በአባታቸው በእስራኤል ዘንድ ክፉ ነገርን አመጡ።

ያዕቆብ ግን በስተ እርጅናው ወልዶታልና ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር፡ አራት ኅብር ያለው ጌጸኛ ልብስም አድርጎለት ነበር። ዘፍ፡ ፳፰ ፱።

አባታቸው ያዕቆብም ወንድሞቹ ከወንድሞቹ ሁሉ አብልጦ እንደሚወደው በዩ ጊዜ ዮሴፍን ጠሉት፡ በጎ ነገርንም መናገሩን አልቻሉም። ፩ ዜና መዋ፡ ፩ ፴፭።

ዮሴፍም ሕልምን አይቶ ለወንድሞቹ ነገራቸው።

ይህን ያለምኩትንም ሕልም ስሙት አላቸው።

በምድረ በዳ መከከል የያንዳንዳችሁ ነዶዎችን አያለሁ፡ በኔ በኩል ያለው ነዶ ተነሥቶ ሲቆም [በናንተ በኩል ያሉት ነዶዎች ተመልሰው (መጥተው)፤ ሲሰግዱለት አያለሁ አላቸው። ዘፍ፡ ፵፪ ፮ ፱። ፵፫ ፳፮።

በኛ ላይ ትነግሥብን ይሆን፤ ብለው ሕልምን ስለማየቱና ስለመናገሩ ዳግመኛም ክፉኛ ተጣሉት።

ዳግመኛ ሕልም አይቶ እነሆ ሌላ ሕልም አየሁ ብሎ ላባቱ ነገረው፡ ሕልሙም እንዲህ ነው፤ ፀሐይ ጨረቃና ዓሥራ አንድ ከዋክብት ሲሰግዱልኝ አያለሁ።

አባቱም ይህ ያለምከው ሕልም ምንድር ነው፤ ብሎ ገሠፀው፡ እኔ ሳስበው እኔና እናትህ ዐሥራ አንዱ ወንሞችህ መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆናል፤ (ብሎ ተረጐመለት)። ዘፍ፡ ፵፮ ፵፱።

ወንድሞቹም ቀኑበት፡ አባቱ ግን ይህን ነገር በልቡናው አኑሮ ይጠብቀው ነበር። ዳን፡ ፯ ፳፰። ግ፡ ሐ፡ ፯ ፱።

ወንድሞቹም ያባታቸውን በጎች ይጠብቁ ዘንድ ወደ ሴኬም ሄዱ።

እስራኤልም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ ወንድሞችህ በሴኬም አሉና፡ ወደነሱ እልክህ ዘንድ ና አለው፡ (ዮሴፍም) እነሆኝ አለሁ አለው።

ወንድሞችህ በጎቻቸውም ደኅና እንደሆኑ አይተህ ንገረኝ ብሎ ከኬብሮን ቈላ ላከው፡ እሱም ወደ ሴኬም ደረሰ። ዘፍ፡ ፲፫ ፲፰። ኢያሱ ፲፬ ፲፬ - ፲፭።

በምድረ በዳም ሲዞር ሲባክን አንድ ሰው አገኘ፡ እሱም ማንን ትሻለህ፤ ሲል ጠየቀው።

ዮሴፍም ወንድሞቹ (በጎች) የሚጠብቁበት ቦታ ወዴት ነው፤ አለው። መኃ፡ ፩ ፯።

ያም ሰው ከዚህስ ተጕዘዋል ወደ ዶታይን እንሂድ ሲሉም ሰምቻቸዋለሁ አለው፡ ዮሴፍም ወንድሞቹን ተከትሏቸው ሄዶ በዶታይን አገኛቸው። ፪ ነገ፡ ፮ ፲፫።

ገናም ወደነሱ ሳይቀርብ ከሩቅ ሆነው አይተዉት እንግደለው ብለው ተማከሩ። ፩ ሳሙ፡ ፲፱ ፩።

| | | |
|---|---|---|
| ወተባሀሉ አሐዱ ምስለ ካልኡ ነዋ ዝኩ ሐላሚ ። | ፲፱ | እንዱም ከንዱ ጋር ሁነው ያ ሐላሚ እነሆ መጣ ተባባሉ ። |
| ንዑ ትቅትሎ ወንግድፎ ውስተ አሐዱ ግብ ወንበል አርዌ እኩይ በልዖ ወንርአይ ምንት እማንቱ ሕልሚሁ ። | ፳ | ኑ ገድለን በአንድ ጉድጓድ ጥለን ክፉ አውሬ በላው እንበል፣ (ያን ጊዜ) ሕልሞቹ ምን እንደሚሆኑ እንይ ተባባሉ ። ምሳ፥ ፩ ፲፭ ። ፩ ዮሐ፥ ፫ ፲፪ - ፲፫ ። |
| ወሰሚዖ ሮቤል አድኅኖ እምእዴሆሙ ወይቤ ሎሙ ኢትቅትሉ ነፍሰ፡ ወኢትክዐዉ ደሞ፡ ደይዎ ኀበ ዝንቱ ዓዘቅት ዘውስተ ገዳም፤ ወበሕቱ እዴክሙ ኢታውርዱ ላዕሌሁ ። | ፳፩ | ሮቤልም በየው ጊዜ ከእጃቸው አዳነው፣ ነፍሱን አትግደሉ፣ ደሙንም አታፍሱ፣ በምድረ በዳ ካለው ከዚህ ጉድጓድ ጣሉት እንጂ እጃችሁ አትጣሉበት አላቸው ። |
| ወከመዝ ይቤ ሮቤል ከመ ያድኅኖ እምእዴሆሙ ወያግብኦ ኀበ አቡሁ ። | ፳፪ | ሮቤል እንዲህ ማለቱ ከእጃቸው አድኖ ወደ አባቱ እመልሰዋለሁ ብሎ ነው ። |
| ወእምዝ ሶበ በጽሐ ዮሴፍ ኀቤሆሙ ሰለብዎ ክዳኖ ዘዐሥቅ ዘይለብስ ። | ፳፫ | ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወደነሱ በደረሰ ጊዜ፣ የለበሰውን አራት ኅብር የሆነ ልብሱን ገፈፉት ። |
| ወነሥእዎ ወወረውዎ ውስተ ዐዘቅት ወዐዘቅትሰ ሐዳስ ወአልቦቱ ማይ ። | ፳፬ | ወስደውም ወርውረው ወደ ጉድጓድ ጣሉት፣ ጉድጓዲቱም አዲስ ነበረች ውኃም አልነበራትም ። |
| ወነበሩ ይብልዑ እክለ፡ ወሶበ አልዐሉ አዕይንቲሆሙ ርእዩ ናሁ ነጋድያን ይመጽኡ እምገለዓድ ወይስማኤላውያን እሙንቱ ወአሡዓን አግማሊሆሙ አፈዋተ ወርጤነ ወማየ ልብን ወየሐውሩ ያውርዱ ብሔረ ግብጽ ። | ፳፭ | እንጀራም ሊበሉ ተቀመጡ፣ ዓይናቸውን አቅንተው ቢያዩ ነጋዴዎች እነሆ ከገለዓድ ሲመጡ አዩ፣ እነሱም ይስማኤላውያን ናቸው፣ ግመሎቻቸውም ሽቱን በለሳንንና ከርቤንም ተጭነው ነበር፣ ወደ ግብጽ አገር ለመውረድ ይሄዱ ነበር ። ሆሴ ፯ ፯ ። ኤር፥ ፰ ፳፪ ። |
| ወይቤሎሙ ይሁዳ ለአኀዊሁ ምንት ይበቍዐነ ለእመ ቀተልናሁ ለእኁነ ወኀባእነ ደሞ ። | ፳፮ | ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ ወንድማችንን ገድለን ደሙን ብንሠውረው ምን ይረባናል ። |
| ንዑ ንሢጦ ኀበ እሉ ይስማኤላውያን ወእዴነሰ ኢናውርድ ላዕሌሁ እስመ እኁነ ውእቱ ወሥጋነ፡ ወሰምዕዎ አኀዊሁ ዘይቤሎሙ ። | ፳፯ | ኑ፣ ለነዚህ ይስማኤላውያን እንሽጠው፣ ወንድማችን ሥጋችን ነውና እጃችንን ግን በርሱ ላይ አንጣል አላቸው ወንድሞቹም የነገራቸውን ነገር ሰሙት፣ ፩ ሳሙ፥ ፲፰ ፲፯። |
| ወእንዘ የኀልፉ እሙንቱ ይስማኤላውያን ሰሐብዎ አኀዊሁ ወአውፅእዎ እምዐዘቅት ወሤጥዎ ለዮሴፍ ኀበ ይስማኤላውያን በዕሥራ ዲናር፡ ወወሰድዎ ለዮሴፍ ብሔረ ግብጽ ። | ፳፰ | እነዚያም የይስማኤላውያን ነጋዴዎች ሲያልፉ ወንድሞቹ ከጉድጓድ ጎትተው አውጥተው ለይስማኤላውያን በሃያ ብር ሸጡት፣ እነሱም ዮሴፍን ወደ ግብጽ አገር ወሰዱት ። |
| ወገብአ ሮቤል ኀበ ዐዘቅት ወሶበ ኢረከቦ ለዮሴፍ ሠጠጠ አልባሲሁ ። | ፳፱ | ሮቤልም ወደ ጉድጓድ ተመልሶ ዮሴፍን በጣው ጊዜ ልብሶቹን ቀደደ ። መሳ፥ ፯ ፫ ። መዝ፥ ፲፭ ፲፯ ። |
| ወሐረ ሮቤል ኀበ አኀዊሁ ወይቤሎሙ ኢሀሎ ወልድ ውስተ ዐዘቅት ወአይቴ አሐውር እንከ አነ ። | ፴ | ሮቤል ወደ ወንድሞቹ ሄዶ ልጁ በጉድጓዱ የለም፣ እኔ እንግዲህ ወዴት እሄዳለሁ አላቸው ። ኤር፥ ፴፩ ፲፭ ። |
| ወነሥኡ ክዳኖ ዘዐሥቅ ወሐረዱ ላዕሌሁ ማሕስአ ጠሊ ወመልእዎ ደሞ ለክዳኑ ። | ፴፩ | (ከዚህ በኋላ) አራት ኅብር ያለውን ልብሱን ወስደው የፍየል ጠቦት አርደው በልብሱ ላይ ደም መሉበት ። |
| ወወሰዱ ኀበ አቡሆሙ ወይቤልዎ ዘንተ ልብሰ ረከብነ ወርኢ ለእመ ውእቱ ክዳኑ ለወልድከ ወለእመ ኢኮነ ። | ፴፪ | ወደ አባታቸውም ወስደው ይህን ልብስ አገኘነው የልጅህ ልብስም እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ (እዩ) እየው አሉት ። |
| ወአእመረ ወይቤ ክዳኑ ለወልድየ ውእቱ፡ ወአርዌ እኩይ በልዖ ወሠጠጦ ለዮሴፍ ። | ፴፫ | እርሱም አውቆ ይህ የልጄ ልብስ ነው ክፉ አውሬ ነጥቆ በልቶታል አለ ። |
| ወሠጠጠ አልባሲሁ ያዕቆብ ወለብሰ ሠቀ ወቅንተ ውስተ ሐቌሁ ወላሐዎ ለወልዱ ብዙኀ መዋዕለ ። | ፴፬ | ያዕቆብም ልብሱን ቀድዶ ማቅ ለበሰ፣ በወገቡም ታጥቆ ለልጁ ብዙ ቀን አለቀሰለት ። ፪ ሳሙ፥ ፲፱ ፲፯ ። |
| ወተጋብኡ ደቂቁ ወአዋልዲሁ ወመጽኡ ወአስተብቍዕዎ ለአቡሆሙ ከመ ያንግፍዎ ላህ ወአበዮሙ ነጊፈ ላህ ወይቤሎሙ ዳእሙ እወርድ ውስተ መቃብር ኀበ ወልድየ እንዘ እላሁ፡ ወበከዮ አቡሁ ። | ፴፭ | ወንዶችና ሴቶች ልጆቹም ተሰብስበው መጥተው ልቅሶውና ኀዘኑ ይበቃሃል ብለው አባታቸውን ማለዱት ስልጄ እያዘንኩና እያለቀስኩ ወደ መቃብር እወርዳለሁ እንጂ ልቅሶዬን አልተውም ብሎአቸው፣ አባቱ አለቀሰ ። |
| ወአልአክቱሰ ይስማኤላውያን ሤጥዎ ለዮሴፍ ብሔረ ግብጽ ለጲጥፋራ ሊቀ መበስላኒሁ ለፈርዖን ። | ፴፮ | እነዚያም ይስማኤላውያን ወደ ግብጽ ወርደው ለፈርዖን ቢትወደድ ለጲጥፋራ ሸጡት ። |

| ምዕራፍ ፴፰ ። | | ምዕራፍ ፴፰ ። |
|---|---|---|
| ወእምዝ ወረደ ይሁዳ በእማንቱ መዋዕል እምኀበ አኃዊሁ ወኀደረ ኀበ አሐዱ አዶላማዊ ዘስሙ ኤራስ ። | ፩ | ከዚህ በኋላ ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ በዚያ ወራት ወርዶ ስሙ ኤራስ ወደ ሚባል ወደ አንዱ አዶሎማዊው ሰው አደረ ። |
| ወርእየ አሐተ ወለተ አሐዱ ብእሲ ከነናዊ ወስማ ሤዋ ወነሥአ ወአውሰባ ። | ፪ | (በዚያም) ይሁዳ አንዲት የአንድ ከነናዊ ልጅ አየ ፣ ስሟም ሴዋ ይባላል ፣ ወስዶም አገባት ። |
| ወፀንሰት ወወለደት ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ኤር ። | ፫ | (እሷም) ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ስሙንም ኤር አለችው ። ዘኍ ፳፮ ፲፱ ። |
| ወፀንሰትዳግመ ወወለደት ወልደ ወሰመየቶ ስሞ አውናን። | ፬ | ዳግመኛም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ስሙንም አውናን አለችው ። |
| ወዓዲ ደገመት ወወለደት ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ሴሎም ወአመ ወለደቶሙ ሀለወት በውስተ ብሔር ዘስሙ ኬሴቤ ። | ፭ | እንደገና ደግሞ ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ስሙንም ሴሎም አለችው ፣ በወለደቻቸውም ጊዜ ኬሴቤ በሚባል አገር ተቀመጠች ። |
| ወነሥአ ይሁዳ ብእሲተ እንተ ስማ ትእማር ለኤር በኵሩ ። | ፮ | ይሁዳ ለበኩር ልጁ ለኤር ስሟ ትእማር የሚባል ሚስትን አመጣለት ። |
| ወኮነ ኤር በኵሩ ለይሁዳ እኩየ በቅድመ እግዚአብሔር ፣ ወቀተሎ እግዚአብሔር ። | ፯ | የይሁዳ የበኩር ልጁ ኤርም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሰው ሆነ ፣ እግዚአብሔርም ገደለው ። |
| ወይቤሎ ይሁዳ ለአውናን ባእ ኀበ ብእሲተ እኁከ ወተሐመዋ ወአቅም ዘርአ ለእኁከ ። | ፰ | ይሁዳም አውናንን ወደ ወንድምህ ሚስት ግባ ፡ አግባትም ፡ ለወንድምህ ለኤርም ዘር ተካለት አለው ። |
| ወሶበ አእመረ አውናን ከመ ኢኮነ ሎቱ ዘርአ ሶበ ቦአ ኀበ ብእሲተ እኁሁ ይክዑ ዘርአ ዲበ ምድር ከመ ኢየሀብ ዘርአ ለእኁሁ ። | ፱ | አውናን ዘሩ ለርሱ እንዳልሆነ አውቆ ወደ ወንድሙ ሚስት በገባ ጊዜ ለወንድሙ ልጅ እንዳይተካለት ዘሩን በምድር ላይ ያፈሰው ነበር ። ዘዳ፣ ፳፭ ፮ ። |
| ወእኩየ ኮነ ውእቱኒ ቅድመ እግዚአብሔር እስመ ከመዝ ገብረ ወቀተሎ ሎቱኒ ። | ፲ | እሱም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆነ ፣ እንደዚያ (እን ደ ወንድሙ) አድርጓልና እሱንም (እግዚአብሔር) ቀሠፈው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፲፱ ። |
| ወይቤላ ይሁዳ ለትእማር መርዓቱ ንበሪ መበለተኪ ውስተ ቤተ አቡኪ እስከ ይልህቅ ሴሎም ወልድየ እስመ ይቤ ዮጊ ይመውተኒ ዝኒ ከመ አኃዊሁ ፣ ወሖረት ትእማር ወነበረት ቤተ አቡሃ ። | ፲፩ | ይሁዳም ምራቱ ትእማርን ልጄ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ ሂደሽ ባባትሽ ቤት ጋለሞታ ሁነሽ ተቀመጪ አላት ፣ እርሱም እንደ ወንድሞቹ ይሞትብኛል ብሎአልና ፣ ትእማርም ሂዳ ባባቷ ቤት ተቀመጠች ። ዘሌዋ፣ ፳፪ ፲፫ ። |
| ወሶበ ተፈጸመ መዋዕሊሃ ሞተት ሤዋ ብእሲተ ይሁዳ ወነጊፎ ላሀ ይሁዳ ዐርገ ኀበ ይቀርፅ አባግዒሁ ውእቱ ወኤራስ ኖላዊሁ አዶላማዊ ውስተ ቴምናታ ። | ፲፪ | ዘመኗም በተፈጸመ ጊዜ የይሁዳ ሚስት ሴዋ ሞተች ይሁዳም ልቅሶዋን ጨርሶ ከአዶሎማዊው ሰው ከበግ መል ከኛው ከኤራስ ጋር በጎቹን ወደሚሸልትበት ወደ ቴምታ ወጣ ። ፪ ሳሙ፣ ፲፫ ፴፱ ። |
| ወአይድዕዋ ለትእማር መርዓቱ ወይቤልዋ ናሁ ሐሙኪ የዐርግ ውስተ ቴምናታ ይቀርፅ አባግዒሁ ። | ፲፫ | እነሆ አማትሽ በጎቹን ሊያሸልት ወደ ቴምናታ ይወጣል ብለው ለምራቱ ለትእማር ነገሯት ፡ ኢያ፣ ፲፭ ፲-፶፯። |
| ወኀደገት አልባሲሃ ዘመበለታ ወለብሰት ሞጣሕታ ወተከድነት ወነበረት ውስተ አንቀጽ ዘፍኖተ ቴምናታ ፣ እስመ ርእየት ከመ ልሀቀ ሴሎም ወውእቱሰ ኢፈቀደ የሀባ ኪያሃ ትኩኖ ብእሲተ ። | ፲፬ | ሴሎም እንዳደገ አይታለችና እሱም ሚስት ልትሆ ነው እሷን ለሴሎም ሊሰጠው እንዳልወደደ አውቃለችና የመበለትነትዋን ልብስ አውልቃ ሰርመዴዋን ለብሳና ተጐ ናጽፋ በቴምናታ መንገድ ዳር ባለ በር ተቀመጠች ። |
| ወሶበ ርእየ ይሁዳ አምሰላ ዘማ እስመ ተገልበበት ገጻ ወኢያእመራ ። | ፲፭ | ይሁዳም ፊቷን ተሸፋፍና ስለነበረች አላወቃትምና ዘማን አስመሰላት ። |
| ወተግኅሠ ኀቤሃ እምውስተ ፍኖት ወይቤላ አብእኒ ኀቤኪ እስመ ኢያእመረ ከመ ብእሲተ ወልዱ ይእቲ ወትቤሎ ምንተ ትሁበኒ እመ ቦእከ ኀቤየ ። | ፲፮ | ያን ጊዜ ከጐዳናው ወጥቶ (ጐራ ብሎ) የልጁ ሚስት እንደሆነች አላወቀምና ወዳንቺ ልግባ አላት ፣ (እሷም) ወ ደኔ ብትገባ ምን ትሰጠኛለህ፤ አለችው ። |
| ወይቤላ እፌኑ ለኪ ማሕስአ ጠሊ እምውስተ አባግዕየ ፣ ወትቤሎ ሀበኒ አኅዞ እስከ ትፌኑ ሊተ ። | ፲፯ | እሱም ከበጎቼ ለይቼ የፍየል ጠቦትን እልክልሻለሁ አላ ት ፣ (እሷም) እስክትልክልኝ ድረስ መያዣ ስጠኝ አለችው። |
| ወይቤላ ምንተ እሁበኪ አኅዞ ፣ ወትቤሎ ኀልቀተከ ፣ ወቆብዐከ ፣ ወበትረከ ዘውስተ እዴከ ፣ ወወሀባ ወቦአ ኀቤሃ ወፀንሰት ። | ፲፰ | ምን መያዣ ልስጥሽ፤ አላት ፣ ቀለበትህን ኩፌትህንና በጅህ ያለው በትርህን (ስጠኝ) አለችው ፣ ሰጥቶ ወደርሷ ገባ ፣ ፀነሰችም ። |

፲፱ ወተንሥአት ወሖረት ወአንበረት ውእተ አልባሲሃ ወለብሰት አልባሰ መበለታ ።

(ከዚህ በኋላ) ተንሥታ ሄደች፡ የለበሰችውን ልብስ ዘማ አውልቃ የድኅነት ልብሷን ለበሰች ።

፳ ወፈነወ ላቲ ይሁዳ ውእተ ማሕስአ ጠሊ ምስለ ኖላዊሁ አዶላማዊ ከመ ይንሣእ አኅዞ እምኀበ ይእቲ ብእሲት ወኢረከባ ።

ይሁዳም መያዣውን ከዚያች ሴት ሊቀበል ያን የፍየል ጠቦቱን ከበግ መልከኛው ከአዶሎማው ሰው ጋር ሰደደላት፡ ነገር ግን አላገኛትም ።

፳፩ ወተስእሎ ውእቱ ሰብአ ውእቱ ብሔር ወይቤ፡ አይቴ ይእቲ ዘማ እንተ ነበረት ውስተ ፍኖት፡ ወይቤልዎ ኢሀለወት ዝየ ዘማ ።

እርሱም በጐዳና ዳር ተቀምጣ የነበረች ያች ዘማ የትናት፤ ብሎ የአገሩን ሰዎች ጠየቀ፡ በዚህስ በታ ዘማ የለችም አሉት ።

፳፪ ወገብአ ኀበ ይሁዳ ወይቤሎ ኢረከብክዋ ወሰብአ ውእቱኒ ብሔር ይቤሉኒ ኢሀለወት ዝየ ዘማ ።

ወደ ይሁዳም ተመልሶ አላገኘኋትም የአገሩም ሰዎች በዚህስ ዘማ የለችም አሉኝ አለው ።

፳፫ ወይቤ ይሁዳ ኅድግዎ ላቲ ከመ ኢይስሐቁ ላዕሌነ ፈነውኩ አንሰ ማሕስአ ወሰበ ኢረከብክሃስ ከነ ሊተ ።

ይሁዳም (ሰዎች) እንዳይዘብቱብን ተዉላት አለ፡ የፍየል ጠቦት ላክሁ፡ ካላገኘሃት ግን ለኔ ይሆናል አለ ።

፳፬ ወእምዝ እምድኅረ ሠለስቱ አውራኅ ዜነውዎ ለይሁዳ ወይቤልዎ ዘመወት ትእማር መርዓትከ ወናሁ ፀንሰት በዝሙት፡ ወይቤ ይሁዳ ያውፅእዋ ወያውዕይዋ በእሳት ።

ከዚህ በኋላ ከሦስት ወር በኋላ ትእማር ምራትህ ሰሰነች እነሆም ፀነሰች ብለው ነገሩት፡ ይሁዳም ከከተማ (በእፍአ) አውጥተው በእሳት ያቃጥሏት ብሎ አዘዘ ።

፳፭ ወእንዘ ይወስድዋ ለአከት ኀበ ሐሙሃ ወትቤሎ ዝንቱአ ዘመኑአ ወዘአይኑአ ብእሲእ ዝንቱአ ዕንስአ ወትቤሎ ርኢአ ዘንተአ ቀብሀአ ወዘንተአ በትረአ ።

ሊወስዱዋትም ወደ አማቷ እንዲህ ብላ ላከች፡ ይህ ኩፌት፡ ይህ በትር፡ የማን ነው፤ ይህስ ዕንስ የማን ሰው ነው እይ ብላ ላከችበት ።

፳፮ ወርእየ ይሁዳ ወይቤ ጸድቀት ትእማር እምኔየ እስመ ኢወሀብክዋ ሴሎምሃ ወልድየ፡ ወኢደገመ ይሁዳ ቀሪበ ቀሪበታ ።

ይሁዳም፡ የላከችለትን አይቶ ከኔ ይልቅ ትእማር ረታች ልጄ ሴሎምን አልሰጠኋትምና፡ ከዚህ በኋላ መግደሏን ተወ፡ ይሁዳም ዳግመኛ አልደረሰባትም ።

፳፯ ወሰበ ቀርበ ወሊዶታ ናሁ ሀለዉ መንታ በውስተ ከርሣ ።

መውለጂያም በቀረበ ጊዜ እነሆ በማኅፀኗ ውስጥ ሁለት መንታ (ልጆች) ነበሩ ።

፳፰ ወእምዝ እንዘ ትወልድ አውፅአ እዴሁ አሐዱ ወነሥአት መወልዲት ፈትለ ቀይሐ ወአሰረት ውስተ እዴሁ ወትቤ ዝንቱ ይቀድም ወፂአ ።

ከዚህ በኋላ ስትወልድ (ከሁለቱ) አንዱ እጁን አወጣ፡ አዋላጂቱም ቀይ ፈትል አምጥታ (በአውራ ጣቱ) በእጁ አሰረችለት፡ ይህ አስቀድሞ ይወለዳል ስትል ነው ።

፳፱ ወሰበ አሰሰለት እዴሃ ናሁ ወፅአ እኁሁ ወትቤ ዕፁብ ውእቱ ወሰመየቶ ስሞ ፋሬስ ።

(አዋላጂቱ) እጅዋን በነሣችለት ጊዜ እነሆ ወንድሙ ተወለደ፡ ይህ ነገር ድንቅ ነው ስትልም ስሙን ፋሬስ አለችው ።

፴ ወእምድኅሬሁ ወፅአ እኁሁኒ ዘተአሰረ እዴሁ ወሰመየት ስሞ ዛራ ።

ከሱም ቀጥሎ ጣቱ በቀይ ፈትል የታሰረ ወንድሙ ተወለደ፡ ስሙንም ዛራ አለችው ።

ምዕራፍ ፴፱ ።

፩ ወዮሴፍሰ ወረደ ብሔረ ግብጽ ወተሣየጠ ጲጥፋራ ኅጽው ለፈርዖን ሊቀ መበስላኒሁ ውእቱ ብእሲ ግብጻዊ እምእደ ይስማኤላውያን እለ አውረድዎ ህየ ።

ዮሴፍ ተሸጦ ወደ ግብጽ አገር ወረደ፡ የፈርዖን ባለሟል የአበዛዎች አለቃን የሆነ የግብጽ ሰው ጲጥፋራም ወደ ግብጽ ከወረዱት ይስማኤላውያን እጅ ገዛው ።

፪ ወሀሎ እግዚአብሔር ምስለ ዮሴፍ ወከነ ብእሴ ብፁዐ ወተሠይመ ላዕለ ቤተ እግዚኡ ።

እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበርና የተመሰገነ ሰው ሆነ፡ በጌታውም ቤት ላይ ተሾመ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፱ ።

፫ ወሰበ ርእየ እግዚኡ ከመ ሀሎ እግዚአብሔር ምስሌሁ ወኵሎ ዘገብረ ይሤርሕ እግዚአብሔር በእዴሁ ሤሞ ላዕለ ኵሉ ቤቱ፡ ወአወፈዮ ኵሎ ዘቦ ለዮሴፍ ።

ጌታውም እግዚአብሔር ከርሱ ጋር እንዳለ የሠራውንም ሥራ ሁሉ በእጁ እንደሚያከናውንለት በየ ጊዜ በቤተ ሰቡ ላይ ሾመው፡ ያለውንም (ገንዘብ) ሁሉ ለዮሴፍ ሰጠው ። መዝ፡ ፩ ፫ ።

፬ ወረከበ ዮሴፍ ሞገሰ በቅድመ እግዚአብሔር እስመ ያሠምሮ ።

ዮሴፍ ደስ አሰኝቶታልና በጌታው ፊት ባለ ሟልነትን አገኘ ።

፭ ወእምዝ እምድኅረ ተሠይመ ላዕለ ኵሉ ቤቱ ባረከ እግዚአብሔር ለውእቱ ግብጻዊ በእንተ ዮሴፍ፤ ወከነ በረከተ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ።

ከዚህ በኋላ፡ ዮሴፍ በሰ ቤቱ ሁሉ ከተሾመ በኋላ በዮሴፍ ምክንያት ያንን ግብጻዊ እግዚአብሔር አከበረው፡ የእግዚአብሔርም በረከት በላዩ ላይ አደረ ።

፮ ወኵሎ ንዋዮ ዘሐቅል ወዘሀገር፡ አግብአ ኵሎ ዘቦ ውስተ እዴሁ ለዮሴፍ ወአልቦ ዘየአምር ውእቱ ዘሀሎ

በገጠር በከተማም ያለው ገንዘቡ ሁሉ ለዮሴፍ በእጁ አስረከበው ከሚበላውም እኽል በቀር ያለውን ገንዘቡ ሁሉ

ንዋየ ዘእንበለ እክል ዘይበልዕ፤ ወሠናይ ውእቱ ዮሴፍ ወላህይ ርእየተ ገጹ ጥቀ ።

የሚያውቀው አልነበረም፤ ዮሴፍም ያማረ ይልቁንም የፊቱ መልክ ውብ ነበር ። ፩ ሳሙ ፲፮ ፲፪ ።

፯ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር ወደየት አዕይንቲሃ ላዕለ ዮሴፍ ብእሲተ እግዚኡ ወትቤሎ ስክብ ምስሌየ ።

ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ፤ የጌታው ሚስት ዓይኗን በዮሴፍ ላይ ጣለች ከኔም ጋር ተኛ አለችው ።

፰ ወአበየ ወይቤላ እግዚእየ አግብአ ሊተ ኵሎ ዘበ ውስተ እዴየ ወአልቦ ዘየአምር ዘውስተ ቤቱ ወኢምንትኒ ።

ጌታዬ ያለውን ገንዘቡ ሁሉ ለኔ በእጄ አስረክቦኛል፤ በቤቱ ካለው ገንዘቡ ሁሉ ምንም የሚያውቀው የለም ብሎ እምቢ አላት ።

፱ ወአልቦ ዘሀሎ ውስተ ዝ ቤት ዘኢኮነ ብውሐ ሊተ ዘእንበሌኪ፤ እስመ ብእሲቱ አንቲ ወእፎ እንከ እገብሮ ለዝንቱ ነገር እኩይ ።

በዚህም ቤት ካለው ሁሉ ውስጥ ካንቺ በቀር የማይሠለጥንበት የለም፤ አንቺ ግን ሚስቱ ስለሆንሽ አሁን ይህን ክፉ ሥራ እንዴት አደርገዋለሁ፤ አላት ።

፲ ወትትናገሮ ከመዝ እንተ ጸብሐት ለዮሴፍ ወየአብያ ሰኪበ ምስሌሃ ወቀሪቦታ ።

እንዲህም እያለች በነጋ በጠባ ለዮሴፍ ትወተውተው ነበር፤ እርሱ ግን ከርሷ ጋር መተኛትን (መድረሷን) እምቢ አለ ።

፲፩ ወኮነ በአሐቲ ዕለት በአ ዮሴፍ ውስተ ቤት ይግበር ግብሮ ወአልቦ ዘሀሎ ሰብአ ውስተ ውሳጤ ቤት ።

ከዕለታት በአንድ ቀን እንዲህ ሆነ፤ ዮሴፍ ሥራውን ለመሥራት ወደ ቤት ገባ፤ በቤትም ውስጥ የነበረ ሰው የለም ።

፲፪ ወአኀዘት ልብሶ ወትቤሎ ነዓ ስክብ ምስሌየ፤ ወኀደገ አልባሲሁ በእዴሃ ወጕየ ወወፅአ ።

ልብሱንም ይዛ ና ከኔ ጋር ተኛ አለችው፤ እርሱ ግን ልብሱን በእጅዋ ጥሎላት ሸሽቶ ወጣ ።

፲፫ ወሶበ ርእየት ከመ ወፅአ ወኀደገ አልባሲሁ በእዴሃ፤ ጸውዐቶሙ ለእለ ሀለዉ ውስተ ክልእ ቤት ወትቤሎሙ ምንተ አምጻእክሙ ላዕሌየ ።

እሷም ልብሱን በእጅዋ ጥሎላት እንደ ወጣ በየች ጊዜ፤ በሌላው ቤት ያሉትን ሰዎች ጠርታ ምን አመጣችሁብኝ አለቻቸው ።

፲፬ ርእዩ ዘገብረ ዝንቱ ገብር ዕብራዊ ከመ ይሣለቅ ላዕሌየ፤ በአ ኀቤየ ወይቤለኒ ስክቢ ምስሌየ፤ ወጸራኅኩ በዐቢይ ቃል ።

ይህ ዕብራዊ አገልጋይ ያደረገውን እዩ፤ በኔ ሊዘብት ብኝ ወደኔ ገብቶ ከኔ ጋር ተኚ አለኝ፤ እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ ጮኽሁ ።

፲፭ ወሶበ ሰምዐ ከመ አልዐልኩ ቃልየ ወጸራሕኩ ኀደገ አልባሲሁ ወጕየ አፍአ ።

ድምፄንም ከፍ አድርጌ እንደ ጮኽሁ በሰማ ጊዜ፤ ልብሱን ጥሎልኝ ሸሽቶ ወደ ውጭ ወጣ ። መዝ ፻፳ ፫ ።

፲፮ ወአንበረት አልባሲሁ ኀቤሃ እስከ አመ ይመጽእ እግዚኡ ውስተ ቤቱ ።

(እሷም) ጌታው ወደ ቤቱ እስኪመጣ ድረስ የዮሴፍን ልብስ ከሷ ዘንድ አኖራ አቈየችው ።

፲፯ ወነገረቶ ዘንተ ነገረት ለምታ ወትቤሎ ገብርከ ዕብራዊ ዘአምጻእከ በአ ኀቤየ ይሣለቅ ላዕሌየ ወይቤለኒ እስክብ ምስሌኪ ።

ይህንንም ነገር ለባሏ ነገረችው፤ ያመጣኸው ዕብራዊ ባርያህ በኔ ሊዘብትብኝ ወደኔ ገብቶ ካንቺ ጋር ልተኛ አለኝ ።

፲፰ ወሶበ ሰምዐ ከመ አልዐልኩ ቃልየ ወጸራኅኩ ኀደገ አልባሲሁ ወጕየ አፍአ ።

ቃሌን ከፍ አድርጌ እንደጮኽሁ በሰማ ጊዜ፤ ልብሱን ጥሎልኝ ወደ ውጭ ሸሽቶ ወጣ ብላ ነገረችው ።

፲፱ ወሶበ ሰምዐ እግዚኡ ነገረ ብእሲቱ ዘትቤሎ ከመዝ ረሰየኒ ገብርከ ዕብራዊ ተምዐ መዓተ ዐቢየ ።

ጌታውም ሚስቱ ይህ ዕብራዊ ባርያህ እንዲህ አደረገኝ ብላ የነገረችውን ነገር በሰማ ጊዜ፤ እጅግ ተቈጣ ።

፳ ወነሥኦ ለዮሴፍ ወአንበሮ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ኀበ ይነብሩ እለ ሞቅሖሙ ንጉሥ ውስተ ሙዓል ።

ዮሴፍንም ወስዶ የንጉሥ እስረኞች ወደሚታሰሩበት እስር ቤት ወደ ግዞት ቤት አገባው ።

፳፩ ወሀለወ እግዚአብሔር ምስለ ዮሴፍ ወከዐወ ላዕሌሁ ምሕረቶ ወወሀቦ ሞገሰ በቅድመ ሊቀ ዐቀብተ ሞቅሕ ።

እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረና ምሕረቱን አበዛለት፤ በእስረኞች ቤትም አለቃ ፊት መወደድን ሰጠው ።

፳፪ ወአወፈዮ ለዮሴፍ ኵሎ ቤተ ሞቅሕ ወውእቱ ይገብር ኵሎ ዘከመ ይደሉ ።

(የግዞት ቤት አለቃው) የእስረኞችን ቤት ሁሉ ለዮሴፍ ሰጠው ።

፳፫ ወአልቦ ዘየአምር ኵሎ ዘይትገበር በቤተ ሞቅሕ ሊቀ ዐቀብተ ሞቅሕ ወኢምንተኒ፤ እስመ ኀደገ ሎቱ ኵሎ ለዮሴፍ፤ እስመ እግዚአብሔር ሀሎ ምስሌሁ ወበኵሉ ዘገብረ ይሴርሖ እግዚአብሔር በእዴሁ ።

እግዚአብሔር ከሱ ጋር ስለነበረ የሚሠራውንም ሁሉ እግዚአብሔር የሚያከናውንለት ስለነበረ የእስረኞች ቤት አለቃ በግዞት ቤቱ የሚደረገውን ሁሉ ምንም የሚያውቀው አልነበረም፤ ሁሉን ለዮሴፍ ትቶለታልና ።

## ምዕራፍ ፵ ።

፩ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር አበሱ ሊቀ ቀዳሕያን ወሊቀ ኀባዝያኒሁ ለንጉሠ ግብጽ ለእግዚኦሙ ።

ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ፤ የግብጽ ንጉሥ የጠጅ አሳላፊና የእንጀራ አበዛ ሁለቱ በለሚሎቹ በደሉ ። ነህ ፩ ፲፩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወተመዐ ላዕለ ክልኤሆሙ ኅጽዋኒሁ፡ ወአንበሮሙ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ውስተ መካን ኀበ ሀሎ ዮሴፍ። | ፪ | በሁለቱ በሎሚሎቹም ላይ ተቈጣ፡ ዮሴፍ በታሰረበትም በታ አግዞ አኖራቸው። ምሳ፡ ፲፯ ፲፬። |
| ወሊቀ ዐቀብተ ሞቅሕ አንበሮሙ ውስተ ሞቅሕ ምስለ ዮሴፍ ወውእቱሰ ይትቀነዮሙ፡ ወነበሩ ውስተ ቤተ ሞቅሕ አሐተ ዓመተ። | ፫ | የግዞቱ እስረኞችን ከዮሴፍ ጋር በእስር ቤት አኖራቸው፡ እርሱም ያገለግላቸው ነበር፡ በግዞት ቤቱም አንድ ዓመት ኖሩ። |
| ወሐለሙ ሕልመ ክልኤሆሙ በአሐቲ ሌሊት አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ ርእዩ ሕልሞሙ ሊቀ ቀዳሕያን ወሊቀ ኅባዝያን ዘንጉሠ ግብጽ እለ ሀለዉ ውስተ ቤተ ሞቅሕ። | ፬ | በግዞት ቤት ያሉ የግብጽም ንጉሥ ጠጅ አሳላፊውና እንጀራ አበዛውም በአንድ ሌሊት አንዱም አንዱም እየራሳቸው ሕልም አዩ። |
| ወቦአ ዮሴፍ ኀቤሆሙ ወርእዮሙ ትኩዛኒሆሙ። | ፭ | ዮሴፍም ወደነሱ ገብቶ አዝነው (ተክዘው) አያቸው። |
| ወተስእሎሙ ዮሴፍ ወይቤሎሙ ምንትኑ ኅዙናን ገጽክሙ ዮም። | ፮ | ዮሴፍ ዛሬ ፊታችሁ አዝኗልና ምንድር ነው፤ ብሎ ጠየቃቸው። |
| ወይቤልዎ ሐለምነ ሕልመ ወኅጣእነ ዘይፈክር ለነ። | ፯ | (እነሱም) ሕልም አይተን የሚተረጕምልን አጣን አሉት። |
| ወይቤሎሙ አኮኑ ዘእግዚአብሔር ወሀበ ይፈክር ሕልመ ወይእዜኒ ንግሩኒ ምንትኑ ሕልምክሙ። | ፰ | ዮሴፍም ሕልም የሚተረጕም እግዚአብሔር የገለጠለት ነው አሁንም ሕልማችሁ ምንድር ነው፤ (እስኪ) ንገሩኝ አላቸው። |
| ወነገሮ ሊቀ ቀዳሕያን ሕልሞ ለዮሴፍ ወይቤሎ እሬኢ በሕልምየ ሐረገ ወይን በቅድሜየ። | ፱ | የጠጅ አሳላፊዎች አለቃም ሕልሙን ነገረው፡ እነሆ፤ የወይን ሐረግ በፊቴ አያለሁ አለው። ዘዳ፡ ፪ ፲፭። |
| ወውስተ ውእቱ ሐረግ ሠረፀ ሠለስቱ አዕፁቅ ወአውፅአ ሠለስተ አስካለ ወጸዋዐ ለፈርዖን ውስተ እዴየ። | ፲ | በዚያውም ሐረግ ላይ ሦስት አጽቆች አቈጥቍጠዋል አጽቆቹም ሦስት ዘለላ አውጥተዋል፡ የፈርዖንም ጽዋ በእጄ ተይዟል። |
| ወነሣእክዎሙ ለአልክቱ አስካል ወዐጸርክዎሙ ውስተ ጽዋዐ ለፈርዖን ወመጠውክዎ። | ፲፩ | እነዚያን ሦስት ዘለላዎች አምጥቼ በፈርዖን ጽዋ ላይ ጨምቄ ሰጠሁት። |
| ወይቤሎ ዮሴፍ ዝንቱ ውእቱ ፍካሬሁ ለሕልምከ እሉ ሠለስቱ አስካል ሠላስ መዋዕል እማንቱ። | ፲፪ | ዮሴፍም የሕልምህ ትርጓሜ ይህ ነው፤ እነዚያ ሦስት ዘለላዎች ሦስት ቀኖች ናቸው አለው። |
| ወእስከ ሠላስ መዋዕል ይዜከር ፈርዖን ሢመተከ ወያገብአከ ውስተ ሊቀ ቀዳሕያን ወትሜጥዎ ጽዋዐ ለፈርዖን በእዴከ ከመ ቀዲሙ ሢመትከ አመ ውስተ ሊቀ ቀዳሕያን አንተ። | ፲፫ | እስከ ሦስት ቀን ድረስ ፈርዖን የቀድሞ ሹመትህን አስቦ ወደ ቀድሞው ሹመትህ ይመልስሃል፡ አንተ የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ በነበርክበት ጊዜ ትሰጠው እንደ ነበረ ዛሬም እንደ ፡ ድሞው ተሹመህ ጽዋውን ለፈርዖን በእጅህ ትሰጠዋለህ ሲል ተረጐመለት። ዳን፡ ፪ ፴፯፡ ፬ ፲፱። |
| ወተዘከረኒ አመ አሠነየ ለከ ወግበር ምሕረተ ላዕሌየ ወአዘክሮ ለፈርዖን በእንቲአየ ወአውፅአኒ እምዝንቱ ቤተ ሞቅሕ። | ፲፬ | ነገር ግን በጎ ነገር በደረገልህ ጊዜ፡ አንተም ለኔ በጎ ነገር አድርግልኝ፡ የኔን ነገር ለፈርዖን አሳስበህ ከዚህ እስር ቤት አውጣኝ። |
| እስመ ሰረቅት ሰረቁኒ ጽሚተ እምብሔረ ዕብራውያን ወበዝየኒ በዘአልቦ ዘገበርኩ ወኢምንተኒ አንበሩኒ ውስተ ቤተ ሞቅሕ። | ፲፭ | ሌቦች ከዕብራውያን አገር ሰርቀው አምጥተው በዚህም (አገር) ምንም ያደረግሁት ሳይኖር አስረው ከዚህ ግዞት ቤት አግብተውኛልና። ሉቃ፡ ፳፫ ፵፪። |
| ወሶበ ርእየ ሊቀ ኅባዝያን ከመ ሠናየ ፈከረ ሎቱ ይቤሎ ለዮሴፍ አነሂ ርኢኩ ከመዝ በሕልምየ ሠለስቱ አክፋር ላዕለ ርእስየ። | ፲፮ | እንጀራ አዛዡም ሕልሙን በጎ አድርጎ እንደተረጐመለት በየ ጊዜ ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ በሕልሜ ሦስት መሶቦች በራሴ ላይ ተሸክሜ አያለሁ። ፩ ሳሙ፡ ፳ ፲፱። |
| ወውስተ ሠለስቱ አክፋር ሀሎ ላዕሌሁ ኵሉ ዘመደ መብልዕ ዘይበልዕ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወበልዕዎ አዕዋፍ በውስተ ክፈር ዘላዕለ ርእስየ። | ፲፯ | በነዚያም በሦስት መሶቦች ላይ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን የሚበላው የመብል ወገን ሁሉ አለበት፡ ወፎችም መጥተው በራሴ ላይ ካለው መሶብ ሲበሉ አየሁ አለው። |
| ወአውሥአ ዮሴፍ ወይቤሎ ዝንቱ ውእቱ ፍካሬሁ ለሕልምከ እልክቱ ሠለስቱ አክፋር ሠላስ መዋዕል እማንቱ። | ፲፰ | ዮሴፍም የሕልምህ ትርጓሜው እንዲህ ነው፤ በራስህ ላይ የተሸከምካቸው ሦስት ቅርጫቶች ሦስት ቀኖች ናቸው፡ ብሎ መለሰለት። |
| ወእስከ ሠላስ መዋዕል ይመትር ፈርዖን ርእሰከ እምኔከ ወይሰቅለከ ላዕለ ዕፅ ወይበልዑ አዕዋፈ ሰማይ ሥጋከ። | ፲፱ | እስከ ሦስት ቀን ድረስ ራስህን (ከቾብቾበህ) ከንተ ቈርጦ በዕንጨት ላይ ይሰቅልሃል፡ የሰማይ ወፎችም ሥጋህን ይበሉታል። |

| | | |
|---|---|---|
| ወኮነ በሣልስት ዕለት ዘእመ ዕለተ ተወልደ ፈርዖን ገብረ በዓለ ወማእደ ዓቢየ ለሰብኡ ወተዘከረ ሢመቶ ለሊቀ ቀዳሕያን ወሢመቶ ለሊቀ ኅባዝያን በማእከለ ሰብእ ። | ፳ | በሦስተኛውም ቀን እንዲህ ሆነ፣ ፈርዖን በተወለደ በት ቀን ለሠራዊቱ ታላቅ ማእድ አደረገ፣ በሠራዊቱም መከከል ፈርዖን የእንጀራ አዛዡን ሹመትና የጠጅ አዛዡን ሹመት አሰበ ። ማቴ፣ ፲፬ ፮ ። ማር፣ ፮ ፳፩ ። |
| ወአግብአ ለሊቀ ቀዳሕያን ውስተ ሢመቱ ወመጠዎ ጽዋዖ ለፈርዖን ውስተ እዴሁ ። | ፳፩ | (ከዚህ በኋላ) የጠጅ አሳላፊውን ወደ ሹመቱ መለሰው፡ ጽዋውንም ለፈርዖን በእጁ ሰጠው ። ነህ፣ ፪ ፩ ። |
| ወለሊቀ ኅባዝያንሰ ሰቀሎ ዲበ ዕፅ በከመ ፈከረ ሎቱ ዮሴፍ ። | ፳፪ | የእንጀራ አበዛዎችን አለቃ ግን ዮሴፍ እንደተረጐመለት በዕንጨት ላይ ሰቀለው ። አስቴ፣ ፯ ፳ ። |
| ወኢተዘከሮ ሊቀ ቀዳሕያን ለዮሴፍ አላ ረስዖ ። | ፳፫ | የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ግን ዮሴፍን ረሳው እንጂ አላሰበውም ። ኢዮብ፣ ፲፱ ፲፬ ። |

## ምዕራፍ ፵፩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወኮነ እምድኅረ ክልኤቱ ዓመት ርእየ ፈርዖን ሕልመ፣ ከመ ዘይቀውም መልዕልተ ፈለግ ። | ፩ | ይህ ከሆነ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ፈርዖን በወንዙ ዳር እንደ ቆመ ሁኖ ሕልምን አየ ። |
| ወናሁ ከመ ዘእምፈለግ የዐርጉ ሰብዓቱ አልሕምት ሠናይ ራእዮሙ ወሥቡሕ ሥጋሆሙ ወይትረዐዩ ውስተ ማዕዶት ። | ፪ | እነሆም መልካቸው ያማረ ሥጋቸው የወፈረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው ወደ ማዶ ይሰማራሉ ። |
| ወየዐርጉ ካልኣን ሰብዓቱ አልሕምት እምድኅሬሆሙ እምውስተ ፈለግ ወእኩይ ራእዮሙ ወድግዱግ ሥጋሆሙ ወይትረዐዩ ኀበ እልክቱ አልሕምት ውስተ ማዕዶተ ፈለግ ። | ፫ | ከነሱም ቀጥሎ መልካቸው የከፋ ሥጋቸው የከሳ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው በነዚያ ላሞች አጠገብ በወንዙ ዳር ተሰማርተው ይታዩ ነበር ። |
| ወውኅጥዎሙ እልክቱ ሰብዐቱ አልሕምት እለ እኩይ ራእዮሙ ወድግዱግ ሥጋሆሙ ለእልክቱ አልሕምት እለ ሥቡሕ ሥጋሆሙ ወሠናይ ራእዮሙ ። | ፬ | እነዚህም መልካቸው የከፋ ሥጋቸው የከሳ ሰባት ላሞች እነዚያን መልካቸው ያማረ ሥጋቸው የወፈረውን ሰባቱን ላሞች ዋጡዋቸው ። |
| ወነቅሐ ፈርዖን ወኖመ ወደገመ ሐሊመ ወናሁ ሰብዓቱ ሰዊት የዐርጉ እምነ አሐዱ ሥርው ኅሩያን ወሠናያን ። | ፭ | ፈርዖንም ነቃ ዳግመኛም ተኝቶ ሕልምን አየ፤ እነሆ ከንድ (አገዳ) (ዘለላ) ያማሩ የተመረጡ ሰባት እሸቶች ወጡ ። |
| ወናሁ ሰብዓቱ ሰዊት ቀጢናን ወዕቡራን ወፅኡ እምድኅሬሆሙ ። | ፮ | ከነሱም ቀጥሎ የሰለቱ የደረቁ ሰባት እሸቶች ወጡ ። |
| ወውኅጥዎሙ እልክቱ ሰብዓቱ ሰዊት ቀጢናን ወዕቡራን ለእልክቱ ሰብዓቱ ሰዊት ኅሩያን ወምሉኣን፣ ወተንሥአ ፈርዖን ወአእመረ ከመ ሕልም ውእቱ ። | ፯ | ሰባቱ የሰለቱ የደረቁ እሸቶችም ከነሱ በኋላ ወጥተው እነዚያን ያማሩና የወፈሩትን ሰባቱን እሸቶች ሲውጡዋቸው አየ፤ ፈርዖንም ተነሣ ሕልም እንደሆነም አወቀ ። |
| ወኮነ ሶበ ጸብሐ ተሀውከቶ ነፍሱ ወለአከ ይጸውዕዎሙ ለኵሎሙ መፈክራነ ግብጽ ወለኵሎሙ ጠቢባኒሆሙ ወመጽኡ ወነገሮሙ ፈርዖን ሕልሞ ወስእኑ ፈክሮቶ ሎቱ ለፈርዖን ። | ፰ | በነጋም ጊዜ የፈርዖን ነፍሱ ታወከችበት፣ የግብጽ ሕልም ተርጓሚዎችን ሁሉ ፈላስፎችንም ሁሉ ጥሩልኝ ብሎ አስጠርቷቸው መጡ ፈርዖንም ሕልሙን ነገራቸው፣ ነገር ግን ሕልሙን ተርጕሞ ለፈርዖን መንገር ተሳናቸው ። |
| ወይቤሎ ሊቀ ቀዳሕያን ለፈርዖን ኀጢአትየ እዜከር ዮም ። | ፱ | የጠጅ አሳላፊዎች አለቃም ለፈርዖን ኃጢአቴ ዛሬ አስባለሁ አለው ። |
| ፈርዖን ንጉሥ ተምዖሙ ለአግብርቲሁ ወአንበረነ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ኪያየ ወሊቀ ኅባዝያን ። | ፲ | ንጉሥ ፈርዖን ባሮቹን ተቈጥቶ እኔንና የእንጀራ አሰላፊዎች አለቃን እስር ቤት አገባን ። |
| ወሐለምነ ሕልመ ክልኤነ አነሂ ወውእቱሂ ዘዘዚአነ ሐለምነ ። | ፲፩ | ሁለታችን በግዞት ቤት ሳለን እሱና እኔ እየራስ እየራሳችን ሕልም አየን ። |
| ወሀሎ ምስሌነ ወልድ ዕብራዊ ወሬዛ ዘሊቀ መበስላን ወነገርናሁ ወፈከረ ለነ ። | ፲፪ | (በዚያም) የእንጀራ አበዛዎች አለቃ የሆነ አንድ ዕብራዊ ጕልማሳ ልጅ ከኛ ጋር ነበረ፣ ሕልማችንን ነግረነው ተረጐመልን ። ፪ ነገ፣ ፭ ፬ ። |
| ወኮነ በከመ ፈከረ ለነ ወከማሁ ረከብነ አነሂ ገባእኩ ውስተ ሢመትየ፣ ወለዝክቱሂ ሰቀልዎ ። | ፲፫ | እንደ ተረጐመልንም ሆነ፣ እሱ እንደ ተረጐመውም እኔ ወደ ሹመቴ ተመለስኩ፣ ያኛንም ሰቀሉት ። |
| ወለአከ ፈርዖን ወጸውዕዎ ለዮሴፍ ወአውፅእዎ እምቤተ ሞቅሕ ወላፀይዎ ርእሶ፣ ወወለጡ አልባሲሁ ወአምጽእዎ ኀበ ፈርዖን ። | ፲፬ | ፈርዖንም ዮሴፍን ልኮ አስጠራው፣ ከእስር ቤትም አወጡት፣ ራሱን ላጭተው ልብሱንም ለውጠው ወደ ፈርዖን አመጡት ። መዝ፣ ፻፭ ፳ ። |
| ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ ሕልመ ሐለምኩ ወዘይፈክር | ፲፭ | ፈርዖንም ዮሴፍን ሕልም አይቼ የሚተረጕምልኝ አጣ |

ሊተ ኅማእኩ ወሰማዕኩ አነ በእንቲአከ ከመ ሰማዕከ ሕልመ ወፈከርከ ።
፲፮ ወአውሥአ ዮሴፍ ለፈርዖን ወይቤሎ ዘእንበለ እግዚ
አብሔር ዘወሀበ ኢይክል ፈክሮ ።
፲፯ ወነገሮ ፈርዖን ለዮሴፍ ወይቤሎ አሬኢ በሕልምየ
ከመ ዘይቀውም በማዕዶተ ፈለግ ።
፲፰ ወእምውስተ ፈለግ የዐርጉ ሰብዓቱ አልሕምት ሥቡ
ሓን ሥጋሆሙ ወሠናይ ራእዮሙ ወይትረዐዩ ውስተ
ማዕዶት ።
፲፱ ወናሁ ካልኣን ሰብዐቱ አልሕምት የዐርጉ እምድኅሬ
ሆሙ እምውስተ ፈለግ እኩያን ወሕሡም ራእዮሙ ወድ
ማዱግ ሥጋሆሙ ወኢርኢኩ ዘከማሆሙ ሕሡመ በኵሉ
ምድረ ግብጽ ።
፳ ወውሕጥዎሙ እልክቱ ድግዱጋን ለእልክቱ ሰብዓቱ
አልሕምት ሥቡሓን ወሠናያን ።
፳፩ ወበኡ ውስተ ከርሦሙ ወክነ ከመ አልበ ዘቦአ ውስተ
ከርሦሙ ወገጾሙኒ ሕሡም ከመ ቀዳሚ ፣ ወነቃሕኩ ።
፳፪ ወሰከብኩ ካዕበ ወርኢኩ በሕልምየ ከመዝ ሰብዓቱ
ሰዊት ይወጽኡ እምአሐዱ ሥርው ምሉኣን ወሠናያን ።
፳፫ ወካልኣን ሰብአቱ ሰዊት ቀጢናን ወይቡሳን ወፀኡ
እምድኅሬሆሙ ።
፳፬ ወውሕጥዎሙ እልክቱ ቀጢናን ወይቡሳን ለእልክቱ
ሰብዓቱ ሰዊት ምሉኣን ወሠናያን ፣ ወነገርክዎሙ ለመፈክ
ራን ወአልበ ዘፈከሩ ሊተ ።
፳፭ ወይቤሎ ዮሴፍ ለፈርዖን ሕልሙ ለፈርዖን አሐዱ ው
እቱ ፣ ዘይገብር እግዚአብሔር አርአዮ ለፈርዖን ።
፳፮ እልክቱ ሰብንቱ አልሕምት ሠናያን ሰብዓቱ ዓመት
እሙንቱ ፣ ወእልክቱሂ ሰብዓቱ ሰዊት ሠናያን ሰብዓቱ ዓ
መት እሙንቱ ፣ ሕልሙ ለፈርዖን አሐዱ ውእቱ ።
፳፯ ወእልክቱ ሰብዓቱ አልሕምት ዱግዱጋን እለ ዐርጉ
እምድኅሬሆሙ ሰብዓቱ ዓመት እሙንቱ ፣ ወእሉሂ ሰብ
ዓቱ ሰዊት ቀጢናን ወዕቡራን ሰብዓቱ ዓመት እሙንቱ ፣
ወይከውን ሰብዓቱ ዓመት ዘረኃብ ።
፳፰ ወዝንቱ ቃል ዘይቤሎ ለፈርዖን ዘይገብር እግዚአብ
ሔር አርአዮ ለፈርዖን ።
፳፱ ናሁ ይመጽእ ሰብዓቱ ዓመት ዘብዙኅ ጽጋብ ውስተ
ኵሉ ምድረ ግብጽ ።
፴ ወይመጽእ ሰብዓቱ ዓመተ ዘረኃብ እምድኅሬሁ ወይ
ረስዕዎ ለጽጋብ በኵሉ ምድረ ግብጽ ።
፴፩ ወየኅልቅ በረኃብ ኵሉ ሰብእ እምውእቱ ረኃብ ዘይ
መጽእ እምድኅሬሁ እስመ ዐቢይ ውእቱ ጥቀ ።
፴፪ ወዘደገመ ፈርዖን ሐሊሞቶ እስመ እሙን ውእቱ
ነገሩ እምኀበ እግዚአብሔር ወፍጡነ ይገብሮ እግዚአብ
ሔር ለዝንቱ ።
፴፫ ወይእዜኒ ኅሥሥ ለከ ብእሴ ጠቢበ ወልብወ ወሢሞ
ላዕለ ኵሉ ምድረ ግብጽ ።

ሁ ፣ ሕልምን ሰምተህ እንደ ተረጐምክ ስላንተ ሰማሁ ፣ አለው ። ዘዳ፣ ፳፱ ፳፱ ። መዝ፣ ፳፭ ፲፬ ።

ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ ብሎ መለሰለት ፣ እግዚአብ ሔር የገለጸለት ካልሆነ በቀር መተርጐም አይቻልም ።

ፈርዖን ለዮሴፍ ሕልሙን ነገረው ፣ በሕልሜ በወንዝ ዳር እንደቆምኩ ሆኜ አያለሁ ።

መልካቸው ያማረ ሥጋቸው የወፈረ ሰባት ላሞች ከወንዝ ወጥተው ከወንዙ ማዶ ሲሠማሩ አያለሁ ።

እነሆም መልካቸው እጅግ የከፋ ሥጋቸው የከሳ ሌሎች ሰባት ላሞች ከነሱ በኋላ ከወንዙ ወጥተው ሲሄዱ አየሁ ፣ በግብጽ ምድር ሁሉ እንደነሱ የከፋ አላየሁም ።

እነዚያ መልካቸው የከፋ ሥጋቸው የከሳ ላሞች መልካቸው ያማረውንና ሥጋቸው የወፈረውን እነዚያን ሰባት ላሞች ዋጡዋቸው ።

ከሆዳቸውም ውስጥ ገብተው ከሆዳቸው ውስጥ የገባ እንደሌለም ሆኑ ፊታቸውም እንደ ነበረው እንደ በፊቱ የከፋ ሆነ ፣ ይህን አይቼ (ከእንቅልፌ) ነቃሁ ።

ዳግመኛም ተኝቼ በሕልሜ እንዲህ አየሁ ፤ ሰባት ያማሩና ፍሬያማዎች የሆኑ እሸቶች ከአንድ ዘለላ ሲወጡ አየሁ ።

የሰለቱና የደረቁም ሌሎች ሰባት እሸቶች ከነሱ በኋላ ከአንድ ዘለላ (ሥር) ወጡ ።

እነዚያ የሰለቱና የደረቁ ሰባት እሸቶች (ገብሶች) ያማሩና ፍሬያማዎች የሆኑትን ሰባት እሸቶች ሲውጡዋቸው አየሁ ፣ ብዬ (ለሕልም) ተርጓሚዎች ነገርኳቸው ነገር ግን የተረጐመልኝ የለም አለው ።

ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ አለው ፤ የፈርዖን ሕልሙ አንድ ነው ፣ እግዚአብሔር (ወደ ፊት) ሊያደርገው ያለውን ለፈርዖን ገልጦለታል ። ዳን፣ ፪ ፳፰ ። ራ፣ ዮሐ፣ ፬ ፩ ።

እነዚያ መልካሞች ሰባት ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው ፣ እነዚያ መልካቸው ያማሩ ሰባት እሸቶችም ሰባት ዓመታት ናቸው ፣ (ስለዚህ) የፈርዖን ሕልሙ አንድ ነው ።

እነዚያ ከነርሱ በኋላ የወጡ የከሱ ሰባት ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው ፣ እነዚያ የሰለቱና የደቀቁ ሰባት እሸቶችም ሰባት ዓመታት ናቸው ፣ ሰባት ዓመት ረኃብ ይሆናል ።

ለፈርዖን የነገርኩት ቃል ይህ ነው ፣ እግዚአብሔር (በኋላ ዘመን) የሚያደርገውን ነገር ለፈርዖን ገልጦለታል ።

እነሆ ሰባት ዓመት በግብጽ አገር ሁሉ ብዙ ጥጋብ ይመጣል ።

ከሱም በኋላ የሰባት ዓመት ረኃብ ይመጣል ፣ በግብጽ አገር ሁሉ (ሰዎች) የሰባቱን ዓመት ጥጋብ ይዘነጉታል ።

ከጥጋብ ቀጥሎ ከሚመጣው ረኃብ የተነሣ ሰው ሁሉ በረኃብ ያልቃል እጅግ ጽኑ ነውና ።

ሕልሙን ለፈርዖን ደጋግሞ ማሳየቱ ግን ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚደረግ እውነተኛ ስለሆነ ነው ፣ እግዚአብሔርም ይህን ነገር ፈጥኖ ያደርገዋል ።

አሁንም ብልህ አዋቂ ሰው ፈልገህ በግብጽ አገር ሁሉ ሹመው ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይግበር ፈርዖን መዘግብተ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ወይድፍንዎ ለእክለ ግብጽ ዘሰብዐቱ ዓመት ። | ፴፬ | ፈርዖን በግብጽ አገር ሁሉ ፊቅ ጐተራ ያሠራና፡ በሰባቱ የጥጋብ ዘመን የሚገኘውን የግብጽ እህል በዚያ ይከተቱት ። |
| ወያስተጋብእዎ ለኵሉ እክል ዘሰብዐቱ ዓመት ዘጽጋብ ወያስተጋብእ ፈርዖን ሥርናዮ ወእክሎ ውስተ ኵሉ አህጉር ወይትዐቀብ ። | ፴፭ | የሰባቱን ዓመት የጥጋቡን ዘመን እህል በፊቅ በጐተራ ይሰብስቡት ፈርዖንም ሥንዴውንና (ሌላውን) እህል ሁሉ በየሀገሩ ሁሉ ያከማችና (ለሰባት ዓመት) ይጠበቅ ። |
| ወይኩን ውእቱ እክል ዘየዐቀቡ ሲሳየ ለኵሉ ብሔር ለእመ ረኃብ ዘይመጽእ ውስተ ብሔረ ግብጽ፡ ወኢይመውት ሰብእ በረኃብ ። | ፴፮ | ለሀገሩ ሁሉ ምግብ ሊሆን የሚጠብቁት እኽል ሁሉ በግብጽ አገር ለሚመጣው (ለ፯ ዓመት) ረኃብ ጊዜ ይሆናል፡ ሰው ሁሉ በረኃብ አይሞትም (አይሙት) ። |
| ወአደሞ ለፈርዖን ዝንቱ ነገር ወለኵሉ ሰብኡ ። | ፴፯ | ይህ ነገር ለፈርዖን ደስ አለው ለሰዎቹም ሁሉ ። |
| ወይቤሎሙ ፈርዖን ለኵሉ ሰብኡ ቦኑ እንከ ዘተረክበ ከመ ዝንቱ ብእሲ ዘመንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ። | ፴፰ | ፈርዖንም ለመኳንንቱ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት እንደዚህ ያለ ሰው በውኑ የተገኘ አለን፤ አላቸው ። |
| ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ እስመ ለከ አርአየከ እግዚአብሔር ዘንተ ኵሎ ወአልቦ ብእሲ ዘይጠብበከ ወዘይሌቡ እምኔከ ። | ፴፱ | ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው ይህን ሁሉ ነገር እግዚአብሔር ላንተ ገልጦልሃልና፤ ካንተም የሚበልጥ ብልህ አዋቂ ሰው የለምና ። |
| አንተ ኩን ላዕለ ኵሉ ቤትየ ወለቃለ ዚአከ ይትአዘዝ ኵሉ ሕዝብ፡ ወዘእበለ መንበር አልቦ ዘእፈደፍደከ አነ ። | ፵ | አንተ በቤቴ ሁሉ ላይ ተሾም፡ ሕዝቡም ሁሉ ላንተ ቃል ይታዘዝ፡ እኔም ከዙፋኔ በቀር ካንተ የምበልጥበት መብለጥ የለም ። |
| ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ ናሁ ሤምኩከ አነ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ። | ፵፩ | ፈርዖን ዮሴፍን በግብጽ አገር ሁሉ ላይ እነሆ እኔ ሾምኩህ አለው ። |
| ወአውፅአ ፈርዖን ኅልቀቶ እምእዴሁ ወወደየ በእዴሁ ለዮሴፍ ወአልበሶ ልብሰ ሜላት ወአዕነቆ ባዝግና ወርቅ ላዕለ ክሳዱ ። | ፵፪ | ፈርዖን ቀለበቱን ከእጁ ጣት አውጥቶ በዮሴፍ እጅ ጣት አደረገለት፡ ነጭ ሐርም አለበሰው፡ በአንገቱም የወርቅ ዝርግፍ አሰረለት ። |
| ወአጽዐኖ ዲበ ፈረስ ዘዚአሁ ወአዖደ አዋዴ ቅድሜሁ ወሤሞ ላዕለ ኵሉ ምድረ ግብጽ ። | ፵፫ | በራሱ ፈረስ ላይም አስቀመጠው አዋጅ ነጋሪም በፊቱ ቁሞ አዋጅ አስነገረ፡ በግብጽ አገር ሁሉ ላይም ሾመው ። |
| ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ አነ ለልየ ፈርዖን ዘእንበሌከ አልቦ ዘአንበር ወኢምንተኒ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ። | ፵፬ | ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፡ እኔ ፈርዖን ቅሉ ብሆን በግብጽ አገር ሁሉ ያላንተ ምንም የማደርገው ነገር የለም ። |
| ወሰመዮ ፈርዖን ስሞ ለዮሴፍ እስፍንቶፎኔህ፡ ወወሀቦ አስኔትሃ ወለተ ጴሜጤፌራ ማሬ ዘሀገረ ሄልዮቱ ትኩኖ ብእሲተ ። | ፵፭ | ፈርዖን ለዮሴፍ ስሙን እስፍንቶፎኔህ (የአዋቂዎች አዋቂ ማለት) የሔልዮቱ አገር ካህን የጴሜጤፌራ ልጅ አስኔትንም ሚስት ልትሆነው አጋባው ። |
| ወሠላሳ ዓመቱ ሎቱ ለዮሴፍ አመ ይቀውም ቅድመ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ፡ ወሰበ ወፅአ ዮሴፍ እምቅድመ ገጹ ለፈርዖን አንሰሰወ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ። | ፵፮ | ዮሴፍም በግብጽ ንጉሥ በፈርዖን ፊት በቆመ ጊዜ ለሱ ሠላሳ ዓመት ሁኖት ነበር፡ ከፈርዖን ፊትም በወጣ ጊዜ በግብጽ አገር ሁሉ ተመላለሰ ። |
| ወዘኵሉ እክላ ዘአውፅአት ምድር ዘብሔረ ግብጽ እስከ ሰብዐቱ ዓመት ዘጽጋብ ከላስስቲሁ ። | ፵፯ | እስከ ሰባቱ የጥጋብ ዘመን ድረስ የግብጽ ምድር ያስገኘችውን እኽል ሁሉ ነዶውን እያስከመረ በፊቅ በጐተራ ሰበሰበ ። ፩ ነገሥ፡ ፲፱ ፯-፰። |
| ወኵሎ እክሎ አስተጋብአ ወዘገበ እክለ ውስተ ኵሉ አህጉር ወአድያመ ብሔር ከመ ይኩን ሲሳየ ። | ፵፰ | በአገሩም በአውራጃውም ሁሉ ለሰባት ዓመት ረኃብ ምግብ ሊሆን እህሉን ሰብስቦ አኖረ ። |
| ወዘገበ ዮሴፍ ሥርናየ ከመ ኆፃ ባሕር ብዙኀ ጥቀ እስከ ስእኑ ኈልቆቶ ወዘእንበለ ኍልቍ ኮነ ። | ፵፱ | ዮሴፍም (የግብጽ ሰዎች) መቍጠር እስኪ ታሳናቸው ድረስ እኽሉን እንደ ባሕር አሸዋ አድርጎ እጅግ ሰበሰበ፡ (ከብዛቱም የተነሣ) የማይቈጠር ሆነ ። |
| ወተወልዱ ለዮሴፍ ክልኤቱ ደቂቅ ዘእንበለ ይምጻእ መዋዕለ ረኃብ ዘወለደት ሎቱ አስኔት ። | ፶ | የረኃቡ ዘመን ገና ሳይመጣ አስኔት የወለደቻቸው ሁለት ልጆች ለዮሴፍ ተወለዱለት ። |
| ወሰመዮ ስሞ ለበኵሩ ምናሴ፡ እንዘ ይብል እስመ ገብረ ሊተ እግዚአብሔር ከመ እርስዕ ኵሎ ሕማምየ ወኵሎ ዘቤተ አቡየ ። | ፶፩ | እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ ያባቴ ቤተሰብም መከራ ሁሉ እንድዝነጋው አድርጎኛልና ሲል ዮሴፍም የበኩር ልጁን ስም ምናሴ ብሎ ጠራው ። |
| ወሰመዮ ስሞ ለካልኡ ኤፍሬም፡ እንዘ ይብል እስመ አዕበየኒ እግዚአብሔር በብሔረ ሥቃይ ። | ፶፪ | የሁለተኛውንም ስም እግዚአብሔር በመከራዬ አገር አበዛኝ ሲል ስሙን ኤፍሬም አለው ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወኀልፈ ሰብዓቱ ዓመት ዘጽጋብ እኁዘ ይምጻእ ሰብዓቱ ዓመት ዘረኀብ በከመ ይቤ ዮሴፍ ። | ፶፫ | የጥጋቡ ዘመን ሰባት ዓመት አልፎ ዮሴፍ እንደተናገረ የሰባት ዓመት ረኃብ ይመጣ ጀመር ። |
| ወከነ ረኃብ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ፡ ወጸርኀ ኵሉ ሕዝብ ኀበ ፈርዖን በእንተ እክል ። | ፶፬ | በግብጽ አገር ሁሉ ረኃብ ሆነ ፡ ሕዝቡም ሁሉ ስለ እኽል ወደ ፈርዖን ጮኸ (አቤት አለ) ። |
| ወይቤሎሙ ሑሩ ኀበ ዮሴፍ ወዘይቤለክሙ ውእቱ ግበሩ ። | ፶፭ | (ፈርዖንም) ወደ ዮሴፍ ሂዱ እሱ ያላችሁንም አድርጉ አላቸው ። |
| ወረኃብሰ በጽሐ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር ፡ ወርእዮ ዮሴፍ አርኀወ መዛግብተ እክል ወሤጠ ለኵሉ ሰብአ ግብጽ ። | ፶፮ | በምድርም ሁሉ ላይ ረኃብ ደረሰ ፡ ዮሴፍም እኽል ያለበትን ሪቅ ጐተራ ከፍቶ ለግብጽ አገር ሰዎች እኽሉን ሸጠላቸው ። |
| ወመጽኡ ኵሉ በሐውርት ውስተ ምድረ ግብጽ ከመ ይሣየጡ እክለ እምኀበ ዮሴፍ በእንተ ረኃብ እስመ ዐቢይ ረኃብ ኮነ ውስተ ኵሉ ብሔር ። | ፶፯ | በአገሩ ሁሉ ጽኑ ረኃብ ሁኗልና ስለ ረኃቡ ጽናት የግብጽ አህጉር ሰዎች ሁሉ እኽል ሊሸምቱ ወደ ዮሴፍ መጡ ። |
| **ምዕራፍት ፵፪ ።** | | **ምዕራፍ ፵፪ ።** |
| ወሰምዐ ያዕቆብ ከመ ቦ እክል ዘይሠይጡ በብሔረ ግብጽ ። | ፩ | ያዕቆብም በግብጽ አገር የሚሸምቱት እኽል እንዳለ ሰማ ። |
| ወይቤሎሙ ለደቂቁ ለምንት ትቴክዙ ናሁ ሰማዕኩ አነ ከመ ቦ እክል በብሔረ ግብጽ ሑሩ እንከ ወተሣየጡ ለነ ከመ ንሕየው ወኢንሙት በረኃብ ። | ፪ | ልጆቹንም ለምንት ታዝናላችሁ እነሆ እኔ በግብጽ አገር እኽል እንዳለ ሰምቻለሁ ፡ እንግዲህ በረኃብ እንዳን ሞትና እንድንኖር ሂዳችሁ ሸምታችሁ አምጡልን አላቸው ። |
| ወወረዱ ዐሠርቱ አኃዊሁ ለዮሴፍ ከመ ይሣየጡ እክለ እምብሔረ ግብጽ ። | ፫ | የዮሴፍም ዓሥሩ ወንድሞቹ ከግብጽ እኽል ሊሸምቱ ወደ ግብጽ ወረዱ ። |
| ወለብንያምሰ እኁሁ ለዮሴፍ ኢፈነዎ አቡሁ ምስለ አኀዊሁ እስመ ይቤ ኢይድወየኒ ውእቱሂ ። | ፬ | የዮሴፍ ወንድም ብንያም ግን አባቱ ከወንድሞቹ ጋር አልሰደደውም ፡ እሱም ታሞ ይሞትብኛል ብሎአልና ። |
| ወበጽሑ ደቂቀ እስራኤል ኀበ ዮሴፍ እስመ ዐቢይ ረኃብ ኮነ ውስተ ምድረ ከነአን ። | ፭ | የእስራኤልም ልጆች በከነዓን አገር ቻላቅ ረኃብ ሆኖ ነበርና ሂደው ከዮሴፍ ዘንድ ደረሱ ። |
| ወዮሴፍሰ መልአክ ውእቱ ለብሔረ ግብጽ ወውእቱ ይሠይጥ እክለ ለኵሉ አሕዛበ ምድር ፡ ወሶበ በጽሑ አኀዊሁ ሰገዱ ሎቱ በገጾሙ ውስተ ምድር ። | ፮ | ዮሴፍ በግብጽ አገር ገዢ ነበር ፡ እርሱም ለአሕዛብ ሁሉ እኽል ይሸምት ነበር ፡ ወንድሞቹም (ከሱ ዘንድ) በደረሱ ጊዜ በግምባራቸው ከምድር ወድቀው ሰገዱለት ። |
| ወሶበ ርእዮሙ ዮሴፍ ለአኀዊሁ አእመሮሙ ወተናገሮሙ እኪተ ወይቤሎሙ እምአይቴ መጻእክሙ ወይቤልዎ እምብሔረ ከነአን ንሣየጥ እክለ መጻእነ ። | ፯ | ዮሴፍም ወንድሞቹን በያቸው ጊዜ አወቃቸው ክፉ ቃልም ተናገራቸው ፡ ከወዴት መጥታችኋል ፡ ብሎ ጠየቃቸው ፡ እኽል ልንሸምት ከከነዓን አገር መጥተናል አሉት ። |
| ወዮሴፍሰ አእመሮሙ ለአኀዊሁ ወእሙንቱሰ ኢያእመርዎ ። | ፰ | ዮሴፍ ወንድሞቹ (መሆናቸውን) አወቃቸው ፡ እነሱ ግን አላወቁትም ። |
| ወተዘከረ ዮሴፍ ሕልሞ ዘሐለመ ወይቤሎሙ ሰብአ ዐይን አንትሙ ወመጻእክሙ ትርአዩ ግዕዘ ብሔር ። | ፱ | ዮሴፍም (ቀድሞ) ያለመውን ሕልም አስቦ እናንተ የአገሩን አኳኋን ለማየት የመጣችሁ ሰላዮች ናችሁ አላቸው ። |
| ወይቤልዎ አልቦ እግዚኦ አግብርቲከሰ መጽኡ ይሣየጡ እክለ ። | ፲ | እነሱም አቤቱ (እንዲህ) አይደለም ፡ አገልጋዮችህስ እኽል ሊሸምቱ የመጡ ናቸው አሉት ። |
| ወኵልነ ደቂቀ አሐዱ ብእሲ ንሕነ ወሰብአ ሰላም ወኢኮነ ሰብአ ዐይን አግብርቲከ ። | ፲፩ | ሁላችንም የአንድ ሰው ልጆችና የሰላም ሰዎች ነን (እንጂ) አገልጋዮችህስ ሰላዮች አይደለንም ። |
| ወይቤሎሙ አልቦ አላ ሰብአ ዐይን አንትሙ ወመጻእክሙ ታእምሩ ግዕዘ ብሔር ። | ፲፪ | አይደለም የአገሩን ሁኔታ ለማየት የመጣችሁ ሰላዮች ናችሁ እንጂ እኽል ለመሸመት የመጣችሁ አይደላችሁም አላቸው ። |
| ወይቤልዎ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ንሕነ አግብርቲከ ወአኀው ንሕነ በብሔረ ከነዓን ወሀሎ አሐዱ እኁነ ዘይንእስ ኀበ አቡነ ወክልኡሰ ሞተ ። | ፲፫ | እኛ አገልጋዮችህ ከከነዓን አገር ከአንድ አባት የተወለድን ዓሥራ ሁለት ወንድማማች ነን ፡ አንዱ ትንሹ ከአባታችን ዘንድ አለ ፡ ሁለተኛው ግን ሙቷል አሉት ። |
| ወይቤሎሙ በእንተዝ እብለክሙ ሰብአ ዐይን አንትሙ ። | ፲፬ | ሰላዮች ናችሁ ያልኳችሁም ስለዚህ ነው አላቸው ። |
| ወበዝ ትትዐወቁ ሕይወተ ፈርዖን ! ከመ ኢትወፅኡ እምዝየ ለእመ ኢያምጻእክምዎ ለእኁክሙ ዘይንእስ ። | ፲፭ | በዚህም ትታወቃላችሁ ትንሹ ወንድማችሁን ካላመጣችሁት ከዚህ እንደማትወጡ የፈርዖን ሕይወት (ፈርዖን |

፲፮ ፈንዉ አሐደ እምኔክሙ ያምጽእ ለእኁክሙ ፡ ወአን
ትሙሰ ንበሩ እስከ ይትዐወቅ ነገርክሙ ለእመ አማነ ትብ
ሉ ወለእመ አልቦ፡ ወእመአኮሰ ሕይወተ ፈርዖን! ከመ
ሰብአ ዐይን አንትሙ ።
፲፯ ወአንበሮሙ ውስተ ቤተ ሞቅሕ እስከ ሠሉስ መዋዕል።

፲፰ ወእምዝ ይቤሎሙ በሣልስት ዕለት ከመዝ ግበሩ ወተ
ሐይዉ እስመ አንሰ እፈርሆ ለእግዚአብሔር ።

፲፱ ወእመሰ ሰንዐ አንትሙ ይንበር አሐዱ እምኔክሙ
ውስተ ቤተ ሞቅሕ ወአንትሙሰ ሑሩ ወሰዱ እክለክሙ
ዘተሣየጥክሙ ።
፳ ወአምጽኡ ኀቤየ እኁዋክሙ ዘይንእስ ወነአምነክሙ
ቃለክሙ ወእመ አኮሰ ትመውቱ ወገበሩ ከማሁ ።

፳፩ ወተበሃሉ በበይናቲሆሙ አማን በኃጢአትነ ረከበነ
እስመ ተዐወርነ ሥቃዮ ለእኁነ እንዘ ያስተምሕረነ ወኢሰ
ማዕናሁ አሜሁ ፡ ወበእንተ ዝንቱ መጽአ ላዕሌነ ዝንቱ
ሥቃይ ።

፳፪ ወአውሥአሙ ሮቤል ወይቤሎሙ ኢይቤለክሙኑ
ኢተዐምፁ ሕፃነ ወኢሰማዕክሙኒ ናሁ ዮም ደሙ ይትኀ
ሠሥክሙ ።
፳፫ ወእሙንቱሰ ኢያእመሩ ከመ ይሰምዖሙ ዮሴፍ እስ
መ መተርጕም ሀሎ ማእከሎሙ ።
፳፬ ወተግኅሠ ዮሴፍ እምኀቤሆሙ ወበከየ ፡ ወእምዝ ገብ
አ ኀቤሆሙ ወተናገሮሙ ፡ ወነሥአ ለስምዖን ወአሰሮ
በቅድሜሆሙ ።
፳፭ ወአዘዘ ዮሴፍ ያምጽኡ አሕሳሊሆሙ ወይደዩ ሎሙ
እክለ ወወርቆሙኒ ለለአሐዱ ይደዩ ውስተ አሕስሊሆሙ
ወገብሩ ከማሁ ።
፳፮ ወጸዐኑ እክሎሙ ዲበ አእዱጊሆሙ ወኀለፉ እምህየ ።

፳፯ ወፈትሐ አሐዱ ሐስሎ በኀበ ኀደሩ ከመ ያውጽእ
እክለ ለአእዱጊሆሙ ወረከበ ዕቍረ ወርቆ ውስተ አፈ
ሐስሉ ።
፳፰ ወይቤሎሙ ለአኀዊሁ ገብአኒ ሊተሰ ወርቅየ ወናሁ
ውስተ አፈ ሐስልየ ረከብክዎ ፡ ወደንገፆሙ ልበሙ ወተ
ሀውኩ በበይናቲሆሙ ወይቤሉ ምንተ ረሰየነ እግዚአብ
ሔር ወምንትኑ ዝ ከመዝ ።
፳፱ ወበጽሑ ኀበ ያዕቆብ አቡሆሙ ውስተ ምድረ ከነዓን
ወነገርዎ ኵሎ ዘረከቦሙ ።
፴ ወይቤልዎ እኪተ ተናገረነ ብእሲ በዓለ ብሔር ወወደ
የነ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ወይቤለነ ከመ ሰብአ ዐይን ንሕነ
ለብሔር ።
፴፩ ወንቤሎ ሰንዐ ንሕነ ወኢኮነ ሰብአ ዐይን ።
፴፪ ወዐሠርቱ ወክልኤቱ አኀው ንሕነ ደቂቀ አሐዱ ብእ
ሲ ወአሐዱ እምኔነ ሞተ ወዘይንእስ ሀሎ ኀበ አቡሁ ውስ

ይሙት) ። ፩ ነገ፡ ፲፯ ፶፭ ።
ከናንተ አንዱን ልካችሁ ወንድማችሁን በታመጡት
እናንተ ግን ነገራችሁ እውነትም ሐሰትም እንደሆነ እስኪ
ታወቅ ድረስ ከዚህ ተቀመጡ ይህ ካልሆነ ግን የፈርዖን
ሕይወት (ፈርዖን ይሙት) ሰላዮች ናችሁ አላቸው ።
(ይህን ብሎ) እስከ ሦስት ቀን ድረስ በግዞት ቤት አሰ
ነበታቸው ።
ከዚህ በኋላ በሦስተኛው ቀን እንዲህ አላቸው፡ እግ
ዚአብሔር እፈራዋለሁና ትድኑ ዘንድ እንዲህ አድርጉ
አላቸው ። ነህ፡ ፭ ፲፭ ።
ስምም ከሆናችሁ ከናንተ አንዱ በእስር ቤት ይቆይ ፡
እናንተ ግን የሸመታችሁትን እኽል ይዛችሁ ሂዱ ።

ያን ትንሹ ወንድማችሁን ወደኔ አምጡ ፡ ያመጣች
ሁት እንደሆነ ነገራችሁን እናምንላችኋለን ፡ አለበለዚያ
ግን ትሞታላችሁ እንዲሁም አድርጉ አላቸው ።
እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ በእውነት በሠራነው
ኃጢአት ይህ ሁሉ መከራ አገኘን (ምን በደረግሁ ትሸጡኝ
አላችሁ ትደበድቡኝ አላችሁ) እያለ ሲማጠነን የወንድማች
ንን መከራ ቸል ብለናል ያን ጊዜም አልሰማነውምና፡ ስለዚህ
(በወንድማችን ግፍ ይህ ሁሉ መከራ መጣብን ተባባሉ ።
ሮቤልም አልሰማችሁኝም እንጂ እኔማ ይህን ብላቴና
አትበድሉ ብያችሁ አልነበረምን! እነሆ ዛሬ ደሙ ይፋረ
ዳችኋል ብሎ መለሰላቸው ። ፩ ነገ፡ ፪ ፴፪ ።
እነሱ ግን በመካከላቸው አስተርጓሚ ነበርና፡ ዮሴፍ
እንደሚሰማቸው አላወቁም ነበር ።
ዮሴፍም (ያን ጊዜ) ከነሱ ተለይቶ ሂዶ አለቀሰ፡ ከዚ
ህም በኋላ ተመልሶ ተነጋገራቸው ፡ ስምዖንንም በፊታቸው
ይዞ አሰረው ።
ዮሴፍ ዳውላቸውን አምጥታችሁ ሙሉላቸው ወርቃ
ቸውንም ለያንዳንዱ በዳውላቸው ይጨምሩላቸው ዘንድ
አዘዘ ፡ እንዲሁም አደረጉ ። ማቴ፡ ፭ ፵፬ ።
እኽላቸው በአህዮቻቸው ላይ ጭነው ከግብጽ ወጥ
ተው ሄዱ ።
ከነዚያ አንዱ ካደሩበት ቦታ ለአህዮቻቸው ገፈራ ለመ
ስጠት ዳይበቱን ቢፈታ ወርቁን ከዳይበቱ አፍ ተቋጥሮ
አገኘ ።
ለወንድሞቹም ለኔስ ወርቄ ተመለሰልኝ እነሆ በአቍ
ማዳዬ ተቋጥሮ አገኘሁት አላቸው ፡ ልቡናቸው ደነገጠባ
ቸው እርስ በርሳቸውም ታወኩ፡ እግዚአብሔር ምን አደ
ረገን ይህ ነገር ምንድር ነው፤ አሉ ።
ወደ ከነዓን ተመልሰው ከባታቸው ከያዕቆብ ዘንድ ደር
ሰው ያገኛቸውን ነገር ሁሉ ነገሩት ።
የአገሩ ጌታ የሆነው ሰው ክፉ ነገር ተናገረን ከእስር
ቤትም አገባን ፡ የአገሪቱም ሰላዮች ናችሁ አለን ።

እኛስ ደኅና ነን እንጂ ሰላዮች አይደለንም አልነው ።
ዓሥራ ሁለታችንም ያንድ አባት ልጆች ወንድማማ
ች ነን ከኛም አንዱ ሙቷል ፡ ትንሹ (ወንድማችንም) በከ

ተ ምድረ ከነዓን ።

ነዓን አገር ከበቱ ዘንድ አለ አልነው ።

፴፫ ወይቤላነ ውእቱ ብእሲ በዓለ ብሔር በዝንቱ ትትዐወቁ ከመ ሰብአ ዐይን አንትሙ አሐደ እምኔክሙ ኅድጉ ዝየ ኀቤየ ወእክለክሙሰ ዘተሣየጥክሙ ንሥኡ ወሑሩ ።

የአገሩም ጌታ ሰው እንዲህ አለን ፤ ከናንተ አንዱን ከኔ ዘንድ ትታችሁ ሂዱችሁ ያን ወንድማችሁን ያመጣችሁት እንደሆነ የታመናችሁ መሆናችሁ በዚህ ትታወቃላችሁ የሸመታችሁት እኽላችሁ ግን ይዛችሁ ሂዱ አለን።

፴፬ ወአምጽእዎ ለእኁክሙ ኀቤየ ወአእምር ከመ ስንዕ አንትሙ ወኢኮንክሙ ሰብአ ዐይን፡ ወአገብእ እንከ ለክሙ ለእኁክሙ፤ ወትትጌበሩ ውስተ ብሔርነ ።

ወንድማችሁንም ወደኔ አምጡት ወንድማችሁን ከመጣችሁ ስምም እንደሆናችሁ ሰላዮችም እንዳልሆናችሁ አውቃለሁ ፤ ወንድማችሁንም ወደናንተ እመልስዋለሁ ፤ ወደ አገራችንም (እየመጣችሁ) ትነግዳላችሁ አለን ብለው ነገሩት ።

፴፭ ወእምዝ ሶበ ሦጡ አሕሰሊሆሙ ረከቡ ኵሎሙ ዕቍረ ወርቆሙ ውስተ አሕሰሊሆሙ፤ ወሶበ ርእዩ ወርቆሙ ፈርሁ እሙንቱኒ ወአቡሆሙኒ ።

ከዚህ በኋላ ዳውላቸውን በገለበጡ ጊዜ፤ በዳውላቸው ውስጥ የተቋጠረ ወርቃቸውን ሁሉም አገኙ፤ ወርቃቸውንም በዩ ጊዜ እነሱም አበታቸውም ፈሩ ።

፴፮ ወይቤሎሙ ያዕቆብ ሊተ ዳእሙ አኅጣእክሙኒ ውሉደ ዮሴፍኒ ኢሀሎ ወስምዖንኒ ኢሀሎ፤ ብንያምሃኒ ትነሥኡኒ፤ ላዕሌየኑ ዳእሙ ኮነ ኵሉ ዝንቱ ነገር ።

ያዕቆብም እኔን ብቻ ልጅ አሳጣችሁኝ ዮሴፍ የለም፤ ስምዖንም የለም፤ ደግሞ ብንያምንም ልትወስዱብኝ ነውን፤ ይህ ሁሉ መከራ በኔ ላይ እንጂ ሆነ አላቸው ።

፴፯ ወይቤሎ ሮቤል ለአቡሁ ክልኤሆሙ ደቂቅየ ቅትል ለእመ ኢያግባእክዎ ኀቤከ ወአወፍየንዮ ሊተ ውስተ እዴየ ለወልድከ ወአነ አገብኦ ለከ ።

ሮቤልም አባቱን ልጅህን ለኔ ስጠኝ፤ እኔን መልሼ አመጣዋለሁ ወዳንተ ባልመልሰው ግን ሁለቱን ልጆቼ ግደል አለው ።

፴፰ ወይቤሎሙ ኢይወርድ ወልድየ ምስሌክሙ እስመ እኁሁኒ ሞተ ወውእቱ በሕቲቱ ተርፈ፤ ለእመቦ ከመ ደወየ ወሞተ በፍኖት እንዘ ተሐውሩ ታወርድዎ ለሢበትየ በኀዘን ውስተ መቃብር ።

ያዕቆብም ልጄ ከናንተ ጋር ወደ ግብጽ አይወርድም፤ ወንድሙ (ዮሴፍ) ሞተ፤ እሱም ብቻ ቀርቷልና ስትሄዱ በጉዳና ቢታመም (ታሞ ቢሞት) በኃዘን ያረጀ ሰውነቴን በኃዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ አላቸው ።

## ምዕራፍ ፵፫ ።

፩ ወእምዝ ጸንዐ ረኀብ ውስተ ብሔር ።

ከዚህ በኋላ በሀገሩ ረኃብ ጸና ። ዘፍ፡ ፵፩ ፶፬ - ፶፯።

፪ ወሶበ አኅለቁ ተሴስዮ እክለ ዘአምጽኡ እምብሔረ ግብጽ ይቤሎሙ አቡሆሙ ሑሩ ካዕበ አምጽኡ ለነ እክለ ተሣይጠክሙ ኅዳጠ ።

ከግብጽ ያመጡትን እኽልም ተመግበው በጨረሱ ጊዜ አበታቸው ዳግመኛ ሂዱችሁ ጥቂት እኽል ሸምታችሁ አምጡልን አላቸው ።

፫ ወይቤሎ ይሁዳ በሰማዕት አስምዐ ለነ ውእቱ ብእሲ በዓለ ብሔር ወይቤለነ ኢትሬእዩ እንከ ገጽየ ለእመ ኢመጽአ እኁክሙ ዘይንእስ ምስሌክሙ ።

ይሁዳም እንዲህ አለው ታናሹ ወንድማችሁ ከእናንተ ጋራ ካልመጣ እንግዲህ ፊቴን አታዩም ብሎ ያ አገረ ገዥው ሰው በምስክር ፊት አዳኝቶብናል አለው ።

፬ ወእመሰ ትፌንዎ ለእኁነ ምስሌነ ነሐውር ወንሣየጥ ለከ እክለ ።

ወንድማችንን ከእኛ ጋራ ከላክኸው ሂደን እኽልን እንሸምትልሃለን ።

፭ ወለእመሰ ኢትፌንዎ ለእኁነ ምስሌነ ኢነሐውር እስመ ይቤለነ ውእቱ ብእሲ ኢትሬእዩ እንከ ገጽየ ለእመ ኢያምጻእክምዎ ምስሌክሙ ለእኁክሙ ዘይንእስ ።

ወንድማችንን ከእኛ ጋራ ካልሰደድከው ግን እንሄድም ያ ሰው ታናሹ ወንድማችሁን ከእናንተ ጋራ ካላመጣችሁት እንግዲህ ፊቴን አታዩም ብሎናል ።

፮ ወይቤሎሙ እስራኤል ምንትኑ ዛቲ እኪት ዘገበርክሙ ላዕሌየ ዘነገርክምዎ ለውእቱ ብእሲ ከመ ብክሙ እኁ።

ያዕቆብም ወንድም እንዳላችሁ ለዚያ ሰው ወንድም አለን ብላችሁ የነገራችሁት በኔ ያደረጋችኋት ይህች ክፉ ነገር ምንድር ናት፤ አላቸው ።

፯ ወይቤልዎ እስመ ተስእለነ ብእሲ ፍጥረተነ ወይቤለነ ሀለወኑ አቡክሙ አረጋዊ ሕያውኑ፤ ወቦኑ ዘብክሙ እኁ ወነገርናሁ ዘከመ ተስእለነ፤ በኑ አእመርነ ከመ ይብለነ አምጽእዎ ለእኁክሙ ።

ያ ሰው ትውልዳችንን ጠየቀን ሽማግሌው አበታችሁ አለን፤ ከጕልበት ነውን፤ ወንድምስ አላችሁን፤ ብሎ እንደ ጠየቀን ነገርነው በውኑ ወንድማችሁን አምጡት እንደሚለን አውቀን ኖርአልን፤ አሉት ።

፰ ወይቤሎ ይሁዳ ለአቡሁ ፈንዎ ለዝ ሕፃን ምስሌየ ንትነሣእ ወንሑር ከመ ንሕየው ወኢንሙት ንሕነኒ ወደቂቅነኒ ።

ይሁዳም አባቱን እንዲህ አለው፤ ይህን ሕፃን ከእኔ ጋር ስደደው እንነሣ እንሂድ በሕይወት እንድንኖር አንተም እኛም ልጆቻችንም እንዳንሞት ። ዘፍ፡ ፵፪ ፪ ።

፱ ወአነ እትሐበዮ ወኪያየ ኅሥሦ ለእመ ኢያግባእክዎ ኀቤከ ወለእመ ኢያቀምክዎ ቅድሜከ ጊጉየ ከንኩ ላዕሌከ በኵሉ መዋዕልየ ።

እኔ እዋሰዋለሁ እኔን ፈልግ ወደ አንተ ባልመልሰው አምጥቼም በፊትህ ባልቆመው በዘመኔ ሁሉ አንተን የበደልኩ ልሁን ። ዘፍ፡ ፵፬ ፴ ።

፲ ወሶበ አከ ዘጕንደይነ እምደገምነ ካዕበ ገቢአ ።

በልዘገየን ኖሮ ሁለተኛ በተመለስን ነበር ።

፲፩ ወይቤሎሙ እስራኤል አቡሆሙ ለእመሰ ከመዝ ውእቱ ነገር ንሥኡ እምፍሬ ምድር ወደዩ ውስተ አሕስሊክሙ ወሰዱ ለብእሲ አምኃ ርጢነ ወመዓረ ወዕጣነ ወማየ ልብን ወጠርቤንቶስ ወክርካዐ ።

አባታቸው እስራኤልም እንዲህ አላቸው ፤ ነገሩስ እንዲህ ከሆነ ከምድር ፍሬ ወስዳችሁ በሸልቻችሁ ቋጥሩ ፤ ለሰውየውም እጅ መንሻ መድኃኒት ማር ፤ ዕጣን ፤ ልባንጃ ለውዝገውዝ ሎሚ ውሰዱ ። ዘፍ፣ ፴፫ ፳፫ ።

፲፪ ወርቅክሙሰ ንሥኡ ካዕበቶ ምስሌክሙ ወዝንቱሂ ዘረከብክሙ በውስተ አሕስሊክሙ ወንሣእክምዎ በኢያእምሮ ከነ ዮጊ ።

ወርቃችሁን ዕጥፍ አድርጋችሁ ይህንም በዳውላችሁ ውስጥ ያገኛችሁትንም ያዙ ምናልባትም በለማወቅ ተደርጎ ይሆናል ። ዘፍ፣ ፵፪ ፳፭ ፣ ፳፯ ፴፭ ።

፲፫ ወንሥእዎ ለእኁክሙ ምስሌክሙ ወተንሥኡ ወረዱ ኀበ ብእሲ ።

ወንድማችሁንም ከናንተ ጋራ ውሰዱት ተነሥታችሁም ወደዚያ ሰው ውረዱ ።

፲፬ ወአምላኪየ የሀብክሙ ሞገሰ በኀበ ውእቱ ብእሲ ወያግብእ ለክሙ ለውእቱ እኁክሙ ወለብንያምኒ ወአንሰ ዳእሙ በከመ ኀጣእኩ ውሉደ ኃጣእኩ ።

ፈጣሪዬም በዚያ ሰው ዘንድ መወደድን ይስጣችሁ ፤ ያኛውንም ወንድማችሁን ብንያምንም ይመልስላችሁ እኔ ብቻ ልጆቼን እንዳጣሁ ቀረሁ ። ዘፍ፣ ፺ ፩ ።

፲፭ ወነሥኡ እሙንቱ እደው ውእተ አምኃ ወርቆሙኒ ካዕበተ ነሥኡ ምስሌሆሙ ወለብንያምኒ ነሥእዎ ወተንሥኡ ወወረዱ ብሔረ ግብጽ ወበጽሑ ቅድሜሁ ለዮሴፍ ወሰገዱ ሎቱ ።

እነዚያ ሰዎችም ያንን እጅ መንሻ ወርቃቸውንም በዕጥፍ ወሰዱ ፤ ብንያምንም ይዘውት ተነሥተው ወደ ግብጽ አገር ወረዱ ፤ ከዮሴፍ ፊት ደርሰውም ሰገዱለት ።

፲፮ ወርእዮ ዮሴፍ ለብንያም ምስሌሆሙ ይቤሎ ለመጋቤ ቤቱ አብእሙ ለእሉ ሰብእ ውስተ ቤት ወጥባሕ ወአስተዳሉ ፤ እስመ ምስሌየ ይመስሑ እሉ እደው ፤ ወምስሌየ ይበልዑ መዓልተ ።

ዮሴፍም ብንያምን ከእነሱ ጋራ አየው የቤቱን ሹም እነዚህን ሰዎች ወደ ቤት አስገባቸው ፤ ፍሪዳ እረድ ፤ ምግብ አዘጋጅ ፤ እሊህ ሰዎች ከኔ ጋር ምሳ ይበላሉና ፤ በቀትር ጊዜም ከእኔ ጋር ይበላሉ አለው ። ዘፍ፣ ፵፫ ፲፱ ።

፲፯ ወገብረ ውእቱ ብእሲ በከመ ይቤሎ ዮሴፍ ወአብእሙ ለእሙንቱ እደው ውስተ ቤተ ዮሴፍ ።

ያም ሰው ዮሴፍ እንዳዘዘው አድርጎ እነዚያን ሰዎች ወደ ዮሴፍ ቤት አስገባቸው ።

፲፰ ወሶበ ርእዩ እሙንቱ እደው ከመ አብእዎሙ ውስተ ቤተ ዮሴፍ ይቤሉ በእንተ ዝንቱ ወርቅ ዘገብአ ውስተ አሕስሊነ ዘቀዲሙ ይወስዱነ ከመ ይኰንኑነ ወይቅንዩነ ወይንሥኡነ እንስሳነ ።

እነዚያም ሰዎች ወደ ዮሴፍ ቤት እንዳስገቧቸው በዩ ጊዜ ቀድሞ በዳውላችን ስለተመለሰው ስለዚህ ወርቅ አስጨንቀው ሊገዙን ከብቶቻችንንም ሊወስዱብን ይሆናል አሉ ።

፲፱ ወቀርቡ ኀበ ውእቱ ብእሲ ዘላዕለ ቤተ ዮሴፍ ወተናገርዎ በኆኅተ ቤቱ ።

በዮሴፍ ቤት ላይ ወደ ተሾመው ወደዚያ ሰው ቀርበው በቤቱ በራፍ ላይ አነጋገሩት ።

፳ ወይቤልዎ ናስተበቍዐከ እግዚእ ቀዲሙ ወረድነ ንሣየጥ እክለ ።

እንዲህም አሉት አቤቱ እንማልድሃለን ቀድሞ እኽል ልንሸምት ወርደን ነበር ። ዘፍ፣ ፵፪ ፫ - ፲ ።

፳፩ ወኮነ ሶበ በጻሕነ ለኀዲር ወፈታሕነ አሕሳሊነ ረከብነ ወርቀ ውስተ አሕስሊነ ዘዘዚአነ ፤ ወይእዜኒ ወርቀሰ አግባእነ ምስሌነ በመድሎቱ ።

ሸምተን ከምናድርበት ቦታ በደረስን ጊዜ እንዲህ ሆነ አይበታችንን ፈትተን የየራሳችንን ወርቅ በአይበታችን ውስጥ አገኘነው አሁንም ወርቁን በሚዛኑ ከኛ ጋር መልሰን አምጥተናል ። ዘፍ፣ ፵፪ ፳፯ ።

፳፪ ወካልእኒ ወርቀ አምጻእነ በዘንሣየጥ እክለ ወኢያእመርነ መኑ ወደዮ ለውእቱ ወርቅ ውስተ አሕሳሊነ ።

እኽልን የምንሸምትበት ሌላም ወርቅ አምጥተናል ፤ ግን ያንን ወርቅ በአይበታችን ማን እንደጨመረው አላወቅንም ።

፳፫ ወይቤሎሙ ውእቱ ብእሲ ሐሰ ለክሙ ኢትፍርሁ አምላክክሙ ወአምላከ አበዊክሙ ወሀበክሙ መድፍነ በውስተ አሕሳሊክሙ ወርቅክሙሰ ሠሚርየ ነሣእኩ ፤ ወአውጽአ ለስምዖንሂ ኀቤሆሙ ።

ያም ሰው አይዟችሁ አትፍሩ ፤ ፈጣሪያችሁ የአባቶቻችሁም ፈጣሪ የተቀበረ ወርቅን በዳውላችሁ ሰጥቶአችኋል ወርቃችሁንስ ወድጄ ተቀብያለሁ አላቸው ፤ ስምዖንንም እነሱ ወዳሉበት አወጣው ።

፳፬ ወአምጽአ ማየ ለአገሪሆሙ ወወሀበ እክለ ለአእዱጊሆሙ ።

ለእግራቸውም ውኃ አመጣ ፤ ለአህዮቻቸውም ገፈራ ሰጠ ። ዘፍ፣ ፲፰ ፬ ፣ ፲፱ ፪ ፣ ፳፬ ፴፪ ።

፳፭ ወአስተዳለዉ አምኃሆሙ እስከ ይበውእ ዮሴፍ መዓልተ እስመ ሰምዑ ከመ በህየ ይመስሕ ።

ዮሴፍም በቀትር ጊዜ እስኪገባ ድረስ እጅ መንሻቸውን አዘጋጁ ፤ በዚያ ምሳ እንደሚያደርግ ሰምተዋልና ።

፳፮ ወሶበ መጽአ ዮሴፍ ውስተ ቤቱ አምጽኡ ሎቱ አምኃሁ ዘውስተ እደዊሆሙ ውስተ ቤት ፤ ወሰገዱ ሎቱ በገጾሙ ውስተ ምድር ።

ዮሴፍም ወደ ቤቱ በመጣ ጊዜ በእጃቸው ያለውን እጅ መንሻ በቤት ውስጥ አቀረቡለት ፤ በግንባራቸውም በምድር ላይ ወድቀው ሰገዱለት ።

፳፯ ወተስእሎሙ ዜናሆሙ ወይቤሎሙ ዳኅንኑ ዝኩ አቡ
ክሙ አረጋዊ ዘትቤሉኒ ዓዲሁ ሕያውኑ ውእቱ ።

፳፰ ወይቤልዎ ዳኅን ገብርከ አቡነ አረጋዊ ወዓዲሁ ሕያ
ው ውእቱ ወይቤ ዮሴፍ ቡሩክ ውእቱ ብእሲሁ ለእግዚ
አብሔር ወአትሐቱ ርእሶሙ ወሰገዱ ሎቱ ።

፳፱ ወሶበ ነጸሮ ዮሴፍ ወርእዮ ለብንያም እኁሁ ወልደ
እሙ ይቤሎሙ ዝኑ ውእቱ እኁክሙ ዘይንእስ ዘትቤሉኒ
ናመጽእ ኀቤከ፤ ወይቤልዎ እወ፤ ወይቤሎ ዮሴፍ እግዚ
አብሔር ይሣሀልከ ወልድየ ።

፴ ወተሀውከ ዮሴፍ አማዑቲሁ ወፈቀደ ይብኪ ወቦአ
ውስተ ቤቱ ወበከየ ።

፴፩ ወተሐፅበ ገጾ ወወፅአ ተዐጊሦ ወይቤ አቅርቡ ለነ
ኅብስተ ።

፴፪ ወአቅረቡ ሎሙ እንተ በሕቲቶሙ ወሎቱኒ እንተ
ብሕቲቱ፤ ወለሰብአ ግብጽ እለ ይመስሑ ምስሌሁ እንተ
በሕቲቶሙ እስመ ኢይክሉ ሰብአ ግብጽ በሊዐ እክል
ምስለ ዕብራውያን እስመ ያስቆርርዎሙ ሰብአ ግብጽ ለኵ
ሎሙ ኖሎት ።

፴፫ ወነበረ ቅድሜሆሙ በኵርሙ ዘይልህቅ፤ ወዘይንእስኒ
በበናእሱ፤ ወነበሩ አሐዱ አሐዱ ምስለ ካልኡ ።

፴፬ ወነሥኡ ክፍሎሙ በኀቤሁ ዘዘዚአሆሙ፤ ወዐብየ ክ
ፍሉ ለብንያም እምክፍሎሙ ኃምስተ እደ ወበልዑ ወሰ
ትዩ ወሰክሩ ምስሌሁ ።

ምዕራፍ ፵፬።

፩ ወአዘዘ ዮሴፍ ለመጋቢሁ ወይቤሎ ምላእ ሎሙ አሕ
ሳሊሆሙ ለእሉ እደው መጠነ ይክሉ ፆዊረ፤ ወደይ ለለአ
ሐዱ ወርቆሙ ውስተ አሕሳሊሆሙ ።

፪ ወክራየ ዘብሩር ደይ ውስተ ሐሰሉ ለዘይንእስ ወሤ
ጠ እክሉኒ ደይ፤ ወገብረ በከመ አዘዞ ዮሴፍ ።

፫ ወሶበ ኀሀ ጽባሕ ፈነዎሙ ለእሙንቱ እደው ምስለ
እንስሳሆሙ ።

፬ ወሶበ ወፅኡ እሙንቱ እደው ዘእንበለ ይርኃቁ እም
ሀገር ነዋኀ ይቤሎ ዮሴፍ ለመጋቤ ቤቱ ተንሥእ ዴግኖሙ
ወትልዎሙ ለእሉ እደው ወአኀዞሙ ወበሎሙ እፎ አኪ
ተ ትፈድዩኒ ህየንተ ሠናይ ።

፭ ለምንት ትሰርቁኒ ገይበ ብሩር ዘቦቱ ይሰቲ እግዚእየ
እኩየ ገበርክሙ በሎሙ ።

፮ ወሐረ ወረከቦሙ ወይቤሎሙ ለምንት ትገብሩ ከመ
ዝ ወትፈድዩኒ እኪተ ህየንተ ሠናይ ዘገበርኩ ለክሙ ወት
ሰርቁኒ ገይበ ብሩር ዘእግዚእየ ።

፯ ወይቤልዎ ለምንት ትብል ከመዝ እግዚእነ ሐሰ ሎሙ
ለአግብርቲከ ኢይገብርዎ ለዝንቱ ነገር ።

፰ ወርቀ ጥቀ ዘረከብነ በውስተ አሕሳሊነ አግባእነ ኀቤ
ከ እምድረ ከነዓን ወእፎኬ ንሰርቅ እምቤትከ ወርቀ አው
ብሩረ ።

አለ ገና ከጉልበት ነው ያላችሁኝ ያ ሽማግሌ አባታ
ችሁ ደኅና ነውን፤ ገና ከጉልበት ነውን፤ ብሎ ደኅንነታ
ቸውን ጠየቃቸው ። ፩ ሳሙ፤ ፲፯ ፲፡ ።

አገልጋይህ ሽማግሌ አባታችን ደኅና ነው፤ ከጉልበ
ትም ነው አሉት፤ ዮሴፍም ሰውየው ለእግዚአብሔር ደግ
ፍጥረት ነው አለ፤ ራሳቸውንም ዝቅ አድርገው ሰገዱለት።

ዮሴፍም የእናቱን ልጅ ወንድሙ ብንያምን አሻግሮ
በየው ጊዜ ወዳንተ እናመጣዋለን ያላችሁኝ ታናሽ ወን
ድማችሁ ይህ ነውን፤ አላቸው፤ አዎን አሉት፤ ዮሴፍም
ልጄ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ አለው ። ዘፍ፤ ፴፭ ፲፰።

ዮሴፍም አንጀቱ ታወከ ሊያለቅስም ፈለገ ወደ እል
ፍኙም ገብቶ አለቀሰ ። ፩ ነገ፤ ፫ ፳፯ ። ሆሴ፤ ፲፩ ፰ ።

እንባውን ታግሦ ፊቱን ታጥቦ ወጣና እንጀራ አቅር
ቡልን አለ ። ዘፍ፤ ፵፭ ፩ ።

ለነሱም ለብቻቸው አቀረቡላቸው፤ ለሱም ለብቻው
ከርሱም ጋር ምሳ ለሚበሉ ለግብጽ ሰዎችም ለብቻቸው፤
የግብጽ ሰዎች ዘላኖችን ሁሉ ስለሚጸየፉዋቸው ግብጻው
ያን ከዕብራውያን ጋራ አብሮ መብላትን አይችሉምና ።
ዘፍ፤ ፴፯ ፴፩ ። ዘፀ፤ ፰ ፯ - ፺ ።

ታላቅ ወንድማቸውም በፊታቸው ተቀመጠ፤ ታናሹም
እንደታናሽነቱ ተቀመጠ፤ አንዱም ከንዱ ጋራ ተቀመጡ ።

የየራሳቸውን ፈንታቸውን ከሱ ዘንድ ተቀበሉ፤ የብን
ያም ፈንታ ግን ከእነሱ ፈንታ አምስት እጅ በለጠ፤ ከሱም
ጋራ አብዝተው በልተው ጠጥተው ደስ አላቸው ።

ምዕራፍ ፵፬።

ዮሴፍ አዛዡን ጠርቶ እንዲህ አለው፤ ለነዚህ ሰዎች
አይበታቸው የሚችሉትን ያህል ሙላላቸውን የያንዱንም
ወርቃቸውን የያንዳንዱ በየአይበታቸው አድርግላቸው ።

የብር ጽዋዬንም በታናሹ አይበት አድርግ የእኽሉንም
ዋጋ አብረህ አድርግ፤ እሱም ዮሴፍ እንዳዘዘው አደረገ ።

ጎህም በቀደደ ጊዜ እነዚያን ሰዎች ከከብቶቻቸው
ጋራ ሸኝቶ ሰደዳቸው ።

እነሱም በወጡ ጊዜ ከከተማ በጣም ሳይርቁ ዮሴፍ
አዛዡን ጠርቶ እንዲህ አለው፤ ተነሥተህ እነዚያን ሰዎች
ተከትለህ ያዛቸው እንዲህም በላቸው ስለ በጎ ነገር ፈንታ
እንዴት ክፉ ነገር ትከፍሉኛላችሁ፤

ጌታዬ የሚጠጣበትን የብሩን ጽዋ ለምን ሰረቃችሁኝ፤
ክፉ ነገር አደረጋችሁ በላቸው ። ዘፍ፤ ፵፬ ፲፭ ።

ሂዶም ባገኛቸው ጊዜ ለምን እንደዚህ ታደርጋላችሁ፤
በጎ ስለ አደረግሁላችሁስ ፈንታ ለምን ክፉ ነገር ትከፍሉ
ኛላችሁ፤ የጌታዬንስ የብሩን ጽዋ ለምን ትሠርቁኛላችሁ፤
አላቸው ።

እነሱም እንዲህ አሉት ጌታችን ለምን እንዲህ ትላ
ለህ፤ ለኛ ለአገልጋዮችህ አገባባቸው አይደለም ይህንን
ነገር አያደርጉትም ።

በአይበታችን ያገኘነውን ወርቅን እንኳ ከከነዓን ምድ
ር መልሰን አመጣንልህ ከቤትህ ወርቅ ወይስ ብር እን
ዴት እንሰርቃለን ። ዘፍ፤ ፵፫ ፳፩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ይእዜኒ በኀበ ዘረከብከ ክራከ እምአግብርቲከ ለይሙት ወንሕነኒ ንኩን አግብርተ ለእግዚእከ ። | ፱ | አሁንም ከአገልጋዮችህ ጽዋህን ያገኘህበት ሰው ይሙት እኛም ለጌታህ ባሮች እንሁን አሉት ። |
| ወይቤሎሙ ይእዜኒ ይኩን በከመ ትቤሉኒ ዘኀቤሁ ተረክበ ውእቱ ገይብ ይኩነኒ ገብረ፣ ወአንትሙሰ አንጹሕክሙ ርእሰክሙ ። | ፲ | አሁንም እንዳላችሁኝ ያ ጽዋ የተገኘበት ሰው ባርያ ይሁነኝ፣ እናንተ ግን ራሳችሁን ነፃ አድርጋችኋል አላቸው ። |
| ወአውረዱ አሕሳሊሆሙ ውስተ ምድር ፍጡነ ። | ፲፩ | አይበታቸውንም ፈጥነው ወደ ምድር አወረዱው ። |
| ወአኀዘ ይፍትሑ እምነ ዘይልህቅ እስከ ዘይንእስ፣ ወረከበ ውእተ ገይበ በውስተ ሐስለ ብንያም ። | ፲፪ | ከታላቅ ወንድማቸው ጀምረው እስከ ታናሽ ወንድማቸው ድረስ ይፈቱ ጀመሩ፣ (እሱም) ጽዋውን በብንያም አይበት አገኘ ። |
| ወሰጠጡ አልባሲሆሙ ወጸዐኑ አሕስሊሆሙ ዲበ አእዱጊሆሙ ወገብኡ ውስተ ሀገር ። | ፲፫ | (እነሱም) ልብሳቸውን ቀደዱ፣ አይበታቸውንም በአህዮቻቸውን ጭነው ወደ ከተማ ተመለሱ ። |
| ወቦኡ ኀበ ቤተ ዮሴፍ እንዘ ሀሎ ውእቱ ህየ ወወድቁ ውስተ ምድር በገጸሙ ። | ፲፬ | እሱ ከዚያ ሳለም ወደ ዮሴፍ ቤት ገቡ፣ በምድርም ወድቀው ሰገዱለት ። ዘፍ፡ ፴፯ ፯ ፱ - ፲ ። |
| ወይቤሎሙ ዮሴፍ ምንትኑ ዝንቱ ዘገበርክሙ ። | ፲፭ | ዮሴፍም ይህ ያደረጋችሁት ነገር ምንድር ነው፤ አላቸው ። ዘፍ፡ ፵፬ ፭ ። |
| ወይቤ ይሁዳ ምንተ ናወሥእ ለእግዚእነ ወምንተ ንብል ወበምንት ንነጽሕ ዘእግዚአብሔር አግብአ ለዐመፃነ ላዕሌነ ወበሕቱ ናሁ ክነ አግብርቲሁ ለእግዚእነ ንሕነኒ ወዝንቱኒ ዘተረክበ በኀቤሁ ገይብ ። | ፲፮ | ይሁዳም ለጌታችን ምን እንመልስለታለን ምንስ እንላለን እግዘ አብሔር ፍዳችንን በኛ ላይ ከመጣው በምን እንነጻለን፣ ነገር ግን እኛም ጽዋው ከሱ ዘንድ የተገኘበት እሱም እነሆ ለጌታችን ባሮች ሆን አለ ። |
| ወይቤ ዮሴፍ ሐሰ ሊተ እስከ እገብሮ ለዝንቱ ነገር አላ ውእቱ ብእሲ ዘበላዕሌሁ ተረክበ ክራይ ውእቱ ይኩነኒ ገብረ አንትሙሰ ሑሩ ወግብኡ ኀበ አቡክሙ በዳኅን። | ፲፯ | ዮሴፍም ይህን ነገር አደርገው ዘንድ አይገባኝም፣ ጽዋዬ የተገኘበት ያ ሰው ብቻ ባርያዬ ይሁነኝ እንጂ እናንተስ ተመልሳችሁ ወደ አባታችሁ በደኅና ሂዱ አላቸው። |
| ወቀርበ ይሁዳ ኀቤሁ ወይቤ ብቍዐኒ እግዚኦ ወአብሐኒ እንብብ ቅድሜከ እግዚእየ ኢትትመዓዖ ለገብርከ እስመ አንተ እምድኅረ ፈርዖን እግዚእ ። | ፲፰ | ይሁዳም ወደሱ ቀርቦ እቤቱ በጅ በለኝ ጌታዬ ! በፊትህ እንድናገር ፍቀድልኝ ባርያህን አትቆጣው አንተ ከፈርዖን ቀጥሎ ገዥ ነህና ። ዘፀ፡ ፴፪ ፳፪ ። |
| አንተ ተስእልከሙ ለአግብርቲከ ወትቤሎሙ ቦኑ ዘብክሙ አብ አው እኍ ። | ፲፱ | አባት ወይም ወንድም አላችሁን፣ ብለህ አንተ ባሮችን ጠየቅኸን ። |
| ወንቤለከ እግዚኦ ብነ አብ አረጋዊ ወቦ ወልድ ንኡስ ዘበርሥዓኑ ወለዶ ወእሁኊሰ ሎቱ ሞተ ወውእቱ በሕቲቱ ተርፈ ለእሙ ወያፈቅሮ አቡሁ ። | ፳ | አቤቱ፣ ሽማግሌ አባት አለን በእርጅናው ጊዜ የወለደው ትንሽ ልጅም አለው፣ ወንድሙ ግን ሙቶ ለናቱ እሱ ብቻ ቀርቷል፣ አባቱም ይወደዋል አልንህ ። |
| ወትቤሎሙ ለአግብርቲከ አምጽእዎ ኀቤየ ወአዐቅቦ። | ፳፩ | ባሮችህን ወደኔ አምጡት፣ እኔም እከባከበዋለሁ አልከቸው ። ዘፍ፡ ፵ ፲፭ - ፳ ። |
| ወንቤለከ ኢይክል ኀዲገ አቡሁ ውእቱ ሕፃን ወእመሰ ኀደጎ ይመውት ። | ፳፪ | (እኛም) ያ ልጅ አባቱን መተው አይችልም ቢተወውም ይሞታል አልንህ ። ዘፍ፡ ፵፬ ፴፩ ። |
| ወአንተሰ በሕቱ ትቤሎሙ ለአግብርቲከ ለእመ ኢያምጻእክምዎ ለእኁክሙ ዘይንእስ ኢትሬእዩ ገጽየ ዳግመ። | ፳፫ | አንተ ግን ባሮችህን ታናሽ ወንድማችሁን ካላመጣችሁት ዳግመኛ ፊቴን አታዩም አልከን ። |
| ወኮነ ሰበ ዐረግነ ኀበ አቡነ ገብርከ ዜነውናሁ ዘንተ ዘትቤለነ እግዚእነ ። | ፳፬ | ወደ ባርያህ ወደ አባታችን በተመለስንም ጊዜ አንተ ጌታችን ያዘዝከንን ነገርነው ። |
| ወይቤለነ አቡነ ሑሩ ካዕበ ተሣየጡ ለነ ኅዳጠ እክለ። | ፳፭ | አባታችንም ዳግመኛ ሂዳችሁ ጥቂት እኽል ሸምቱልን አለን ። ዘፍ፡ ፵፫ ፩ ። |
| ወንቤሎ ንሕነሰ ኢንክል ሐዊረ ለእመ እኁነ ዘይንእስ ኢመጽአ ምስሌነ እስመ ኢንክል ርእየ ገጹ ለውእቱ ብእሲ እመ ኢሀሎ እኁነ ዘይንእስ ምስሌነ ። | ፳፮ | እኛም ታናሽ ወንድማችን ከኛ ጋራ ካልሄደ መሄድን አንችልም፣ ወንድማችን ከኛ ጋራ ከሌለ የዚያን ሰው ፊት ማየት አንችልምና አልነው ። |
| ወይቤለነ ገብርከ አቡነ ተአምሩ ለሊክሙ ከመ ክልኤተ ወለደት ሊተ ይእቲ ብእሲት ። | ፳፯ | ባርያህ አባታችንም እንዲህ አለን ያች ሴት ሁለት ልጆች እንደወለደችልኝ እናንተ ታውቃላችሁ ። |
| ወአሐዱሰ ወፅአ እምኀቤየ ወትቤሉኒ አርዌ በልዖ ወኢርኢክዎ እንከ ዳግመ እስከ ይእዜ ። | ፳፰ | አንዱ ግን ከኔ ተለይቶ ሂዶ አውሬ በላው አላችሁኝ እንግዲህ እስከሁን ድረስ መልሼ አላየሁትም ። |
| ወለእመ ነሣእክምዎ ለዝኒ እምቅድመ ገጽየ ወአምከመ ደወየ በፍኖት ታወርድዎ ለርስዓንየ በኀዘን ውስተ መቃብር ። | ፳፱ | ይህንንም ከፊቴ ወሰዳችሁት በመንገድ ታሞም (ቢሞት) ያረጀ ሰውነቴን በኃዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ አለን ። |

፴፩ ወይእዜኒ ለእመ ሖርነ ኀበ ገብርከ አቡነ ወኢሀሎ
ምስሌነ ዝንቱ ሕፃን ይመውት ወናወርዶ ውስተ መቃብር
በጻዕር ለርስዓኒሁ ለገብርከ አቡነ ።

አሁንም እኛ ወደ ባርያህ ወደ አባታችን ብንሄድ
ብላቴናውም ከእኛ ጋራ ከሌለ ይሞታል ያረጀ ሰውነቱ
ንም በኃዘን ወደ መቃብር እናወርደዋለን ።

፴፪ እስመ ገብርከ ተሐበዮ ለዝንቱ ሕፃን እምአቡሁ ወይ
ቤሎ ለእመ ኢያግባእክዎ ኀቤከ ወኢያቀምክዎ ቅድሜከ
ጌጉየ ለአቡነ ሳዕሌከ አበ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ ።

እኔ ባርያህ ብላቴናውን ከባቱ ዋስ ሆኜ አምጥቼ
ዋለሁና ወደ አንተ መልሼ አምጥቼ ከፊትህም ባላቆመው
በዘመኔ ሁሉ አንተን የበደልሁ ልሁን ብዬ ዋስሁት ።

፴፫ ወይእዜኒ እከውንከ ገብረ ህየንተ ዝ ሕፃን፤ ወእንብር
ኀቤከ እግዚእ ወሕፃንሰ ይሑር ምስለ አኀዊሁ ።

አሁንም እኔ ስለዚህ ሕፃን ፈንታ ባርያህ እሆንሃለሁ
አቤቱ ከንተ ዘንድም እቀመጣለሁ ብላቴናው ግን ከወንድ
ሞቹ ጋር ይሂድ ። ዘፍ፡ ፵፬ ፴ ።

፴፬ እስመ ኢይክል አነ ሐዊረ ኀበ አቡነ ለእመ ኢሀሎ
ዝንቱ ሕፃን ኀቤነ ከመ ኢይርአይ እኪተ እንተ ትረክቦ
ለአቡነ ።

ይህ ብላቴና ከኛ ጋራ ከሌለ አባታችንን የሚያገኘውን
መከራ እንዳላይ ወደ አባቴን መሄድ አልችልምና ።

## ምዕራፍ ፵፭ ።

፩ ወሰበ ስእነ ዮሴፍ ተዐግሦ እንዘ ኵሉ ይቀውም ቅድ
ሜሁ፤ ይቤ ዮሴፍ ያሰስሉ ኵሎ ሰብአ እምቅድሜሁ ወአ
ውዕኡ ኵሎ ሰብአ እምቅድሜሁ ወአልቦ ዘተርፈ ህየ ኀበ
ዮሴፍ ሰበ ይትአመር ምስለ አኀዊሁ ።

ዮሴፍም ሰው ሁሉ በፊቱ ቁሞ ሳለ መቻል በተሳነው
ጊዜ ሰውን ሁሉ ከፊቱ ያስወጡ ዘንድ አዘዘ፤ ከፊቱም
ሰውን ሁሉ አስወጡ፤ ከወንድሞቹም ጋራ በሚተዋወቅ
በት ጊዜ ከዚያ ከዮሴፍ ዘንድ የቀረ ሰው አልነበረም ።

፪ ወጸርሐ በዐቢይ ቃል ወበከየ፤ ወሰምዑ ኵሉ ሰብአ
ግብጽ ወተሰምዐ በቤተ ፈርዖንሂ ።

ቃሉንም አሰምቶ አለቀሰ፤ የግብጽ ሰዎችም ሁሉ
ሰሙ፤ በፈርዖን ቤትም (በቤቱ) ተሰማ ። ዘኍ፡ ፲፬ ፩ ።

፫ ወይቤሎሙ አነ ውእቱ ዮሴፍ እኁክሙ፤ ሕያውኑ
ዓዲሁ ውእቱ አቡየ ወኢክህሉ አውሥኦቶ እስመ ደንገፁ ።

እርሱም እኔ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ፤ አባቴ ገና በሕ
ይወት አለን፤ አላቸው፤ ደንግጠዋልና ሊመልሱለት አል
ቻሉም ። ኢዮብ ፬ ፭ ። ፳፫ ፲፭ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፲፫ ።

፬ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለአኀዊሁ ቅረቡ ኀቤየ፤ ወቀርቡ
ኀቤሁ ወይቤሎሙ አነ ውእቱ ዮሴፍ እኁክሙ ዘሤጥክ
ሙኒ ኀበ ብሔረ ግብጽ ።

ዮሴፍም ወንድሞቹን ወደኔ ቅረቡ አላቸው፤ ወደሱም
ቀረቡ እንዲህም አላቸው፤ ወደ ግብጽ የሸጣችሁኝ እኔ
ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ ።

፭ ወይእዜኒ ኢትፍርሁ እስመ ሤጥክሙኒ ዝየ እስመ
ለሕይወት ፈነወኒ እግዚአብሔር ቅድሜክሙ ።

አሁንም ወደዚህ ስለሸጣችሁኝ አትፍሩ እግዚአብሔር
ከናንተ አስቀድሞ ለሕይወት ሰዶኛልና፤ መዝ፡ ፻፭ ፲፯ ፲፯፡

፮ እስመ ናሁ ክልኤቱ ዓመት ኀለፈ ዘረኃብ ላዕለ ምድር
ወዓዲ ሀሎ ኀምስቱ ዓመት ወአልቦ ዘየሐርስ ወዘይዘርእ ።

እነሆ በምድር ላይ ሁለቱ የራብ ዘመን አልፎአል ገና
አምስት ዓመት አለ፤ የሚያርስም የሚዘራም የለም ።

፯ ወፈነወኒ እግዚአብሔር ቅድሜክሙ ከመ ትሕየዉ
ወትትርፉ ዲበ ምድር ከመ እሴሲክሙ ።

እንድትድኑ በምድር ላይም እንድትተርፉ እመግበ
ችሁ ዘንድ እግዚአብሔር ከእናንተ አስቀድሞ ልኮኛልና፡

፰ ወይእዜኒ አኮ አንትሙ ዘፈነውክሙኒ ዳእሙ እግዚ
አብሔር ፈነወኒ ወረሰየኒ ወልደ ለፈርዖን፤ ወእግዚአ
ለኵሉ ቤቱ፤ ወመልአከ ለኵሉ ግብጽ ።

አሁንም እግዚአብሔር ልከ የፈርዖን ልጅ ለቤቱም
ሁሉ ገዥ ለግብጽም ሁሉ አለቃ አደረገኝ እንጂ እናንተ
የላካችሁኝ አይደለም ። ዘፍ፡ ፵፫ ፳፯ ። ፵፬ ፵፫ ።

፱ ወይእዜኒ ሑሩ ንግርዎ ለአቡየ ፍጡነ ወበልዎ ከመ
ዝ ይቤ ወልድከ ዮሴፍ፤ እግዚአብሔር ረሰየኒ እግዚአ
ለኵሉ ብሔረ ግብጽ፤ ወረድ እንከ ፍጡነ ወኢትንበር ህየ ።

አሁንም ፈጥናችሁ ሂዳችሁ ለአባቴ ንገሩት፤ እንዲ
ህም በሉት፤ ልጅህ ዮሴፍ እንዲህ ብሏል፤ እግዚአብሔር
ለግብጽ አገር ሁሉ ገዥ አድርጎኛል እንግዲህ ፈጥነህ ው
ረድ እዚያም አትቀመጥ ።

፲ ወተኀድር ውስተ ምድረ ጌሴም ዘዓረብ ወትሄሉ ቅሩ
ብየ አንተ ወደቂቅከ ወአበግዒከ ወአልሕምቲከ ወኵሉ
ዘብከ ።

በምዕራብ በኩል ባለ በጌሴም ምድር ትቀመጣለህ
በአጠገቤ ትኖራለህ አንተም ልጆችህም በጎችህም ላሞች
ህም የአንተም ያለህም ሁሉ ።

፲፩ ወእሴስየከ በህየ፤ እስመ ዓዲ ሀሎ ኀምስቱ ዓመት ዘረ
ኃብ ከመ ኢትሙት አንተ ወኵሉ ቤትከ ወኵሉ ጥሪትከ።

በዚያም እመግብሃለሁ ገና አምስት ዓመት የረኃብ
ዘመን አለና አንተ እንዳትሞት ልጆችህም ገንዘብህም
ሁሉ እንዳይሞቱ ። ምሳ፡ ፳ ፲፫ ።

፲፪ ወናሁ ትሬእዩ በአዕይንቲክሙ ወብንያምኒ እኁየ
ርእየ በአዕይንቲሁ ከመ ለልየ ተናገርኩክሙ በአፉየ ።

እኔ በቃሌ እንደተናገርኳችሁ እነሆ በዓይኖቻችሁ ታያ
ላችሁ ወንድሜ ብንያምም በዓይኖቹ አይቷል ።

፲፫ ወዜንውዎ ለአቡየ ኵሎ ክብርየ ዘብሔረ ግብጽ ወኵ
ሎ ዘርኢክሙ በአዕይንቲክሙ ወአፍጥኑ አምጽኦቶ ለአ
ቡየ ዝየ ።

በግብጽ አገር ያለ ጌትነቴን ባይናችሁም ያያችሁትን
ሁሉ ላባቴ ንገሩት፤ አባቴን ፈጥናችሁ ወደዚህ አምጡት
አላቸው ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፲፬ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወሐቀፎ ክሳዶ ለብንያም እኁሁ ወበከየ ላዕሌሁ ወብንያምኒ በከየ ላዕለ ክሳዱ ። | ፲፬ | የወንድሙ የብንያምን አንገት እቅፍ አድርጎ በርሱ ላይ አለቀሰ ብንያምም አንገቱን አቅፎ አለቀሰ ። |
| ወሰዓሞሙ ለኵሎሙ ወበከየ ላዕሌሆሙ ፤ ወእምድኅረዝ ተናገርዎ አኃዊሁ ለዮሴፍ ። | ፲፭ | ሁሉንም ሳማቸው በነርሱም ላይ አለቀሰ ፤ ከዚህም በኋላ ወንድሞቹ ዮሴፍን አጫወቱት ። |
| ወተሰምዐ ነገሩ በቤተ ፈርዖን ፤ ወይቤልዎ አኃዊሁ ለዮሴፍ መጽኡ ወተፈሥሐ ፈርዖን ወኵሉ ሰብኡ ። | ፲፮ | ነገሩም በፈርዖን ቤት ተሰማ ፤ የዮሴፍ ወንድሞች መጡ ብለው ነገሩት ፤ ፈርዖንም ደስ አለው ቤተሰቦቹም ። |
| ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ በሎሙ ለአኃዊከ ምልኡ ንዋያቲክሙ ወሑሩ ብሔረ ከነአን ። | ፲፯ | ፈርዖንም ዮሴፍን አለው ፤ ወንድሞችህን ገንዘባችሁን ይዛችሁ ወደ ከነዓን ሂዱ በላቸው ። |
| ወንሥእዎ ለአቡክሙ ወለኵሉ ንዋይክሙ ወንዑ ኀቤየ ወእሁበክሙ እምኵሉ በረከተ ግብጽ ወትበልዑ አንጕዓ ለምድር ። | ፲፰ | አባታችሁን ገንዘባችሁንም ሁሉ ይዛችሁ ወደኔ ኑ የግብጽንም ሀብት ሁሉ እሰጣችኋለሁ የምድርንም ፍሬዋ ትበላላችሁ ። ዘኍ ፲፰ ፳፭ ፤ ፲፪ ፳፱ ። |
| ወአንተሰ ከመዝ አዝዞሙ ለአኃዊከ ይንሥኡ ሎሙ ሠረገላተ ዘብሔረ ግብጽ ለደቂቆሙ ወለአዋልዲሆሙ ወለአንስትያሆሙ ወይንሥእዎ ለአቡሆሙ ወያምጽእዎ ። | ፲፱ | አንተም ወንድሞችህን እንዲህ ብለህ እዘዛቸው ፤ ለወንዶች ልጆቻቸው ለሴቶች ልጆቻቸው ለሚስቶቻቸውም የግብጽ ሠረገሎችን ይውሰዱ አባታቸውንም ያምጡት ። |
| ወኢይምሀክሙ ቈሰቍሰሙ ወዘርእየት ዐይኖሙ እስመ ኵሉ በረከተ ግብጽ ሎሙ ውእቱ ። | ፳ | ለጥቃቅን ዕቃቸው ዓይናቸው ያየችውን ሁሉ አያስቡ የግብጽ በረከት ሁሉ ለነሱ ነውና ። |
| ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል በከመ ይቤሎሙ ፤ ወወሀቦሙ ሠረገላተ ዮሴፍ በከመ ይቤሎ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ፤ ወወሀበሙ ስንቆሙ ለፍኖት ። | ፳፩ | የእስራኤልም ልጆች እንዳላቸው አደረጉ ፤ ዮሴፍም የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን እንዳለው ሠረገሎችን ሰጣቸው ለመንገድም ስንቃቸውን ሰጣቸው ። ዘኍ ፫ ፲፯ ። |
| ወወሀቦሙ ዐራዘ በበክልኤቱ ፤ ወለብንያምሰ ወሀበ ሠለስተ ምእተ ዲናረ ወኃምስተ ዐራዘ በዘያስተባርሪ ወለአቡሆሙኒ ከማሁ ። | ፳፪ | ሁለት ሁለት ልብስንም ሰጣቸው ለብንያም ግን ሦስት መቶ ብርና እያፈራረቀ የሚለብሰው አምስት ልብስ ሰጠው ፤ ላባታቸውም እንዲሁ ። ፪ ነገሥ ፭ ፭ - ፳፫ ። |
| ወፈነወ ዐሠርተ አእዱገ ዘይፀውሩ እምኵሉ በረከተ ግብጽ ፤ ወዐሠርተ አብቅለ እለ ይፀውሩ ስንቀ ለአቡሁ በፍኖት ። | ፳፫ | ከግብጽ የሚገኘውን ሀብት ሁሉ የሚጫኑ አሥር ወደ ሎጋዞች ፤ ለአባቱም በመንገድ ስንቅ የሚጫኑ አሥር በቅሎች ሰደደ ። ፩ ዜና መዋ ፲፩ ፳፫ ። ዳን ፬ ፲፪ - ፳፩ ። |
| ወፈነዎሙ ለአኃዊሁ ወይቤሎሙ አልብ ዘትትጋአዙ በፍኖት ። | ፳፬ | (ዮሴፍም) ወንድሞቹን በጕዳና እርስ በርሳችሁ አትጣሉ ብሎ አሰናበታቸው ። መዝ ፬ ፬ ። |
| ወወፅኡ እምብሔረ ግብጽ ወሖሩ ወበጽሑ ምድረ ከነአን ኀበ አቡሆሙ ። | ፳፭ | ከግብጽም አገር ወጥተው ወደ ከነዓን ሄደው ወደ አባታቸው ዘንድ ደረሱ ። |
| ወዜነውዎ ወይቤልዎ ሕያው ዮሴፍ ወልድከ ወውእቱ መልአከ ለብሔረ ግብጽ ወለኵሉ ደወላ ወደንገፀ ልቡ ወኢአምኖሙ ። | ፳፮ | ልጅህ ዮሴፍ በሕይወት አለ እሱ ለግብጽ አገርና ለአውራጃዋም ሁሉ ገዥ እሱ ነው ብለው ነገሩት (ያዕቆብም) ልቡ ደነገጠበት አላመናቸውም ። |
| ወነገርዎ ኵሎ ዘይቤሎሙ ዮሴፍ ወኵሎ ዘተናገሮሙ ወሰበ ርእየ ሠረገላተ ዘፈነወ ዮሴፍ ሐይወ ልቡ ወተፈሥሐ ነፍሱ ለያዕቆብ አቡሆሙ ። | ፳፯ | ዮሴፍ ያላቸውን ነገር የተናገራቸውንም ነገር ሁሉ ነገሩት ዮሴፍ የላከለትን ሠረገላዎችን በየ ጊዜም ያባታቸው የያዕቆብ ልቡ ተመለሰ ሰውነቱንም ደስ አለው ። |
| ወይቤ ያዕቆብ ዐቢይ ውእቱ ሊተ ዝንቱ እመ ዓዲሁ ሕያው ውእቱ ዮሴፍ ወልድየ አሐውር እርአዮ ዘእንበለ እሙት ። | ፳፰ | ያዕቆብም ልጄ ዮሴፍ በሕይወት ካለ ይህ ለኔ ትልቅ ነገር ነው ፤ ሳልሞት እንዳየው እሄዳለሁ አለ ። |

## ምዕራፍ ፵፮ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወተንሥአ እስራኤል ምስለ ኵሉ ንዋዩ ወበጽሐ ኀበ ዐዘቅተ መሐላ ወሦዐ መሥዋዕተ ለአምላከ ይስሐቅ አቡሁ ። | ፩ | እስራኤልም ገንዘቡን ሁሉ ይዞ ተነሣ ፤ ወደ ቤርሳቤህም ደርሶ ለአባቱ ለይስሐቅ ፈጣሪ መሥዋዕትን ሠዋ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር በሕልም ለእስራኤል ያዕቆብ ያዕቆብ „ ! ወይቤ ምንት ውእቱ ። | ፪ | እግዚአብሔርም እስራኤልን በሕልም "ያዕቆብ ያዕቆብ„ ብሎ ጠራው ምንድነው ፤ አለ ። |
| ወይቤሎ አነ ውእቱ አምላከ አበዊከ ኢትፍራህ ወሪደ ኀበ ብሔረ ግብጽ እስመ ሕዝበ ዐቢየ እሬስየከ በህየ ። | ፫ | አለውም የአባቶችህ አምላክ እኔ ነኝ ወደ ግብጽ አገር መውረድን አትፍራ ፤ በዚያ ትልቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና ። |
| ወአነ እወርድ ምስሌከ ውስተ ብሔረ ግብጽ ወአኄሉ | ፬ | እኔ ወደ ግብጽ አገር አብሬህ እወርዳለሁ ፤ በዚያም |

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ምስሌከ ዘልፈ ወዮሴፍ ወልድከ ይከድነከ አዕይንቲከ ።

ሁል ጊዜ እኔ ከአንተ ጋር እኖራለሁ፣ ልጅህ ዮሴፍም ዓይኖችህን ያብሳል (ያማውተሃል)። ዘፍ፣ ፲፭ ፲፮ ።

፭ ወተንሥአ ያዕቆብ እምኀበ ዐዘቅተ መሐላ ወነሥእዎ ደቂቁ ለያዕቆብ እስራኤል አቡሆሙ ወንዋዮሙኒ ምስሌሆሙ ወአንሶሰትያሆሙኒ ጸዐኑ ላዕለ ሠረገላት ዘፈነወ ዮሴፍ በዘያመጽእዎሙ ።

ያዕቆብም ከቤርሳቤህ ተነሣ፣ የያዕቆብም ልጆች አባታቸው ያዕቆብ እስራኤልን ወሰዱት፣ ገንዘባቸውንም ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውንም አብረው እነሱን እንዲያመጡባቸው ዮሴፍ በላካቸው ሠረገሎች ጫኑ ።

፮ ወነሥኡ ንዋዮሙ ወኵሎ ጥሪቶሙ ዘአጥረዩ በምድረ ከነአን ወበአ ያዕቆብ ብሔረ ግብጽ ወኵሉ ዘርኡ ምስሌሁ ።

ንዛቸውንም በከነዓን አገር ያጠራቀሙትን ገንዘባቸውንም ሁሉ ወሰዱ፣ ያዕቆብም ወደ ግብጽ አገር ገባ፣ ዘሩም ሁሉ ከሱ ጋራ ።

፯ ደቂቁ ወደቂቀ ደቂቁ ወአዋልዲሁ ወአዋልደ አዋልዲሁ ምስሌሁ ።

ወንዶች ልጆቹ የልጅ ልጆቹ፣ የሴቶች ልጆቹ የሴቶች ልጆቹም ልጆች ከሱ ጋራ ገቡ ። መዝ፣ ፻፭ ፳፫ ።

፰ ወከመዝ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ በኡ ብሔረ ግብጽ በኵሩ ለያዕቆብ ሮቤል ።

ወደ ግብጽ አገር የገቡ የያዕቆብ ልጆች ስማቸው እንዲህ ነው፤ የያዕቆብ የበኵር ልጅ ሮቤል ።

፱ ወደቂቀ ሮቤል ሄኖኅ ወፍሉስ ወአስሮን ወከርሚ ።

የሮቤልም ልጆች ሄኖህ ፍሉስ አሥሮንና ከርሚ ናቸው ። ፩ ዜና መዋ፣ ፭ ፫፬ ።

፲ ወደቂቀ ስምዖን የሙኤል ወያሚን ወአኁድ ወያኩን ወሱሐር ወሰኡል ዘእምነ ከናናዊት ።

የስምዖንም ልጆች የሙኤል ያሚን አኁድ ያኩን፣ ሱሐር፣ ከከናናዊቱ የተወለደው ሰኡል ።

፲፩ ወደቂቀ ሌዊ ገርሶን ወቀዓት ወሜራሪ ።

የሌዊም ልጆች ገርሶን ቀዓትና ሜራሪ ።

፲፪ ወደቂቀ ይሁዳ፣ ኤር ወአውናን ወሴሎም ወፋሬስ ወዛራ ወሞቱ ኤር ወአውናን በምድረ ከነአን ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ፋሬስ ኤስሮም ወይሞሔል ።

የይሁዳም ልጆች ኤር፣ አውናን፣ ሴሎም፣ ፋሬስና ዛራ፣ ናቸው ኤርና አውናን ግን በከነዓን አገር ሙተዋል፣ የፋሬስ ልጆችም እሊህ ናቸው፤ ኤስሮምና ይሞሔል ።

፲፫ ወደቂቀ ይሳኮር ቶላዕ ወፎሐ ወያሱብ ወሰምራ ።

የይሳኮር ልጆች ቶላዕ፣ ፎሐ፣ ያሱብና ሰምራ ናቸው ። ፩ ዜና መዋ፣ ፯ ፩ ።

፲፬ ወደቂቀ ዛብሎን ሳሬድ ወአሎን ወአሴል ።

የዛብሎንም ልጆች ሳሬድ፣ አሎንና አሴል ናቸው ።

፲፭ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ልያ ዘወለደት ለያዕቆብ በመስጴጦምያ ዘሶርያ ወዲና ወለቱ ወኵሉ ነፍስ ደቂቅ ወአዋልድ ሠላሳ ወአርባዕቱ ።

የሶርያ ክፍል በምትሆን በመስጴጦምያ ልያ ለያዕቆብ የወለደችለት ልጆች እሊህ ናቸው፤ ዲናም ሴት ልጇዋ የልያም ልጆች የሆኑ ሁሉ ሴቱም ወንዱም ሠላሳ አራት ነፍስ ናቸው ። ዘፍ፣ ፳፱ ፴፣ ፴፪ ፳፩ ።

፲፮ ወደቂቀ ጋድ ስፎን ወሕግ ወሱኒ ወአዜን ወአድ ወአሮሐድ ወአሪሔል ።

የጋድም ልጆች ስፎን፣ ሐን፣ ሕግ፣ ሱኒ፣ አዜን፣ አድ፣ አሮሔድና አርሔል ናቸው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፲፭፣ ፲፮ ፲፯ ።

፲፯ ወደቂቀ አሴር ኢያምን ወኢያሱ ወኢዩል ወበርያ ወማራ እኅቶሙ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ በርያ ክቦር ወሚልኪየል ።

የያሴር ልጆች ኢያምንና ኢያሱ ኢዩል በርያ እኅታቸው ማራም የበርያም ልጆች እሊህ ናቸው፤ ክቦርና ሚልኪየል ። ፩ ዜና መዋ፣ ፯ ፴ ።

፲፰ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ዘለፋ እንተ ወሀባ ላባ ለልያ ወይእቲ ዘወለደት ለያዕቆብ ዐሠርቱ ወስድስቱ ነፍስ እሙንቱ ።

ላባ ለልያ የሰጣት የዘለፋም ልጆች እሊህ ናቸው፤ እሷም ለያዕቆብ የወለደችለት ልጆች አሥራ ስድስት ነፍስ ናቸው ።

፲፱ ወደቂቀ ራሔል ብእሲተ ያዕቆብ ዮሴፍ ወብንያም ።

የያዕቆብ ሚስት የራኄል ልጆችም ዮሴፍና ብንያም ናቸው ።

፳ ወተወልዱ ሎቱ ደቂቅ ለዮሴፍ በብሔረ ግብጽ ዘወለደት ሎቱ ወለተ ጴጥሬፍራ አስኔት ወለተ ማሬ ዘሀገረ ሄልዮቱ ምናሴ ወኤፍሬም ።

ለዮሴፍም በግብጽ አገር ልጆች ተወለዱለት እሊህም የሄልዮቱ አገር ካህን የሚሆን የጴጥፌራ ልጅ አስኔት የወለደችለት ናቸው ።

፳፩ ወደቂቀ ምናሴ ዘወለደት ሎቱ ዕቅብቱ ሶርያዊት ማኪር ወማኪር ወለዶ ለገለአድ ወደቂቀ ኤፍሬም እኁሁ ለምናሴ ሱታላ ወጠኃን ወደቂቀ ሱታላ ኤዴን ።

የሶርያ ወገን የሆነች አገልጋዩ ለምናሴ የወለደችለት ማኪር፣ ማኪርም ገለአድን ወለደ፣ የምናሴ ወንድም የኤፍሬም ልጆች ሱታላ ጠኃን፣ የሱታላም ልጅ ኤዴን ነው ።

፳፪ ወደቂቀ ብንያም ቤላ ወበከር ወአሲቤር፣ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ በዕል ጌራ ወኖሔማን ወኤሒ ወሮስ ወመፊም ወጌራ ወለዶ ለአራድ ።

የብንያም ልጆች ቤላ፣ በከር፣ አሲቤር፣ የቤላም ልጆች ጌራ፣ ኖሔማን፣ ኤሒ፣ ሮስ፣ መፊም ናቸው፤ ጌራም አራድን ወለደ

፳፪ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ራሄል ዘወለደት ለያዕቆብ ዐሠርቱ ወአርባዕቱ ነፍስ ።
፳፫ ወደቂቀ ዳን አሳ ።
፳፬ ወደቂቀ ንፍታሌም አሲሔል ወጎሂን ወየሲር ወሴሌም ።

፳፭ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ባላ እንተ ወሀባ ላባ ለራኄል ወለቱ ወወለደቶሙ ለእሉ ለያዕቆብ ወኵሉ ነፍስ ዘወለደት ባላ ሰብዓቱ ።
፳፮ ወኵሉ ነፍስ ዘቦአ ብሔረ ግብጽ ምስለ ያዕቆብ ዘእንበለ አንስትያ ደቂቁ ስሳ ወሰብዓቱ ።
፳፯ ወደቂቀ ዮሴፍ እለ ተወልዱ ሎቱ በብሔረ ግብጽ ክልኤቱ፥ ወኮነ ኵሉ ነፍስ እንተ ቦአት ብሔረ ግብጽ ምስለ ያዕቆብ ሰብዓ ።
፳፰ ወለይሁዳ ፈነዎ ቅድሜሁ ኀበ ዮሴፍ ከመ ይትቀበሎ ውስተ ምድረ ራምሴ እንተ ስማ ቃቴሮአስ ።
፳፱ ወአንሥአ ዮሴፍ ሠረገላቲሁ ወሖረ ይትቀበሎ ለያዕቆብ አቡሁ ውስተ ምድረ ቃቴሮአስ፥ ወሶበ ረከቦ ሐቀፎ ክሳዶ ወበከየ ዐቢየ ብካየ ።
፴ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ እምይእዜሰ ለእሙት እንከ እስመ ርኢኩ ገጸከ እንዘ ሕያው አንተ ።
፴፩ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለአኀዊሁ አሐውር እንግሮ ለፈርዖን ወእብሎ አኀውየ ወቤተ አቡየ እለ ሀለዉ በምድረ ከነአን መጽኡ ኀቤየ ።
፴፪ ወኖሎተ እንስሳ ወሰብአ መራዕይ እሙንቱ ሰብእ ወአባግዒሆሙ ወአልሕምቲሆሙ ወኵሎ ንዋዮሙ አምጽኡ።

፴፫ ወእመ ጸውዐክሙ ፈርዖን ወይቤለክሙ ምንት ተግባርክሙ በልዎ ኖሎተ እንስሳ ንሕነ አግብርቲከ እምንእስነ እስከ ይእዜ ወአበዊነኒ ከማሁ ከመ፥ ከመ ትኅድሩ ምድረ ጌሴም እንተ ዓረብ ።
፴፬ እስመ ያስቆርርዎሙ ሰብአ ግብጽ ለኵሎሙ ኖሎተ አባግዕ ።

ምዕራፍ ፵፯ ።

፩ ወቦአ ዮሴፍ ወነገሮ ለፈርዖን ወይቤሎ አቡየ ወአኀውየ ምስለ እንስሳሆሙ ወንዋዮሙ መጽኡ እምድረ ከነአን ወናሁ በጽሑ ውስተ ምድረ ጌሴም ።
፪ ወነሥአ ዮሴፍ ኀምስተ እደወ እምአኀዊሁ ወአብጽሖሙ ምስሌሁ ኀበ ፈርዖን ።
፫ ወይቤሎሙ ፈርዖን ለአኀዊሁ ለዮሴፍ ምንት ተግባርክሙ ወይቤልዎ ኖሎተ እንስሳ ንሕነ አግብርቲከ ወአበዊነኒ ።
፬ ወይቤልዎ ለፈርዖን ኣኅድረነ ውስተ ምድር እንተ ኀበ መጻእነ እስመ አልቦ ምርዐይ ለእንስሳ አግብርቲከ ወጸንዐ ረኃብ ውስተ ምድረ ከነአን፥ ወይእዜኒ አኅድረነ ለአግብርቲከ ውስተ ምድረ ጌሴም ።
፭ ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ እምከመ መጽኡ አቡከ ወአኀዊከ ኀቤከ ናሁ ኵላ ምድረ ግብጽ ቅድሜከ ይእቲ ውስተ እንተ ትኄይስ ምድር ይኅድሩ ።

ለያዕቆብ የወለደችለት የራኄል ልጆች እሊህ ናቸው አሥራ አራት ነፍስ ናቸው ።
የዳን ልጅ አሳ ነው ። ዘኍ፥ ፳፮ ፵፪ ።
የንፍታሌም ልጆች አሴሔል፥ ጉኒን፥ ዮሴር ሴሌም፥ ናቸው ። ፩ ዜና መዋ፥ ፯ ፲፫ ።
ባላ ለልጅ ለራኄል የሰጣት የባላ ልጆችም እሊህ ናቸው፤ ለያዕቆብ እኒህን የወለደችለት ባላ የወለደቻቸው ነፍስ ሁሉ ሰባት ናቸው ። ዘፍ፥ ፴ ፭ - ፰ ።
ከልጆቹ ሚስቶች በቀር ከያዕቆብ ጋራ ወደ ግብጽ አገር የገቡት ስሳ ሰባት ሰዎች ናቸው ። ዘፀ፥ ፩ ፭ ።
በግብጽ ለዮሴፍ የተወለዱለት ልጆች ሁለት ናቸው፤ ከያዕቆብም ጋራ ግብጽ የገባው ሰው ሰባ ሆነ ።
ዘዳ፥ ፲ ፳፪፥ ግብ፥ ሐዋ፥ ፯ ፲፬ ።
ስሟ ቃቴሮአስ እስከ ምትባል እስከ ራምሴ ድረስ ይቀበለው ዘንድ ይሁዳን አስቀድሞ ወደ ዮሴፍ ላከው ።
ዮሴፍም አባቱ ያዕቆብን ይቀበለው ዘንድ ሠረገላውን ጭኖ ወደ ቃቴሮአስ ሄደ፥ ባገኘውም ጊዜ አንገቱን አቅፎ እጅግ አለቀሰ ።
እስራኤልም ዮሴፍን አንተ በሕይወት ሳለህ ፊትህን አይቻለሁና እንግዲህስ ልሙት አለው ።
ዮሴፍም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ ለፈርዖን እንዲህ ብዬ እነግረዋለሁ በከነዓን ምድር የሚኖሩት ወንድሞቼ የአባቴ ወገኖች ወደ እኔ መጡ ። ዘፍ፥ ፵፯ ፩ ።
ከብት የሚጠብቁ መንጋ የሚያረቡ ናቸው፥ ከብቶችን ለማሰደግ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው፤ በጎቻቸውን ላሞቻቸውን ገንዘባቸውን ሁሉ አምጥተዋል ።
ፈርዖን ጠርቶ ሥራችሁ ምንድነው ቢላችሁ፤ እኛ አገልጋዮችህ ከሕፃንነታችን ጀምሮ እስከዛሬ ከብት አርቢዎች ነን፥ አባቶቻችንም ፈጽመው እንደዚሁ ነበሩ በሉት፥ በምዕራብ በኩል ባለችው በጌሴም እንድትቀመጡ።
የግብጽ ሰዎች በግ አርቢዎችን ሁሉ ይጸየፍዋቸዋልና ።

ምዕራፍ ፵፯ ።

ዮሴፍ ገብቶ ወንድሞቹና አባቴ ከጓዛቸውና ከከብቶቻቸው ጋራ ከከነዓን አገር መጡ፥ እነሆም ወደ ምድረ ጌሴም ደረሱ ብሎ ለፈርዖን ነገረው ። ዘፍ፥ ፵፮ ፴፩ ።
ዮሴፍም ከወንድሞቹ አምስት ሰዎችን አምጥቶ ከሱ ጋራ ወደ ፈርዖን አደረሳቸው ። ግብ፥ ሐዋ፥ ፯ ፲፫ ።
ፈርዖንም የዮሴፍን ወንድሞች ሥራችሁ ምንድነው፤ አላቸው፥ እነሱም እኛ አገልጋዮችህ ከብት አርቢዎች ነን አባቶቻችንም (ዘላኖች) ናቸው አሉት ።
ፈርዖንንም በመጣንበት አገር አሳድረን ለባሮችህ ከብቶች መሠማሪያ የለምና በከነዓን ምድርም ረኃብ ፀንቶ አልና አሁንም (እኛን) ባሮችህን በጌሴም ምድር አኑረን አሉት ። ዘዳ፥ ፳፮ ፭ ።
ፈርዖንም ዮሴፍን እነሆ አባትህና ወንድሞችህ ወዳንተ ከመጡ የግብጽ አገር ሁሉ በፊትህ ናት በምትሻለው ምድር ይኑሩ ።

፮ ወእመኒ ተአምር ከመ ቦሙ ጽኑዓን እደው በውስቴቶሙ ሚሞሙ መላእክተ ኖሎት ለእንስሳየ ።

ከእነሱም መካከል ብርቱዎች እንዳሉ ብታውቅ ለከብቶቼ የዘላኖች አለቆች አድርገህ ሹማቸው አለው ።

፯ ወአብአ ዮሴፍ ለአቡሁ ወአቀሞ ቅድመ ፈርዖን ወተአምኆ ያዕቆብ ለፈርዖን ።

ዮሴፍም አባቱን አግብቶ በፈርዖን ፊት አቆመው፤ ያዕቆብም ፈርዖንን እጅ ነሣው ።

፰ ወይቤሎ ፈርዖን ለያዕቆብ ሚ መጠን መዋዕል ዘሐየውከ ።

ፈርዖንም ያዕቆብን (በዚህ ዓለም) የኖርከው ዘመን ምን ያህል ነው፤ አለው ። ፪ ሳሙ፣ ፲፱ ፴፱ ።

፱ ወይቤሎ ያዕቆብ ለፈርዖን መዋዕለ ሕይወትየሰ ዘሐየውኩ ምእት ወሠላሳ ዓመት እማንቱ ኅዳጣት ዓመታት ወእኩያተ ኮናኒ መዋዕለ ሕይወትየሰ ወንመታትየኒ ከመ ወኢምንት ኮናኒ በኀበ መዋዕለ ሕይወተ አበውየ ዘሐይዉ ።

ያዕቆብም ፈርዖንን በሕይወት የኖርኩበት ዘመኔስ መቶ ሠላሳ ዓመታት ናቸው ጥቂት ዓመታት ናቸው እንዚህም ክፉዎች ሆኑብኝ በሕይወት የኖርኩባቸው ዘመኖች ዓመቶችም አባቶቼ በኖሩባቸው የሕይወት ዘመናት መጠን እንደ ኢምንት ናቸው አለው ። መዝ፣ ፴፱ ፲፪ ።

፲ ወባረከ ያዕቆብ ለፈርዖን ወወፅአ እምኀቤሁ ።

ያዕቆብም ፈርዖንን መርቆት ከሱ ዘንድ ወጣ ።

፲፩ ወአኀደሮሙ ዮሴፍ ለአቡሁ ወለአኀዊሁ ወወሀቦሙ ምኩናነ በምድረ ግብጽ ውስተ እንተ ትኄይስ ምድር ውስተ ምድረ ራምሴ ዘአዘዘ ሎሙ ፈርዖን ።

ዮሴፍም ወንድሞቹንና አባቱን በምድረ ግብጽ ግዛት ሰጥቶ ፈርዖን በዘዘላቸው በመልካሚቱ ምድር በራምሴ አኖራቸው ። ዘፀ፣ ፩ ፲፩፣ ፲፪ ፴፯ ።

፲፪ ወዮሴፍ ይሰፍር ሥርናየ ሲሳየ ለአቡሁ ወለአኀዊሁ ወለኵሉ ቤተ አቡሁ ለለአሐዱ ነፍስ ይሰፍር ሥርናየ ።

ዮሴፍም ለአባቱና ለወንድሞቹ ላባቱም ቤተሰቦች ሁሉ ምግብ የሚሆን ሥንዴን ይሰፍር ነበር፤ ለእያንዳንዱም ነፍስ ምግብ ሥንዴን ይሰፍር ነበር ።

፲፫ ወአልቦ ሥርናይ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ እስመ ፀንዐ ረኃብ ጥቀ፣ ወኀልቀ በረኃብ ብሔረ ግብጽ ወከነአን ።

በመላ የግብጽ አገር ሥንዴ አልነበረም፤ ረኃብ እጅግ ጸንቷልና የግብጽና የከነዓን አገር በረኃብ አለቀ ።

፲፬ ወአስተጋብአ ዮሴፍ ኵሎ ወርቀ ዘአምጽኡ ሰብአ ግብጽ ወሰብአ ከነአን ሤጠ እክል ዘሤጠ ሎሙ ወአብአ ዮሴፍ ኵሎ ወርቀ ውስተ ቤተ ፈርዖን ።

ዮሴፍም የሸመተላቸውን የእኽሉን ዋጋ የሆነ የግብጽና የከነዓን ሰዎች ያመጡለት የእኽል ዋጋ የሆነውን ወርቅ ሁሉ ሰብስቦ ወርቁንም በሙሉ ወደ ፈርዖን ቤት አገባ ። ዘፍ፣ ፵፩ ፶፩ ።

፲፭ ወኀልቀ ኵሉ ወርቅ ዘብሔረ ግብጽ ወዘኵሉ ብሔረ ከነአን፣ ወመጽኡ ወበኡ ኵሉ ሰብአ ግብጽ ኀበ ዮሴፍ ወይቤልዎ ሀበነ እክለ ከመ ኢንሙት በቅድሜከ እስመ ኀልቀ ወርቅነ ።

በግብጽ አገር በከነዓን አገር ያለ ወርቅ ሁሉ አለቀ፤ የግብጽም ሰዎች ሁሉ ወደ ዮሴፍ መጥተው ወርቃችን አልቆአልና በፊትህ እንዳንሞት እኽል ስጠን አሉት ።

፲፮ ወይቤሎሙ ዮሴፍ አምጽኡ እንስሳክሙ ወእሁበክሙ እክለ ህየንተ እንስሳክሙ እመ ኀልቀ ወርቅክሙ ።

ዮሴፍም ወርቃችሁ ካለቀ ከብቶቻችሁን አምጡና ስለ ከብቶቻችሁ ፈንታ እኽልን እሰጣችኋለሁ አላቸው ።

፲፯ ወአምጽኡ እንስሳሆሙ ኀበ ዮሴፍ ወወሀቦሙ እክለ ህየንተ አብግዒሆሙ ወአልሕምቲሆሙ ወህየንተ አእዱጊሆሙ ወሴሰዮሙ እክለ በይእቲ ዓመት ።

ከብቶቻቸውንም ወደ ዮሴፍ አመጡ፤ እሱም ስለላሞቻቸውና ስለበጎቻቸው ስለአህዮቻቸውም ፈንታ እኽልን ሰጣቸው፤ በዚያችም ዓመት እኽልን መገባቸው ።

፲፰ ወተፈጸመት ይእቲ ዓመት ወመጽኡ ኀቤሁ በካልእት ዓመት ወይቤልዎ ሀበነ እክለ ከመ ኢንሙት ወኢንኅልቅ ለእግዚእነ እስመ ተወድአ ወርቅነሂ ወንዋይነሂ ወእንስሳነሂ ወአኀለቅናሁ ለኵሉ እግዚኦ ወአልቦ ዘተርፈ ለነ በቅድሜከ እግዚኦ ዘእንበለ ሥጋ ዚአነ ወምድርነ ።

ያችም ዓመት አለቀች በሁለተኛውም ዓመት ወደሱ መጥተው እንዲህ አሉት፤ እንዳንሞት እኽል ስጠን ለጌታችንም ረኃብ እንዳናልቅበት ወርቃችንም ከብታችንም አልቋል ገንዘባችንም ሁሉ ተጨርሷልና አቤቱ፤ ሁሉን ሽጠን ጨረስነው፤ ከሰውነታችንና ከምድራችን በቀር በፊትህ ለእኛ የቀረን ነገር የለም አሉት ።

፲፱ ከመ ኢንሙት እንከ በቅድሜከ ወምድርነሂ ከመ ኢትማስን ንሥአነ ወአጥርየነ ኪያነሂ ወምድረነሂ ህየንተ እክል ወንኩን አግብርተ ለፈርዖን ህየንተ እክል ወምድርነሂ ትኩን ሎቱ ወሀበነ ዘርአ ከመ ንዝራእ ከመ ንሕየው ወኢንሙት ወምድርነሂ ከመ ኢትማስን ።

እንግዲህ በፊትህ እንዳንሞት ምድራችንም እንዳትጠፋ ስለ እኽል ፈንታ እኛንም ምድራችንንም ይዘን ግዛን፤ እኛም ለፈርዖን ባሮች እንሁን፤ ምድራችንም ለሱ ትሁን፤ እንዳንሞት እንድን ዘንድ ምድራችንም እንዳትጠፋ እንድንዘራ ዘርን ስጠን ።

፳ ወአጥረየ ዮሴፍ ኵሎ ምድሮሙ ለግብጽ ወአግብአ ለፈርዖን ኵሎ ምድሮሙ እስመ ኀየሎሙ ረኃብ ወኮነ ኵሉ ምድር ለፈርዖን ።

ረኃብም በርትቶባቸዋልና ዮሴፍ የግብጽ ምድራቸውን ሁሉ ገዝቶ ለፈርዖን አገባው፤ ምድሩም ሁሉ ለፈርዖን ሆነ ።

፳፩ ወኵሎ ሕዝብ ከንዎ አግብርቲሁ ወቀነዮሙ እምአጽናፈ ምድር ወአድባሪሆሙኒ ወኵሎ ደወሎሙ ለግብጽ

ሕዝቡም ሁሉ ባሮቹ ሆኑ ከዳር እስከዳርም ገዛቸው ጕልታቸውንም አገራቸውንም ሁሉ እስከ ከነዓን ምድር

እምአጽናፈ ደወሎሙ ለከነአን ዘእንበለ ምድሮሙ ለማርያን በሕቲታ ዘኢያጥረየ ዮሴፍ ።

፳፪ እስመ ወሀበሙ ፈርዖን ለማርያን ወፈተቶሙ ወጸገዎሙ ወበእንተ ዝ ኢሤጡ ምድሮሙ ።

፳፫ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለኵሎሙ ሰብአ ግብጽ ናሁ ተሣየጥኩክሙ ኪያክሙሂ ወምድረክሙሂ ለፈርዖን ፡ ንሥኡ ለክሙ ዘርአ ወዝርእዋ ለምድርክሙ ።

፳፬ ወታገብኡ ለፈርዖን እክለ ኃምስተ እደ ወአርበዕቱ እድ ለክሙ ዘይከውነክሙ ዘርአ ለምድርክሙ ወለሲሳይክሙ ወለሲሳየ ኵሉ ሰብእክሙ ።

፳፭ ወይቤልዎ አሕየውከነ ወረከብነ ሞገሰ በቅድሜሁ ለእግዚእነ ወኮነ አግብርተ ለፈርዖን ።

፳፮ ወኮነት ዛቲ ሥርዓት እንተ ሠርዐ ዮሴፍ ውስተ ምድረ ግብጽ ወቆመት እስከ ዛቲ ዕለት ከመ ያግብኡ ኃምስተ እደ ለፈርዖን እስከ ዮም ዘእንበለ ምድረ ማርያን በሕቲታ እንተ ኢኮነት ለፈርዖን ።

፳፯ ወነበረ እስራኤል ውስተ ጌሴም ወኮነት ይእቲ ክፍሎሙ ወበዝኁ ወመልኡ ጥቀ ።

፳፰ ወሐይወ ያዕቆብ በምድረ ግብጽ ዐሠርተ ወሰብዐተ ዓመተ ፡ ወኮነ ኵሉ ዓመተ ሕይወቱ ለያዕቆብ ምእተ ወአርብዐ ወሰብዓተ ዓመተ ።

፳፱ ወቀርበ መዋዕሊሁ ለእስራኤል ለመዊት ወጸውዖ ለዮሴፍ ወልዱ ወይቤሎ እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ደይ እዴከ ላዕለ እዴየ ወግበር ምስሌየ ምሕረተ ወጽድቀ ከመ ኢትቅብረኒ ውስተ ምድረ ግብጽ ዳእሙ ከመ እኑም ምስለ አበውየ ።

፴ ወአውጽአኒ እምብሔረ ግብጽ ወቅብረኒ ውስተ መቃብሮሙ ለአበውየ፡ ወይቤሎ ዮሴፍ አሆ እገብር ለከ ዘትቤለኒ።

፴፩ ወይቤሎ መሐልኬ ሊተ ፡ ወመሐለ ሎቱ ወሰገደ እስራኤል ውስተ ከተማ በትሩ (ላዕለ ርእሰ ዓራቱ) ።

## ምዕራፍ ፵፰ ።

፩ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር ይቤልዎ አኃዊሁ ለዮሴፍ ደክመ አቡነ ፡ ወነሥአ ዮሴፍ ክልኤተ ደቂቆ ምናሴሃ ወኤፍሬምሃ ።

፪ ወይቤልዎ ለእስራኤል ናሁ ወልድከ ዮሴፍ መጽአ ኀቤከ ወተኀየለ እስራኤል ወተንሥአ ነበረ ዲበ ምስከቢሁ።

፫ ወይቤሎ ያዕቆብ ለዮሴፍ አምላኪየ ዘአስተርአየኒ በሎዛ በምድረ ከነአን ባረከኒ ።

፬ ወይቤለኒ ናሁ አነ አበዝኀከ ወአስተበዝኀከ ወእገብረከ ማኅበረ አሕዛብ ወእሁበከሃ ለዛቲ ምድር ወለዘርእከ እምድኅሬከ ከመ ይምልክዋ ለዓለም ።

፭ ወይእዜኒ እሉ ደቂቅከ ክልኤቱ ኤፍሬም ወምናሴ እለ ተወልዱ ለከ በብሔረ ግብጽ ዘእንበለ እምጻእ አነ ዝየ ኀቤከ ከመ ሮቤል ወስምዖን ሊተ እሙንቱ ።

፮ ወእመበ ዘወለድከ እምይእዜ በአስማተ አበዊሆሙ

ድንበር ድረስ ፡ ዮሴፍ ከልገዛው ከካህናት ማእቱ በቀር ሁሉንም ሁዳድ አደረገው ።

ፈርዖን ለካህናት ድርጎ ሰጥቷቸዋልና ፈርዖን የሰጣቸውንም ይመገቡሉና ስለዚህ ምድራቸውን አልሸጡም ።

ዮሴፍም የግብጽን ሰዎች ሁሉ እንዲህ አላቸው እናንተንም ምድራችሁንም እነሆ ለፈርዖን ገዝቻችኋለሁ ዘር ወስዳችሁ ምድራችሁን ዝሩአት ።

አምስቱን እጅ ለፈርዖን ታገባላችሁ ፡ አራቱ እጅ ለምድራችሁ ዘር ለናንተና ለቤተ ሰቦቻችሁም ሁሉ ምግብ ይሆናችኋል ።

(በረኃብ ከመሞት) አንተ አዳንከን በጌታችንም ፊት ሞገስ አገኘን ፡ ለፈርዖንም ባሮች ሆን አሉት ።

ለፈርዖን ካልሆነች ከካህናቱ ምድር ብቻ በቀር እስከ ዛሬ ድረስ ለፈርዖን አምስት እጅ ያገቡ ዘንድ ዮሴፍ የሠራት ይህች ሕግ እስከዚች ቀን ድረስ በግብጽ አገር ሥርዓት ሆና ጸናች ። ዘፍ፡ ፵፯ ፳፪ ።

እስራኤልም በጌሴም አገር ኖረ ፡ እሷም ክፍላቸው ሆነች ፡ መሉ እጅግም በዙ ። ዘፍ፡ ፵፰ ፲ ።

ያዕቆብም በምድረ ግብጽ አሥራ ሰባት ዓመት ኖረ ፡ የያዕቆብ መላው የሕይወቱ ዘመን ፻፵፯ ዓመት ሆነ ።

ያዕቆብም የሚሞትበት ቀን በደረሰ ጊዜ ልጁ ዮሴፍን ጠርቶ እንዲህ አለው ፤ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ በጅህ እጄን ምታ በግብጽ ምድር እንዳትቀብረኝ ምሕረትንና ቸርነትን አድርግልኝ ፡ ከአባቶቼ ጋር ላንቀላፋ እንጂ። ዘዳ፡ ፴፩ ፲፬ ፡ ፩ ነገ፡ ፪ ፩ ።

ከግብጽ ምድር አውጥተህ በአባቶቼ መቃብር ቅበረኝ ዮሴፍም እሺ ያልከኝን አደርግልሃለሁ አለው ።

ማልልኝም አለው (እሱም) ማለለት ያዕቆብም ወደ አልጋው ራስጌ ዘንበል አለ ። ፩ ነገ፡ ፵፰ ፪ ። ዕብ ፲፩ ፳፩።

## ምዕራፍ ፵፰ ።

ከዚህም ነገር በኋላ እንዲህ ሆነ ወንድሞቹ አባታችን ደከመ ብለው ለዮሴፍ ነገሩት ፡ ዮሴፍም ሁለቱን ልጆቹን ኤፍሬምንና ምናሴን ይዞ ሄደ ።

ለእስራኤልም እነሆ ልጅህ ዮሴፍ ወደ አንተ መጥቷል ብለው ነገሩት ፡ ያዕቆብም ተበረታቶ ተነሥቶ በአልጋው ላይ ተቀመጠ ።

ያዕቆብ ዮሴፍን እንዲህ አለው ፤ በከነዓን ምድር በሎዛ የተገለጠልኝ ፈጣሪዬ ባረከኝ ። ዘፍ፡ ፲፯ ፩ ።

እኔ አበዛሃለሁ የብዙ ብዙም አደርግሃለሁ የአሕዛብም ጉባኤ አደርግሃለሁ ፡ ይህችንም ምድር ለአንተ እሰጥሃለሁ ከንተም በኋላ የዘላለም ርስት ያደርጓት ዘንድ ለዘርህም ብሎኛል ። ዘፍ፡ ፲፯ ፲፰ ።

አሁንም እኔ ወደዚህ ወደ አንተ ሳልመጣ በግብጽ አገር የተወለዱልህ እሊህ ሁለቱ ልጆችህ ኤፍሬምና ምናሴ እንደ ስምዖንና እንደ ሮቤል የኔ ናቸው ።

እንግዲህም ወዲህ የምትወልዳቸው ልጆች ቢኖሩ

ይሰመዩ ወይኩኑ ውስተ ክፍለ አኃዊሆሙ ።

፯ ወአመ መጻእኩ አነ እመስጴጦምያ ዘሶርያ ሞተት ራ ኄል እምከ በምድረ ከነአን በፍኖት ሶበ ቀረብኩ ኀበ ምርዋጸ አፍራስ ዘኤጴፍራታ ለበጺሐ ኤፍራታ ወቀበርክዋ ውስተ ፍኖት ዘምርዋጸ አፍራስ ዘስሙ ቤተ ልሔም ።

፰ ወሶበ ርእየ እስራኤል ደቂቆ ለዮሴፍ ይቤሎ ምንትክ እሉ ።

፱ ወይቤሎ ዮሴፍ ለአቡሁ ደቂቅየ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር በዝየ፡ ወይቤሎ ያዕቆብ አምጽኦሙ ኀቤየ ከመ እባርኮሙ ።

፲ ወአዕይንቲሁሰ ለእስራኤል ክብዳ ወተከድና እምርስእ ወኢይክል ከሚቶተ ወነጽሮ፡ ወአቅረቦሙ ኀቤሁ ወሐቀቀፎሙ ወሰዓሞሙ ።

፲፩ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ ናሁ ኢተፈለጥኩ እምገጽከ ወናሁ ዘርአከኒ አርአየኒ እግዚአብሔር ።

፲፪ ወአውፅኦሙ ዮሴፍ እማእከለ ብረኪሁ ወሰገደ ሎቱ በገጹ ውስተ ምድር ።

፲፫ ወነሥኦሙ ዮሴፍ ለክልኤቱ ደቂቁ፡ ወአቀሞ ለኤፍሬም በየማኑ ኀበ ፀጋመ እስራኤል፡ ወለምናሴ አቀሞ በፀጋሙ ኀበ የማነ እስራኤል ወአቅረቦሙ ኀበ አቡሁ ።

፲፬ ወሰፍሐ እስራኤል እዴሁ እንተ የማን ወአንበረ ላዕለ ርእሰ ኤፍሬም ወውእቱ ይንእስ እምእኁሁ፡ ወእዴሁ እንተ ፀጋም አንበረ ላዕለ ርእሰ ምናሴ ወአስተኀለፈ እደዊሁ ወባረኮሙ ።

፲፭ ወይቤ ውእቱ እግዚአብሔር ዘአሥመርዎ አበውየ ቅድሜሁ አብርሃም ወይስሐቅ ወእግዚአብሔር ውእቱ ዘሐፀነኒ ወሴሰየኒ እ ንእስየ እስከ ዛቲ ዕለት ።

፲፮ ወመልአከ እግዚአብሔር ዘአድኀነኒ እምኵሉ እኩይ ውእቱ ለይባርኮሙ ለእሉ ሕፃናት ወይሰመይ ስምየ በሙ ወስመ አበውየ አብርሃም ወይስሐቅ ይብዝኁ ወይትባዝኁ ወይምልኡ ዲበ ምድር ።

፲፯ ወሶበ ርእየ ዮሴፍ ከመ አንበረ አቡሁ እዴሁ እንተ የማን ላዕለ ርእሰ ኤፍሬም ወእዴሁ እንተ ፀጋም ላዕለ ርእሰ ምናሴ ከነ ሎቱ ክቡደ፡ ወአኀዘ ዮሴፍ እደ አቡሁ ያስተኃልፍ እምርእሰ ኤፍሬም ላዕለ ርእሰ ምናሴ ።

፲፰ ወይቤሎ ዮሴፍ ለአቡሁ አኮ ከመዝ አባ እስመ ዝንቱ በኵርየ አንብር እዴከ እንተ የማን ላዕሌሁ ።

፲፱ ወይቤሎ እስራኤል አአምር ወልድየ አአምር፡ ዝኒ ይከውን ሕዝበ ዓቢየ፡ አላ እኁሁ ዘይንእስ የዐብዮ ወዘርኡ ብዙኀ አሕዛበ ይከውን ።

፳ ወባረኮሙ በይእቲ ዕለት ወይቤ ይትባረክ ብክሙ፡ እምላከ እስራኤል ወይበሉ ይባርክ እግዚአብሔር ከመ ኤፍሬም ወምናሴ፡ ወአቅደመ ኤፍሬም እምናሴ ።

፳፩ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ ናሁ አነ እመውት፡ ወየሀሉ እግዚአብሔር ምስሌክሙ ወያግብአክሙ ውስተ ም

ግን በወንድሞቻቸው ስም ይጠሩ፤ በወንድሞቻቸውም ዕጣ ይግቡ ።

እኔ ከሶርያ ወንዞች መካከል በመጣሁ ጊዜ ኤፍራታ ለመድረስ ስቃረብ ፈረስ በሚፈትኑበት በከነዓን ምድር እናትህ ራኄል ሞተች በጐዳና ላይ ወደ ፈረስ መፈተኛው ስሙ ቤተልሔም በሚባለውም መንገድ ቀበርኋት ።

እስራኤልም የዮሴፍን ልጆች ባየ ጊዜ እነዚህ ምንህ ናቸው፤ አለው ።

ዮሴፍም አባቱን እግዚአብሔር በዚህ የሰጠኝ ልጆቼ ናቸው አለው፤ ያዕቆብም ልባርካቸው ወደኔ አምጣቸው አለው ። ዕብ፡ ፲፩ ፳፩ ።

የእስራኤልም ዐይኖቹ ከእርጅና የተነሣ ፈዘው (ተጨፍነው) ነበር ዓይኑን መግለጥም ማየትም አይቻልም ነበር፤ ወደሱም አቀረባቸው አቀፋቸው ሳማቸውም ።

እስራኤልም ዮሴፍን እነሆ ከፊትህ አልተለየሁም እነሆም ዘርህን እግዚአብሔር አሳየኝ አለው ።

ዮሴፍም ከጕልበቱ መካከል ፈቀቅ አደረጋቸው በምድር ላይም በግንባሩ ወድቆ ሰገደለት ።

ዮሴፍም ሁለት ልጆቹን አምጥቶ ኤፍሬምን በያዕቆብ ግራ በሱ ቀኝ አቆመው፤ ምናሴንም በሱ ግራ በያዕቆብ ቀኝ አቁሞ ወደ አባቱ አቀረባቸው ።

እስራኤልም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረ እሱም ከወንድሙ ያንስ ነበር፤ ግራ እጁንም በምናሴ ራስ ላይ አኖረ፤ እጆቹን አመሳቅሎም ባረካቸው ። ዘፍ፡ ፵፰ ፲፱ ።

እንዲህም አለ አባቶቼ አብርሃም ይስሐቅ በፊቱ ያገለገሉት እሱ እግዚአብሔር ከሕፃንነቴ ጀምሮ የተከባከበኝ እስከ ዛሬ እስከዚች ቀን ድረስ የመገበኝ እሱ እግዚአብሔር ነው ። ዘፍ፡ ፲፯ ፩፡ ፳፬ ፵ ።

ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ የእግዚአብሔር መልአክም እነዚህን ልጆች እሱ ይባርካቸው (ያክብራቸው) ስሜም በነሱ ይጠራ፤ የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅ ስምም በነሱ ይጠራ ይብዙ፤ የብዙ ብዙም ይሁኑ፤ ምድርንም ይምሉአት ። ፪ ሳሙ፡ ፬ ፱ ። ኢሳ፡ ፵፬ ፳፪ - ፳፫ ።

ዮሴፍም አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ግራ እጁን በምናሴ ራስ ላይ እንዳኖረ ባየ ጊዜ ክብድ ነገር ሆኖበት፤ የአባቱንም እጅ ይዞ ከኤፍሬም ራስ ላይ ወደ ምናሴ ራስ ላይ ያስተላልፍ ጀመር ። ዘፍ፡ ፳፰ ፰፡ ፴፰ ፲ ።

ዮሴፍም አባቱን አባቴ እንዲህ አይደለም፤ የበኵር ልጄ ይህ ነውና ቀኝ እጅህን በሱ ላይ አኑር አለው ።

አባቱም አውቃለሁ ልጄ አውቃለሁ ይህም ታላቅ ሕዝብ ይሆናል፤ ይህም ታላቅ ነው ግን ታናሽ ወንድሙ ይበልጠዋል ዘሩም ብዙ ሕዝብ ይሆናል አለው ።

በዚያችም ቀን ባረካቸው በእና ምክንያት የእስራኤል ፈጣሪ ይክበር (ሰዎች) እንደ ኤፍሬምና እንደ ምናሴ እግዚአብሔር ይባርክህ ይበሉ አለ፤ ኤፍሬምን ከምናሴ አስቀደመ ። ሩት ፬ ፲፩ ፲፪ ።

እስራኤልም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ እነሆ እኔ እሞታለሁ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይኑር ወደ አባቶቻችሁ

ድረ አበዊክሙ ።
፳፪ ወአነ እሁበከ ምህርከ ሡናየ ዘይኄይስ እም፤ አኀዊከ ዘነሣእኩ እምእዴሆሙ ለአሞሬዎን በቀስትየ ወበኲናትየ።

## ምዕራፍ ፵፱ ።

፩ ወጸውዖሙ ያዕቆብ ለደቂቁ ወይቤሎሙ ተጋብኡ ኀቤየ ወአየድዓክሙ እንተ ትረክበክሙ በደኃሪ መዋዕል ።
፪ ወተጋብኡ ወመጽኡ ደቂቁ ለያዕቆብ፣ ወይቤሎሙ ስምዕዎ ስምዕዎ„ ለአቡክሙ ።
፫ ሮቤል በኵርየ ኀያል ውእቱ ዘቀዳሚ ወልድየ እኩየ ከነ ወአግዘፈ ክሳዶ ወዕፁበ ገብረ ።

፬ ቈረ ከመ ማይ እስመ ዐርገ ዲበ ምስካበ አቡሁ ወአርኰሰ ለውእቱ ምስካብ ይእተ አሚረ ዘዲቤሁ ዐርገ።
"ሮቤል በኵርየ ርእሰ ጥብዓንየ ጸነ ከመ ማይ ጊዜ
"ስቅየተ ምድር ወበሕቱ ትኀድር ላዕሌሁ ጸጋ እግዚ
"አብሔር እስመ ገብረ ምሕረተ ምስለ ዮሴፍ ወልድየ„።

፭ ስምዖን ወሌዊ አኀው እሙንቱ ፈጸምዋ ለዐመፃ በቃሕዎሙ ወበኲናቶሙ ።

፮ ነፍስየ ኢትትራከበሙ ወኢይረድ ውስተ ሁከቶሙ እስመ በመዐቶሙ ቀተሉ ሰብአ ወበፍትወቶሙ መተሩ ሥርወ አህጉር ።
፯ ርጉመ ለይኩን መዐቶሙ እስመ ኢገገጹ እምቍጥዓሆሙ ወኢተመይጡ እመዓቶሙ እከፍሎሙ ውስተ ያዕቆብ ወእዘርዎ ውስተ እስራኤል ።
፰ ይሁዳ፣ ይሴብሑከ አኀዊከ፣ እደዊከ ላዕለ ዘባናሙ ለጸላእትከ፣ ይሰግዱ ለከ ደቂቀ አቡከ ።
፱ ይሁዳ እጓለ አንበሳ እምኀዝአትከ ዕርግ ወልድየ ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ እጓለ አንበሳ አልቦ ዘያነቅሐከ ።
፲ ኢይጠፍእ ምልክና እምይሁዳ ወሥስፍና እምአባሉ እስከ አመ ይረክብ ዘጽኑሕ ሎቱ ወውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ ።
፲፩ የአስር በዐፀደ ወይን ዕዋሎ ወበዕፀ ዘይት እድጎ ወየሐፅብ በወይን አልባሲሁ ወበደመ አስከል ሰንዱኖ ።

፲፪ ፍሡሐት አዕይንቲሁ እምወይን ወፀዓዳ ከመ ሐሊብ ስነኒሁ ።
፲፫ ዛብሎን፣ ሥሑና የኀድር ከመ መርሰ አሕማር ወይሰፍሕ እስከ ሲዶና ።
፲፬ ይሳኮር፣ ፈተዋ ለሠናይት ወየዐርፍ ማእከለ መዋርስት።

፲፭ ወሰበ ርእየ ከመ ሠናይት ይእቲ ዕረፍት አትሐተ መትከፍቶ ከመ ይትቀነይ ለምድር ወጸመወ ወከነ ሐረሳዌ ብእሲ ።
፲፮ ዳን፣ ይኴንን ሕዝበ ከመ አሐቲ እምነገደ እስራኤል ።
፲፯ ከመ ለዳን አርዌ ምድር ዘይጸንሕ ውስተ ፍኖት ዘይነ

ምድርም ይመልሳችሁ ። ዘፍ፣ ፵፯ ፲ ።
እኔም ከወንድሞችህ የሚበልጥ መልካም ምርኮን እሰጥኻለሁ (ይኸውም) በቀስቴ በጦሬ ከአሞራውያን እጅ ያመጣሁት ነው አለው ። ኢያሱ ፳፬ ፴፪ ።

## ምዕራፍ ፵፱ ።

ያዕቆብ ልጆቹን ጠርቶ ወደኔ ተሰብሰቡ በኋላ ዘመን የምታገኛችሁን እነግራችኋለሁ አላቸው ።
የያዕቆብ ልጆችም ተሰብስበው መጡ እሱም እንዲህ አላቸው፤ ስሙት አባታችሁን ስሙት አድምጡት ።
የበኵር ልጄ ሮቤል የብርታቴ መገኛ ነበር የበኵር ልጄ ነበር ነገር ግን ክፉ ሆነ አንገቱንም አደነደነ ጭንቅ ነገርንም አደረገ ። ዘዳ፣ ፳፩ ፲፯ ። መዝ፣ ፸፰ ፶፩ ።
እንደ ውኃም ሆነ (አይላቅ) ወደ አባቱ መኝታ ወጥቷልና ያንጊዜም የወጣበትን አልጋ አሳድፎታልና ።
"ጨክኜ የረገምሁት ልጄ ሮቤል ምድር ውኃ በምትጠግብበት ጊዜ ወኃው እንዲያዘነብል ወደ ኃጢአት
"አዘነበለ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ይደርበት፣
"ለልጄ ለዮሴፍ በጎ ነገር አድርጓልና„ ።
ወንድማማቾች ስምዖንና ሌዊ በጦራቸውና በፉከራቸው ዓመፅን ፈጸሚት ። ዘፍ፣ ፴፬ ፴፫ ።
ሰውነቴ አትገናኛቸው በጥፋታቸውም አልግባ ተቈጥተው ሰውን ገድለዋልና በፈቃዳቸውም የአህጉርን ሥር ቈርጠዋልና ። መዝ፣ ፲፯ ፲፱ ። ምሳ፣ ፲፩ ፲፫ ።
ቍጣቸው ርጉም ይሁን ከቍጣቸው አልተመለሱምና ከኵርፍታቸውም ተግ አላሉምና በያዕቆብ እከፍለዋለሁ፣ በእስራኤልም እበትነዋለሁ ።
ይሁዳ ወንድሞችህ ያመሰግኑኻል እጆችህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ናቸው ያባትህ ልጆችም ላንተ ይሰግዱልሃል ።
የይሁዳ አንበሳ ግልገል ከመደብህ ውጣ ልጄ እንደ አንበሳ ተኛህ አንቀላፋህ እንደ አንበሳም ደቦል ሊቀሰቅስህ የሚችል የለም ። ዘኍ፣ ፳፫ ፳፬ ። ዘዳ፣ ፴፫ ፳፪ ።
መንግሥት ከይሁዳ አይወጣም ምስፍናም ከወገኑ ለእሱ የሚጠበቀውን እስኪያገኝ ድረስ እሱም ለአሕዛብ አለኝታቸው ነው ። ዘኍ፣ ፳፬ ፲፯ ። ዘዳ፣ ፳፰ ፶፯ ።
በወይን ሐረግ ውርጫውን ያስራል፣ አህያይቱንም በዘይት ዛፍ ያስራል ልብሶቹንም በወይን ያጥባል መጐናጸፊያውንም በዘለላው ደም ። ዘኍ፣ ፲፫ ፳፫ ።
ዓይኖቹም ከወይን ይልቅ ደስ ያሰኛሉ ጥርሶቹም እንደ ወተት ነጭ ናቸው ። መሳ፣ ፳፫ ፳፱ ።
ዛብሎን ጫማውን አዝቦ ይኖራል የመርከቦች ወደብ እንደመሆኑ እስከ ሲዶና ድረስ ይስፋፋል ።
ይሳኮር መልካም ነገርን ወደደ በተወራራሾቹም መካከል ይኖራል ። መሳ፣ ፭ ፲፯ ፣ ፭ ፲፭ ። መዝ፣ ፰ ፰ ፲፫ ።
ሥራም መልካም እንደሆነች በየ ጊዜ ምድርን ያርሳት ይቈፍራት ዘንድ ትከሻውን ዝቅ አደረገ ደከመ አራሽ ሰውም ሆነ ። ዘፀ፣ ፩ ፲፩ ። ኢያሱ ፲፯ ፲ ።
ዳን ከእስራኤል ነገድ እንደ አንዲቱ በወገኑ ይፈርዳል።
ለዳን በመንገድ ላይ የሚያደባ እባብ ተሰጠው የፈረ

ሰኰና ለፈረስ ወይወድቅ ዘይጼዕኖ ድኅሬሁ ።

፲፰ ወይጸንሕ ከመ ያድኅኖ እግዚአብሔር ።
፲፱ ጋድ፣ ፈያት ፈየትዎ፣ ውእቱሂ ፈየቶሙ ተሊዎ
ኣሰሮሙ ።
፳ አሴር፣ ጽጉብ እክል ወውእቱ ይሁብ ሲሳየ ለመ
ላእክት ።
፳፩ ንፍታሌም፣ በቀልት ዕፍረት እንተ ትሜኒ አውዕአት
እክለ ።
፳፪ ወልድ ዘይልህቅ ውእቱ ዮሴፍ ወልድየ ዘይልህቅኒ
ወዘይቀንእ ሊተ ወልድየ ወሬዛ ዘይገብእ ኀቤየ ።
፳፫ እለ ጸአልዎ በምክሮሙ ወኮንዎ አጋእዝተ ወነደፍዎ።
፳፬ ወተቀጥቀጡ አቅስስቲሆሙ በኀይል ወደክመ ሥርወ
መዝራእተ እደዊሆሙ በእደ ኀይሉ ለያዕቆብ፣ በህየ አጽ
ንዖ ለእስራኤል በኀበ አምላኩ ለአቡከ ።
፳፭ ወረድአከ አምላከ ዚአየ ወባረከከ በበረከተ ሰማይ
እምላዕሉ፣ ወበበረከተ ምድር እንተ ባቲ ኵሉ በበረከተ
አጥባት ወማኅፀን ።
፳፮ በበረከተ አቡከ ወእምከ ጽኑዓን፣ ወእምበረከቶሙ
ለአድባር እለ ውዱዳን ወበረከተ መላእክቲሁ ለእግዚአብ
ሔር ተሀሉ ዲበ ርእሱ ለዮሴፍ ወዲበ ርእሶሙ ለአሰ
ከንዎ አኀዊሁ ።
፳፯ ብንያም፣ ተኵላ መሣጢ ይበልዕ በነግህ ወፍና ሠርክ
ይሁብ ሲሳየ ለሕዝብ ።
፳፰ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ለያዕቆብ ዐሠርቱ ወክልኤቱ፣
ወዘንተ ነገረ ነገሮሙ አቡሆሙ ወባረኮሙ ለለ አሐዱ
በከመ በረከቱ ።
፳፱ ባረኮሙ ወይቤሎሙ ናሁ አሐውር እንሰ ኀበ ሕዝብየ
ወቅብሩኒ ምስለ አበውየ ውስተ በዐት እንተ ሀለወት ው
ስተ ገራህቱ ለኤፍሮን ኬጥያዊ ።
፴ ውስተ በዐተ ካዕበት እንተ አንጻረ ምንባሬ ውስተ
ምድረ ከነአን እንተ ተሣየጣ አብርሃም እምኀበ ኤፍሮን
ኬጥያዊ ለመቃብር ።
፴፩ ህየ ቀበርዎ ለአብርሃም ወለሣራ ብእሲቱ ወበህየ ቀበ
ርዎሙ ለይስሐቅ ወለርብቃ ብእሲቱ ።
፴፪ ወበህየ ቀበርክዋ ለልያሂ ውስተ በዐተ ገራህት እንተ
ተሣየጡ እምኀበ ደቂቀ ኬጢ ።
፴፫ ወአኅሊቆ ያዕቆብ አዝዞቶሙ ለደቂቁ ሰፍሐ እደዊሁ
ወእገሪሁ ዲበ ምስካቢሁ ወሞተ ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ ።

ምዕራፍ ፶።

፩ ወወድቀ ዮሴፍ ቅድመ ገጸ አቡሁ ወበከየ ላዕሌሁ
ወሰዓሞ ።
፪ ወአዘዞሙ ዮሴፍ ለአግብርቲሁ እለ ይቀርቡ ኀቤሁ
ያምዕዝዎ ለአቡሁ ወአምዐዝዎ ለእስራኤል እለ ያምዕዙ።
፫ ወፈጸሙ ሎቱ አርብዐ ጽባሐ እስመ ከማሁ ይኌልቁ
መዋዕለ በዘያምዕዙ ወለሀዉዎ ሰብአ ግብጽ ሰብዓ መዋዕለ።

ሱንም ሰኰና ይነክሳል በላዩ ላይ የተቀመጠውም ወደ
ኋላው ይወድቃል ።
እግዚአብሔርም ያድነው ዘንድ ይጠብቀዋል ።
ጋድን ወንበዴዎች ቀሙት እሱም ፍለጋቸውን ተከ
ትሎ ቀማቸው ። ዘፍ፣ ፴ ፲፩ ።
አሴር እኽልን የጠገበ ነው እሱም ለአለቆች ምግብ
ይሰጣል ።
ንፍታሌም ዘኁበበ ነው የምታምርም ሽቱ ዘሳላን
አወጣች ።
ዮሴፍ ታዳጊ ልጅ ነው፤ የሚበልጠኝ ልጄ ለኔም የሚ
ቀና ከሞተ በኋላ የተመለሰልኝ ጉልማሳው ልጄ ።
ተማክረው የሰደቡት ጌቶች የሆኑት ይወጉት ነበር።
ቀስቶቻቸው በኃይል ተቀጠቀጡ ያዕቆብን ከአበረ
ታው እጅም ክንዳቸው ዛለ፤ እስራኤልን በከነዓን ያጸናው
የአባትህ ፈጣሪ አንተንም በግብጽ አገር አጸናህ ።
የኔ ፈጣሪ ረዳህ፣ ከላይ ከሰማይ በሚገኝ በረከት እስ
በረሀ ሁሉ በሚገኝበት በምድርም በረከት፣ ከማኅፀንና
ከጡት በሚገኝ በረከት ያክብርህ ። ዘፍ፣ ፴፫ ፫ ።
ጽኑዓን በሆኑት በናትህና በአባትህ በረከት፣ ጽኑዓን
ከሚሆኑ ተራሮች (አብርሃምና ይስሐቅ) በሚገኝ በረከት
ያክብርህ፤ የእግዚአብሔር መላእክት በረከት በዮሴፍ ራስ
ላይ ይደር፣ ወንድሞቹም በሆኑት ራስ ላይ (ይደር) ።
ብንያም፣ ነጣቂ ተኵላ ነው፣ ምግቡን በጧት ይበላል
ማታ ጊዜም ለሌሎቹ ያካፍላል ። ሕዝቅ፣ ፳፬ ፳፮ ።
አሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች እነዚህ ናቸው፤ አባታ
ቸውም ይህንን ነገር ነገራቸው፤ እያንዳንዱን አባታቸው
በረከቸው፤ እያንዳንዱንም እንደ በረከቱ በረከቸው ።
እንዲህም አላቸው፤ እነሆ እኔ ወደ ወገኖቼ እሄዳለሁ
በኬጥያዊው በኤፍሮን እርሻ ውስጥ ባለችው ዋሻ ከአባ
ቶቼ ጋር ቅበሩኝ ። ዘፍ፣ ፵፱ ፴፫ ።
አብርሃም ከኬጥያዊው ከኤፍሮን ለመቃብር በገዛት
በከነዓን ምድር በመምሬ አንፃር ባለችው ድርብ ዋሻ ።

አብርሃምን በዚያ ቀበሩት ሚስቱ ሣራንም ይስሐ
ቅንና ሚስቱ ርብቃንም በዚያ ቀበሩዋቸው ።
እኔም ልያን ከኬጢ ልጆች በገዟት ድርብ ዋሻ
ቀበርኳት ።
ያዕቆብም ልጆቹን አዝዞ ከጨረሰ በኋላ በመኝታው
ላይ እግሮቹንና እጆቹን ዘርግቶ ሞተ፣ ወደ ወገኖቹም
ተጨመረ ። ዘፍ፣ ፵፱ ፳፱ ።

ምዕራፍ ፶።

ዮሴፍ በአባቱ ፊት ላይ ወድቆ አለቀሰ ሳመውም ።

ዮሴፍም ወደሱ የሚቀርቡ ባሮቹን አባቱን ሽቱ ይቀ
ቡት ዘንድ አዘዛቸው፤ ሽቱ የሚቀቡ ሰዎችም እስራኤልን
ሽቱ ቀቡት ። ሉቃ፣ ፳፫ ፶፮ ። ዮሐ፣ ፲፱ ፵ ።
አርባ ቀንም ፈጸሙለት ሽቱ የሚቀቡበትን ወራት እንዲ
ሁ ይቈጥሩ ነበርና የግብጽም ሰዎች ሰባ ቀን አለቀሱለት።

፬ ወእምድኅረ ተፈጸመ መዋዕለ ላሁ ይቤሎሙ ዮሴፍ ለኅያላነ ፈርዖን እንዘ ይብል እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜክሙ ንግርዎ ለፈርዖን በእንቲአየ ።

የልቅሶም ወራት ከተፈጸመ በኋላ ዮሴፍ የፈርዖን መኳንንት እንዲህ አላቸው፤ በፊታችሁ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ የኔን ነገር ለፈርዖን ንገሩት። ዘፍ፥ ፵፮ ፳፱ ።

፭ ወበልዎ አቡየ አምሐለኒ ዘእንበለ ይሙት ወይቤለኒ ውስተ መቃብር ዘከረይኩ ሊተ በምድረ ከነአን ህየ ቅብረኒ ወይእዜኒ እዕርግ ወእቀብሮ ለአቡየ ወእግባእ ።

እንዲህ በሉት፤ አባቴ በከነዓን ምድር ለእኔ በቆፈርኩት መቃብር በዚያ ቅበረኝ ብሎ ሳይሞት አምሎኛል፤ አሁንም ወጥቼ አባቴን ቀብሬ ልመለስ ።

፮ ወነገርዎ ለፈርዖን፡ ወይቤሎ ፈርዖን ዕርግ ወቅብሮ ለአቡከ በከመ አምሐለከ ።

እነሱም ለፈርዖን ነገሩት፤ ፈርዖንም እንደ አማለህ ወጥተህ አባትህን ቀብረው አለው ። ፩ ዜና መዋ፥ ፲፮ ፲፬።

፯ ወዐርገ ዮሴፍ ይቅብሮ ለአቡሁ ወዐርጉ ምስሌሁ ኵሎሙ ደቀ ፈርዖን ወኵሎሙ ዐበይተ ግብጽ ።

ዮሴፍም አባቱን ይቀብረው ዘንድ ወጣ፤ የፈርዖን አሽከሮችም ሁሉ አብረዉት ወጡ፤ የግብጽ መኳንንቶችም ሁሉ ።

፰ ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ለዮሴፍ ወኵሉ አኀዊሁ ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ለአቡሁ ወሕፃናቲሆሙሰ ወአባግዒሆሙ ወአልሕምቲሆሙ ኀደጉ ውስተ ምድረ ጌሴም ።

የዮሴፍ ቤተ ሰቦችም ሁሉ ወንድሞቹም ሁሉ የአባቱም ቤተ ሰቦች ሁሉ ከሱ ጋራ ወጡ፤ ልጆቻቸውን ላሞቻቸውንና በጎቻቸውን ግን በጌሴም ምድር ተዉ ።

፱ ወአዕረገ ምስሌሁ ሠረገላተ ወአፍራሰ ወኮነ ትእይንቶሙ ዐቢየ ጥቀ ።

ከሱም ጋራ ፈረሶችንና ሠረገላዎችን አወጣ፤ ሰፈራቸውም እጅግ ሰፊ ሆነ ። ዘፍ፥ ፵፩ ፲ ።

፲ ወበጽሑ ኀበ ዐውደ እክል ዘአጣታ ዘሀሎ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ወበከይዎ ዐቢየ ብከየ፤ ወጽኑዐ ጥቀ ላሁ ገብሩ ለአቡሆሙ ሰቡዐ መዋዕለ ።

በዮርዳኖስ ማዶ ወደ አለ ወደ አጣታ እኽል አውድማ ደርሰው ጽኑ ልቅሶን አለቀሱለት፤ ላባታቸውም ሰባት ቀን እጅግ ብርቱ ኃዘን አደረጉ ።

፲፩ ወርእዩ እለ ይነብሩ ውስተ ምድረ ከነአን ውእተ ላሁ በኀበ ዐውደ እክል ዘአጣታ ወይቤሉ ከመዝኑ ላሁ ዘግብጽ ዐቢይ ወበእንተዝ ሰመይዎ ስሞ ላሁ ግብጽ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

በከነዓን የሚኖሩ ሰዎችም በአጣታ የእኽል አውድማ የሆነውን ያንን ልቅሶ አይተው የግብጽ ልቅሶ እንዲህ የጸና ነውን! አሉ፤ ስለዚህም ስሙን የግብጽ ልቅሶ ብለው ጠሩት፤ እርሱም በዮርዳኖስ ማዶ ነው ።

፲፪ ወከመዝ ገብሩ ሎቱ ደቂቁ ።

ልጆቹም እንዲህ አደረጉለት ።

፲፫ ወአግብእዎ ውስተ ምድረ ከነአን ወቀበርዎ ውስተ በዐት እንተ ተሣየጠ አብርሃም ለመቃብር እምኀበ ኤፍሮን ኬጥያዊ እንተ አንጻረ ምንባሬ ።

አምጥተው አብርሃም ከኬጥያዊው ከኤፍሮን ለመቃብር በገዛት በመሰብሰቢያው ዘፍ አንፃር ባለችው ዋሻ ቀበሩት ። ግ፥ ሐ፥ ፯ ፲፮ ።

፲፬ ወገብአ ዮሴፍ ውስተ ግብጽ ውእቱ ወኵሎሙ እለ ዐርጉ ምስሌሁ ኅቡረ ይቅብርዎ ለአቡሆሙ ወአኀዊሁኒ ።

ዮሴፍም ወደ ግብጽ ተመለሰ፤ እሱና አባታቸውን ይቀብሩት ዘንድ ከሱ ጋራ አንድነት የወጡትም ወንድሞቹ ሁሉ ተመለሱ ።

፲፭ ወእምዝ ሶበ ርእዩ አኀዊሁ ከመ ሞተ አቡሆሙ፤ ይቤሉ ዮጊ ይዜክር ብነ ዮሴፍ እኪተ እንተ ገበርነ ላዕሌሁ ወያገብእ ለነ ፍዳሃ ለኵላ እኪት እንተ አርአይናሁ ።

ከዚህም በኋላ ወንድሞቹ አባታቸው እንደሞተ ባዩ ጊዜ እንዲህ አሉ፤ ምናልባት እነሆ ዮሴፍ በርሱ ላይ ያደረግነውን ክፋት አስበ ያሳየነውን ክፋት ሁሉ ብድራቱን ይመልስብን ይሆን፤ አሉ ። ዘፍ፥ ፵፱ ፳፫ ።

፲፮ ወመጽኡ ኀበ ዮሴፍ አኀዊሁ ወይቤልዎ አቡከ አምሐሎ አምሐለነ ዘእንበለ ይሙት ።

ወንድሞቹም ወደ ዮሴፍ መጥተው እንዲህ አሉት፤ አባትህ ሳይሞት መሐላን አምሎናል ። ዘፍ፥ ፲፯ ፲፰ ።

፲፯ ወይቤ ከመዝ በልዎ ለዮሴፍ ኅድግ ሎሙ አበሳሆሙ ወጌጋዮሙ እስመ እኪተ አርአዩከ ወይእዜኒ ሥረይ ሎሙ ኀጢአቶሙ ለአግብርቲከ በአምላኩሙ ለአበዊከ፤ ወበከየ ዮሴፍ እንዘ ይትናገርዎ ።

እንዲህ ብሉ ዮሴፍን እንዲህ በሉት፤ መከራ አሳይተዉኻልና ኃጢአታቸውን በደላቸውን ይቅር በላቸው አሁንም ስለ አባቶችህ አምላክ ብለህ የባሮችህን ኃጢአት ይቅር በል ዮሴፍም እንዲህ ሲሉት አለቀሰ ።

፲፰ ወመጽኡ ኀቤሁ ወይቤልዎ ናሁ ክነ ንሕነ ለከ አግብርተ ።

ወደ እርሱም መጥተው እነሆ እኛ ላንተ ተገዥዎች ሆነናል አሉት ።

፲፱ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ኢትፍርሁ እስመ እምእግዚአብሐር ክነ ።

ዮሴፍም እንዲህ አላቸው፤ ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ታዝ ሆኖአልና አትፍሩ አላቸው ። ፩ ነገ፥ ፩ ፯ ።

፳ አንትሙሰ መከርክሙ እኪተ ላዕሌየ ወእግዚአብሐር ባሕቱ መከረ ሠናይተ ላዕሌየ ከመ ይኩን ዮም በዘይሴሰይ ሕዝብ ብዙኅ ።

እናንተስ በኔ ላይ ክፉ ነገር መክራችሁ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን በእኔ ላይ መልካም ነገር አደረገ፤ ዛሬ ብዙ ሕዝብ ምግብ እንዲያገኝ ይሆን ዘንድ ።

፳፩ ወይቤሎሙ ኢትፍርሁ አነ እሴስየክሙ ወለቤትክሙኒ ወፀውዖሙ ወተናገሮሙ ዘይበውእ ውስተ ልቦሙ ።

አትፍሩ እናንተንም ቤተ ሰቦችሁንም እኔ እመግባችኋለሁ ብሎ አጽናናቸው ጠ፡ቶም ከልባቸው የሚገባውንነገራቸው

፳፪ ወነበረ ዮሴፍ ውስተ ግብጽ ውእቱ ወአኀዊሁ ወኵሉ ቤተ አቡሁ፤ ወሐይወ ዮሴፍ ምእተ ወዐሠርተ ዓመተ ።

፳፫ ወርእየ ዮሴፍ ደቂቀ ኤፍሬም እስከ ሣልስ ትውልድ ወደቂቀ ማኪር ወልደ ምናሴ እለ ተወልዱ ላዕለ ሕፅነ ዮሴፍ ።

፳፬ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለአኀዊሁ አንሰ እመውት ወእግዚአብሔር ይሔውጸክሙ ወያወፅአክሙ እምዛቲ ምድር ወያበውአክሙ ውስተ ምድር ዘመሐለ ለአበዊነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ።

፳፭ ወአምሐሎሙ ዮሴፍ ለደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ አመ ይሔውጸክሙ እግዚአብሔር አውፅኡ አዕፅምትየ እምዝየ ምስሌክሙ ።

፳፮ ወሞተ ዮሴፍ በምእት ወዐሠርቱ ዓመት፤ ወአምዐዝዎ ወሤምዎ በነፍቅ ውስተ ብሔረ ግብጽ ።

ተፈጸመ ኦሪት ዘልደት
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ፈጣሬ ኵሉ ፍጥረት
አሜን ።

፳፪ ዮሴፍም በግብጽ ኖረ እሱ ወንድሞቹም ያባቱም ቤተ ሰቦች ሁሉ፤ ዮሴፍም መቶ አሥር ዓመት ኖረ ።

፳፫ ዮሴፍ የኤፍሬምን ልጆች እስከ ሦስት ትውልድ ድረስ አየ፤ በዮሴፍ ጉልበት ላይ ያደጉትን የምናሴ ልጅ የማኪርንም ልጆች አየ ። ዘኍ፤ ፴፪ ፴፱ ። ሩት፤ ፬ ፲፮ ።

፳፬ ዮሴፍም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤ እኔ እሞታለሁ እግዚአብሔርም (በረድኤት) ይጎበኛችኋል ከዚችም ምድር ያወጣችኋል ለአባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ወደ ማለላቸው ምድር ወደ ከነዓን ያገባችኋል ።

፳፭ ዮሴፍም የያዕቆብን ልጆች እግዚአብሔር በጎበኛችሁ ጊዜ አጥንቴን ከዚህ ከግብጽ ከናንተ ጋራ አውጡ ብሎ አማላቸው ። ዘፀ፤ ፲፫ ፲፱ ። ኢያሱ ፳፬ ፴፪ ።

፳፮ ዮሴፍም በ፻፲ ዓመቱ ሞተ፤ ሽቱም ቀብተው በሣጥን አድርገው በግብጽ አገር አኖሩት ።

ተፈጸመ ኦሪት ዘልደት
ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው በእውነት
አሜን ።